

# ሱፊ ዝም

ታሪኮች፣ ተረቶች፣ ወጎች፣ ምሳሌዎች፣....

## ከጺ.ላጦስ

(ኃይለጊዮርጊስ ማሞ)

pdf by @shuktus_books

# ሱፊዝም

ታሪኮች፣ ተረቶች፣ ወጎች፣ ምሳሌዎች፣....



pdf by @shuktus_books

## ከጲላጦስ

(ኃይለጊዮርጊስ ማሞ)

2007 ዓ. ም.

የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው
All rights reserved
2007 ዓ. ም.

በደራሲው የታተሙ፡-

1. ጥበብ 1
2. ጥበብ 2
3. ጥበብ 3
4. ጥበብ 4
5. ጥበብ 5
6. ጥበብ 6 (ኦሾ)
7. ሴት እና ፈጣሪ (የግጥም ስብስብ)
8. ዜን ቡድሂዝም (ጥበብ 7)
9. እውነት እና እምነት (ጥበብ 8)
10. የፍርሀት ካቦች (ጥበብ 9)
11. የተጣለው መልዐክ (የአጭር ልቦለድ ስብስብ)
12. ኢየሱስ የሰው ልጅ

---

ማናቸውንም አስተያየት ለደራሲው መላክ ከፈለጉ፡-
ፖ.ሳ.ቁ. 18099
አዲስ አበባ

ኢ-ሜይል Hailempilate@gmail.com

# መግቢያ

ሱፊዝም መለኮታዊ ስሙቀትና ምግባር በተግባር የሚገለጥበት እስተሳሰብ ነው:: ሱፊዝም መሰረቱ የእስልምና እምነት ይሁን እንጂ በተከታዮቹ ዘንድ ሁሉም ሀይማኖት እኩልና ወደ አንዱ ፈጣሪ የመድረሻው የተለያዩ መንገዶች ተደርገው ይወሰዳሉ:: የእያንዳንዱ ሀይማኖት የመጨረሻ ግቡ ፈጣሪ ጋ መድረስ መሆኑ ቢታወቅም ለሱፊዎች ግን በዚህ በአሁኑ ህይወትና አሁን ወደ ፈጣሪ መድረስ፣ የእሱንም ማንነት በኛ ላይ መግለጥ እንችላለን ይላሉ:: ለዚህም ነው "የገነት ምኞትም ሆነ፣ የገሃነም ፍርሀት ከኛ ይራቅ" የሚሉት::

"የእኛ ስራ ፈጣሪን ማፍቀር፣ በዚህም ማንነቱንና ምንነቱን በምድራዊ ህይወታችን መግለጥ ነው" የሚሉን ሱፊዎች ከዚያ ተሻግረን ስለገነትና ገሃነም መጨነቅም ሆነ ማሰብ "በፈጣሪ ስራ ጣልቃ እንደመግባት ይቆጠራል" ይላሉ:: እናም የኛ ተግባር ሊሆን የሚገባው ዛሬና አሁን ህይወትን በሙላት መኖር፣ በዚህም የፈጣሪን ጥበብ በኛ ውስጥ መግለጥ ነው:: መለኮታዊውን ጥበብና ፍቅር በአለም ላይ ይገለጽ ዘንድ ደግሞ እለት እለት ራስን በፈጣሪ ሚዛን መለካት የግድ ይላል:: ይህን ሳይታክት የሚያደርግ የተዋበውን የሀር ጨርቅ በላዩ እንደሚደርብ፣ ደርቦም እንደሚዋብ ሰው ይሆናል:: የሱፊዝም የቃሉ ምስጢርም ይኸው ነው:: ከፈጣሪ ጋር መዋሀድ፣ አንድ መሆን በሀር ጨርቅ እንደመዋብ ነውና! ይህንንም "ታሳዉፍ" ይሉታል:: "ታሳዉፍ" ቃሉ አረብኛ ሲሆን "ሀር መልበስ" እንደማለት ነው:: ይህን ቃል የምዕራቡ ዓለም ወሰደና የራሱን መጠሪያ ደግሞ በተራው አበጀለት:: "ሱፊዝም" አለው:: "ሱፍ" አረብኛ ሲሆን ሀር እንደማለት ነው:: በሱፍ ተውቦ መታየት የማይሻ እንደሌለ ሁሉ ሱፊዎች ደግሞ ከዚያ በላይ የመዋቢያውን ምስጢር ይዘናል ይላሉ:: እሱም "ፈጣሪን መልበስ" ነው::

እነሆ ከሱፊዎች የዘመናት አስተምሀሮት፣ ታሪኮች፣ ወጎች፣ ተረቶች፣ ቀልዶች... ቆንጥሬ ለአንባቢያን ሳቀርብ ውስጣዊውን ሰው የማስዋብ ዓላማን ዛሬም እንደሰነቅሁ ይቆጠርልኝ እላለሁ::

ጲላጦስ (ኃይለጊዮርጊስ ማሞ)

# ‹‹ታላቅ ምስጢር ማለት የራስ ማንነት ነው››

ሱፊዝም የእስልምና እምነት የወለደው መንፈሳዊ ተመስጥኦ (mysticism) ሲሆን የእምነቱ አራማጆችም ‹‹እስላማዊ ተሰጥኦ›› (Islamic mysticism) ነው ይሉታል:: በእንፃሩ የእስልምና እምነት መሪዎች ደግሞ ‹‹ሱፊዝም›› ከእስልምና እምነት መሠረታዊ መርሆዎችና አስተሳሰቦች ጋር የሚጋጩ የስህተት አስተሳሰቦች ላይ ተመስርቶ የሚካሄድ በመሆኑ የስህተት እምነት ነው በማለት ይነቅፉታል:: ምንም እንኳን ልዩነቱ በምድራዊው የሕይወት ፈለግ እና አስተሳሰብ ላይ የተመሰረተ ይምሰል እንጂ ይህንኑ በወጉ የመረመሩት የሚነግሩን ግን ልዩነቱ በፈጣሪ ፍለጋ ላይ ከሚከተሉት የተለያየ ጎዳና የተነሣ ነው ይሉናል:: እያንዳንዱ ፃድቅ ሙስሊም ከሞት በኋላ ፈጣሪውን እንደሚያይ ያምናል፤ በሱፊዝም ግን ፈጣሪን የሚፈልጉት አሁንና በቅፅበት፣ ዕለት ተዕለት. . . በዚህ በባሬው ሕይወት ነው:: ለዚህም ነው ሱፊዎች እምነታቸውን ‹‹ማንነትን የማወቂያውና ወደ ፈጣሪም የመድረሻው ታላቅ ፍፃሜ›› አድርገው የሚወስዱት:: ምንም እንኳን ሱፊዝም መሰረቱ እስልምና ይሁን እንጂ የእምነቱ መሪዎች ወደ ሕንድ ተጉዘው ከሂንዱይዝም እምነት በስፋት የወሰዱትና የተቀበሉት ነገር እንዳለ ደግሞ ይታመናል:: እንግዲህ በዚህ መሰረታዊ እውነት ላይ ተመስርተን ጉዟችንን ስንጀምር ሱፊዎች እምነትን፣ ፍቅርን፣ ትዕግስትን፣ ደስታን፣ ተስፋን. . . ወዘተ አስመልክተው በተለያዩ ጣፋጭ ወጎችና ትረካዎች የሚያስተላልፉትን ቁም ነገር በመቋደስ ይሁን:: በቅድሚያ መነሻችን የምናደርገው ደግሞ የሱፊው ምሁር

ሩሚ ስለ ፍቅር የሚነግሩንን በመያዝ ይሆናል::

አንድ ቀን የሱፊው ደቀመዝሙር ወደ ሩሚ ዘንድ በመምጣት፡ - ‹‹መምህር ሆይ! ፍቅርን ፈልጎ ለማግኘት መንገዱን ይምሩኝ›› ይላቸዋል:: ሩሚም ‹‹የአንተ ድርሻ ፍቅርን መፈለግ አይደለም፤ ነገር ግን ከእሱ ጋር እንዳትገናኝ ያገደህንና በልብህ የገነባኸውን የጥላቻ ቅጥር ማፍረስ ነው›› በማለት አስናበቱት:: ለዚህም ነው ፈጣሪ ፍቅርን በልባችን ያስቀመጠው ቢሆንም ነገር ግን በራሳችን የተፈጥሮ ባህርይ የጥላቻ ቅጥር ሠርተንበት ዘወትር በፍለጋው የምንደክም ይሉናል ሱፊዎች::

ለሩሚ ፍቅር ከፈጣሪ የተሰጠ ስጦታ በመሆኑ ይህንን ስጦታ የምናገኝበት ቀላሉ መንገድ ሰዉን አጥብቆ መፈለግ ነው ይላሉ:: ለዚህም ነው ሩሚ ሲናገሩ፡- ‹‹በፈጣሪ ብርሃን ፍቅርን አገኘሁ፤ ለእሱም ውበት ቅኔን ተቀኘሁ፤ የሰው ልጅ ዓይኖች ሊያዩህ በማይችሉት ልቤ ውስጥ ሆነህም ዘወትር አሸበሸባለሁ፤ እናም አንዳንዴ በአንተ ብርሃን ታጅቤ ስወዛወዝ ሰዎች ይመለከታሉ፤ ይህንን ደግሞ ጥበብ በማለት ይጠሩታል::››

በአንድ ወቅት ሩሚ እንዲህ ተጠየቁ፡- ‹‹ለመሆኑ ከሞት በኋላ የነፍስ መጨረሻዋ የት ይሆን?››

ሩሚም፡- ‹‹ነፍስ የመጣችው ከሌላ ሥፍራ እንደሆነ አውቃለሁ፤ ሥፍራውን ባላውቀውም መጨረሻዋ ግን ወደመጣችበት መመለስ መሆኑን አልጠራጠርም›› አሉ::

ወደሌላው የሱፊው ምሁር ቢያዚድ ቢስታሚ እለፍን:: ቢስታሚ በደቀመዝሙራቸው አንድ ቀን እንዲህ የሚል ጥያቄ ቀረበላቸው፡ - ‹‹መምህር ሆይ! ለመሆኑ ወደፈጣሪ ስንፀልይ ከምድር ቋንቋዎች ሁሉ እሱ በሚገባ የሚሰማን በየትኛው ይመስልዎታል››

ቢስታሚም፡- ‹‹የፈጣሪ ቋንቋ ዝምታ ነው፤ ሌላው ሁሉ ከንቱ ትርጉም ነው›› በማለት መለሱለት:: ከቢስታሚ አባባል የምንረዳው የሰው ልጅ ቋንቋ የልቡን ፍላጎትና መሻት እንጂ የፈጣሪውን ሐሳብ

መግለጫ ባለመሆኑ እሱ ከእንደበታችን ቋንቋ ይልቅ የውስጣችን ዝምታ ዘልቆ ይሰማዋል::

ሱፊዎች ልዩ ልዩ አስተምህሮታቸውን ለማስተላለፍ የሚጠቀሙበትን ሙላ ናስሩዲንን እዚህ ላይ እናመጣዋለን:: ናስሩዲን እንደ እኛው አለቃ ገብረሃና በቀልዱ አዋዝቶ በሚያስተላልፋቸው ቁም ነገሮች በመላው የዓረቡ ዓለም የታወቀ ሰው ነው:: የናስሩዲን ወጎች የመጀመሪያውን የምንቆነጥረው ከፈላስፋ ጋር ሙግት ለመግጠም ቀጠሮ የያዘበትን ገጠመኝ ይሆናል:: አንድ ፈላስፋ ስለ ሙላ ናስሩዲን ነገር አዋቂነት ሲወራ ሰምቶ ከእሱ ጋር ክርክር ለመግጠም ይወስንና ወደ እሱ ዘንድ በመምጣት ቀጠሮ ይዞ ይመለሳል::

የክርክሩ ቀን ደርሶ ፈላስፋው በቀጠሮው መሠረት ወደ ናስሩዲን ቤት ያመራል:: ይሁንና ከሥፍራው ደርሶ ቤቱን ቢያንኳኳም ናስሩዲንን ለማግኘት አልቻለም:: በዚህ የናስሩዲን ድርጊት የተበሳጨው ፈላስፋ ከቤቱ ደጃፍ ላይ ወድቆ ያገኘውን ጠመኔ በማንሳት ከናስሩዲን በር ላይ፡- ‹‹የማይረባ ከንቱ›› የሚል በመጻፍ ተመልሶ ሄደ:: ናስሩዲን ከሄደበት ሲመለስ በሩ ላይ ፈላስፋው ፅፎት የሄደውን ሲመለከት በፍጥነት ተመልሶ ወደ ፈላስፋው ቤት መገስገስ ጀመረ::

ናስሩዲን ከፈላስፋው ቤት እንደደረሰም፡- ‹‹ዛሬ ቀጠሮ እንደነበረን ዘንግቼው ሰዓት ባለማክበሬ ይቅርታ እጠይቅሃለሁ! ቀጠሯችንን ፈፅሞ ከመዘንጋቴ የተነሳ ክርክር እንኳን እንደነበረን ያስታወስኩት ስምህን ከበሬ ላይ ፅፈህ ስመለከት ነው›› በማለት ይቅርታ ጠይቆት ተመለሰ::

እንግዲህ ሱፊዎች ጥልቅ በሆነው የፈጣሪ ሐሳብና ምስጢር ላይ ለመከራከር የሚደክም እሱ ከንቱ ነው፤ ይልቁንስ ጠቢብ ሰው በራስ ፍሲጋ ላይ ተሰማርቶ የሚጓዝ ማለት ነው ይሉናል::

ከሙላ ናስሩዲን ወጎች አንድ እንመርቅ:: አንድ ቀን የንጉሱ

አሳዋች የሆነ የናስሩዲን ጓደኛ በምሳ ሰዓት ወደ ቤቱ ሲመጣ ናስሩዲን ንፍሮና ዳቦ ሲመገብ አገኘው፤ በዚህ ጊዜ ፈገግ ብሎ እየተመለከተው ‹‹ናስሩዲን! የንጉሱ አሳዋች መሆን አሻፈረኝ ብለህ ንፍሮና ዳቦ ምግብህ ሆኖ ቀረ?›› ይለዋል::

በዚህ ጊዜ ናስሩዲንም ፈገግ ብሎ፡- ‹‹አንተም በንፍሮና ዳቦ መኖር አሻፈረኝ ብለህ የንጉሥ አሳዋች ሆነህ ቀረህ አይደለም?›› በማለት መለሰለት::

ሥጋዊ የሕይወትህን ጥሪ ተከትለህ የምትሄድበት መንገድ መልሶ የሚያመጣህ እስከሆነ ድረስ ቁምነገሩ ከመንገዱ ፈጣሪ ጋር ያለህ ግንኙነት እንጂ ከሥጋዊ ደስታህ የምታገኘው እርካታ ዋጋ ቢስ መሆኑን አትዘንጋ የሚሉን ሱፊዎች ‹‹በሕይወት መንገድ ስትጓዝ አዳልጦህ ብትወድቅና ተስፋ ብትቆርጥ የተስፋ መቁረጥህ ምክንያት የስጋህ ሳይሆን የእምነትህ መውደቅ መሆኑን አስተውል›› ይሉናል::

ወደሱፊው ሩሚ እንመለስ:: አንድ ቀን ደቀመዝሙራቸው ወደ እሳቸው ዘንድ በመምጣት፡- ‹‹መምህር ሆይ! አንድ ወንድሜ ከአንዲት ቆንጆ ጋር በፍቅር ወድቆ እየተሰቃየ መሆኑን ነግሮኛልና ምን ምክር ብሰጠው ይሻላል?›› በማለት ጠየቃቸው:: ሩሚም፡- ‹‹ፍቅር ማለት ከሚያፈቅራት ሴት ጋር ስትሆን እንቅልፍ አልባ ሌሊት ማሳለፍ፤ እሷ ሳትኖር ደግሞ እንዲሁ ያለ እንቅልፍ ተቀምጦ ማንጋት ነው:: ሁለቱም ሌሊቶች እንቅልፍ አልባ ይሁኑ እንጂ የሚያልፍባቸው ዕብደቶች የተለያዩ ናቸውና ፈጣሪውን ያመስግን›› በማለት ሸኙት::

በሱፊዝም እንዲህ ዓይነቱን ፍቅር ‹‹በምስጢራዊ ሰማይ ላይ መብረር፤ በየቅፅበቱ ከፊታችን የተጋረዱ እያሌ መጋረጃዎችን መግፈፍ፤ እንዲሁም ሕይወትን እንዳሻት እንድትበር መልቀቅና ያለ እግር መራመድ መቻል ነው›› በማለት ይገልፁታል::

ወደ ሌላው የሱፊ መምህር ጁናይድ እንሻገር:: አንድ ቀን ጁናይድ

በኤፍራጤስ ወንዝ ዳርቻ ሲራመዱ የተመለከተ ደቀመዝሙር ወደ እሳቸው መገስገስ ሲጀምር ጁናይድ በድንገት ወደወንዙ ገብተው በውሃው ላይ መራመድ ይጀምራሉ:: በዚህ ጊዜ ደቀመዝሙሩ በጁናይድ ተግባር ተደንቆ እሱም በውሃው ላይ፡- ‹‹አላህ! አላህ!›› እያለ መሮጥ ይጀምራል:: ይሁንና ደቀመዝሙሩ ብዙም ሳይርቅ መስመጥ ይጀምራል:: በድንጋጤም መጮህ ሲጀምር ጁናይድ ይደርሱና እጁን በመሳብ በግማሽ ከሰጠመበት ውሃ ያወጡታል::

‹‹አየህ! አንተ ማለት ያለብህ ጁናይድ! ጁናይድ! ነው:: የእኔን ስም ብትጠራ በውሃው ላይ መራድ ትችላለህ›› በማለት ውሃው ላይ እንዲቆሙት ጥለውት ይሄዳሉ:: በዚህ ጊዜ ደቀመዝሙሩ እንደተነገረው ‹‹ጁናይድ!›› እያለ በመጥራት ወደ መካከለኛው የወንዙ ክፍል መራመድ ይጀምራል:: በዚህ ጊዜ ሰይጣን ይመጣል:: ወደደቀመዝሙሩ ጆሮም ጠጋ ብሎ፡- ‹‹አንተ ሰው! በፈጣሪህ ስም ፋንታ የሰው ሰው መጥራትህ ትልቅ ኃጢአት እንደሆነ አታውቅምን? ጁናይድ ‹‹ስሜን ጥራ›› የሚሉህ ሊያሳስቱህ ነውና ሳትሞኝ የፈጣሪህን ስም መጥራት ጀምር›› ብሎት ከአጠገቡ ይሰወራል::

በዚህ ጊዜ ደቀመዝሙሩ በቅፅበት ጥሪውን ወደፈጣሪው ቀይሮ ‹‹አላህ!›› ማለት ይጀምራል:: ነገር ግን እንደቀድሞው መስመጥ ሲጀምር በድጋሚ ጁናይድን በጩኸት መጥራት ይጀምራል::

ጁናይድም ተመልሰው ደቀመዝሙሩን መስመጥ ከጀመረበት ውሃ ውስጥ እያወጡት ለምን ቃላቸውን እንዳልጠበቀ ይጠይቁታል፤ ደቀመዝሙሩም ‹‹መምህር ሆይ! በሆነው ነገር እጅግ ግራ ተጋብቻለሁ:: የአላህን ስም ጠርቼ ስሰምጥ እንዴት በእርስዎ ስም ውሃው ላይ ልራመድ ቻልኩ?›› በማለት ይጠይቃቸዋል::

ጁናይድም፡- ‹‹መምህርህ ጁናይድ ጋ በወጉ መድረስ የማትችል እንዴት አላህ ጋ መድረስ ትችላለህ?›› በማለት ጥያቄውን በጥያቄ መለሱለት::

እዚህ ላይ ሱፊዎች የሚነግሩን ቁም ነገር፡- ‹‹ልብህ ከፈጣሪ ጋር

ካልተገናኘ የቱንም ያህል ቃላት በፊቱ ብትደረድር ከንቱ ድካም ነው:: እንዲህ ዓይነቱ ሰው ምንጊዜም ከቤቱ ውስጥ ቆሞ በሩን የሚያንኳኳ ሰውን ይመስላል:: ይልቁንስ የልቦናህ ዓይኖች እንዲበሩ ፈጣሪህን ጠይቀው፤ ያን ጊዜ እጆችህ የሚያንኳኩ ሳይሆን የሚከፍቱ ይሆናሉ›› ይሉናል::

ወደ ሙላ ናስሩዲን ደግሞ እንመለስና በእሱ አማካይነት ሱፊዎች የሚያስጨብጡንን ሌላ ቁም ነገር እንመልከት::

‹‹ሙላ ናስሩዲን አዋቂና ጠቢብ ሳይሆን ሞኝ መሆኑ መታወቅ አለበት›› የሚሉ አንድ ፈላስፋ፤ አንድ የሃይማኖት ሰባኪ እና አንድ የሕግ ባለሙያ በንጉሱ ፊት በመቅረብ ክስ ይመሰርታሉ:: ክሱም ናስሩዲን በየመንደሩ እየዞረ የተገላቢጦሽ እነሱን አላዋቂ፤ የማያስቡና ግራ የተጋቡ መሆናቸውን በመንገር ስማቸውን እያጠፋ መሆኑን የሚገልፅ ነበር:: ናስሩዲን በንጉሱ ፊት ቀርቦ ሲጠየቅ ድርጊቱን መፈፀሙን አላስተባበለም:: ይህ ደግሞ የናስሩዲንን ወንጀል የከፋ አደረገውና ምላሽ እንዲሰጥ በንጉሱ ተጠየቀ::

‹‹መጀመሪያ እንድትናገር ዕድሉን ሰጥቼሃለሁ›› አለ ንጉሱ::

‹‹ንጉስ ሆይ! መጀመሪያ ወረቀትና ብዕር ይምጣልኝ›› አለ ሙላ ናስሩዲን::

ብዕርና ወረቀት እንደቀረበለት፡- ‹‹የከሳሼ ፈራጆች ሆነው በንጉሱ ለተሾሙት ሰባት ሰዎች ለእያንዳንዳቸው ይሰጥልኝ›› አለና ይኸው ተፈፀመ::

‹‹አሁን ቀጥሎ ለምጠይቃችሁ ጥያቄ መልሳችሁን በየራሳችሁ ወረቀት ላይ አስፍሩ›› አለና ቀጣዩን ጥያቄ አቀረበ፡- ‹‹ዳቦ ምንድነው?››

የመጀመሪያው፡- ‹‹ዳቦ ምግብ ነው?››

ሁለተኛው፡- ‹‹ከዱቄትና ውሃ ቅልቅል የተሰራ ነው››

ሦስተኛው፡- ‹‹የፈጣሪ ስጦታ ነው››

አራተኛው፡- ‹‹የተጋገረ ሊጥ ነው››

አምስተኛው፡- ‹‹ዳቦ እንደያንዳንዱ ሰው ትርጓሜ የሚቀያየር ነው››

ስድስተኛው፡- ‹‹ሰውነት ገንቢ ንጥረ ነገር ነው››

ሰባተኛው፡- ‹‹ማንም በእርግጠኝነት አያውቀውም››

‹‹እንግዲህ ንጉሥ ሆይ!›› አለ ናስሩዲን የሁሉንም ምላሽ ንጉሡ እንብቦ ሲጨርስ፡- ‹‹በየዕለቱ የሚመገቡትን ዳቦ ምን እንደሆነ እንኳን በጋራ ለመወሰን የማይችሉ ሰዎች እንዴት በእኔ ላይ የተመሰረተውን ክስ በአንድ ተስማምተው መፍረድ ይችላሉ?›› በማለት ንጉሱን ጠየቀ:: ናስሩዲን አስከትሎም፡- ‹‹እነዚህ ሰዎች በየቀኑ ለሚመገቡት ዳቦ ምንነት የጋራ የሆነና የሚያስማማቸውን ትርጉም መስጠት ሳይችሉስ እኔ ስም አጥፊ ነህ ተብዬ ለቀረበልኝ ክስ የጋራ የሆነ ስምምነት ላይ እንዴት ይደርሳሉ ብለህ አሰብክ?››

ንጉሡም በናስሩዲን ሃሳብ ተደንቆ በነፃ እንዲሰናበት ከፈረደለት በኋላ፡- ‹‹ለመሆኑ እነዚህን ሰዎች እውነት አላዋቂ ናቸው ብለህ ሰብከሃል?›› በማለት ጠየቀው::

ናስሩዲንም እየሳቀ፡- ንጉሥ ሆይ! ፈላስፋውም ሆነ ሰባኪው እንዲሁም የሕግ ባለሙያው ሁሉም አላዋቂዎች ብቻ ሳይሆን ራሳቸውን እንኳን የማያውቁ ናቸው:: ለዚህም ነው ከእነሱ የቀደሙት ሰዎች የገለጡትን እውቀት እንደበቀቀን እየደገሙ አዋቂነታቸውን ለማሳየት የሚደክሙት›› በማለት ተሰናብቶት ሄደ::

ሱፊው ቢስታሚ ይህን ወግ መሠረት አድርገው የሚነግሩን ቁም ነገር ቢኖር ‹‹ታላቅ ሚስጥር ማለት የራስ ማንነት ነው፤ ይህን ምስጢር የገለጠም በእርግጥ አዋቂ ነው›› ይሉናል::

ሱፊው ሩሚ ደግሞ ይህን ሐሳብ ሲያጠናክሩልን፡- ‹‹ፈጣሪህን ፈልግ ራስህን ታገኛለህ፤ ራስህን ስትፈልግ ግን ፈጣሪህን ታገኛለህ›› ይሉናል:: ራስን መፈለግና ራስን መውደድ ግን ታላቅ ልዩነት እንዳለው ልብ እንድንል ሩሚ አክለውም ያሳስቡናል::

የዚህን ምዕራፍ ጉዳችንን የምንቋጨው በቀጣዩ የናስሩዲን ወግ

ይሆናል::

የናስሩዲን አህያ ይጠፋና በየመንደሩ እየዞረ በጩኸት ማስታወቂያ መንገር ይጀምራል፡- ‹‹ማንም አህያዬን ያገኘና ያመጣልኝ እሷኑ መልሼ እንደምሸልመው አስታውቃለሁ!››

ይህን የናስሩዲንን ማስታወቂያ የሰማ ጎረቤቱ፡- ‹‹ዕብድ ትመስለኛለህ፣ እንዴት አህያዬን ላገኘ መልሼ እሸልመዋለሁ ትላለህ?›› በማለት ሳቀበት::

በዚህ ጊዜ ናስሩዲን፡- ‹‹አየህ! ማንኛውም ነገር የአንተ ከመሆኑ በላይ ጠፍቶ ሲገኝ የሚሰማህ ደስታ ከፍተኛ መሆኑን ተረዳ›› አለው::

በቀጣይዋ ድንቅ የሱፊዎች አባባል ልሰናበት፡- ‹‹አንተን ከፈጣሪህ የሚሰርቅህን ነገር ሁሉ ፈጣሪ ከአንተ በመስረቅ ፍቅሩን ያሳይሃል::››

◻

pdf by @shuktus_books

# ‹‹ፈጣሪህን የምታምነው አስቀድመህ ማንነቱን ስታውቅ ብቻ ነው››

በሱፊዝም አስተምህሮትና ታሪኮች ዙሪያ ጉዞ ከመቀጠላችን በፊት ስለሱፊዎች በጥቂቱ እንበል፤-

ሱፊዝም ራሱን ከፈጣሪ ጋር የማዋሃድ እምነት ነው፡፡ ይኸ እምነት በዋነኛነት መሠረቱን የጣለው ደግሞ በእስልምና ሃይማኖት ላይ መሆኑ የሚካድ አይደለም:: ምንም እንኳን ሱፊዝም ከእስልምና እምነት አንዱ ሆኖ ይቆጠር እንጂ ሙስሊም ያልሆኑ በርካታ ሱፊዎችና እንዲሁም ሱፊዝምን የእስልምና እምነት እንደ ዘርፍ አድርገው የማይቀበሉ በርካታ ሙስሊሞች መኖራቸውን ደግሞ መረዳት ያሻል:: እንዲያውም ሁሉም ሀይማኖቶች ፈጣሪን ወደማወቅና መረዳት የሚያደርስ መንገድ እንደሚያዘጋጁ በሱፊዎች ተቀባይነት እያገኘ ከመምጣቱ ጋር በተያያዘ ሱፊዎች የሀይማኖቶች ድንበር የማያግዳቸውና አንድን ዓይነት ግብ የሚያራምዱ ሆነው ከመታየት ደርሰዋል::

በመሠረቱ በአንድ ሀይማኖት ውስጥ የሚገኝ ቅዱስ ሰው በሌላው ሀይማኖት ከሚገኘው ሌላ ቅዱስ ጋር እኩል የመሆኑ ምስጢር የሚገኘው ሁለቱም በአንዱ መለኮታዊ ምንጭ የመንቃቃታቸው እውነት መሆኑን ሱፊዎች አበክረው ይናገራሉ:: እናም አንድ ሰው ሱፊ የሚለውን መጠሪያ ማግኘት የሚችለው ፈጣሪውን ለማወቅ፣ ወደእሱም ለመድረስና አንድነት ለመመስረት የመቻሉን ብቃት በሕይወቱ ማሳየት ሲችል ብቻ ነው:: እንዲህ ዓይነቱን መንፈሳዊ መንገድ መከተል የቻለ ሰው ሱፊ የሚለውን የመጠሪያ ክብር

የሚጎናፀፈው ደግሞ የቃሉ ትርጉም በዋናኛነት የያዘውን እውነት በትርጉሙ ማሳየት በመቻሉ ነው:: ሱፊ ቃሉ በሁለት ቋንቋዎች ትርጓሜ ላይ የተመሠረተ ሲሆን በአረብኛ ‹‹የሱፍ ጨርቅ›› ሲሆን በፐርሽያ ደግሞ ‹‹ንፁህ›› ማለት ነው:: በመሆኑም አንድ ሰው የንፅህና መንገድን ተከትሎ ከፈጣሪው ጋር ሲዋሃድ የመጀመሪያው ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ምድራዊ ሕይወቱን መናቁና መካዱን ማሳያው የሆነው ዘወትር የሚለብሰው በዋጋ ዝቅተኛ የሆነው የሱፍ ጨርቅ ሊላው ይሆናል::

ሱፊዝም ሀይማኖታዊ አስተምህሮት ሆኖ ለመጀመሪያ ጊዜ ብቅ ያለው በመካከለኛው ምሥራቅ ሲሆን በዚያም የእስልምና እምነት በውስጡ የያዘውን እውነት በነቢዩ መሀመድ ቃል ላይ ተመስርቶ ማስተላለፍ ጀመረ:: በወቅቱ ከመምህር ወደ ደቀመዝሙር በማስተላለፍ ሂደት ሲከናወን የነበረው ፈጣሪን የመወደድና እሱንም የመከተል አስተምህሮት በሂደት የእስልምና እምነት የሻኢና ሱኒ የእምነት አንጓዎችን በውስጡ ሲያበጅ ሱፊዝምም ራሱን የቻለ አንድ አንጓ ሆኖ ብቅ ማለት ጀመረ:: በተለይም ሱፊዝም በመሠረታዊነት የሚያራምደው ራስን ዝቅ የማድረግና ማንነትን ለፈጣሪ የማስገዛት አካሄድ ጋር ተያይዞ አንድ ሀይማኖት ሥር ብቻ የሚቆም አስተሳሰብ ለማድረግ መሞከር እርስ በርሱ የሚጋጭ በመሆኑ የሱፊ ምሁራን እምነቱን በማንኛውም ሃይማኖት ሥር ለሚገኝ የሰው ልጅ ሁሉ የሚሰራ መሆኑን በማስተማር መንፈሳዊ መንገዱም በዚሁ አስተሳሰቡ የተቃኘ እንዲሆን አደረጉት::

(ስለሱፊዝም ሊሎች መሠረታዊ የሚባሉ አስተሳሰቦችን በቀጣዮቹ ምዕራፎች እልፍ እልፍ እያነሳን መዝለቃችን እንደተጠበቀ ሆኖ ወደተለያዩ ታሪኮቻቸውና አስተምህሮቶቻቸው በቀጥታ እናምራ::)

ሱፊው ጁናይድ ዘወትር በመንገዳቸው ላይ የምታጋጥማቸውና በጭንቀት ፈጣሪዋን የምታመልክ ሴት ተመልክተው ወደ ደቀመዝሙራቸው ዞረው፡-‹‹እየሀ! የፈጣሪህን ማንነት ሳታውቅ እምነዋለሁ ብትል እንደዚህች ሴት ጭንቀት ብቻ እንደምታተርፍ ተረዳ›› አሉት::

ደቀመዝሙር በዚህ ጊዜ ግራ ተጋብቶ ፡-‹‹መምህር ሆይ! ፈጣሪን ማመን እንዴት ጭንቀት ያተርፋል:: እምነት ማለት ከእሱ ጋር መንገዝ አይደለምን?›› በማለት ጠየቃቸው::

ጁነይዲም፡-‹‹ከእግርህ መጠን እጅግ ያነሰ ጠባብ ጫማ አጥልቀህ በመንገድ ላይ ጥቂት ደቂቃዎች ተጉዘህ ታውቃለህ:: የማታውቀውን ፈጣሪ እምነዋለሁ ማለትም እንዲሁ ነው›› አሉት::

ለዚህ ይመስላል ሱፊዎች ሲናገሩ፡-‹‹ፈጣሪህን በእውነት የምታምነው እስተድመህ ማንነቱን ስታውቅ ብቻ ነው›› የሚሉት:: እንዲያ ካልሆነ የአንተ እምነት በዘወትር የጥርጣሬ ስቃይ የታጀበ ሆኖ ይቀራል::

በሌላ ጊዜ ጁነይዲ ወዳጃቸው የሆነና አዘውትሮ የሚጎበኛቸውን አገረ ገገር በተራቸው ሊጎበኙት ወደቤቱ ይሄዳሉ:: ከአገረ ገገርው ቤት ሲደርሱ ከበሩ ላይ ዝናው በሰፊው የሚነገርለትን ጠባቂ ቆሞ አገኙት:: ይኸ ጠባቂ ዝናውን በሀገሩ ያገነነለት አንድ ተግባሩ ነብርን በዓይኑ ቁጣ ብቻ ሰውን ሳይተናኮል ከምድር ላይ እንዲተኛ ወይም ወደተዘጋጀለት የተከለለ ሥፍራ እንዲገባ የማድረግ ችሎታው ነበር:: ጠባቂው መምህሩ ጁነይዲን ከበር ተቀብሎ ወደአገረ ገገርው ቤት ሲያመሩ ግን እጅግ የሚያስፈራ ውሻ ከፊታቸው ቆሞ መጮህ ይጀምራል:: በዚህ ጊዜ ጁነይዲ ውሻው እንዳይተናኮላቸው በመስጋት ጠባቂውን አንድ ነገር እንዲያደርግና ከፊታቸው እንዲርቅ እንዲያዘው ጠየቁት::

ጠባቂው በዚህ ጊዜ ፈገግ ብሎ፡-‹‹መምህር ሆይ! ስንት ነገር ሲያውቁ እንዴት ይኼን ያጡታል? የሚጮህ ውሻ አኮ አይናከስም›› አላቸው::

ጁናይዲም መልሰው፡-‹‹ወዳጄ! ይኸን እውነትማ እንኳን እኔ አንተም ታውቀዋለህ፣ ጥያቄው ግን ውሻው ያውቀዋል ወይ? የሚለው ነው›› አሉት::

ከሱፊው ጁናይዲ አንድ እንመርቅ:: አንድ ልጅ የዘወትር ድርጊቱ ከበሮ መምታት ሆነና የሰፈሩ ሰው ተቸገረ:: በተለይም የከበሮው ድምጽ ነዋሪውን በማወኩ ልጁ ከድርጊቱ እንዲታቀብ ብዙ

ተመከረ፤ ነገር ግን አልሆነም:: በዚህ ጊዜ የሰፈሩ ነዋሪ ከሱፊዎች መላ ይገኛል በማለት ወደጁነይዲ ዘንድ በመምጣት ችግራቸውን አስረዱ:: መምህሩም አራት ደቀመዛሙርቶቻቸውን ልጁ ከበሮ እየደለቀ ከሚፈፅመው ረብሻ እንዲገቱት ላኩላቸው::

የመጀመሪያ ደቀመዛሙር ወደልጁ በመቅረብ ከፍተኛ ድምጽ ለጆሮ ጤንነት ጥሩ እንዳልሆነ በማስረዳት ተግባሩን እንዲያቆም መከረው:: ነገር ግን ልጁ በዕድሜው ትንሽ በመሆኑ እንዲህ አይነቱ የእውቀት ምክር ሊገባው የማይችል ነበርና በድርጊቱ ቀጠለ:: ሌላው ደግሞ ከበሮ የሚመታው ለሀይማኖታዊ ክብረበዓል ብቻ መሆኑን አስረዳው:: ሦስተኛው ነዋሪዎቹ ጆሮአቸውን በጨርቅ እንዲደፍኑ መከራቸው:: አራተኛው ለልጁ የተረት መጽሐፍ በመስጠት እያነበበ እንዲደሰትባቸው ነገረው:: ነገር ግን ልጁ ከበሮ በመምታት ከዚያ በሚወጣው ድምፅ መደሰትን ምርጫው በማድረጉ የሁሉንም ምክር አሻፈረኝ አለ:: የሰፈሩ ነዋሪም ተመልሶ ወደጁናይዲ በመሄድ ይኸንኑ አስረዳ::

በዚህ ጊዜ ጁናይዲ ተነስተው ልጁ ወደሚገኝበት ሥፍራ በመሄድ :-‹‹መያሻና ትንሽ መጥረቢያ ስጡት›› አሉ::

የሠፈሩ ነዋሪ ግራ ተጋብቶ፡-‹‹መምህር ሆይ! ልጁ ከበሮ በመምታት ፍቅር የተያዘ ነው:: የጠየቁት መሣሪያ ምን ያደርጋል?›› በማለት ጠይቁ::

ጁነይዲም፡-‹‹ልጁ የተያዘው ከበሮ በመምታት ፍቅር ሳይሆን ከከበሮ በሚያወጣው ድምፅ ነው:: የዚህን ድምፅ ምስጢር ደግሞ ለማወቅ ሰለሚሻ ዘወትር ከበሮውን ይደበድባል:: እናም በመያሻና በመጥረቢያ ተጠቅሞ የከበሮው ድምፅ ከየት እንዲሚወጣ መፈለጉ አይቀርምና ያን ጊዜ ታርፋላችሁ›› በማለት ወደገዳማቸው ተመልሰው ሄዱ::

ወደሱፊው ሩሚ እናምራ:: ታላቁ የሱፊ መምህር ሩሚ በጥበብ ስለመናገር ሲያስተምሩ አንዱ ደቀመዝሙራቸው፡-‹‹መምህር ሆይ! ጥበብ የተሞላበት ትምህርት እንዴት ያለ ነው?›› በማለት ጠየቀ::

ሩሚም፡-‹‹ዘወትር ስትናገር በሌሎች ዘንድ ጥያቄ የሚያስከትል

ንግግር ማስተላለፍህን ልብ በል›› አሉት:: ደቀመዝሙሩ ግራ ተጋብቶ በምሳሌ እንዲገለፁለት ጠየቃቸው::

‹‹ለምሳሌ በማርስ ላይ አንድ ሚሊዮን ሕዝብ ይኖራል፤ እኔም በመንፈስ አይቻቸዋለሁ›› ብትል ማንም ሊከራከርህ አይችልም:: ነገር ግን ‹‹የዛሬው ቀን ደስ ይላል›› ብትል‹‹ከትናንቱ ግን አይሻልም›› የሚልህ ቢያንስ አንድ ሰው አታጣም:: በደጃፍህ ላይ ‹‹እርጥብ ቀለም›› የሚል ምልክት ብትተክል ደግሞ ብዙም ሳይቆይ በምልክቱ ላይ በርካታ ጣቶች ሰፍረው ማየትህ አይቀሬ ነው›› በማለት አስረዱት::

አንድ ቀን ሩሚ ከምዕራብ ዓለም ከመጣ ጎብኚ ጋር በቤተመቅደስ አካባቢ ሲዘዋወሩ ጥቂት የቻይና ሰዎች አንድ አስከሬን በመከበብ የተለያዩ መዓዛ ያላቸውን የሚጨሱ እንጨቶች እያቃጠሉ ለሟቹ ክብር ሲሰጡ ተመለከቱ::

በዚህ ጊዜ ከምዕራብ ዓለም የመጣው ሰው በሰዎቹ ድርጊት ተደንቆ፡-‹‹መምህር ሩሚ! እነዚህ ቻይናውያን የሟቹን አስከሬን እንደዚህ በጢስ ማጠናቸው ሞኝነት አይመስልዎትም?›› በማለት ጠየቃቸው::

ሩሚም በአግራሞት እየተመለከቱት፡-‹‹ከእናንተ ድርጊት ብዙም የተለየ ነገር ግን አላየሁበትም፤ እናንተስ በሙታኖቻችሁ መቃብር ላይ አበባ የምታስቀምጡት ምን እንዲያደርጉት ይሆን?›› በማለት ጠይቁት::

በመግቢያችን ላይ በጥቂቱ ለማየት እንደሞከርነው ሱፊዝም ለፈጣሪ ራስን የመስጠት ልምምድ ነው:: በዚህ ልምምድ ውስጥ ፈጣሪህን ወደማወቅ ስትደርስ ምድራዊው ሕይወት ለአንተ የፈጣሪን ክብርና ጥበብ የምትገልጥበት ከመሆን ያለፈ ምስጢርም ሆነ ቁምነገር የለውም:: ይኸ ዓይነቱ ሕይወት ደግሞ በሱፊ መምህራን ዘንድ ብቻ ሳይሆን አስተምህሮቱን ተቀብለው የዓለማዊ ሕይወታቸውን ዘይቤ በዚያ መንገድ በቃኙ ሰዎችም ዘንድ የሚገለጥ መሆኑ ይታመናል:: ለዚህም ነው ሱፊዝም መሠረቱ እስልምና ይሁን እንጂ በሌሎች ሀይማኖት ተከታዮች ዘንድም ይኸው አስተሳሰብ ሲገለጥ

የሚስተዋለው:: ቀጣይዋ ወግ ይኸንኑ የምታሳይ ትመስለናለች::

አንድ አባት ለረዥም ዓመታት የሱፊ ትምህርት ሲከታተል ቆይቶ የተመለሰ ልጁን ከእንቅልፉ ቀስቅሶ፡‹‹ልጄ! ዘወትር በማለዳ መነሣትን ልምድህ አድርግ ፤መልካም ልምምድ ነው›› አለው::

ልጁም፡‹‹ በማለዳ መነሣትን መልካም የሚያደርገው ምን ይሆን?›› ሲል አባቱን ጠየቀው:-

አባቱም መለሰ፡‹‹አንድ ቀን በማለዳ ተነስቼ በጎዳና ላይ እየተጓዝሁ እግሬን ሳፍታታ በከረጢት የተሞላ ወርቅ አግኝቻለሁ›› አለው::

በዚህ ጊዜ ልጁ፡‹‹ለመሆኑ ወርቁ ባለፈው ሌሊት የጠፋ እንዳልሆነስ በምን አወቅህ? በዚያ ሥፍራ ከወደቀ ብዙ ቀናትን ያስቆጠረና ሰዎች ልብ ሳይሉ ያለፉት ሊሆንስ አይችልም?›› አለው::

አባትም፡‹‹ ቁምነገሩ እሱ አይደለም:: ከዚያ ማለዳ በፊት ከረጢቱ በሥፍራው እንዳልነበር እርግጠኛ ነበርኩ:: ሥፍራውን በየቀኑ ሳልፍ እመለከተዋለሁና›› አለው::

ልጁ ግን በማቅማማት ፡‹‹ነገር ግን በማለዳ የሚነሣ ሰው ሁሉ ዕድለኛ ነው ብለህ አባቴ እንዳታስብ እመክርሃለው:: ቢያንስ ወርቁን የጣለው ሰው ከእኔ ቀድሞ በማለዳ ከቤቱ መውጣቱ አይቀርምና›› አለው::

ሱፊዝም ሕይወትን በአንድ መነፅር ከመመልከት የምታላቅቅህና እያንዳንዱን ገጠመኝህም በተለየ ጥበብ እንድትመረምር የምታደርግህ መሆኗን ከተከታዮቿ አኗኗር መረዳት ይቻላል:: የምዕራፉን የሱፊዝም ጉዞ የምንቋጨው የዚሁ እምነት ዋነኛ ምሳሌ ተደርጎ ዘወትር በሚጠቀሰው ሙላ ናስሩዲን ይሆናል::

አንድ ቀን ናስሩዲን በሰፈሩ ከሚገኝ ሱቅ በመሄድ ባለቤቱን ‹‹ቆዳ ይኖርሃል›› ሲል ጠየቀው::

ባለሱቁም፡‹‹አለኝ›› አለ::

ናስሩዲንም፡- ‹‹ሚስማርስ አለህ?›› ሲል ጠየቀ::

ባለሱቁ፡‹‹አለኝ›› ሲል በድጋሚ መለሰ

ናስሩዲን አሁንም ጠየቀ፡- ‹‹ክርስ አለህ?›› አለው::

ባለሱቁም መለሰ፡- ‹‹ክር አለኝ›› አለ::

‹‹መርፌስ አለህ?›› ሲል ናስሩዲን ጠየቀው

ባለሱቁ አሁንም በትዕግስት ፡-‹‹መርፌም አለኝ›› የሚል ምላሽ ሰጠ::

በዚህ ጊዜ ናስሩዲን በአግራሞት እየተመለከተው፡-‹‹ታዲያ ለምንድነው ሱሪማ ሰፍተህ የማትሸጠው?›› በማለት ስቆበት ሄደ::

አንዳንድ ጊዜ የሙላ ናስሩዲን ድርጊት ሞኝነት ይመስላል የሚሉን ደግሞ ቀጣይዋን ወግ ያቀርቡልናል::

አንድ ቀን ሙላ ናስሩዲን በቤቱ መስኮት በኩል ግማሽ አካሉን አውጥቶ ዳቦ ወደመንገዱ ሲወረውር የተመለከተ ጎረቤቱ፡-‹‹ናስሩዲን! ምን እያደረግህ ነው?›› በማለት ተገርሞ ጠየቀው::

ናስሩዲንም፡- ‹‹ከእዚህ አካባቢ ነብሮች እንዲርቁ ነው›› አለው::

ጎረቤቱም መገረሙ ጨምሮ፡-‹‹ነገር ግን እዚህ አካባቢ እኮ ነብር የለም›› አለው::

ናስሩዲንም ፈገግ ብሎ፡-‹‹አየህ! ድርጊቱ ውጤታማ ሆኗል ማለት ነው›› በማለት መስኮቱን ዘግቶ ተመለሰ::

ምንም እንኳን ይህ የናስሩዲን ድርጊት እንደሞኝነት የሚቆጥር ነው የሚሉ ቢኖሩም በእንፃሩ በሕይወት ውስጥ የሰው ልጅ እንደጥበብ ቆጥሮ የሚፈፅመው ተግባር ለጥያቄውም ሆነ ለጭንቀቱ ምላሽ የሚያስገኝለት አድርጎ እንዲቆጥር ያደረገው የራሱ ሞኝነት መሆኑን ናስሩዲን ለማሳየት የተጠቀመበት ጥበብ ነው የሚሉ ደግሞ በርካታዎች ናቸው::

በቀጣይዋ የናስሩዲን ወግ ሱፊዎችን ለጊዜው እናሰናበታለን::

አንድ ቀን በሀገሩ የታወቀ ምሁር ናስሩዲንን፡-‹‹ዕጣ ፋንታ ምንድነው? ሲል ጠይቀው::

ናስሩዲንም፡-‹‹አንዱ በአንዱ ላይ ተዕዕኖውን እያሳረፈ የተያያዘ የህይወት ክስተት ነው›› አለው::

በናስሩዲን ምላሽ ምሁሩ ግራ ተጋብቶ ፡-ይኸ በፍፁም በቂ ምላሽ ሊሆን አይችልም:: በሕይወት ውስጥ በሚከሰት ምክንያትና

ውጤት እምናለው:: ዕጣ ፋንታም አንድ ምክንያትን የያዘ ውጤት ነው›› አለው::

በዚህ ጊዜ ናስሩዲን በፊት ለፊታቸው በሰዎች ተከቦ ሊገደል ወደሚወሰድ ሰው ጣቱን ጠቁሞ ፡-‹‹ይኸን ሰው ተመልከት›› አለውና፡- ‹‹ሰውዬውን በስቅላት ሊቀጡት እየወሰዱት ነው:: የፈፀመው ወንጀል ደግሞ በስለት ሰውን ወግቶ መግደል ነው:: ለመሆኑ የዚህ ሰው ዕጣ ፋንታ በስቅላት መገደል እንዲሆን ያደረገው ሰው መግደሉ ነው? ወይስ ስለት እንዲገዛ ገንዘብ የሰጠው ሰው? ወይስ ሰው ሲገድል ሌላ ሰው ሊመለከተው በመቻሉ? ወይስ ሰው ከመግደሉ በፊት ከድርጊቱ ሊያስቆመው የፈለገ ሰው ባለመኖሩ? እንግዲህ የእያንዳንዳችንም ዕጣ ፈንታ ውጤቱ አንድ ይመስላል እንጂ ከብዙዎች ሕይወት ጋር የተያያዘ የሕይወት ክስተት ነው›› በማለት አስረዳው:: □

pdf by @shuktus_books

## ‹‹ጥበብ የምትፀነሰው ሊሎችን ከማድመጥ፣ የምትወለደው ደግሞ ራስን በማድመጥ ነው››

ባለፈው ሱፊዎችን በቃኘንበት ምዕራፍ የመካከለኛው ምስራቅ ሀገራት ጠቢብ ሙላ ናስሩዲንን እግረ መንገድ አንስተነው ነበር:: እነሆ በቀልድ በተዋዙት የሙላ ናስሩዲን ፍልስፍናዊ አስተሳሰቦች ዙሪያ በስፋት ጉዞ ማድረግ እንጀምራለን:: ስለ ሙላ ናስሩዲን ማንነት በጥቂቱም ቢሆን ለማሳየት የሞከርኩት እንደተጠበቀ ሆኖ ለጉዟችን ያግዘን ዘንድ ደግሞ በድጋሚ ላስታውሳችሁ::

ናስሩዲን በተለይ በመካከለኛው ምስራቅ ሀገራት ዘንድ በጠቢብነቱ የሚታወቅና በ1300 ዓ.ም በተለይ በዛሬዋ ኢራን አብዛኛውን የሕይወት ዘመኑን እንደኖረ የሚታመን ጠቢብ ሰው ነበር:: ናስሩዲን በተለያዩ የሕይወት ገጠመኞች ውስጥ እየተገኘ የሚሰጣቸው ምላሾችና ገጠመኞቹንም የሚመለከትበት አቅጣጫ በእርግጥም ጠቢብነቱንና የተለየ አሳቢነቱን የሚያረጋግጥ ነው የሚሉን እስከዘመናችን ድረስ የዘለቁ አሳብያን በርካታ ናቸው:: ለዚህም ነው ከናስሩዲን ወጎችና ቀልዶች ሰምተን በፈገግታ ማለፍ ብቻ ሳይሆን በፍልስፍናዊ ምልከታውም እንደነቅ ዘንድ ግድ የሚለን::

በናስሩዲን ዘመን በጥበብ የታነፀ፣ በዕውቀትም የነቃ ሰው ማህበረሰቡ የሚገባውን ክብር ከሚቸርበት መንገድ አንዱ ለሰው የሚሰጠው ሌላ የክብር ወይም የማዕረግ መጠሪያ ነበር:: በዚህም መሠረት ‹‹ሙላ፣ ሆጃ ወይም ሆካ›› የሚሉት ማዕረጎች ከስሙ በፊት መጠሪያው ያደረገ እሱ ጠቢብ ሰው መሆኑን ማህበረሰቡ በቀላሉ መለየት አይቸግርም:: ለዚህም ነበር ‹‹ሙላ›› የሚል ማዕረግ ናስሩዲን በመካከለኛው ምስራቅ ባሉ ሀገራት ሁሉ ተንናዕ

የኖረው:: ይሁንና የናስሩዲን ጠቢብነት ደግሞ መገለጫው የተለያየ መልክ እንደነበረው ማስታወስ ያሻል:: አንዳንድ ጊዜ እጅግ ጠቢብ ሆኖ የምናገኘው ሙላ ናስሩዲን በሌላ ቦታ ደግሞ ቀልደኛ ወይም ደግሞ ሞኝ ሆኖ ማየታችን የጠቢብ መምህር ወይም የፈላስፋ ባህርይ ከዚህ የራቀ አለመሆኑን እንድንረዳ ያደርገናል እንጂ ለእሱ የሚኖረንን ግምት ዝቅ የሚያደርገው አይሆንም::

በአብዛኞቹ የመካከለኛው ምስራቅ ሀገራት የሙላ ናስሩዲን ቀልዶች፣ ወጎችና ተረቶች በስፋት ከመነገራቸው ባሻገር ናስሩዲንን የእነሱ ዜጋ እንደነበር አድርገው የማቅረቡ ነገር አሁንም በስፋት ይታያል:: የናስሩዲንን ታሪክ በስፋት ያጠኑ ግን ከናስሩዲን ማንነት ይልቅ በአስተሳሰቡ ላይ ማተኮር የተሻለ ነው ይላሉ:: እኛም ከእነሱ ጋር በመስማማት የናስሩዲንን ሀገራዊ ማንነት ወደጎን አስቀምጠን ዓለም አቀፋዊ ይዘት ያላቸውን ጥበባዊና ፍልስፍናዊ የሕይወት ምልከታዎቹን ወደ መፈተሽ እናምራ:: በሙላ ናስሩዲን ፈለግ ስንጓዝ በቅድሚያ የምናገኘው ደግሞ የዓለም መጨረሻን አስመልክቶ በአንድ ፈላስፋ ለተጠየቀው በሰጠው ምላሽ ይሆናል፡-

ፈላስፋ፡- ‹‹ሙላ፤ የዓለም መጨረሻ መቼ የሚሆን ይመስልሃል?››

ናስሩዲን፡- ‹‹ስለየትኛው ዓለም መጨረሻ ነው የምትጠይቀኝ?››

ፈላስፋ፡- ‹‹ስንት የዓለም መጨረሻ ይኖራል?››

ናስሩዲን፡- ‹‹ሁለት!?››

ፈላስፋ፡- ‹‹እንዴት ሆኖ? አስረዳኝ!››

ናስሩዲን፡- ለእኔ የመጀመሪያው የዓለም መጨረሻ ሚስቴ ስትሞት ነው፤ ሁለተኛው ደግሞ እኔ ስሞት ይሆናል?››

በቀልድ ተዋዝቶ በቀረበልን በዚህ የሙላ ናስሩዲን ምላሽ ውስጥ አንድ የምንረዳው ቁም ነገር የእያንዳንዱ ሰው የዓለም መጨረሻ መገለጫው የራሱ ሕልፈተ ሕይወት (ሞት) እንጂ ሌላ አይደለም የሚለውን ነው::

ወደ ሌላዋ የናስሩዲን ፍልስፍናዊ አስተሳሰብ ወደምታሳይ ወግ ደግሞ ስንሻገር ቀጣይዋን እናገኛለን::

አንድ ቀን በመንደሩ በጠቢብነቱ የሚታወቅ ሰው ወደ ናስሩዲን ቤት በመምጣት ስለ ሰፈሩ፣ የግል ሕይወታቸውን፣ ስለ ቤተሰብ፣ ሥራ እንዲሁም ፍልስፍናዊ ርዕሰ ጉዳዮች አስመልክቶ ሲጨዋወቱ

ቆይተው ሰውዬው ለመሄድ ተነሳ::

‹‹ናስሩዲን! አሁን ወደ ቤቴ መሄድ ይኖርብኛል›› አለ ሰውዬው

‹‹ይቅርታ ወዳጄ!›› አለ ናስሩዲን በበኩሉ እየተነሳ፡- ‹‹ግን አንተ ማነህ?›› በማለት ጠየቀው::

‹‹የእኔን ማንነት አላውቅም እያልከኝ ነው ናስሩዲን?›› በማለት ሰውዬው ግራ ተጋብቶ ይመለከተው ጀመር::

‹‹በፍፁም አላወቅሁም›› አለ ናስሩዲን በድጋሚ::

‹‹እስካሁን በብዙ ጉዳዮች ላይ ስንጨዋወት መቆየታችንንስ ረስተኸዋል?›› አለ ሰውዬው::

‹‹በእርግጥ ልብስህ፣ ድምፅህን እንዲሁም ጫማህን ስመለከተው አንድ የማውቀው ሰው መስለኸኝ ነበር›› አለ ናስሩዲን ፈርጠም ብሎ::

‹‹ማንን ይሆን?›› አለ ሰውዬው እስካሁን ባለመታወቁ ቅር እያለው::

‹‹እኔን›› አለ ናስሩዲን::

የናስሩዲን የሕይወት ምልከታዎች ከማንኛውም ተራ ሰው የተለዩ መሆናቸውንም የምንረዳው እንዲህ ዓይነት አስተሳሰቦች ሲያጋጥሙን ነው:: ከዚህ ጋር አብራ የምትሄድና ተመሳሳይነት ያላትን የናስሩዲን ፍልስፍና እዚህ ላይ እንመልከት::

አንድ ቀን ናስሩዲን በመንገድ ሲጓዝ በታላቅ መምህርነታቸው የሚታወቁ የቡድሂዝም መነኩሴ ጋር ይገናኛል:: ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ መምህሩ ‹‹ይገርምሃል! ከራሴ ፈፅሞ የመላቀቅ ደረጃ ላይ ደርሻለሁ:: በዚህም ስለ ራሴ ማሰብም ሆነ ማሰላሰል በማቆም አእምሮዬ በሌላው የሰው ልጅ ነገር የተያዘ ሆኗል፣ በእኔም ውስጥ የምመለከተው ሌሎችን ነው›› አሉት::

ናስሩዲንም ‹‹እኔ ግን ከዚያ ባለፈ ደረጃ ላይ መድረሴን ልነግርዎት እወዳለሁ›› አላቸው::

በዚህ ጊዜ መምህሩ ተደንቀው፡- ‹‹እንዴት ይሆናል?›› በማለት ጠየቁት::

ናስሩዲንም ‹‹አንድን ሰው ተመልክቼ በእሱ ውስጥ በእርግጠኝነት ራሴን መመልከት ችያለሁ፣ በዚህም ከምንጊዜውም በላይ ስለ ራሴ ብቻ ማሰብ ችያለሁ›› አላቸው::

እንግዲህ የቱንም ያህል በዕውቀት የመንቃት ደረጃችን የላቀ ይሁን የሰው ልጅ ከራሱ አስበልጦ ስለ ሌላው ማሰብ የሚችል ብቃት እንደሌለው ናስሩዲን ተረዱ ይለናል:: ወደ ናስሩዲን የግል ሕይወት ደግሞ እንምጣ::

ሙላ ናስሩዲን ከሕይወት ገጠመኙ ሁሉ ዘወትር አስበልጦ የሚማረርበት ጉዳይ ቢኖር የትዳር ሕይወቱ ነው:: ነገሩን በሚስቱ፥ ፍላጎቱን በትዳሩ የተነጠቀ ሰው ሆኖ ከምናየው ናስሩዲን ቀጣዮቹን ወጎች ስንቆነጥር ብዙዎች በናስሩዲን የትዳር ቀልዶች የሚገነዙት «ትዳር» በሚባለውና አንድ ወንድና ሴት ወደውና ፈቅደው ኮንትራት በሚገቡበት ተቋም ላይ በድብቅ የሚያብሰለስላቸውን ሐቅ ይፋ በማውጣቱ ይመስለናል::

አንድ ቀን የናስሩዲን አህያ ትጠፋና በከፍተኛ ሐዘን ተውጦ ማልቀስና መጮህ ይጀምራል:: በዙሪያው የተሰበሰቡት ሊያፅናኑትም ቢሞክሩ አሻፈረኝ ብሎ ማልቀሱን እንደቀጠለ የቅርብ ጓደኛው ወደ እሱ ቀረብ ብሎ እጁን ያዘው::

«ስማ ናስሩዲን! አህያህ መጥፋቱን ለምን እንደዚህ ታላቅ ሐዘን እንዳደረግኸው አልገባኝም፤ የመጀመሪያዋ ሚስትህ ስትሞት እንኳን እንደዚህ እንዳላዘንህ ልብ አላልክም?» አለው::

ናስሩዲንም፦ «ነገር ግን ሚስቴ ስትሞት ሁላችሁም ሌላ ሚስት እናመጣልሀለን በማለት ስታፅናኑኝ ነበር፤ ዛሬ ግን ማንም ሌላ አህያ አመጣልሃለሁ ያለኝ አላገኘሁም» በማለት ልቅሶውን ቀጠለ::

እንግዲህ የናስሩዲን የትዳር (የሚስት) ዋጋ እንዲህ ዝቅ ያለበትና ምሬት የሞላበት ምክንያቱ ምናልባት የትዳር ሕይወትን እሱ የተመለከተበት መነፅር ከሌሎች በእጅጉ የተለየ መሆኑን መገመት ይቻላል:: ወደ ቀጣዩ የናስሩዲን የትዳር ወግ ደግሞ እልፊን እንመልከት::

ናስሩዲን አንድ ቀን ወደ መንደሩ ዳኛ ዘንድ በመሄድ ከሚስቱ መፋታት እንደሚፈልግ ይነግራቸዋል::

ዳኛውም ነገሩን ካደመጡ በኋላ የናስሩዲንን ጥያቄ በመቀበል እላቸው በተራቸው ይጠይቁት ጀመር::

«ለመሆኑ የሚስትህ ስም ማን ይባላል?» አሉ ዳኛው::

ናስሩዲን «አላውቀውም» ሲል መለሰ::

በስሙጭው ምላሽ የተደነቁት ዳኛው ግራ ተጋብተው፡- ‹‹አብራችሁ ስትኖሩ ስንት ዓመት ሆናችኋል?›› አሉ::

‹‹አምስት ዓመት›› በማለት ናስሩዲን መለሰ::

‹‹አምስት ዓመት ከሚስትህ ጋር አብረህ በትዳር ስትኖር ስሟን አታውቀውም?›› በማለት ዳኛው መደነቃቸው ብሶ ጠየቁት::

‹‹ትክክል ነው›› አለ ናስሩዲን እርግጠኝነቱን በመግለፅ::

‹‹እንዴት ሊሆን ይችላል?›› አሉ ዳኛው::

‹‹ምክንያቱማ ከእሷ ጋር ምንም አይነት ማህበራዊ ግንኙነት አልነበረኝማ!›› በማለት ናስሩዲን አስረዳቸው::

የሙላ ናስሩዲን መንፈስ ከትዳር የራቀው እንግዲህ ምን ያህል እንደሆነ በቂ ማሳያ ትመስለናለች:: በፍቅር፣ በፍላጎትና በነፃነት ላይ ያልተመሰረተና ማህበረሰቡ ከገቡ የማይወጡበት አድርጎ ያዋቀረው የትዳር ተቋም ለናስሩዲን የዘወትር ሕመሙ ነበር:: ቀጣይዋን በተመሳሳይ ሃሳብ ላይ ያነጣጠረች ወግ እንመርቅ::

አንድ ቀን የናስሩዲን መንደር ሰዎች በከፍተኛ ሐዘንና ቅሬታ ተሞልተው ወደ ቤቱ መጡና ከመካከላቸው በዕድሜ የገፉት ያዘኑበትን ምክንያት እንዲህ ገለፁለት፡-

‹‹አየህ ናስሩዲን! ሚስትህን ዘወትር በዚህ መንደር ማልዶ እስኪመሽ ስትዞር መዋልን ሥራዬ ብላ ከያዘችው ቆይታለች:: እንዲህ ከአንዱ ቤት ወደ ሌላው ሲዞሩ መዋል ደግሞ ለሴት ተገቢ ያልሆነና ነውርም ነው:: ስለፈጣሪ ብለህ ሚስትህ እንዲህ መንደሩን ስታካልል መዋሏን እንድትከለክላት ልንነግርህ መጥተናል›› አሉት::

ናስሩዲንም፡- ‹‹አታስቡ! ወደቤት ከመጣች ቅሬታችሁን እነግራታለሁ›› በማለት አሰናበታቸው::

ከናስሩዲን የትዳር ሕይወት ወጣ ብለን ደግሞ ቀጣይዋን ፍልስፍናዊ ብርሃንን የያዘች ወግ እንመልከት::

አንድ ቀን ናስሩዲን ወንዝ ለመሻገር በውሃው ጥልቀት ፍርሃት አድሮበት ከዳር ቆሞ ይመለከታል:: በዚህ ጊዜ ከወንዙ በሌላ አቅጣጫ ቆሞ እንደ እሱ ለመሻገር የፈለገና ፍርሃት ያደረበት ሰው ናስሩዲንን በጩኸት ይጠራዋል::

‹‹ናስሩዲን! እባክህ እንዴት ነው ወንዙን መሻገር የምችለው?›› በማለት ጮኸ::

በዚህ ጊዜ ናስሩዲን፡- ‹‹ተሻግረሃል እኮ!›› በማለት መለሰለት::

እንዲሁ በሕይወት ውስጥ ለምናነሳው ማንኛውም ጥያቄ ምላሽ ብለን የምንይዘው የእኛን ፍላጎትና ሃሳብ ወይም ምኞት የያዘውን እንጂ በእርግጥ መልዕክቱ ለሁሉም የሚሰራ እውነታነት ያለው በመሆኑ አይደለም:: ለዚህም ነው ከወንዙ በሁለቱም ዳርቻ ለቆሙ ሰዎች ጥያቄአቸው መሻገር ቢሆንም መልሱ ግን በሁለቱ ፍላጎት ላይ ተመስርቶ ሊለያይ የቻለው::

ለናስሩዲን የጠቢብነት ምስጢሩ ከጠቢባን ዘንድ ቀርቦ መስማትና ከእነሱ መማር ብቻ አይደለም፣ ነገር ግን ለሌሎች የሚያስተምሩትን ለራስ የማዳመጥ ብቃትም ማግኘት ነው:: ‹‹ጥበብ የምትፀነሰው ሌሎችን ከማድመጥ ሲሆን የምትወለደው ደግሞ ራስን በማድመጥ ይሆናል›› ይለናል ናስሩዲን::

በዘመኑ ሁሉ ‹‹የእኔ ሃይማኖት ፍቅር ነው›› በማለት የሚታወቀው ናስሩዲን ስለሚኖርበትም ሆነ ስለመጪውና ትሂድበታለህ ስለሚሉት ዓለም የሚጨነቅ ሰው አልነበረም:: ለዚህም ነው በመግቢያችን ላይ ስለዓለም መጨረሻ ተጠይቆ በትዳሩና በእሱ የገለፀውን እውነት ይበልጥ አጠንክሮ በቀጣዩ ወግ የሚያቀርብልን:: እኔም በዚህች ወግ ለጊዜው የናስሩዲንን የዚህ ምዕራፍ ጉዞ እቋጫለሁ::

አንድ ፈላስፋ ወደ ናስሩዲን ዘንድ በመምጣት፡- ‹‹ለበርካታ ዓመታት የዓለም መጨረሻ መቼ እንደሚሆን ስመራመር፣ ሳሰላስልና ስፈትሽ ኖሬያለሁ:: ነገር ግን ልደርስበት አልቻልኩም:: ለመሆኑ በአንተ ዘንድ ይኼ ምስጢር ይገኝ ይሆን›› በማለት ጠየቀው::

ናስሩዲንም፡- ‹‹ይኼንንማ ካወቅሁት በርካታ ዓመታት አልፈዋል›› ሲል መለሰለት:: ፈላስፋውም፡- ‹‹እባክህን ይኼን እውቀትህንማ ልታካፍለን ይገባል:: ለመሆኑ የዓለም መጨረሻ መቼ ይሆን?›› በማለት በድንጋጤ ጠየቀው:: ‹‹የዓለም መጨረሻ የሚሆነው እኔ ስሞት ነው›› በማለት መለሰለት:: ‹‹እርግጠኛ ነህ? እንዴት አንተ ስትሞት ለእኛ የዓለም መጨረሻ ይሆናል?›› አለ ፈላስፋው በጥርጣሬ::

ናስሩዲንም ፈገግ ብሎ፡- ‹‹ቢያንስ ለእኔ ይሆናል›› ሲል አረጋገጠለት:: □

# ‹‹እውነት ማለት
# የምታውቀው ነገር ብቻ ነው››

በቀልዱ እያዋዛ አስተማሪና አመራማሪ የሆኑ ፍልስፍናዊ ቀልዶችን የተመለከትንበት የመካከለኛው ምስራቅ ጠቢብ ሙላ ናስሩዲን አሁንም ከእኛ አልተለየምና በዚህም ምዕራፍ መቆያችን እንዲሆን ወደድን:: እንግዲህ ስለሙላ ናስሩዲን ስናነሳ ዘመናትን የተሻገረ ተወዳጅነት ያተረፈለት ሳቅን ከሚጭሩ ቀልዶች ይልቅ ሕይወትን የሚመለከትበት የተለየ መነፅር የመሆኑ ጉዳይ ነው:: ይህ ምልከታው በአብዛኛው ፍልስፍናዊ ይዘቶችን የተሸከመ ከመሆኑ አንፃር ናስሩዲን ከሌላው ሰው የተለየ የሚሰብክና በተለየ አቅጣጫ ነገሮችን የሚመለከት ብቃትን የታደለ ልዩ ሰው አድርጎት ኖሯል:: የናስሩዲንን ጉዞ በቀጣይዋ ወግ ስንጀምር ይህንኑ የእሱን ልዩ የማሰብ ብቃት የምታረጋግጥልን ትሆናለች::

አንድ ቀን የሀገሪቱ የሃይማኖት መሪ ናስሩዲንን በመኖሪያ ቤታቸው የእራት ግብዣ ጥሪ ያቀርቡለትና አመሻሽ ላይ ጥሪውን አክብሮ ይገኛል::

የእራት ግብዣውን አስታውሶ ዕለቱን ብዙም ምግብ ያልቀመሰው ናስሩዲን በሃይማኖት መሪው መኖሪያ ቤት ሲደርስ እጅግ ተርቦ ነበርና እንደደረሰ ምግብ እንዲያቀርቡለት ተመኘ::

ይሁንና አንዳች የሚመገበው ነገር ሳያቀርቡለት የሀይማኖት መሪው ስብከት ጀመሩት:: ሁለት ሰዓታትን ያህል በሀይማኖታቸው ውስጥ ታላላቅ ገድል ስለፈፀሙ ሰዎች ያለ ዕረፍት ሲሰብኩ ናስሩዲንም ሲሰማ ቆየ::

በመጨረሻ ግን የናስሩዲን ትዕግስት እየተሟጠጠና ረሃቡም እየፀናበት በመምጣቱ የሃይማኖት መሪውን ስብከት ድምፁን ከፍ አድርጎ አቋረጠና፡- ‹‹ይቅርታ! አንድ ጥያቄ ባቀርብልዎ ደስ ይለኛል›› አላቸው::

‹‹ምን ይሆን?›› አሉ የሃይማኖት መሪው ከስብከታቸው ጋር የተያያዘ ጥያቄ ሊያነሳላቸው መሆኑን በመገመት ደስ ተሰኝተውና ለማብራራትም እየተዘጋጁ::

‹‹እኔን የደነቀኝና ሊጠይቅዎ የፈለግሁት እስካሁን በነገሩኝ ታሪክ ውስጥ የሚገኙ ሰዎች ምግብ ተመግበው ያውቃሉ?›› አላቸው::

እንግዲህ ለናስሩዲን የሕይወት እውነታ በአሁን ፍላጎትና ስሜት ብቻ ሊገለፅ የሚችል ተደርጎ ከመወሰዱ ላይ ነው:: ናስሩዲን ምንም እንኳን አብዛኛዎቹ ንግግሮቹና ድርጊቶቹ ሳቅን የሚጭሩና በቀልድ የተዋዙም ቢሆኑ ጥበብና ዕውቀትን በእጅጉ የተሞሉ መሆናቸው ደግሞ የብዙዎቹን ታላላቅ አሳብያንና ጠቢባን ቀልብ የሚገዛ መሆኑ አልቀረም:: በተለይ ደግሞ የሱፊዝም እምነት አራማጆች የአስተምሮታቸው ዋነኛ መንገድ የናስሩዲን ወጎች የመሆናቸው ጉዳይ ብዙዎች በእሱ ቀልድ ስቀው ማለፍ ብቻ ሳይሆን በውስጡም ጥበብና ቁምነገርን ዘወትር መፈለጋቸው አልቀረም:: ለምሳሌ ቀጣይዋን የናስሩዲን ድርጊት ስንመለከት ምናልባት ጤነኛነቱን የሚጠራጠሩ ቢኖሩም የሱፊ ታላላቅ ምሁራን ግን በውስጡ ታላቅ ቁም ነገር መኖሩን ያምናሉ::

ሙላ ናስሩዲን ወደየትም ሥፍራ ለሥራም ሆነ ለመዝናናት ሲንቀሳቀስ የቤቱን በር ተሸክሞ ነበር:: ይህንን ድርጊቱን የተመለከቱ ግማሾቹ መሳቃቸው የቀሩት ደግሞ መገረማቸው አልቀረም:: እናም አንዳንዶቹ ‹‹ናስሩዲን! የቤትህን በር ተሸክመህ የምትሄደው ለምንድነው?›› በማለት ሲጠይቁት እሱም በምላሹ ‹‹ለጥንቃቄ የወሰድኩት እርምጃ ነው፣ በር በሌለው ቤት ማንም ለመግባት የሚፈልግ የለም፤ ስለዚህም በሩን ነቅዬ ተሸክሜው እዞራለሁ›› በማለት መለሰላቸው::

ናስሩዲን ከሞተ በኋላ ደቀመዛሙርቱ የቤቱን በርና ቁልፍ

ከመቃብሩ አጠገብ ማስተመጣቸውም ለዚህ ነው ይባላል:: ይሁንና ናስሩዲን በዚህ ድርጊቱ ውስጥ ያስተላለፈው አንድ ጥበብ ደግሞ አለ፣ የሚሉን ሱፊው ሩሚ ‹‹ወደማንኛውም ስውተት የምትሸጋገርበት በር የራስህ አእምሮ እንጂ ሌሎች በአንተ ላይ የሚገጥሙት አስተሳሰብ አይደለም›› ይሉናል::

የናስሩዲን ቀልዶችና ወጎች በአንድ በኩል ከሚስቱ (ትዳሩ) ጋር በእጅጉ ተቆራኝተው የሚነገሩ ናቸውና ወደዚያው እናምራ:: ለናስሩዲን ትዳር ማለት ነፃነቱን አስረክቦ መሻትና ፍላጎቱን የወሰደበት ክስተት ነው:: ከዚህም የተነሳ ይመስላል ሚስቱን እንድም ቦታ በመልካም ሲያነሳት አይታይም:: ቀጣዩዋን ወግ እንመልከት::

አንድ ቀን ናስሩዲን ሥጋ ገዝቶ ይመጣና ለሚስቱ ከባብ የተሰኘውን ጣፋጭ ምግብ እንድታዘጋጅ ይሰጣታል:: ይሁንና ሚስቱ ምግቡን ካዘጋጀችለት በኋላ ስትቀምሰው በጣም ስለጣፈጣት ጥርግ አድርጋ በላችው::

ናስሩዲን ሲዞር ከዋለበት ተመልሶ ምግቡን እንድታቀርብለት ሲጠይቃት ‹‹ድመቷ በላችው›› አለችው:: አንድ ኪሎ ሥጋ ድመቷ ጨርሳ በላች የሚለውን የሚስቱን ወሬ ማመን የተቸገረው ናስሩዲን ድመቷን ይዞ ክብደቷን ሚዛን ላይ አስቀምጦ መለካት ጀመረ::

ይሁንና የድመቷ ክብደት አንድ ኪሎ ግራም መሆኑን ናስሩዲን ሲመለከት ወደ ሚስቱ ዞሮ ‹‹ይህች ድመት የእኛ ድመት አይደለችም እንዴ?›› በማለት ይጠይቃታል:: ሚስቱም ድመቷ የእነሱ ድመት መሆኗን ታረጋግጥለታለች:: በዚህ ጊዜ ናስሩዲን ‹‹ታዲያ የእኛ ድመት ከሆነች ሥጋው የት ሄደ? ወይም ሥጋው ይሄ ከሆነ ደግሞ ድመቷ የት ሄደች?›› በማለት አፋጠጣት::

የሙላ ናስሩዲን ወጎችና ታሪኮች ዛሬ ከመካከለኛው ምስራቅ አልፈው በግሪክ፣ ሩሺያ ፈረንሳይ. . . እስከ ቻይና ድረስ ሁሉ ተዛምተው የሚገኙና ተወዳጅነታቸው ዛሬም ከፍተኛ እንደሆነ ይታወቃል:: ከዚህ ተወዳጅነቱ የተነሳም ብዙዎቹ ሀገራት ናስሩዲን የእነሱ ዜጋ አድርገው እስከመቁጠር በመድረስ መከራከር ጀምረዋል:: ቀጣዩዋን ወግ ስናስከትል የናስሩዲንን ጠቢብነት ብቻ ሳይሆን

ብዙዎች በእሱ አስተሳሰብ ምን ያህል እንደሚማረኩና እንደሚወሰዱ ማሳያው ነው እላለሁ::

አንድ ቀን የናስሩዲንን ትምህርት ለመስማት እጅግ ብዙዎች በዙሪያው ተሰብስበው ባለበት ሰዓት እንዲህ አላቸው፡- ‹‹እውነትን የምትሹ ከሆነ አስቀድማችሁ ከፍተኛ ገንዘብ ልትከፍሉ ይገባል!!››

ከተሰበሰቡት መሀል ግን አንዱ ‹‹እንዴት ለእውነት ገንዘብ ክፈሉኝ ትላለህ?›› በማለት ጠየቀው::

ናስሩዲንም ‹‹የማንኛውንም ነገር ዋጋ የሚወስነው እኮ እጥረት ሲኖር ነው!›› በማለት መለሰለት::

እንግዲህ የእውነት ዋጋ የተወደደበት ምክንያት በሰው ልጅ ዘንድ በቀላሉ ለማግኘት የሚቻል ባለመሆኑ ነው የሚለን ሙላ ናስሩዲን በሕይወት ውስጥም በተመሳሳዩ እውነትነቱን አምነን የምንቀበለው ማንኛውም ነገር ዋጋው የሚወሰነው በእኛ አንፃራዊ ፍላጎትና መሻት መሆኑን ግን እንዲሁ መካድ አንችልም በማለት ይህንኑ ወደምታስረግጥልን ሌላ ወግ ደግሞ ይወስደናል::

በአንድ ቀዝቃዛና ብርዳማ የክረምት ወቅት ሙቀት ለጋሽ ልብሶችን ደራርቦ በመልበስ በመንገድ ላይ የሚሄድ ሰው ናስሩዲን አንዲት ሸሚዝ ብቻ በላዩ ጥሎ ሲሄድ ተመለከተው::

በሁኔታው የተደነቀው ይህ ሰው ወደ ናስሩዲን ቀርቦ ‹‹ሙላ! ይህን ሁሉ ልብስ ደራርቤ ለብሼ እንኳን ብርዱን አልቻልኩትም፤ አንተ ግን በዚህች ሸሚዝ በጎዳና ላይ ስትሄድ ትንሽ እንኳን የመብረድ ስሜት አይታይብህም?›› አለው::

ናስሩዲንም ‹‹አየህ! አንተ ብዙ ልብሶች አሉህ፤ እናም ብርድን የመቋቋም ብቃትህ ተወስዷል:: እኔ ደግሞ ከዚህች ሸሚዝ ሌላ የምለብሰው የለኝምና የብርድ ስሜት ቅንጦት ሆኖ ከውስጤ ጠፍቷል›› በማለት መንገዱን ቀጠለ::

ለዚህም ነው እውነት ለሁላችንም አንድ መስላ ብትታየንም እንደሕይወት ምልከታችን እና እምነታችን የተለያየ ትርጉም እንዲሁም ዋጋ እየሰጠናት ለመኖር የምንገደደው:: የሙላ ናስሩዲን ለመሆናቸው እየታመነባቸው ዘመናትን የዘለቁት ወጎች በሙሉ

ከቀልድ ባለፈ ትልቅ ቁምነገርና ጥበብን የተሸከሙ ለመሆናቸው የሁሉንም ስምምነት ያገኙትም ለዚህ ይመስላል:: ቀጣይዋም ወግ እንዲሁ ከላይ ያመጣነውን የእውነት ቁም ነገር የምታጠናክርልን መስሎ ይሰማኛል::

ሁለት ሰዎች በመንገድ ሲሄዱ ሜዳ ላይ አስራ ሁለት እጅግ የተዋቡ የከበሩ ድንጋዮችን በከረጢት ውስጥ ተደርገው ተጥለው ያገኛሉ:: ይሁንና በክፍፍሉ ላይ ለመስማማት አልቻሉም:: አንዱ ‹‹ቀድሜ እኔ አይቻለሁና አብላጫው ለእኔ ይገባል›› ሲል ሌላው ደግሞ ‹‹እኔ ደግሞ ቀድሜ ከረጢቱን አንስቻለሁና አብላጫው ይገባኛል›› በማለት መጣላት ጀመሩ:: በመጨረሻ ወደ ሙላ ናስሩዲን ዘንድ ሄደው በእሱ ዳኝነት ለመካፈል ተስማምተው ይመጣሉ::

ናስሩዲን ጉዳያቸውን ካዳመጠ በኋላ ጥያቄ አቀረበ ‹‹እንግዲህ እነዚህ የከበሩ ድንጋዮች ያለ አድልኦ በእኩል መካፈል ትፈልጋላችሁ፣ ለመሆኑ እንደሰው ነው ወይስ እንደፈጣሪ እንዳካፍላችሁ የምትፈልጉት?››

ሁለቱም በአንድ ቃል ‹‹እንደፈጣሪ አካፍለን›› በማለት ተናገሩ::

በዚህ ጊዜ ናስሩዲን ለአንዱ ዘጠኝ ለሌላው ደግሞ ሦስት ሰጥቶ ጨረሰ::

ሦስት ብቻ የተሰጠው ግን ንዴቱን መቆጣጠር አልሆነለትም ነበርና ‹‹እንዴት እንደፈጣሪ አካፍለን ስንልህ እንዲህ ታደርጋለህ›› በማለት አፈጠጠበት::

ናስሩዲን ግን ፈገግ ብሎ:- ‹‹በፈጣሪ ዘንድ እኩል ተብሎ የሚታሰበው በሰው ከሚታሰበው በእጅጉ እንደሚለይ አታውቅምን? እኩል የሚለው ሃሳብ የሰው እንጂ የፈጣሪ አይደለም›› በማለት አስናበታቸው::

ማንኛውም በሰው ልጅ ዘንድ ትክክል ተብሎ የሚተላለፈው ፍርድ በፈጣሪ ዘንድ እንዲሁ ነው ብሎ ማሰብ የዋህነት ይሆናል:: በፈጣሪና በሰው መካከል የምናገኘው መሠረታዊ ልዩነትም ይኸው ነውና:: ሙላ ናስሩዲን ያስጀመረንን ጉዞ በቀጣዩ ወግ ልንቋጭ በሌላ ጊዜ ደግሞ እንዲሁ ልንመለስበት ናስሩዲን ቀጠሮ እየሰጠን ነው::

አንድ ቀን ናስሩዲን ከመንገድ ዳር ተቀምጦ ወጪና ወራጁን ሲቃኝ ብዙ ሰዎች አስከሬን በሳጥን ተሸክመውና አጅበው ለቀብር

ሲሄዱ ተመለከተ:: በዚህ መሀል አንድ መንገደኛ ወደ ናስሩዲን ቀረብ ብሎ ‹‹ሙላ! ማነው የሞተው?›› የሚል ጥያቄ ያቀርብለታል::

ናስሩዲንም ‹‹ማን እንደሆነ አላውቅም›› በማለት ከመለሰለት በኋላ ፈገግታውን አስከተለና ‹‹በእርግጠኝነት ግን የሞተው በሳጥኑ ውስጥ የተሸከሙት ሰው እንደሆነ አውቃለሁ›› አለው::

ለዚህም ነው ናስሩዲን ‹‹እውነት ማለት የምታውቀው ነገር ብቻ ነው›› በማለት ዘውትር ሲከራከር የኖረው:: የእኛም ማሳረጊያ ‹‹ሁሉም በራሱ መንገድ ትክክል ነው›› የሚለው ይሆናል:: □

pdf by @shuktus_books

# ‹‹በዕውቀት ክንፍ ተፈጥረህ፣ ባለማወቅ አትዳህ››

ሱፊዝም የእስልምናን እምነት መሰረት አድርገው አዳዲስ ልምምዶችንና አስተሳሰቦችን ወደ እምነቱ ያስተዋወቁ ለመሆናቸው ሲታወቅ እውቀትና የንቃተ ህሊና ማደግን የነፍስ መንፈሳዊ ልምምዶች መሠረት አድርገው የሚያምኑ ናቸው:: ሱፊዝም በራሳቸው በሱፊዎች እንደሚነገረው (Islamic mysitcism) ነው:: በዚህም መሠረት በእስልምና ሃይማኖት የሚገኙ እያንዳንዱ መንፈሳዊ ልምምዶች በዕውቀት ለላቁትና ከፍተኛ መረዳት ላይ ለደረሱት (ለሱፊዎች ብቻ ማለታቸው ተደርጎ ይወሰዳል) ሙተው እንደሚገባ አበክረው ያሳስባሉ::

ይሁንና ሱፊዎች ለራሳቸው የሚሰጡት ከፍተኛ የእዋቂነትና የአሳቢነትን ሥፍራ የእስልምና እምነትን መሰረታዊ መርሆ የሚጥስ እንዲያውም እንደ ዜን ቡድሂዝም ዓይነቶቹን እምነቶችና አስተሳሰቦች ከእስልምና ጋር ደባልቶ የመሄድ ችግርም አለባቸው በማለት የሚተቿቸው በርካቶች ናቸው:: ሱፊዝምን አስመልክቶ የሚነሱ አከራካሪ ሃሳቦች እንደተጠበቁ ሆነው ስለ ሕይወት፣ እምነትና ፈጣሪ ያላቸው ከፍተኛና በእውቀት የታነፀ አስተሳሰብ ግን ታላቅነቱን ብዙዎች እየመሰከሩለት ይገኛሉና እኛም ከዚሁ የሱፊ ምሁራን አስተምህሮት መቆንጠር እንቀጥላለን:: የባሬ የሱፊ

ወጎችን ዋነኛ ማዕከል ሱፊው ሩሚ ሲሆኑ በየመሀሉ ሙላ ናስሩዲንና ሌሎችም እየገቡ ጉዟችንን ያስቀጥሉናል።

አንድ ቀን ወደ ሱፊው መምህር ሩሚ ደቀመዝሙራቸው በመምጣት፡- ‹‹ፍትርን ፈልጌ ለማግኘት ደከምሁ፤ ነገር ግን ማግኘት አልቻልኩም›› አላቸው።

ሩሚም፡- ‹‹የአንተ ተግባር ፍትርን መፈለግ መሆን የለበትም። ይልቁንስ በውስጥህ ወደ ፍትር እንዳትደርስ ያደረገህን እንቅፋት በመፈለግ ትጋ። ችግሩን ስታገኝ መድኃኒቱን ማግኘት ቀላል ነውና›› አሉት። ለዚህም ነው ሱፊዎች ሲመክሩ ወደፈጣሪ ለመድረስ ፈጣሪን መፈለግ ሳይሆን ወደ ፈጣሪ እንዳትደርስ ያደረገኽን ችግር ፈልገህ አስወግድ የሚሉት። ከዚሁ ጋር አብሮ የምትሄድ ሌላ ወግ እናስከትል፡-

አንድ ደቀ መዝሙር ወደ ሩሚ ዘንድ በመምጣት ‹‹መምህር ሆይ! ትክክለኛና መልካሙ ሥፍራ ለመድረስ ይርዱኝ›› ይላቸዋል።

መምህሩ ሩሚም፡- ‹‹በመልካምና መጥፎ መካከል አንድ ሰፊ ሥፍራ አለ፤ በዚያ ሥፍራ ላይ ቆመህ እንገናኝ›› አሉት። ይህ የሩሚ አስተሳሰብ የሚያሳየን ደግሞ የሰው ልጅ የስህተቱና ኃጢአቱ ትልቁ ምክንያት በመልካምና በጎ መካከል ያለውን ልዩነት በውል ለይቶ አለማወቁ ነው፤ የሁለቱን ልዩነት መረዳትን የጨበጠ ግን ወደ መልካሙ ሥፍራ ለመድረስ ብዙም ድካም አይጠይቀውም፤ በራሱም ሊደርስ ይችላልና።

በሌላ ጊዜ ከሱፊው መምህር ሩሚ ደቀ መዛሙርቱ አንዱ መጥቶ ፡-‹‹መምህር ሆይ፤ በተደጋጋሚ ፈጣሪ በችግር እየፈተነኝ ነው፤ እንዳልሸነፍ ስጋት ያዘኝ›› አለ።

ሱፊው ሩሚም፡- ‹‹በእያንዳንዱ መንኮትህ ተሰፋ የምትቆርጥ ከሆነ ችግሩ ከፈጣሪህ ሳይሆን ከአንተ ነው፤ የፈትህን መስታወት በውትር ስታሸው የበለጠ እያበራና በግልፅ እያሳየህ መምጣቱን እንዴት ዘነጋኸው?›› በማለት መለሱለት። የሱፊው ሩሚ ምላሽ

እዚህ ላይ ጥልቅና ታላቅ እውነትን ይዞ እናገኘዋለን:: ችግር በሰው ልጅ ሲመጣ ሊያጠነክረን፣ ሊያበረታታንና ይበልጥ ራሳችንን እንድናይ ለማድረግ እንጂ ተሸንፈንበት በሕይወት በችግር ሲፈተን ተስፋ እንድንቆርጥ አይደለም:: መስታዋት ሲታሽ ይበልጥ እየነፃና እያማረ እንደሚመጣው ሁሉ የሰው ልጅም ሕይወት እንዲሁ ያማረ ይሆናል ማለት ነው::

ሱፊው ሩሚ አንድ ወዳጃቸው ቤት ተጋብዘው እጅግ ደስ የሚል የፍቅር ታሪክ ሰምተው ሲጨርሱ ጋባዣቸው፡- ‹‹ፍቅር በእርግጥም እውር ነው፤ ሰዎችን ባስጠበቁት ሥፍራ ወስዶ ያገናኛቸዋል›› አለ::

ሩሚ ግን እንዲህ በማለት አስተካከሉት፡- ‹‹ፍቅረኞች በመጨረሻ የሚገናኙበት ሥፍራ የሚባል ነገር የለም፤ አስቀድሞ አንዳቸው በሌላው ውስጥ ነበሩና››:: ለዚህ ነው በሱፊዎች እምነት ‹‹ፈልገህ የምታገኘው ነገር የለም፤ ነገር ግን አንተ የምትፈልገው ነገር በአንፃሩ እሱም አስቀድሞ ሲፈልግህ ነበር" የሚሉት::

በሱፊዝም አስተምህሮት ዕውቀትና ተመስጥዖ ወሳኝ ነገሮች ናቸው:: ማንኛውንም የሕይወት እንቆቅልሽ ለመፍታትና ወደ ፈጣሪም ለመድረስ የሚችል ሰው አስቀድሞ ማንነቱንና በውስጡ አብሮት የተፈጠረውን ሀጋ ሊፈትሽና ሊያውቅ ይገባል:: ለዚህ ነው፡- ‹‹በታላቅ ዕውቀትም ሆነ በተመስጥኦ ወደ ፈጣሪ እውነት መድረስ ከባድ ነውን?›› በማለት በደቀመዝሙራቸው የተጠየቁት ሩሚ ሲመልሱ፡- ‹‹በእውቀት ክንፍ ተፈጥረህ ባለማወቅ መዳህን ምርጫህ አታድርግ››በማለት የመከሩት:: ፈጣሪ ለሰው ልጅ የፈጠረለት ክንፍ እውቀትና መስጠት ይባላል፤ ይህን ክንፍ የጣሉ ግን በሕይወት ሲድሁ ማየት የተለመደ ነው ይሉናል::

ሱፊው ሩሚ ካስጀመሩን ጉዞ ጥቂት እረፍ ብለን ለመመለስ ያህል የእነሱው አስተምህሮት ዋነኛ ማስተላለፊያ የሆነውን ሙላ ናስሩዲንን ደግሞ እናምጣ:: ናስሩዲን በዘመኑ ተናገራቸው ተብለው የሚታመኑት በቀልድ የተዋዙት ጥልቅ ሐሳቦቹ ሰውን

ፈገግ ከማስደረግ ባለፈ የሚያስተላልፉት ቁም ነገር እንዳለ በሰፊው ሲታመንባቸው ዘመናት ተቆጥረዋል:: የመጀመሪያውን እንዲህ እናምጣ፡-

ሙላ ናስሩዲን የሚኖርበት መንደር ዳኛ ለእረፍት ወደ ሌላ ሀገር ይሄድና ሕዝቡ በምትኩ ናስሩዲንን ዳኛ እንዲሆን ይሾመዋል:: ናስሩዲንም ሹመቱን ተቀብሎ በወንበሩ እንደተቀመጠ የመጀመሪያው ክስ ቀርቦለት ሁለቱ ተከራካሪዎች በፊቱ ቆሙ:: የመጀመሪያው ተከራካሪ ጉዳዩን ካሰማ በኋላ ናስሩዲን፡- ‹‹ትክክል ነህ›› በማለት ድጋፉን ገለፀለት::

ሁለተኛው ተከራካሪም በተራው ተናግሮ ሲጨርስ ናስሩዲን፡- ‹‹አንተም ትክክል ነህ›› አለው::

በዚህ ጊዜ ከታዳሚዎች አንዱ በመነሳት፡- ‹‹ናስሩዲን ሁለቱም በአንድ ጉዳይ ላይ ትክክል ሊሆኑማ አይችሉም፣ የግድ አንዱ ተሳስቷል›› አለ::

ናስሩዲን በዚህ ጊዜ፡- ‹‹አንተም ትክክል ነህ›› በማለት ከወንበሩ ተነስቶ ወደቤቱ ተጓዘ::

ሱፊዎች ይህን የናስሩዲን ፍርድ አስመልክቶ ሲናገሩ ‹‹ማንም ሰው ባመነበት ጉዳይ የራሱን ሀሳብና አቋም ይዞ እስከተናገረ ድረስ ትክክል ነው፣ እውነት እኮ የሰዎች አንፃራዊ ፍርድ እንጂ የሁሉንም ስምምነት ያገኘች አንድ ነገር አይደለችም ይሉናል::

ሌላ አንድ ስንመርት ደግሞ የምናገኘው ወግ ቀጣዩን ይመስላል፡-

አንድ ቀን በናስሩዲን መንደር የታወቀ ፈላስፋና የእምነት ሰው ሲያልፍ እግረ መንገዱን ናስሩዲንን አግኝቶ ምሣ ለመጋበዝና ከእሱ ጋር ለማውጋት ጉጉት ያድርበትና ወደ እሱ ቤት ያመራል:: ከናስሩዲን ቤት ደርሶም ይዞት ከመጣ በኋላ ምሣ ሊጋብዘው እንደሚፈልግና ከእሱም ጋር ማውጋት እንደሚፈልግ በመንገር ወደ አንድ ምግብ ቤት ያመራሉ::

ከምግብ ቤቱ ደርሰው ሁለት አሣ እንዲመጣላቸው አዘው ሲጠባበቁ አስተናጋጁ አንድ ትልቅና አንድ ትንሽ ዓሣ አስጠብሶ ይዞ በመምጣት ከጠረጴዛቸው ላይ አስቀመጠ:: በዚህ ጊዜ ናስሩዲን ተሽቀዳድሞ ትልቁን ዓሣ ከራሱ ማህን ላይ አስቀምጦ መመገብ ሲጀምር ፈላስፋው በትዝብትና በንዴት ሲመለከተው ቆይቶ፡-

‹‹በድርጊትህ በጣም አፍሬያለሁ፡ ከሞራልም ሆነ ከእምነት አንፃር የሰራኸው ነውር ነው፡ በማንኛውም ግብዣ ላይ ሰዎች ቅድሚያ እስኪሰጡህ መጠበቅ አልያም አንተ ቅድሚያ መስጠት ይገባሃል›› በማለት ልዩ ልዩ ፍልስፍናዊ እና ሃይማኖታዊ እሳቤዎችን እየጠቀሰ ሲመክረው ናስሩዲን ደግሞ ዓሳውን እየተመገበ ሲሰማው ቆየና አቋርጦ ቀና አለ::

‹‹ለመሆኑ ጌታዬ! እርስዎ ቢሆኑ ምን ያደርጉ ነበር?›› በማለት ናስሩዲን ጠየቀው::

ፈላስፋውም፡- ‹‹እኔማ ትንሹን ዓሣ አንስቼ ከሳህኔ በማስቀመጥ እመገብ ነበር›› አለው::

በዚህ ጊዜ ናስሩዲን ቀልጠፍ ብሎ ትንሹን ዓሣ በማንሳት ከፈላስፋው ሰሀን ላይ እያስቀመጠ፡- ‹‹ይኸው! ይበሉ ይመገቡ›› በማለት ወደራሱ ትልቅ ዓሣ ተመለሰ::

ሱፊዎች ከዚህ የናስሩዲን ድርጊት የምንማረው ትልቅ ቁም ነገር በማለት የሚያስቀምጡልን፡- ‹‹የእውነትን ትልቅ ድርሻ መያዝ ከየትኛውም ፍልስፍናና ሞራላዊ እሳቤ የላቀ ነው›› የሚለውን ይሆናል:: ሕይወት በሊጋስነቷ የምታቀርብልንን ስጦታ የሰው ልጅ በወግ፣ በልማድ፣ በእምነት ይሉኝታ ተይዞ ሲቆንጥር መመልከት ይደንቃል የሚሉን ሱፊዎች ይልቁንስ ራስ ወዳድነት ማለት በእነዚህ ሞራላዊ አስተሳሰቦች ታስሮ መሰቃየት ነው ይላሉ::

ወደ ሱፊው ሩሚ ተመልሰን ከአስተምሮታቸው እውቀት ደግሞ መቆንጠር እንቀጥል::

ሩሚን እጅግ አድርጎ የሚወድና ከአጠገባቸው የማይለይ

ደቀመዝሙር ድርጊቱና ንግግሩ እንዲሁም ለእሳቸው ያለው መስጠት ደንቋቸው እንዲህ አሉት፡-

‹‹ወዳጄ! አንተ ከእኔ ጋር ስትሆን ሌሊቱን ተቀምጠን እናድራለን፣ ከእጠገቤ ስትርቅ ደግሞ አንትልፍ በዓይኔ አይዞርም:: ስለነዚህ ሁለት እብደቶች ፈጣሪ የተመሰገነ ይሁን፣ ስለ ልዩነታቸውም እንዲሁ እመሰግነዋለሁ›› አሉት::

በእውነተኛ ፍቅር ውስጥ የሚገኘውን አንድነት ማድነቅ ብቻ ሳይሆን ልዩነትንም ማወቅ ጠቢብነት ነው የሚሉን ሱፊዎች ሰውን ስታፈቅር ፈጣሪን ማወቅ ብቻ ሳይሆን እሱን መግለጥም ጀምረሃልና ልታመሰግነው ይገባሃል ይላሉ::

ሱፊው ኑሚ ዘወትር ደስተኛና ጥበብ የሞላባቸው መሆኑን የተመለከተ ደቀ መዝሙር ምስጢራቸውን ሲጠይቅ እንዲህ አሉት-

‹‹በፈጣሪ ብርሃን ማፍቀርን ተማርኩ፣ የእሱን ውበትም ተመልክቼ ቅኔን መቀኘት ጀመርኩ፤ በልቤ ውስጥ እሱ ሲደንስ እኔም አብሬው መደነስን ቻልኩበት፤ እነዚህ ሁሉ በእኔ ላይ ተባብረው ለሰው ልጅ ሲገለጡ ደግሞ ጥበብ ተብለው ተጠሩ›› አሉት::

ለፈጣሪህ ፍፁም እየተሰጠህ በሄድክ ቁጥር የእሱን አስደናቂ ጥበብ በአንተ ላይ መግለጥ ይጀምራል የሚሉን ሱፊዎች እውነተኛ ውበትም ከሰው የሞራል፣ የእምነት፣ የወግና ሥርዓት ልምምድ የሚገኝ ሳይሆን ፈጣሪን ከማወቅ፣ በእሱም ብርሃን ከመመላለስ የሚጨበጥ ማንነት ነው ይላሉ::

ሌላውን የሱፊ መምህር ቢስታሚን እንምጣ:: በታላቅ የሱፊ ምሁርነታቸው የሚታወቁት ቢስታሚ ወደፈጣሪ መድረሻው መንገድ በእሱ የተዘጋጀና ማንም ሊሄድበት የሚችል ቢሆንም የሰው ልጅ በመንገዱ ከመሄድ ይልቅ መንገዱን ማመንን ምርጫው አድርጎ ጠፍቷል ባይ ናቸው::

አንድ ቀን ደቀመዝሙራቸው ወደ እሳቸው በመምጣት፡- ‹‹መምህር ሆይ! እንኳኩ፣ ይከፈትላችኋል የሚለው አስተምህሮት የእኛን ተግቶ

መፀለይ የሚመለከት አይደለምንን» በማለት ይጠይቃቸዋል::

መምህሩ ቢስጣሚም፡- «ወዳጄ! አለተያጭሰ የተበጋ ዷጅ የት አለና ነው የምታንኳኳው?» በማለት ጥያቄውን በጥያቄ መለሱለት::

ሱፊዎች «ወደፈጣሪ መድረሻው መንገድ ለእሱ መሰጠት እንጂ ወደ እሱ መፀለይ አይደለም» የሚሉን ለዚህ ይመስላል:: ፈጣሪ እንድትገባበት በከፈተልህ ዷጅ ፊት ቆመህ መፀለይ አላዋቂነት (Ignorance) እንጂ ሌላ አይደለም፤ ፈጣሪ የከፈተውን ዷጅ መመልከት ካቃተህ ደግሞ ችግሩ ከእኛ እንጂ ከእሱ አይደለምና በከንቱ እሱን አናድክመው::

ከሱፊው ቢስጣሚ አንድ እንመርቅ፤ ቢስጣሚ በሚኖሩበት ገዳም የሚታወቁት በዝምታቸው ነው:: ይህ የዘወትር ዝምተኝነታቸው የከነከነው ደቀመዝሙር አንድ ቀን ወደሳቸው በመምጣት፡- «መምህር ሆይ! የእርስዎ ዝምታ እጅግ የበዛ ነው:: ማንኛውም እምነትና ሃይማኖት እኮ በሚያምንበት አምላክ ለተከታዩ ያስተምራል» አላቸው::

ቢስጣሚም፡- «ወዳጄ! የፈጣሪ ቋንቋ እኮ ዝምታ ነው፤ ሌላው የሀይማኖት ትምህርት ከንቱ ትርጉሙ ነው» በማለት አሰናበቱት::

የሰው ልጅ ቋንቋን ተጠቅሞ ስለ ፈጣሪ የሚያስተምርበትም ሆነ የሚያስረዳበት ዕውቀት በራሱ የሀሳብ መረዳትና ትርጉም ተመስርቶ እንጂ ሌላ አይደለም:: የሚሉን ሱፊዎች ከዚያ ይልቅ የተሻለው ፈጣሪን በዝምታ ማሳየት ነው ይላሉ::

የዛሬውን በሱፊዎች ላይ የጀመርነውን የጥበብ ጉዞ የዛሬ አስራ አምስት ቀን ልንቀጥልበት ቀጠሮ ሰጥተን የምለያየው የአስተምህሮታቸው አንዱ ማስተላለፊያ አድርገው በሚጠቀሙበት በሙላ ናስሩዲን ታሪክ ይሆናል:: ይህች ታሪክ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ከላይ ካነሳነው የቢስጣሚን ሀሳብ ጋር መመሳሰል እግኝተንበታል::

አንድ የታወቀ ፈላስፋ ወደ ናስሩዲን ዘንድ በመምጣት በጀልባ እንዲያንሸራሽሩ ይጋብዘውና ወደ ባህር ዳርቻ ሄደው ጀልባ ይሳፈራሉ::

በጀልባው ላይ ተቀምጠውም ወደ ባህሩ መሀል እያመሩ ጨዋታ ይጀምራሉ::

ፈላስፋው፡- ‹‹ናስሩዲን! ለመሆኑ ት/ቤት ገብተህ የፍልስፍና ዕውቀት ተምረሃል?›› በማለት ይጠይቀዋል:: ናስሩዲንም እንዳልተማረ ይገልፃል::

በዚህ ጊዜ ፈላስፋው፡- ‹‹በዚህ አይነት የሕይወትህን ግማሽ በከንቱ ነዋ ያጠፋኸው!›› ይላል::

በጀልባው ጥቂት እንደተጓዙ ሞገድ ይነሳና ጀልባው መናወጥ ይጀምራል:: በዚህ ጊዜ ናስሩዲን፡- ‹‹ጌታው! ለመሆኑ ዋና ተምረሃል?›› በማለት ይጠይቃል:: ፈላስፋውም በድንጋጤ እየራደ፡- ‹‹ኧረ አልተማርኩም›› ይላል::

በዚህ ጊዜ ናስሩዲን፡- ‹‹እንግዲያውስ ሕይወትህን በሙሉ ነው ያጠፋኸው፤ ጀልባው እኮ እየሰመጠ ነው›› አለው::

ለዚህ ነው ሱፊዎች ዕውቀት ማለት በተግባር የሚታይ እንጂ በቃላት የሚገለፅ አይደለም የሚሉን:: እሱ ፈጣሪውን በቃላት ማባበል ሳይሆን በተግባሩ የሚያሳይ በእርግጥም ጠቢብ ነውና! □

pdf by @shuktus_books

# ‹‹ፈጣሪ የሰጠህን ተፈጥሮ ሰው እንዲያስተምረህ አትሻ››

የጉዟችን ማዕከል የነበሩት የሱፊው መምህር ሩሚ በዚህ ምዕራፍም እሳቸውንና ሙላ ናስሩዲንን በዋንኛነት በመያዝ አልፎ አልፎ በየጣልቃው ደግሞ ሌሎቹን እያመጣን መመልከታችን አይቀሬ ይሆናል:: በቅድሚያ ሱፊው ሩሚን እናምጣ:-

አንድ ቀን ሩሚ ደቀመዝሙራቸው በከፍተኛ ሀዘን ተውጦ ይመለከቱቱትና ምን እንደሆነ ይጠይቁታል:: ደቀመዝሙሩም የሀዘኑን ምክንያት ለሩሚ ከነገራቸው በኋላ በቁዘማው መቀጠሉን ሲመለከቱ :- ‹‹ወዳጄ፡- የልብ ሀዘን የፈጣሪ የማንነቱ ብርሀን የሚገባበት ሽንቁር ነውና አትጥላው›› የሚል ማዕናኛ ነግረውት አለፉ::

በሱፊዎች እምነት ከደስታ ይልቅ ሀዘን ፈጣሪን የማወቂያውና ወደፈጣሪም የመቅረቢያው የተሻለው መንገድ ነው:: እንዲያውም ሀዘን ፈጣሪን ለማወቅ ካልተጠቀምንበት ከሕይወታችን ፈፅሞ መወገድ ይገባዋል ይላሉ:: ይኸንን ከሕይወት እውነታ በመነሣትም ሲያረጋግጡልን፡-‹‹ አንድን ነገር በማጣትህ ለሐዘንህ ምክንያት ቢሆን እንኳን በሌላ መንገድ ተመልሶ ወደአንተ መምጣቱን እርግጠኛ ሁን›› በማለት ነው::

‹‹ አንድ ሰው እውነተኛ ደስታውን መግለፅ የሚችለው መቼ ነው?‹‹ በማለት በደቀመዝሙራቸው የተጠየቁት ሩሚ እንዲህ መለሱለት ይባላል፡-‹‹ ሐዘን ሲያጋጥምህ ደስተኛ ሆነህ ደንስ፤ የችግር ሰንሰለት በዙሪያህ ሲጠመጠም አሁንም በደስታ ደንስ፤ ከሰዎች ጋር ግጭት ውስጥ የምትገባበት ሁኔታ ሲገጥምህ ደስታን ምርጫህ አድርገህ ደንስ፤ በመውደቅህ ደንስ፤በመከራህ ደንስ፤

በነፃነትህ ደንስ.....:: ይኼን ማድረግ ስትችል ብቻ በዕውቀት የንቃህና የፈጣሪ ብርሃን የበራልህ መሆንህን ታሳያለህ ›› አሉት::

ሱፊዎች ሲመክሩ ፡- ‹‹ በደስታህ ስሜትህን ብትገልፅና ብትደሰት ከሌላው ሰው የሚለይህ ዕውቀት ከወዴት ነው?›› በማለት ይጠይቃሉ:: በዕውቀት የምትገኝ ደስታ ግን ከብዙሃኑ የምትለይህና የደስታንም ትርጉም በሌላው የህይወት ገፅታ መግለጥ እምደምታስችልህ አትዘንጋ›› ይሉናል::

ከሩሚ አስተምህሮት አንድ እንመርጥና ወደ ናስሩዲን ደግሞ እንሸጋገራለን:: ለሩሚ አንድ ደቀመዝሙራቸው እንዲህ የሚል ጥያቄ አቀረበላቸው ‹‹ መምህር ሆይ! በፍቅር የምወድቅለት ውበት እንዴት ያለ ነው?››

ሩሚ እንዲህ አሉት፡-‹‹ በውበቱ ተገዝተህ በፍቅር ልትወድቅለት የሚገባ ነገር የተሰጠህለትና የምትሰራው ሥራ ብቻ ይሁን:: ከዚያ በተረፈ በውበት ስም በህይወት ውስጥ ተሸንፈህለት የምትንበረከክለትና መሬት የምትስምለት በሺህ የሚቆጠር ነገር አለና ከዚያ ተጠንቀቅ›› በማለት አሰናበቱት::

በሱፊዎች እምነት በዚህ ምድር ላይ የማያልፍ ውበት በሥራህ ገልጠህ የምታልፈው ብቻ እንጂ ሌላው ሁሉ በጊዜያዊ ውበት ላይ የተመሠረተ፣ የሚያልፍና የሚጠፋ ነው::

ሱፊዎችከታላላቅምሁራኖቻቸውባሻገርእንዴየአስተምህሮታቸው ማስተላለፊያ አድርገው ሲጠቀሙበት ወደነበረው ሙላ ናስሩዲን ተሻግረን እንቆንጥር:: ናስሩዲን ሕይወትን የሚመለከትበት መነፅር ከእነሱ አስተምህሮት ጋር የሚገጥም መሆኑን አዘውትረው ሲመሰክሩለት የኖረ ሰው ነው:: ምንም እንኳን የናስሩዲን ንግግሮች በቀልድ የተዋዙና አስቂኝነታቸውም ጎልቶ የሚወጣ ቢሆንም በውስጣቸው የያዙት ፍልስፍና ቁምነገር ግን ጥልቅ ነው የሚሉ የሱፊ ምሁራን በርካታ መሆናቸውን በድጋሚ ማስታወስ ይገባል:: ወደ ቀዳሚው የናስሩዲን ገጠመኝ እናምራ፡-

ናስሩዲን አንድ ጉባዔ በወንዶች መቋቋሙን ይሰማና ወደዚያ በመሄድ አባል ይሆናል:: የጉባዔው መጠሪያ፡-‹‹ ሚስቶቻቸውን

የማይፈሩ ወንዶች ጉባዔ›› የሚል መጠሪያ የተሰጠው ነበር:: የዚህ ጉባዔ የመጀመሪያ ቀን ስብሰባ ላይ ሊቀመንበሩ የምስረታ በዓሉን ምክንያት በማድረግ ሁሉም ከመቀመጫቸው በመነሳት የሚያደርገውን አጭር ንግግር እንዲያደርጉ ጥሪ ካቀረበ በኋላ ሁሉም ቆመው ንግግሩን ይሰሙና ያበቃል:: በመጨረሻም ሊቀመንበሩ የጉባዔውን መመስረት ለማብሰር፡-‹‹ አሁን፡- ሚስቶቻችሁን የማትፈሩ ሁሉ ተቀመጡ!›› ይላል::

ከሙላ ናስሩዲን በቀር በጉባዔው ውስጥ ያልተቀመጠ አልነበረም:: ይኸን የተመለከተው ሊቀመንበሩ ግራ በመጋባት፡-‹‹ ናስሩዲን! ሚስትህን ትፈራለህ እንዴ…ለምን አትቀመጥም?›› በማለት ይጠይቀዋል::

ናስሩዲንም ፈገግ ብሎ፡- ‹‹ ሚስቴን እንኳን አልፈራትም ፤ነገር ግን ትናንት ማታ ስትደበድበኝ መቀመጫዬን ክፉኛ ስለመታችኝ ስቀመጥበት ስለሚያመኝ ነው›› በማለት መለሰለት::

ሱፊዎቹ በዚህ የናስሩዲን ምላሽ ፈገግ ብለን ስንመለስ የምናገኝበት ትልቅ ቁምነገር የሚሉን ፤‹‹ ደረጃው ይለያይ እንጂ ወንድ ሆኖ ሚስቱን የማይፈራ ባል አይገኝም›› የሚለው ነው:: ሴት የቱንም ያህል ለባሏ ትሁትና ታዛዥ ብትሆን እንኳን ታዛዥነቷና ትህትናዋ በራሱ መፈራትዋን የምትሸምትበት ግንዛቤ መሆኑን ወንዱ ሊያስተውል ይገባል፡፡ በሀይለኛዋ ሴት ዘንድ ደግሞ ይኸ መፈራትዋ የቱን ያህል ሊብስ እንደሚችል ቀላል እንደሆነ ያስተምራሉ::

ከናስሩዲን አንድ እንመርቅ፡-

አንድ ቀን በናስሩዲን መንደር የሚገኝ መስጊድ በአሳህ ተፈጥሮ ዙሪያ የሚያስተምር ጉባዔ ያዘጋጅና ታዋቂ ኢማሞችና የሀይማኖት ምሁራን በዚሁ‹‹ የአሳህ ተፈጥሮ›› ዙሪያ አጭር ንግግር እንዲያደርጉ ይጋበዛሉ:: በወቅቱ ከተጋባዥ ተናጋሪዎች መካከል ምንም እንኳን ቀልደኛና ዋዘኛ ቢሆንም በርካታ ተከታዮች እንዳሉት የሚታመነው ሙላ ናስሩዲንም አንዱ ነበር:: ኢማሞቹና ምሁራኑ በአሳህ ተፈጥሮ ዙሪያ እውቀታቸውን ካስተላለፉ በኋላ የናስሩዲን ተራ ደርሶ ወደ መድረኩ ተጋበዘ ፤ናስሩዲን በመድረኩ ላይ ወጥቶ ከቆመ በኋላ

ሕዝቡን ለአፍታ ሲያስተውል ቆይቶ፡- ‹‹ አላህ..... አላህ..›› በማለት ዙሪያውን ቃኘና በእጁ የያዘውን የሚበላ ፍሬ ከፍ አድርጎ ፡- ‹‹ አላህ ይኸ ፍሬ ነው›› አለ::

በዚህ የናስሩዲን ምላሽ ሕዝቡ በተለይም ኢማሞቹና ምሁራኑ በቁጣ ማጉረምረምና የፈጣሪን ማንነት ያቃለለ ትምህርት ሰጠ በማለት መሳደብ ይጀምራሉ:: የጉባዔው መሪ ሕዝቡ ፀጥ እንዲል ካደረገ በኋላ ናስሩዲን እንዴት እንዲህ ለማለት እንደቻለ መግለፅ እንደሚገባው ይነግረዋል::

ናስሩዲንም ፈገግ ብሎ ፡- ‹‹ እስካሁን ለአላህ ተፈጥሮ እነዚህ ሁሉ ኢማሞችና ምሁራን ሲናገሩ የሰማሁትና የማያውቁትንና ለአንድ ጊዜ እንኳን በአይናቸው ተመልክተውት የማያውቁትን ተፈጥሮ ነው:: ነገር ግን ሁላችንም ይኸን ማየት እንችላለን:: ለመሆኑ ከእናንተ መካከል አላህ ራሱን በሁሉ ነገር ውስጥ እንደሚገልጥ የሚክድ ይኖራል?›› በማለት ጠየቀ:: በጉባዔው መካከል አንድም ሰው የናስሩዲንን ጥያቄ ማስተባበል የቻለ አልተገኘም:: ‹‹ እንግዲያውስ›› አለ ናስሩዲን በማሸነፍ ስሜት ፡- ‹‹ አላህ ይኸ ፍሬ ነው›› በማለት በእጁ የያዘውን ከፍ አድርጎ በማሳየት ከመድረኩ ወርዶ ወደ ቤቱ አመራ::

ሰዎች በዚህ የናስሩዲን ገጠመኝ ላይ ተመስርተው ሲናገሩ፡- ‹‹ ፈጣሪን በሁሉ ነገር ማየት ካልቻልክ መቼም ልታየው አትችልም ›› ይሉናል:: ስለ ሩሚ ደግሞ ይኸንን ሃሣብ ሲያጠናክሩልን፡-‹‹ የሰው ጥበብ በፈጣሪ ዘንድ ሞኝነት ነው፤የሰው ሞኝነት ደግሞ በፈጣሪ ዘንድ ጥበብ ነው››:: ይሉናል:: ለዚህም ነው ማንኛውንም ነገር ለመግለፅ የምትጠቀምበት ቃል የነገሩ አቻ ሊሆን አይችልም:: ቃሉ የነገሩ አቻ ቢሆንማ ራሱን ነገሩን በሆነ ነበር:: በእጭሩ የፈጣሪ ማንነት ከሰው አስተሳሰብም ሆነ ከቃላት ገለፃ እጅግ የላቀና ያለፈ ነገር መሆኑን እንረዳ ባይ ናቸው::

የሰዎችን አስተምህሮት በተለያየ መንገድ ለመረዳት የምናደርገውን ጉዞ ስንቀጥል ወደ ሌሎች ምሁራን ደግሞ ተሻግሮ መመልከት ግድ ይለናል:: በቅድሚያ አል ጋዛሊን እንመልከት::

አንድ ቀን የአል ጋዛሊ ደቀመዝሙር በሀዘን መንፈስ ተሞልቶ ወደእሳቸው ዘንድ በመምጣት ሀጢአት መፈፀሙንና ድርጊቱም ፈጣሪውን እንዳሳዘነ በመግለፅ መፍትሄውን ይጠይቃቸዋል::

አል ጋዛሊም፦‹‹ ወዳጄ! በሕይወት መንገድ ላይ ሲያዳልጠው ተስፋ የሚቆርጥ ሰው እሱ እምነቱን በድርጊቱ በመግለፅ የሚመኝ ነው:: እምነት ማለት ከመውደቅ በኋላ በመነሳት እንጂ ባለመውደቅ የሚገለጥ ኃይል አይደለም ›› በማለት ሸኙት::

ለዚህ ይመስላል ሰዎች የሰው ልጅ በመውደቁ ምክንያት ተስፋ መቁረጥ የሚገጥመው አስቀድሞ በእምነቱ ሳይሆን በሥራው በመመካቱ ነው የሚሉን:: እናም ለአእምሮህ ማስተዋልን፡ ለልብህ ደግሞ ዕናትና ርኅራኄን መግበው:: ሕይወትን አቅልለህ ስትመለከታት የምትሰጥህ ትርጉም እጅግ ሙሉ ይሆናል፤ ከዓለም የምትሻው እንዲሁ ጥቂት ሲሆን ከፈጣሪህ የምትከፈለው ደግሞ እጅግ ብዙ መሆን ይጀምራል ይላሉ::

ከአል ጋዛሊ ገጠመኝ አንድ እንመርቅ:: አንድ ቀን አል ጋዛሊ ደቀመዛሙርቶቻቸውን ሰብስበው ሲያስተምሩ እንዲህ ተጠየቁ፦ ‹‹ መምህር ሆይ! ፈጣሪን አጥብቀን በፈራነው ቁጥር ከእኛ እየራቀብን ተቸገርን፤ እሱን እናገኝ ዘንድ የእርስዎን የፍለጋ መንገድ ያስተምሩን›› አሏቸው::

አል ጋዛሊም ጥቂት አሰቡና እንዲህ አሉ፦ ‹‹ ፈጣሪዬን አጥብቄ በፈለግሁት(በመረመርኩት) ሰዓት ራሴን ለማግኘት ቻልኩ፤ ራሴን አጥብቄ በፈለግኩት (በመረመርኩት) ሰዓት ደግሞ ፈጣሪዬን አገኘሁት:: ሁሉንም ነገር በውስጤ እንዳስቀመጠው አውቄያለሁ፤ እናም የምሻውን ነገር ሁሉ ለማግኘት ወደውስጤ እመለከታለሁ::››

በሱፊዎች አስተምህሮት መሠረት የፈጣሪ መስተዋት እኛ ነን:: ራሱን የማይፈትሽና የማይመረምር ሰው ከፈጣሪው የሚደርስበትን መንገድ የሳተ ነውና መቼም ቢሆን ፈጣሪውን ለማወቅ አይቻለውም::

ወደ ሩሚ እንመለስ

የሩሚ ደቀመዝሙር እንዲህ ጠየቀ፦‹‹ ፈጣሪዬን ዘወትር ማመስገን እሻለሁና እንዴት ማመስገን እንደሚገባኝ ልምምድም

የስተምሩኝ?››

ሱፊው ኑሚ ጠየቁት፡-‹‹ ወዳጄ ! የወፎችን ዝማሬ ሰምተህ ታውቃለህ?››

ደቀመዝሙሩ፡-‹‹ በሚገባ መምህር! ዘወትር ማለዳ እሰማለሁ›› ሲል መለሰ::

ኑሚም፡- ‹‹ ወፎች ስለድምፃቸው ማማር የሚጨነቁና እንዴት መዘመር እንዳለባቸውስ የተማሩ ይመስልሃል?››

ደቀመዝሙሩም፡- ‹‹ በፍፁም መምህር ሆይ!›› ሲል መለሰ

ኑሚም፡- ‹‹ እየህ! ፈጣሪዬን እንዴት ማመስገን እንደሚገባኝ የተማርኩት ከወፎች ዝማሬ ነው:: ወፎች የማለዳ ዝማሬን በተፈጥሮ የተቀበሉትና ይኸንኑም የሚፈፅሙ ፍጡሮች ናቸው:: ስለድምፃቸው ማማርም ሆነ ማስጠላት አይጨነቁም:: እኔም ፈጣሪዬን ለማመስገን በተፈጥሮ የተቀበልኩት ድምፅ ከበቂ በላይ መሆኑን አምናለሁ:: ምስጋናዬን ሳቀርብም ሰዎች ምን ይሉኛል? ወይም ሰዎች ይተቹኛል ብዬ አላስብም:: እናም ፈጣሪ የሰጠህን ተፈጥሮ ሰው መልሶ እንዲያስተምርህ አትሻ›› በማለት አሰናበቱት::

በሱፊዎች ዘንድ ሰውን ማስተማር የሚባለው ነገር ተቀባይነት የለውም፣ ለዚህ ይመስላል ሰው በፈጣሪው ዘንድ ሙሉ ሆኖ የተሰራ ፍጡር ሲሆን ችግሩ ጎዶሎነቱን እንጂ ሙላቱን የሚረዳበትና የሚገልጥበትን ዕውቀት አለመጨበጡ ነው፣ እናም ይኸን የሙሉነቱን መገለጥ መጨበጥ ይችል ዘንድ መንገዱን ትመራዋለህ እንጂ የአንተን የመገለጥና የዕውቀት ሙላት በእሱ ላይ አትጭንም›› ይላሉ::

ኑሚን በዚህ ታሪክ እንሰናበት:: አንድ ቀን በትምህርታቸው የተማረከ ደቀመዝሙር ታላቅ እውቀትና እውነት ከእሳቸው እንዴት እንደተማረ በመግለፅ ማድነቅ ሲጀምር ኑሚ አቋርጠውት እንዲህ አሉ፡-

‹‹ አትሳሳት! እውነትን አገኘ ዘንድ ከከንፈሮቼ በሚወጡ የእብደት ቃላት በሩን ሳንኳኳ ኖሬአለሁ:: በሩም ተከፈተልኝ! የሚያሳዝነው ግን የእውነት በር እንዲከፈትልኝ ሳንኳኳ የኖርኩት ከውስጥ ቆሜ

ነበር›› አሉት::

ሱፊዎች የፈጣሪ እውነት መገኛዋ በእያንዳንዳችን ልብ ውስጥ እንጂ ከዓለም በሚታይ ዕውቀት ወይም ትምህርት አይደለም የሚሉን ለዚህ ነው:: የትኛውንም ትልቅ ዕውቀት የጨበጠና የፈጣሪውን እውነት የተረዳ ሰው ፈጣሪው በውስጡ ያስቀመጠውን ምስጢር የደረሰበትና የገለጠ ሰው ብቻ ነውና!

የዚህ ምዕራፍ መጠቅለያ የሚሆነው ቀጣዩ የሙላ ናስሩዲን ወግ ይሆናል::

አንድ ቀን በሞኝነቱ በመንደሩ ሁሉ የሚታወቅ ሰው ወደ ናስሩዲን ዘንድ በመምጣት፡- ‹‹ ናስሩዲን ! ፈጣሪ በራሱ እውነት ነውን?›› የሚል ጥያቄ ያቀርብለታል::

ናስሩዲንም፡- ‹‹ ሁሉ ነገር እውነት ነው›› ሲል መለሰለት

ሞኙ ሰው በናስሩዲን ምላሽ ተገርሞ፡-‹‹ ሁሉ ነገር እንዴት እውነት ይሆናል፤ ውሸትም ቢሆን እውነት ነው እንዴ?›› አለው::

‹‹ እዎን! ውሸትም ሁሉ እውነት ነው›› አለ ናስሩዲን

ሞኙ ሰው መገረሙ ባሰና ፡-‹‹ይኸ እንዴት ሊሆን ይቻላል?›› ሲል ጠየቀው::

ናስሩዲንም፡-‹‹ እሱን እንኳን አላውቀውም፤ እኔ አልሰራሁትም እኮ!›› ሲል አሰናበተው::

ይኸችን የናስሩዲንን ወግ መሠረት አድርገው ሱፊዎች የሚያስጨብጡን አንድ ቁምነገር ቢኖር፡- ‹‹ የእውነት መገኛዋ በእያንዳንዳችን ልብ ውስጥ እንጂ በሌላ ሥፍራ አይደለም›› የሚል ይሆናል:: ◻

pdf by @shuktus_books

# ‹‹በሕይወት ስጦታ በቃኝ ማለት የደስታ ሁሉ ምንጭ ነው››

በሱፊዎች ዘንድ በፈጣሪ ላይ የተመሠረተ እውነተኛ ዕውቀት የሚባለው በእሱ ውስጥ መጥፋት ወይም ፈፅሞ እሱን ወደመምሰል ብቃት መሸጋገር ስንችል ነው:: ፈጣሪህን የምታውቀው በቀጥታ ከእሱ ጋር በሚኖርህ ግንኙነት እንጂ የነቢይ፣ የፃድቅ ወይም ደግሞ የካህን መልዕክተኛ በሁለታችሁ መካከል አድርገህ በማቆም ሊሆን አይችልም:: ይኸ መሠረታዊ የአመለካከት ልዩነት ነው እንግዲህ በሱፊዎችና በሌሎች ሃይማኖቶች መካከል ‹‹ፖለቲካዊ ልዩነት›› የሚመስል ግጭት አትርፎ ለዘመናት የዘለቀው:: በአንተና በፈጣሪ መካከል የቆሙት ሰዎች የሚነግሩህን ከመፈፀም ባሻገር የተለየ አማራጭ እስከሌለህ ድረስ ፈጣሪህን በቀጥታ የማወቅ ዕድልም እንዲሁ አይኖርህም:: ሱፊዎች እነዚህን ሰዎች የፈጣሪን ሃሳብና ድምፅ የሚያመጡ በመሆናቸው ክብር እንደሚገባቸው ባይክዱም ነገር ግን አንተንና ፈጣሪህን በቀጥታ እንድትገናኙ ከማገዝ ያለፈ ሚና የላቸውም ይላሉ:: ይኸ አስተሳሰብ በአጭር አገላለፅ ሲቀመጥ ‹‹ፈጣሪ አንድ ነው፣ ይኸ ፈጣሪ ደግሞ መገኛው የእያንዳንዱ የሰው ልጅ ልብ ነው:: ፈጣሪን በእውነት ለማፍቀር እሱ የሚገኝበትን እያንዳንዱን የሰው ልጅ ማፍቀር ብቸኛው መንገድ ነው:: የፈጣሪም

ማንነት ከእዚህ ውጭ የሚገለጥበት ተአምር የለውም›› የሚለው ይሆናል::

እንግዲህ ይኼን የሱፊዝምን መሠረት ጨብጠን ጉዟችንን ስንጀምር በቅድሚያ የምናገኘው የሱፊው ምሁር ቢያዚድ ቢስታሚን ይሆናሉ:: ቢያዚድ ስለፈጣሪ ማንነት እስከዛሬ የተማርነው (የሰማነው) ወደእሱ ለመድረስ ለምን እንዳላስቻለን የተገለጠላቸውን እውነት እንደሚከተለው ያስተምጡታል::

አንድ ቀን ቢያዚድ በመካነ መቃብር መካከል ሲያልፉ ወደ አንድ የሰው ራስ ቅል የተከመረበት ቦታ ይደርሳሉ:: በነገሩ ተደንቀውም ከተከመረው የራስ ቅል መካከል አንዱን አንስተው መመልከት ጀመሩ:: እስከዚያን ቀን ድረስ የሰው ልጅ የራስ ቅል አንድ ዓይነትና ተመሳሳይ ነው በማለት የሚያምኑት ቢያዚድ ከሃሳባቸው ጋር የሚጋጭ ልዩነት በራስ ቅሉ ላይ ይመለከታሉ:: ወደሌሎች የራስ ቅሎችም ዓይናቸውን ሲወረውሩ የተለያየ ቅርፅ የያዙ መሆናቸውን ይረዳሉ:: አንዳንዶቹ የራስ ቅሎች ሁለቱ ጆሮዎቻቸው በቀጥታ በቀጭን ቱቦ መሳይ መንገድ የተገናኙ ሲሆኑ በአንዳንዶቹ ላይ ደግሞ ጆሮዎቻቸውን የሚያገናኝ መንገድ የለም:: እንዲሁም ደግሞ ሌሎቹ ጆሮዎቻቸው ከልባቸው ጋር የሚያገናኝ መንገድ እንዳለው ይመለከታሉ::

ቢያዚድ በተመለከቱት እንግዳ ነገር ተገርመው ወደፈጣሪያቸው ጥያቄያቸውን በፀሎት ያቀርባሉ፡- ‹‹ፈጣሪ ሆይ! ነገሩ ምንድነው? ለእኔስ ልትገልጥልኝ የወደድከው ምስጢር ምን ይሆን?

ፈጣሪም፡- ‹‹ቢያዚድ! ይኼ የምታየው መስመር ሦስት ዓይነት ሰዎች በምድር ላይ የመኖራቸው እውነት ማሳያ ነው:: የመጀመሪያዎቹ በአንድ ጆሮ ይሰማሉ፣ ነገር ግን የሰሙት ነገር ሁለተኛው ጆሮ ላይ እንኳን አይደርስም፣ በአጭሩ የሚሰሙት ከድምፅ ባለፈ ሌላ መልዕክት የለውምና እንደሚሰሙ አይቆጠርም:: ሁለተኛው ዓይነቶቹ ደግሞ በሁለቱም ጆሮአቸው የሚሰሙት ሲሆኑ

ነገር ግን በውስጣቸው የሰሙት ነገር አይቆይም:: በአንድ ጆሮ ሰምተው በሌላው የሚያወጡትና በዓለም ነገር የጠፉት ናቸው:: ከእነዚህ ሁለት ዓይነት የሰው ልጆች ውጭ የሚገኙትና እጅግ ጥቂቶቹ ደግሞ የተለየ ነፍስ ያላቸውና በጆሮዎቻቸው ሰምተው በልባቸው የሚቀበሉት ናቸው›› አላቸው::

ፈጣሪም በመጨረሻ እንዲህ አለ፡- ‹‹ቢያዚድ! ወደዚህ የሰው የራስ ቅል የተከመረበት ሥፍራ ያመጣሁህ አንተም ስለእኔ ስታስተምር ይኸን በማስተዋል እንድትፈፅመው ነው:: ስታስተምር በጆሮአቸው ሰምተው በልባቸው ለሚቀበሉት ብቻ ይሁን፤ ሌሎቹ ጊዜንና ድካምህን በከንቱ የምታጠፋባቸው ናቸው:: መልዕክት አድራሽ አድርጌ የመረጥኳት ሕይወትህ ለእኔ ውድ መሆኗን አትዘንጋ::››

ቢያዚድ ሲናገሩ ፡- ‹‹እኔም በዙሪያዬ ስለፈጣሪ ለመማር ከሚሰበሰቡት እጅግ ብዙ ሰዎች መካከል ጥቂቶቹ ብቻ የዘራሁትን ዘር በልባቸው አብቅለውት መመልከቴን እስታወስኩና የመኖሬ ምክንያት ለጥቂቶች ብቻ መሆኑን ተረዳሁት›› አሉ:: ለዚህም ይመስላል ሱፊዎች በእያንዳንዱ የሰው ልጅ ልብ ውስጥ የሚገኘውን ፈጣሪ ተከታዮችን እንዲያየውና እሱንም እንዲለማመድ ከማገዝ ያለፈ ሚና ሊኖረን አይችልም በማለት ከዳር መቆምን ሲመርጡ የምናገኛቸው::

ለሱፊዎች ማንኛውም ሃይማኖት በሰው ልጅና በፈጣሪው መካከል የቆመ ግርዶሽ ያደርጉታል:: የሰው ልጅ ከፈጣሪው መቀበልም ሆነ ማየት የሚሻው ተዓምር ሲኖር ወደሃይማኖቱ የመሄዱ ምክንያት በውስጡ የተቀመጠውን ፈጣሪን ለመረዳት ባለመቻሉ ነው:: እንዱ ፈጣሪ በሁሉም የሰው ልጅ ልብ እኩል የሚገኝ ከሆነ እሱን የመግለጥ ብቃትም እንዲሁ ሰጥቶናልና ስለምን የፈጣሪን ተዐምር በእኛ መሰል ፍጡር ውስጥ ለመመልከት እንደክማለን? በማለት ይጠይቃል:: ቀጣይዋ ወግ ይኸንኑ የምታሳይ ትመስለናለች::

የሱፊዋ ምሁር ራቢያ አል-አዳቢያ ብዙዎች ፈጣሪያቸውን

በራሳቸው ልብ ውስጥ ፈልገው እንዲያገኙት ያደረገች ታላቅ ጠቢብ መሆኗን ይመሰክሩላታል:: አንድ ቀን የሱፊው ምሁር ሀሰን ወደ ራቢያ ዘንድ በመምጣት የደረሱበትን ታላቅ መገለጥ ለማሳየት በመሻት፣ - ‹‹እባክሽ ወደውሃው እካል እንሂድና በዚያ ላይ እየተራመድን ስለፈጣሪ እንወያይ›› ይሏታል:: ራቢያም ከሱፊው ምሁር የቀረበላት ጥያቄ በውስጡ የያዘውን መልዕክት ስትመረምር ሀሰን በውሃ ላይ ለመራድ የመቻላቸውን ብቃት ለማሳየት እንደፈለጉ ተረዳች::

ራቢያም፡- ‹‹በውሃ ላይ? ይኸ ለእኔ ብዙም አይማርከኝም:: ይልቁንስ ለምን ወደደመናው ወጥተን በዚያ ላይ ተቀምጠን እንወያይም?›› አለች::

ሀሰን በዚህ ጊዜ ግራ ተጋብተው ፡- ‹‹ነገር ግን ወደ ደመና መውጣትና በዚያ ላይ ተቀምጦ መወያየትን እኔ አልደረስኩበትም›› ይላሉ::

ራቢያም ፈገግ ብላ፡- ‹‹እኔም አልደረስኩበትም:: ነገር ግን በውሃ ላይ እየተራመድንም ሆነ ደመና ላይ ተቀምጠን ፈጣሪን ብናወያየው ለእሱ ምን ለውጥ አለው? እዚሁ ተቀምጠን የምንነጋገረው በእኛ ውስጥ ተአምር መፍጠር ስለቻለው ፈጣሪ አይደለምን?›› በማለት እንዲቀመጡ ጋበዘቻቸው::

ሱፊዎች በየትኛውም ተአምር እንዳንወሰድ ብቻ ሳይሆን እንዳንደነቅም የሚነግሩን ለዚህ ነው:: ጠቢብ ተአምር ቢሰራም የሰራውን ምንጭ ስለሚያውቅ በራሱ አይደነቅም፣ በሌላው መደነቅንም አይሻም:: የሰነፍ ዱካ ግን ዘወትር በተአምር የፍለጋ መንገድ ላይ የሚገኝ ነው::

በዕውቀት ስትነቃ በልብህ ውስጥ ያለውን ፈጣሪን ወደ መረዳት ትደርሳለህና ነገሮች ሁሉ ውብ ሆነው ይታዩሃል፤ ለሰነፍ ሰው ግን ሁሉ ነገር አስቀያሚ ነው ፤ሰነፍ የጥበብ መገለጫ ወደሆነው ፈጣሪው አልደረሰምና ሕይወት ለእሱ አስቀያሚ ትግል ነች:: መኖሩን እንጂ እንዴት መኖር እንዳለበትም አያውቀውም:: በእሱና ነገሮችን ውብ

አድርጎ በስራቸው ፈጣሪ መካከል ሀይማኖቶች በመቆማቸውም የዘወትር ፍለጋው በውስጡ የሚገኘውን ፈጣሪ ሳይሆን በሚከተላቸው ሀይማኖቶች በውስጥ የሚገለጠውን ተአምራት ነው:: ቀጣይዋ ወግ ይህንኑ የምታሳይ ትመስለናለች::

አንድ ሰው ላም ይገዛና ወደቤቱ ሊወስዳት ቀንዷን ይጨብጣል:: ይኸ ሰው ላም ይግዛ እንጂ ከዚህ ቀደም ስለላም የሚያውቀው ነገር ባለመኖሩ የጨበጠውን የላሚን ቀንድ በእጆቹ አጥብቆ በመያዝ መጎተት ይጀምራል:: ላሚ ግን ከቆመችበት የምትንቀሳቀስ አልሆነም:: ይኸን ድርጊት በቅርቡ ሆነው ሲመለከቱ የነበሩት ሱፊው ቢያዚድ ወደሰውዬው ጠጋ በማለት:- ‹‹ወዳጄ! ስመለከትህ ስለላም ባህሪይ የምታውቀው ነገር ያለ አይመስልም፣ ላምን እንዴት በቀላሉ ገርተህ መቆጣጠር እንደምትችልም አላወቅህበትም›› አሉት::

ሰውዬውም:- ‹‹እኔ የላሚን ያህል ጥንካሬ የለኝምና ምን ማድረግ እንደሚገባኝ አላወቅሁም፣ ስጎትታት ይበልጡኑ እሷ እየጎተተችኝ ነው›› አላቸው::

በዚህ ጊዜ ቢያዚድ:- ‹‹ይልቁንስ ቀንዷን ልቀቀውና ይኸን ሣር በእጅህ ጨብጥ›› በማለት በእጆቹ ላይ ሣር አስጨበጡት:- ‹‹አሁን ከፊቷ በቅርብ ርቀት ቀስ ብለህ መጓዝ ጀምር፤ ነገር ግን ሣሩን ወደአፏ አስጠግተህ እንዳትበላው ደግሞ ተጠንቀቅ:: እሷ ወደሣሩ ስትጠጋ አንተ ደግሞ ወደቤትህ ጉዞህን ጀምር›› አሉት::

ሰውዬው ሱፊው ቢያዚድ የነገሩትን መፈፀም ሲጀምር በቀላሉ ላሚ እየተከተለችው ወደቤቱ ጉዞ ጀመረ:: ላሚ ከፊቷ ያለው ሣር እንጂ ማን እንደወሰዳት ችግሯ አልነበረም:: በፊት ለፊቷ የምታየውንና በሰውየው እጅ የሚገኘውን ሣር እንደተከተለች ወደአዲሱ ቤቷ ሰተት ብላ ገባች::

‹‹እንግዲህ›› ይላሉ ቢያዚድ:- ‹‹ሃይማኖትም እንዲሁ በሰው ልጅ ፊት ለፊት ምኞቱን እንጠልጥሎ የሚመራው ነው:: የሰውን ልጅ ምኞትና መሻት ከፊቱ በተስፋ በማንጠልጠል ስለሚመራው

የምኞቱ ፈፃሚ ከሆነውና በውስጡ ከተቀመጠው ፈጣሪ ጋር ሳይገናኝ ዘመኑን በጉዞ ይጨርሳል፡፡›› ከእንዲህ ዓይነቱ የተስፋ ጉዞ ጋር የተዛመደች አንድ ወግ ከሱፊው ቢያዚድ አሁንም እንመርቅ፡፡

አንድ ታላቅ ንጉሥ የሀገሩን ጠቢባን ሰብስቦ ፡-‹‹ታላቅ ፈተናና አደጋ በተጋረጠብኝ ወቅት የምጠቀምባት ጥበብ ከእናንተ ዘንድ እሻለሁና እሷን አቅርቡልኝ›› በማለት ጠየቀ፡፡

የሀገሩ ጠቢባን በንጉሡ ጥያቄ ግራ በመጋባት ተጨንቁና ይኸን ታላቅ ጥበብ ከሱፊው ቢያዚድ እንደሚያገኙ በማመን ወደእሳቸው መጡ፡፡ ቢያዚድም የንጉሡን ጥያቄ ካደመጡ በኋላ አንዲት ወረቀት ጠቀለሉና፡- ‹‹ይኸን እንካችሁ ለንጉሡ ስጡት፡፡ ነገር ግን እንዲህ በሉት፡፡ ይኸችን ወረቀት የምትፈታት የሚጋፈጥህ ችግር ወይም አደጋ የመጨረሻህና የሕይወትህ መጥፊያ መሆኑን እርግጠኛ ስትሆን ብቻ ነው በሉት›› በማለት ሸኟቸው፡፡

ጠቢባኑም ለንጉሡ ወረቀቱን ሰጥተው መልዕክቱንም አክለው ተናገሩ፡፡ ንጉሡም ወረቀቱን እንደተጠቀለለች በደስታ በመቀበል በአልማዝ ቀለበቱ ሥር ሸጎጣት፡፡ ከዚያ በኋላ ንጉሡ የተለየ አደጋና መከራ ሲጋፈጠው ከዚህ የባሰ ሊመጣ ስለሚችል ወረቀቷን ያን ጊዜ ፈትቼ እጠቀምባታለሁ በማለት እያሳለፈ ሲፅናና ኖሮ በድንገት ታመመ፣ ይሁንና ተኝቶም ቢሆን ሕመሜ ለሞት የማይሰጠኝ ሊሆን ስለሚችል ምስጢር አድርጌ የያዝኳትን ጥበብ አላባክንም ሲል አሰበ፡፡ ነገር ግን ንጉሡ የተያዘበት ሕመም ብርቱ ነበርና ለሞት አበቃው፡፡ በዚህ ጊዜ ጠቢባኑ ተሰብስበው የሱፊውን የጥበብ ምስጢር ለማንበብ ሲከፍቷት ባዶና ምንም ያልተፃፈባት ሆና አገኟት፡፡ በነገሩ ተደናግጠው በእርጅና ወደተያዙት ቢያዚድ ዘንድ በመምጣት ከዓመታት በፊት እንደጎበኟቸው በማስታወስ የባዶውን ወረቀት ምስጢር ጠየቋቸው፡፡

ቢያዚድም፡- ‹‹ወዳጆቼ! ንጉሡን ሲያሳስቡ የኖሩት ችግሮችና አደጋዎች ሁሉ እንግዶችና ጎብኚዎች መሆናቸውን አትረዱምን?

እንደመጡ ከሚሄዱ ክስተቶች ጋር ራስን ማጣበቅ ዞሮ ዞሮ ተሸናፊነት ነው:: ከእንግዳ ጋር በፍቅር መውደቅም ሆነ በጥላቻ መሸሽ ትርፉ ስቃይ ነው:: ለማመጣበት ችግርም ሆነ ደስታ ራሱን እንደማስተላለፊያ ቆጥሮ በመካከሉ በተሰፋ ከመቆም በላይስ ምን ጥበብ ይገኛል?›› በማለት አሰናበቷቸው::

ለሱፊዎች እንግዲህ ጥበብ ማለት በውስጣችን የሚገኘውን ፈጣሪን ከማወቅ መድረስና ከእሱም ጋር አንድ መሆን እንጂ ሌላ አይደለም:: የዛሬውን የሱፊዝም ጉዞ የምንቋጨው በሙላ ናስሩዲን ወግ ይሆናል::

አንድ ቀን ሙላ ናስሩዲን በመንገድ ላይ ሲሄድ ፊቱ በሐዘን የተከማተረ ሰው በእጁ ትንሽ ከረጢት አንጠልጥሎ ይመለከታል:: በዚህ ጊዜ ናስሩዲን ተጠግቶ ‹‹ምን ሆነሃል?›› ሲል ይጠይቀዋል::

ሰውዬውም፡- ‹‹በዚህ ዓለም ላይ የደከምኩበት ነገር በሙሉ በዚህች ከረጢት የያዝኩት ብቻ ሆነና አገኘለሁ›› አለው::

ናስሩዲንም፡- ‹‹እንዴት ያሳዝናል›› በማለት የሚያፅናናው መስሎ በመጠጋት ከረጢቱን ነጥቆት ሮጠ::

በምድር ላይ ‹‹አለኝ›› የሚለውን ነገር በሙሉ የተነጠቀው ሰውዬውም በድንጋጤ እየጮኸ ናስሩዲንን መከተል ጀመረ:: ጥቂት ርቀት እንደተጓዘም ናስሩዲን እየሳቀ ቆመና ጠበቀው:: ሰውዬው ከናስሩዲን አጠገብ እንደደረሰ ከረጢቱን ነጥቆ በእቅፉ ይዞ እየተደሰተ ፡- ‹‹ከረጢቴ! ከረጢቴ የጠፋችብኝ መስሎኝ ደንግጬ ነበር›› አለ::

ናስሩዲን መሳቁን ሳያቋርጥ ፡-‹‹እየህ! የሐዘንህ ምንጭ በእጅህ የያዝከው ነገር ትንሽ ከመሆኗ አልነበረም፤ ነገር ግን የሌላውን ሰው ብዙ ነገር ከመመልከት ነበር›› በማለት ጥሎት ሄደ::

ለዚህም ነው ሱፊዎች ሲመክሩ፡- ‹‹በሕይወት ስጦታ በቃኝ ማለት የደስታ ሁሉ ምንጭ ነው›› የሚሉን:: □

# ‹‹የሰው ልጅ የሚኖረው በሕልሙ ልክ ነው››

ሱፊዎችን ደጋግሜ ለማስተዋወቅ እንደሞከርኩት መሰረታቸው የእስልምና ሀይማኖት ሆኖ ነገር ግን ሌላውንም የምድራችንን ሀይማኖት በእኩል ደረጃ ወደፈጣሪ የመቅረቢያና የመድረሻ መንገዶች አድርገው የሚያምኑና የተቀበሉ ናቸው:: አንዳንድ ምሁራን ሱፊዝምን በእስልምና ሀይማኖት ውስጥ የሚገኝ ወደፈጣሪ በተመስጥዖና በሙሉ ኃይል የመቅረቢያ ጥበብ (mysticism) ነው ሲሉ፣ ሌሎች ደግሞ መሰረታቸው እስልምና ያልሆነ በርካታ ታላላቅ ሱፊዎች አሉና መሰረቱ እስልምና ተደርጎ ሊወሰድ አይገባም ባይ ናቸው:: ሱፊዎች ደግሞ ስለራሳቸው የሚናገሩትና የሚያራምዱትን ስንፈትሽ የምንደርስበት እውነት ቢኖር፡- ‹‹ሁሉም ሀይማኖቶች ፈጣሪን ወደመረዳትና ማወቅ የሚወስደው እውነተኛ መዳንና አብርሆ የሚገለጥባቸው መንገዶች ናቸው::...በአንዱ ሀይማኖት የሚገኝ ቅዱስ በሌላው ሀይማኖት ከሚገኘው ቅዱስ ጋር እኩል ነው፤ ምክንያቱም የሁሉም መለኮታዊ ምንጭ አንድ ነውና›› የሚለው ይሆናል:: ከመነሻው ሱፊ የሚለው መጠሪያ ፈጣሪውን ወደመረዳት (ማወቅ) ለደረሰ የሚሰጥ እንደነበር ስንረዳ በኋላ ግን ይኽን መንፈሳዊ መንገድ ለመከተልና በዚያም ለመመላለስ የወሰነ ሰው ሁሉ መጠሪያውን እንዲያገኝ ሆኗል::

እንግዲህ ይኽን ያህል ስለሱፊዝምና ሱፊዎች መሰረት በአጭሩ ደግመን ለማስታወስ ከሞከርን ከሱፊዝም የእምነት መርሆዎች ዋነኞቹ ተብለው የሚታመንባቸውን ደግሞ እንቃኝ፡-

በሱፊዎች እምነት የመጀመሪያው መርኅ፡-‹‹አንድ ፈጣሪ ብቻ አለ፣ ይኸ ፈጣሪ ደግሞ የሁሉ ነገር ባለቤት ነው:: በአንዳንድ ሁኔታዎች ፈጣሪ ሁሉንም ነገር ነው፤ እንዲሁም ምንም (nothing) ነው:: በእሱ ሁሉንም እናውቃለን፤ እንዲሁም ምንም ማወቅ አንችልም::››

ይኸ መርኅ እንዲሁም የሱፊዎች የማንነት መገለጫ የመጀመሪያው ደረጃ ነው:: በፈጣሪ አንድነት ውስጥ የሚገኘው ሁሉንም የመያዝ ብቃት በእኛ (በሰዎች) አቅምና ችሎታ ሊደረስበትና ሊታወቅ የሚችል አይደለም:: ይኸ ማለት ግን ፈጣሪ ሁሉንም ብቃት በውስጡ የመያዙን እውነት እንድንክደው ደግሞ ሊያደርገን አይችልም:: ምክንያቱም የሁሉ ነገር ፈጣሪና በሪ እሱ ብቻና እኛን ጨምሮ በሁሉ ነገር ውስጥ የሚገለጥ ነውና::

በሁለተኛ ደረጃ የምናገኘው የሱፊዝም መርኅ ደግሞ፡- ‹‹ፈጣሪ በልባችን ውስጥ እስካለ ድረስ የሰው ልጅ የቱንም ያህል ከእሱ ቢርቅ ፈጣሪ ግን በውትር በጣም እየቀረበው ይመጣል:: እናም ፈጣሪን በእውነት ማፍቀር ማለት እሱ የሚገኝበትን ፍጡር ሁሉ ማፍቀር ማለት ነው::

ሱፊዎች ከዚህ የእምነት መርኅቸው የምንረዳው እያንዳንዱ ፍጥረት የተቆቀረው ከፈጣሪው በተወሰደ ማንነት ላይ በመሆኑ ሰውን መጥላት ፈጣሪን መጥላት፤ ሰውን ማፍቀር ደግሞ ፈጣሪን ማፍቀር ነው::

ሦስተኛው የሱፊዎች የእምነት መርህ ደግሞ ቀጣዩን ይመስላል፡- ‹‹ያለፈጣሪ ፈቃድ የሚሆን ምንም ነገር የለም፤ የሰው ፈቃድ ደግሞ አስቸጋሪ ነው፤ ይሁንና የሰውም ፈቃድ ቢሆን በመለኮት ፈቃድ ውስጥ የሚጠቃለል ነው::››

የሰው ልጅ ምኞትና መሻት እጅግ ለቁጥር የበዛ ነው:: ይሁንና መሻትና ምኞቱ የቱንም ያህል የበዛ ይሁን የእንዱን ፈጣሪ ፈቃድ ማለፍም ሆነ መሳት አይችልም፤ ይልቁንም የፈጣሪ ፈቃድ የሰውን ልጅ ምኞት ሁሉ ጠቅልሎ የሚገዛ ብቸኛው ኃይል መሆኑን እንቀበል ይሉናል ሱፊዎች::

ከሱፊዝም በርካታ መርሆዎች አንዱን እንመልከትና ወደ ልዩ ልዩ አስተምህሮቶቻቸው እንሻገራለን::

የሱፊዝም ሌላው የእምነት መርኅ እንዲህ ይላል፡- ‹‹ከፈጣሪ ፈቃድ የተነሳ መልካሙም ሆነ ክፉው ነገር ሁሉ የሚሆነው ከእሱ ነው::››

ከዚህ መርህ አንድ የምንጨብጠው እውነት (ቁምነገር) ቢኖር በሁሉ ነገር ፈጣሪን አመስጋኝ የመሆን ማንነትን ጨብጦ የመገኘት ብቃትን ማረጋገጥ ነው:: ፈጣሪን ስለመልካም ነገር ብቻ የሚያመሰግን ነገር ግን በክፉው ገጠመኙ ፈጣሪው ላይ የሚያንጎራጉር እሱ ፈጣሪን ወደማወቅ ሙላት ገና ያልደረሰ ‹‹ሕፃን›› ነው:: እንዲህ አይነቱን ማንነት የጨበጠ ሰው ደግሞ በሱፊዝም እምነት ሊሰራና ሊቀረጽ እንደሚገባ የሱፊ ምሁራን አበክረው ይመክራሉ:: አንዱና ዋነኛው የሰውን ማንነት ለመቅረጽ የሚጠቀሙበት መንገድም ልዩ ልዩ አስተምህሮቶቻቸው ናቸውና ወደእነሱ እናምራ:: ከሱፊዎች አስተምህሮት በቅድሚያ የምናገኘው ደግሞ ቢያዚድ ቢስታሚን ይሆኑ::

የሱፊው ምሁር ቢስታሚ ‹‹የሱፊ መንገድ›› ከተሰኘው አስተምህሮታቸው የሚከተለውን ገጠመኝ ያመጣሉ::

አንድ ኃያልና በብዙ ሀገራት ዘንድ የተፈራ ንጉስ በዙሪያው በርካታ ጠቢባንን ቀጥሮ ዘወትር በእነሱ ምክር እየተመራ ታላቅነቱን ጠብቆ ለበርካታ ዘመን ኖረ:: ይሁንና አንድ ማለዳ ከመኝታው ተነስቶ በታላቅ ቁንቀትና ግራ መጋባት እንደተያዘ በመናገር የሀገሩን ጠቢባን ሁሉ እንዲጠሩለት አዘዘ::

ጠቢባኑ በዙሪያው እንደተኮለኮሉም፡- ‹‹ምክንያቱን አላውቀውም፣ ነገር ግን የማላውቀው መንፈስ አንድ ቀለበት ፈልጊ እንዳገኝ አዘዘኝ:: ይኸን ቀለበት ፈልጌ ካገኘሁ በግዛቴ ሁሉ ሰላምን ለማስፈን እንደምችል አሳውቆኛል›› አላቸው::

ንጉሱ ይኸን ለጠቢባኑ በመንገር አላበቃም፡- ‹‹ይኸን ቀለበት የግድ ማግኘት ይኖርብኛል:: ይኸ ቀለበት ደግሞ ደስታ ሲሰማኝ ውስጤን በሀዘን የሚሞላና እንዲሁም በሐዘኑ የደስታዬ ቅጽበት

ለዘንም መኖሩን የሚያስታውሰኝ ሊሆን ይገባዋል›› አሏቸው፡፡

ጠቢባኑ የንጉሡን ነገር አድምጠው ሲያበቁ መመካከር ጀመሩ፡፡ ‹‹እንዲህ ዓይነቱን ቀለበት ለንጉሡ እንዴት ማግኘት ይቻለናል›› በማለት በጥልቅ ሃሳብና ጭንቀት ተውጠው ከቆዩ በኋላ የሱፊው መምህር ቢስታሚ የመጨረሻውን መፍቻ ለንጉሡ ጥያቄ እንዲያበጁ እምነው ወደእሳቸው አመጡት፡፡

የሱፊው መምህር የጠቢባኑ ጭንቀት ምክንያት የሆነውን የንጉሡን ጥያቄ ካደመጡ በኋላ እንዲህ አሉ፡- ‹‹ለንጉሱ ንገሩት፡- ለንጉሥ የሚገባውን ቀለበት በጣትህ ላይ አጥልቅ፣ በላዩም ‹ይኸም ያልፋል› የሚል ጽሁፍ አስቀርጽበት፡፡ እንግዲህ ደስታም ሆነ መከራ በገጠመህ ሰዓት የጣትህን ቀለበት ተመልክተህ ሁሉቱንም በእኩል ታስተናግዳለህ፡፡››

ከቢስታሚ አስተምህሮት የምንጨብጠው አንድ ቁምነገር ቢኖር ደስታም ይሁን መከራ በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ ተፈራራቂና አይቀሬ ክስተቶች መሆናቸውን ነው፡፡ ይሁንና ሁለቱም ሃላፊ መሆናቸውን በሚረዱ ሰዎች ዘንድ ደግሞ መከራም ሆነ ደስታ የሚፈጥሩት ልዩነት የለውም፡፡ መደነቅም ሆነ መደንገጥ ፈጣሪን ወደማወቅ ስትደርስ ከአንተ ዘንድ አይገኙምና፡፡

ቀጣዮቹን ሁለት ወጎች ደግሞ ሱፊው ማሁድ ፋርሃን ያቀብሉናል፡፡ አንድ በዕድሜው የገፋና ጺሙን በፊቱ ላይ ያንዠረገገ ሰው ወደ ታዋቂው ጸጉር ቆራጭና የሱፊ ደቀመዝሙር ዘንድ በመምጣት፡- ‹እባክህ አዲስና ወጣት የሆነች ሚስት ወደቤቴ አምጥቻለሁና ከጢሜ ውስጥ የሸበቱትን እየመረጥህ ቁረጥልኝ›› ይለዋል፡፡

በዚህ ጊዜ ጸጉር ቆራጩ ለሰውዬው መቀስ እያቀበለው፡- ‹‹ጌታዬ! እንዲህ ዓይነቱን ሥራ ለመስራት የተትረፈረፈ ጊዜ የለኝም፡፡ ለምን አንተ ተቀምጠህ ሽበትህን ስትነቅል አትውልም?›› በማለት መለሰለት፡፡

አንዳንድ ጊዜ ከሕይወት እንቀበለው ዘንድ የሚገባንን እውነታ ለመሸሽ የምንከፍለው ድካም ከንቱነታችንን ብቻ ሳይሆን በዕውቀት ያለመንቃታችንን ድክመት የሚያጋልጥም ይሆናል፡፡ እናም

‹‹መለወጥ የማትችለውን የሕይወት እውነታ መቀበል የደስታህ ምንጭ ሲሆን መታገልህ ደግሞ የስቃይህ ትርፍ ይሆናል›› ይሉናል ሱፊው ፋርዛን::

ማስድ ፋርዘን ቀጣይዋ ወጋቸው በሱፊዎች ዘንድ እንደአንድ የአስተምህሮት ማስተላለፊያ አድርገው የሚጠቀሙበትን ገጸ-ባህርይ ሆጃን በማምጣት ነው::

አንድ ቀን እጅግ የተራበ ሰው በእጁ የዳቦ ቁራጭ ይዞ በጎዳና ሲጓዝ በአቅራቢያው ከሚገኝ ሆቴል የሚወጣ የሥጋ ጥብስ ሽታ አፍንጫውን ይደዘዋል:: ይኸ ሰው ሽታው የሚያመጣውን የምግብ መዓዛ ተከትሎ ዳቦውን መግመጥ ጀመረ:: ይኸንኑ ድርጊቱን የሆቴሉ ባለቤት ሲመለከት ግን ከንዳው በሩጫ በመውጣት አንገቱን ያንቀውና እንዲከፍል ግብግብ ይገጥመዋል::

ሁኔታውን በቅርብ ሆኖ ሲከታተል የቆየው ሆጃ ተጠግቶ በመገላገል ምን እንዳጣላቸው ይጠይቃል:: የሆቴሉ ባለቤትም፡- ‹‹ደረቅ ዳቦ ገዝቶ ሲያበቃ ከሆቴል ቤቴ በሚወጣው የሥጋ ጥብስ ሽታ በልቷልና ለጥብሱ ሽታ ሊከፍለኝ ይገባል›› አለ::

ሆጃም ከሱን አዳምጦ ሲያበቃ ዲናር ከኪሱ በማውጣት መሬቱ ላይ በመጣል ካንቃጨለ በኋላ አንስቶ ኪሱ መልሶ ከተተና፡- ‹‹ይኸው ከፍዬለታለሁ›› አለው::

የሆቴሉ ባለቤት ንዴቱ ይብሱን ገንኖ፡- ‹‹ዲናሩን እኮ መልሰህ ወደኪስህ ከተትኸዋል›› አለው::

ሆጃም፡- ‹‹እሱ የጥብሱን ሽታ ካሸተተ፣ አንተም የዲናሩን ድምጽ ከሰማችሁ እኩል እኮ ነው›› በማለት ፍርዱን ሰጠ::

የምሰራቀን የሱፊዝም ጉዞ የምንቋጨው መንሻችን ወደነበሩት ቢያዚድ ቢስታሚ ተመልሰን በሚነግሩን ቀጣይዋ ወግ ይሆናል::

አንድ ቅዱስ ሰው ደቀመዛሙርቱን አስከትሎ ከአሉ መንደር ወደሌላው ለመሄድ ፈለገና ሁሉቱን መንደሮች የሚከፍለውን ሰፊ ሐይቅ እንዴት መሻገር እንደሚችል ሲያሰላስል በድንገት ጀልባ ይዞ በሐይቁ ላይ የሚመላለስ ሰው ተመለከተ:: በዚህ ጊዜ የጀልባውን ባለቤት ጠርቶ፡- ‹‹እባክህ የጠየቅኸኝን ሁሉ እከፍላለሁ፣ ብቻ

ወደዚያች መንደር በጀልባህ አሻግረኝ ›› ሲል ጠየቀው::

የጀልባዋ ባለቤትም፡- ‹‹ባሬ ምሳዬን የምመግበው ከሰጠኸኝ ላሻግርህ እችላለሁ›› ሲል መለሰለት::

በዚህ ጊዜ ቅዱሱ ሰው የጀልባዋ ባለቤት በጠየቀው የድካሙ ዋጋ ተደነቀ:: ወደ ደቀመዛሙርቱ በመዞርም እንዲህም አላቸው፤ - ‹‹ይኸ ሰው የድካሙን ዋጋ ከቀን ቀለቡ አሳልፎ አለመጠየቁ ያደንቃል:: ተመልከቱ! ከዚህም ተማሩ! የሰው ልጅ የሚኖረው በሕልሙ ልክ ነው:: ታላቅም ሆነ ታናሽ የመሆናችሁ ምስጢር የሚገኘው ከሥራችሁ ሳይሆን በውስጣችሁ ከሰነቃችሁት ሕልም እንደሚሆን እንዲሁ ነገርኳችሁ›› በማለት ወደ ጀልባው ወጣ:: □

pdf by @shuktus_books

# ‹‹ቅድስና የፈጣሪ እንጂ የሰው መለኪያ አይደለም››

በሱፊዝም ጎዳና ስንቀጥል ከሱፊዝም የእምነት መርኅ መካከል ዋንኞቹን በቅድሚያ ቆንጥረን ለማየት እንሞክራለን፡፡ ሁሉ የዚህ መጣጥፍ መነሻችን የሚሆነው ደግሞ አራቱ የሱፊ መንገድ መገለጫ የሆኑት ደረጃዎች ናቸው::

የመጀመሪያውና በሱፊ መንገድ ላይ የምናገኘው ደረጃ ‹‹ሁሉም ሃይማኖቶች የሞራልና የምግባር መገለጫ መሆናቸውን ማስተማር የያዘ ሲሆን ይኸ ደግሞ ለሰኬት የሚበቃው እስልምናን በማጥናት ነው›› የሚለው ይሆናል:: የእስልምና እምነት ተከታይ ያልሆኑ ሱፊዎች ደግሞ ይኸንኑ የሞራልና የምግባር ታላቅነት ለማጽናት የተለያዩ ሀይማኖቶች መጻሕፍትን መስረታቸው ያደርጋሉ::

ሁለተኛው በሱፊዝም መንገድ የምናገኘው ደረጃ የእስልምና ሀይማኖት በሕግና አምልኮ ከሚሰጠን ውጫዊ ልምምድ በተለየ በውስጣዊ ሰብእናችን የምንፈጽመው ልምምድ ላይ ማተኮር ይሆናል:: ሁለቱ በሱፊዝም መንገድ ላይ የምናገኛቸው ቀዳሚ ደረጃዎች የሚፈጸሙት እንግዲህ በልምምድና ሊቃውን (መምህሩን) በመምሰል ላይ በተመሰረተ የአምልኮ ተግባር(መስጠት) ሆነው እናገኛቸዋለን::

ሦስተኛው የሱፊዝም መንገድ ላይ የምንደርስበት ደረጃ ተንዞ ከሱፊዝም አስተምህሮቶችና ልምምዶች ጀርባ የሚገኘውን ትርጉም መረዳት የሚዉብተበትና ፈጣሪውን በሱፊዝም ምስጢራዊ እውነታዎች በተግባር የሚገልጥበት ነው::

አራተኛውና የመጨረሻው ደረጃ ደግሞ ‹‹ማሪፋህ›› ወይም ‹‹ግኖሲስ›› ተብሎ ይጠራል:: ይኸ ደረጃ የፈጣሪን እውቀት በሙላት ወደመረዳት የሚደረስበት ሲሆን ይኸን ደረጃ ግን በነቢያት፣ ታላላቅ መምህራንና ቅዱሳን ብቻ የሚጨበጥ ሥፍራ ሆኖ እናገኘዋለን::

እንግዲህ የሱፊዝምን መንገድ ተከትሎ በመጓዝ (ወይም ለማንኛውም ሀይማኖት ፍጹም የተሰጠ ሆኖ በመጓዝም ሊሆን ይችላል) የሚደረስበት ግብ ቅዱስ መሆን አይደለም፣ ነገር ግን ሕይወትን ለፈጣሪ ፈቃድ ብቻ የተለየ ማድረግና በእሱ ጸጋ መኖር፣ ይኸንንም ብቻ መቀበልን መቻል ነው:: በዚህ ዓይነቱ ጉዞ ተሳታፊ ሆነህ ግብህ ያደረግኸው ግን ቅድስና ከሆነ ይኸ የአንተ ምኞትና ፈቃድ እንጂ የፈጣሪ ባለመሆኑ ከቅዱሳን እንደአንዱ ለመሆንም ሳትታደል ታልፋለህ:: በሱፊዝም ከሰው ልጅ የሚጠበቅ ተግባር ቢኖር እንደፈጣሪ ሃሳብና ፈቃድ ራስን ለእሱ አስገዝቶ መገኘት ብቻ ነው፣ ቅድስና የፈጣሪ እንጂ የሰው መለኪያ አይደለምና::

ይኸን እንደመነሻ ካሰፈርን በቀጥታ የምዘልቀው ወደሱፊዎች አስተምህሮት ይሆናል:: የሱፊዝም ጠቢባን ስለፈጣሪ፣ ሕይወት፣ እውነት፣ እምነት፣ ጥበብ ፣እውቀት...ወዘተ በወግና ምሳሌ እያዋዙ የሚነግሩንን ዛሬም ለመከፈል ስንነሳ በቅድሚያ የምናገኘው የሱፊውን ጠቢብ ቢያዚድ ቢስታሚን ይሆናል::

ቢስታሚን በዚህች ወጋቸው ሁለት ማስተዋል የጎደላቸው (ሞኞች) ሰዎችን ገጠመኝ ያመጡልናል:: ሁለቱ ሞኞች አንድ ቀን ከባህር ዳር ደርሰው ጀልባ በመከራየት ዓሳ ለማጥመድ ጉዞ ይጀምራሉ:: በባህሩ ላይ ጥቂት ርቀት ተጉዘው በአንዱ ስፍራ ሲደርሱ ወጥመዳቸውን ይጥላሉ:: እንደአጋጣሚ ሆኖ በዚያ ስፍራ በርካታ የዓሳ ክምችት ኖሮ ወጥመዳቸው ከሚሸከመው በላይ ለማጥመድ ይችሉና ከፍተኛ ደስታ ይሰማቸዋል:: ዓሳቸውን ወደጀልባዋ አጋብተው ጉዟቸውን ወደ ባህሩ ዳርቻ እንደ ጀመሩ ግን አንዱ፡- ‹‹ወደዚያ በርካታ ዓሳ ወደሚገኝበት ስፍራ ከእንግዲህ ተመልሰን መምጣት እንዴት እንችላለን?›› ሲል ጓደኛውን ጠየቀው:: ጓደኛውም፡- ‹‹አይዞህ! ቀድሜ ይኸንን አስቤበት ጀልባዋ ላይ በጠመኔ ምልክት አድርጌያለሁ›› አለው::

በዚህ ጊዜ ጓደኛው ፡- ‹‹ሲበዛ ሞኝ ነህ! በድንገት ስንመጣ የከራዩን ሰዎች ጠመኔውን አጥፍተው ሌላ ጀልባ ቢሰጡንስ?›› ሲል በቁጣ አፈጠጠበት::

‹‹እንግዲህ›› ይላሉ ቢስታሚ ‹‹አብዛኛው የሰው ልጅ ወደፊጣሪ በረከት መድረሱን እንጂ እንዴትና በምን መንገድ እንደሆነ መረዳት የተሳነው ሰነፍ ነው:: እነዚህን ሞኞችን ልብ በሉ! ወደበረከቱ ሥፍራ ያደረሰቻቸው ጀልባ ከበረከቱም ሆነ ከበረከቱ ስፍራ ጋር የሚያገናኛት ምንም ነገር የለም:: ቁምነገሩ በሰፊው ባህር ላይ የበረከቱን ስፍራ ወይም መንገድ ማወቅና መረዳት ነበር›› ይሉናል

ከቢስታሚ ወግ አንድ እንመርቅ፡- አንድ ሰው በዘመኑ ሁሉ ስጋ በልቶም ሆነ ትምባሆ አጭሶ ወይም ወይን ጠጥቶ አያውቅም:: ይኸ ባህርይ ደግሞ በእጅጉ የተደነቀና ከታላላቆቹ ጠቢባን ተርታ የሚያስቀምጠው ሆነ፤ ምክንያቱም ራሱን ከምድራዊ ፍላጎቶች መግዛት የቻለ ሰው የአዋቂነቱና ጠቢብነቱ ዋነኛ መስፈርት የሆነውን ጉዳይ አሟልቷል ተብሎ በመታሰቡ ነው:: ከዚህ በላይ ይኸ ሰው ዕድሜው ዘጠና ዓመት መሙላቱ ከታላላቆቹ የሱፊ ጠቢባን ስር የመቀመጥን ዕድል አጎናጸፈውና የዘውትር የክብር ስፍራ ተዘጋጀለት::

ይኸ ሰው በሚቀመጥበት ስፍራ የሚገኙ የሱፊ ጠቢባን በሙሉ ዕድሜያቸው ከዘጠና ዓመት ያለፈ በመሆኑ ሌሎች ጥበብና ዕውቀትን ፍለጋ ወደእነሱ ሥፍራ በመምጣታቸው የሰውዬው ደስታ ወሰን አጣ::

ይሁንና አንድ ቀን በዕድሜ በጣም የገፉ የሱፊ ጠቢብ ሲጃራ እያጨሱና በእጃቸው የወይን ብርጭቆ ጨብጠው በመምጣት በስፍራው በክብር ሲቀመጡ ተመልክቶ ተደነቀ:: አጠገቡ ወደተቀመጡት የሱፊ መምህርም በመዞር፡- ‹‹እኚህ በታላቅ ክብር የተቀበላችኋቸው ሰው ማን ናቸው?›› ሲል ጠየቀ::

የሱፊው መምህርም፡- ‹‹እሳቸውም ታላቁ የሱፊ ጠቢብና መምህር ሀሰን አልበሲ ናቸው›› ማለት ይመልሱለታል::

‹‹ታዲያ ስለምንድን ነው ትምባሆ የሚያጨሱት፤ ወይንስ

የሚጠጡት? ለመሆኑ የሚመገቡትስ ምን ይሆን?›› ሲል ጠየቀ::

‹‹እሳቸውማ የሚመገቡት ሥጋ ነው፤ እንደምታየው ትምባሆ ያጨሳሉ፤ ወይንም ይጠጣሉ›› አሉት::

‹‹ታላቅ መምህርና ጠቢብ ሆነው ይኽን ማድረጋቸው የሚደንቅ ነው›› ሲል ሰውዬው በራሱ ማንነት ኩራት እየተሰማው አስተያየቱን ሰጠ::

በዚህ ጊዜ የሱፊው መምህር፡- ‹‹ወንድሜ አትሳሳት! እኚህ ታላቅ የሱፊ መምህር እኮ ዕድሜያቸው አንድ መቶ ሃምሳ ዓመት ተጠግቷል:: ከእንግዲህ መምህሩ የሚፈተኑበት ምንም ዓይነት ምድራዊ ነገር ስለሌለ ነው በቅርቡ ሁሉ ነገር የተፈቀደላቸው›› ሲሉ ምስጥሩን አብራሩለት::

‹‹እንግዲህ›› ይሉናል ቢስታሚ የዚህችን ወግ ዋንኛ ቁምነገር ሲያስጨብጡን፡-‹‹ ሰዎች መፈተናቸውን የሚያልፉበት ዘመንና የዕውቀት ደረጃ አለ:: አንድ ጊዜ ዘመኑንና ደረጃውን ሲያልፉ ከዚያ በኋላ በውስጣቸው የሚቀር ምኞትም ሆነ መሻት አይኖርም:: በሕይወት ውስጥ አጨብጭቤአለሁ፤ እደርስበታለሁ...በማለት የምታልመው ግብም ሆነ ፍፃሜ ሲጠፋ ደግሞ ያን ጊዜ መኖር የምትጀምረው ዛሬን ብቻ ይሆናል::››

በቢስታሚ የጀመርነውን የሱፊ ወግ የሚያስቀጥልልን ሙላ ናስሩዲን ይሆናል:: የሱፊ ጠቢባን የተለያዩ አስተምህሮቶቻቸውን ለዘመናት ማስተላለፊያ መንገድ አድርገው ሲጠቀሙበት የኖሩት በሙላ ናስሩዲን መሆኑን በቀደሙት መጣጥፎቼ ለማሳየት ሞክሬአለሁና በቀጥታ ወደወጎቹና ገጠመኞቹ መዝለቅ ግድ ይሆንብኛል:: ሙላ ናስሩዲንን በቅድሚያ የምናገኘው ደግሞ በሕንድ ይሆናል::

ናስሩዲን ወደ ሕንድ ተጉዞ አንዲት ከተማ በእግሩ እየተዘዋወረ ሲጎበኝ በድንገት ከመንገድ ዳር ተቀምጠው በተመስጦ ማሰላሰል የያዙ አንድ መነኩሴ ይመለከታል:: ናስሩዲን መነኩሴውን እየተመለከተ በውስጡ ፡- ‹‹እኚህ መነኩሴ እንደእኔ በዓለም ጥበብና ዕውቀት የበለጸጉ ፈላስፋ መሆን አለባቸው›› ሲል አሰበና በፍጥነት

ተጠግቶ ከአጠገባቸው ተቀመጠ::

ናስሩዲን ጥቂት ከመነኩሴው ጋር እንደተጨዋወተ እንዲህ አሉት፡- ‹‹እኔ ዮጊ ነኝ:: ህያዋን የሆኑ ነገሮችን ሁሉ በማገልገል የሚደሰት ሰው ማለት ነው:: ለእኔ ደግሞ ወፎችንና ዓሳዎችን ማገልገል ትልቁ ደስታዬ ነው::

ይኽን የሰማው ናስሩዲን ተደንቆ እየተመለከታቸው፡- ‹‹የሚገርም ነው:: እኔና እርስዎ እንደምንመሳሰል አስቀድሚም ገምቼ ነበር:: እኔ ደግሞ ለዓሳዎች ያለኝ ከፍተኛ ፍቅር ከእርስዎ በተለየ መንገድ ይገለፃል:: በአንድ ወቅት አንድ ዓሣ ሕይወቱን ከሞት ታድጎኛል›› አላቸው::

መነኩሴው በሰሙት ነገር በመደነቅ፡- ‹‹እንዴት የሚያስደስት ነገር ነው? እኔ በዘመኔ ከዓሣዎች ጋር ባለኝ ከፍተኛ ቅርበት እንዲህ ዓይነቱን አጋጣሚን ለማስተናገድ አልታደልሁም:: አንተ ታላቅ ጠቢብ መሆንህን ተረድቻለሁና ከፊትህ በአክብሮት ልንበረከክ ይገባኛል›› በማለት መነኩሴው ከናስሩዲን ፊት በጉልበቶቻቸው በመንበርከክ እጆቻቸውን ገጥመው ሰገዱለት::

ናስሩዲን መነኩሴው ወደተቀመጡበት እንዲመለሱ ካግባባቸው በኋላ ለምን ይኽን አክብሮት ሊሰጡት እንደቻሉ ሲጠይቃቸው፡- ‹‹እባክህ! ከአንተ ብዙ ጥበብ መማር እችላለሁና ንገረኝ:: ለመሆኑ ዓሣው እንዴት አድርጎ ነበር ሕይወትህን ከሞት ለመታደግ የበቃው? ›› ሲል ጠየቁት::

ናስሩዲን ምላሽ ለመስጠት ቢያቅማማም መነኩሴው አጥብቀው ስለለመኑት እንዲህ አላቸው፡- ‹‹ይኼን ያህል እንኳን ትልቅ ቁምነገር አይደለም፣ ነገር ግን ንገረኝ ካሉ ደግሞ ምን ማድረግ እችላለሁ:: አንድ ቀን በጣም ተርቤ በመንገድ ስጓዝ ከአንድ የባህር ዳርቻ ደረስሁ:: በዚያም አንድ እንጨት በማንሳት ሜዳን ከጠረብኩት በኋላ በውሃው ውስጥ ደጋግሚ በመስበቅ አንድ ዓሣ ለመያዝ በቃሁና እሱን ጠብሼ በላሁ፣ እንግዲህ ዓሳው የዚያን ቀን በርሃብ ከመሞት የታደገኝ በመሆኑ ዘወትር አስታውሰዋለሁ›› በማለት ተሰናብቷቸው መንገዱን ቀጠለ::

፣ የምዕራፉን የሱፊዝም ጉዞ የምንጠቀልለው በተጣዩ የሙላ ናስሩዲን ወግ ይሁን፡- ናስሩዲን ከሕንድ ወደ ሀገሩ እንደተመለሰ ብዙም ሳይቆይ ይሞታል:: በፍጥነት ነፍሱ የደረሰችበት ስፍራ ደግሞ ገሃነም ሆነ:: ከገሃነም ሲደርስ ሰይጣን ሲጠብቀው አገኘ:: ሰይጣን ለረዥም ጊዜ ሲጠብቀው እንደኖረ ከገለጸለት በኋላ ከዲያብሎስ ጋር ያስተዋውቀውና መኖሪያውን ሊያስገበኘው ይዞት ሄደ::

ጥቂት ተጉዘው ወደ አንድ ሰፊ ክፍል ይዞት ይዘልቅና፡- ‹‹እንግዲህ ናስሩዲን! መኖሪያህ ይኸ ነው›› ይለዋል::

ናስሩዲንም፡- ‹‹በዚህ የገነት ስፍራ በመግባቴ ደስተኛ ነኝ›› ይላል::

ሰይጣን ግራ ተጋብቶ፡- ‹‹ናስሩዲን ተሳስተሃል! ይኸ እኮ ገነት አይደለም›› ይለዋል::

ናስሩዲንም ፈገግ ብሎ፡- ‹‹ይኼ የአንተ አስተሳሰብ ነው:: ሕንድን ብታውቃት ይኸ ስፍራ ገነት ለመሆኑ ከእኔ ጋር ተስማምተህ አገኝህ ነበር›› ብሎት ወደስፍራው ዘለቀ::

በሱፊዎች አስተምህሮት በኑሮአችን ውስጥ መልካም ወይም መጥፎ በማለት የምንወስነው ነገር ሁሉ የአስተሳሰባችን ውጤት እንጂ ነገሩ በራሱ መልካም ወይም መጥፎ ከመሆኑ ላይ አይደለም:: እናም ፡- ‹በሕይወት ጉዞ የምንጓጓለትም ሆነ የምንፈራው ምኞታችንን እንጂ ሌላ እውነት አይደለም:: የሰው ልጅ የመፈጠሩ ግብ ሊሆን የሚገባው ግን ከምኞቱ ጀርባ የሚገኘውን እውነት መጋለጥ ነው፤ ይኸ እውነት ደግሞ ፈጣሪ ነው::› □

# «እምነት ሲናገሩት ቀላል ለማድረግ ግን እጅግ የከበደ ነው»

በዚህ ምዕራፍ ከሱፊዝም የምንመዘው ሀሳብ መልካም ምግባር (Virtues) ነው። ለሱፊዎች ከመልካም ምግባር መካከል አንዱና የመጀመሪያው ደግሞ እምነት (Faith) ነውና በዚሁ ጉዳይ ጥቂት እንግፋ።

ሱፊች ስለእምነት ሲናገሩ «እምነት ሲናገሩት ቀላል ለማድረግ ግን እጅግ የከበደ ነው» ይላሉ። አንዳንዴ እምነታችንን ከእግዚአብሔር በቀር በቀረው ነገር ላይ ሁሉ የምናደርግበት ጊዜ አለ። በፍርድ ቤት ስንከሰስ ወይም ስንከስ እምነታችን ሁሉ በጠበቃችን ላይ ይሆናል፤ እንዲሁም ስንታመም ደግሞ የእምነታችን ታላቅነት በዶክተሮቻችን ላይ ይገለጣል፣ ገንዘባችን እንደሚያድነንና እንደሚጠብቀንም እንታመናለን፤ ዕውቀትና ጥበባችንን ደግሞ ከችግር እንደምንወጣበት እምነን እንመካለን። እናም እምነታችን ሲመረመር የተመሠረተው በተፈጠረው ነገር እንጂ በፈጣሪው ላይ አይደለም።

«ከፈጣሪ 99 መልካም ነገሮች አንዱ ሰላምን መስጠቱ ነው» የሚሉት ሱፊዎች «ሰላም ማለት ጥበቃ፤ ደህንነትና ጤንነት ሲጠቃለል ደግሞ ሙሉነት (ሙሉ መሆን) ነው» ይላሉ። «በበሰበሰ ግንድ ላይ ተደግፎ እንደማይወድቅ የሚታመን ማን ነው? ሙሉ በሆነውና ጤነኛ በሆነው ላይ ብትደገፍ ግን ሳትጠራጠር ትቆማለህ፤ እሱም ፈጣሪ ነው። ከእሱ ውጭ ፍፁም ድጋፍና መታመኛ የሚሆን ነገር ብትፈልግ አታገኝም። ስለዚህም እውነተኛ ሰላም የሚገኘው በፈጣሪ ላይ ባለህ እምነት ብቻ ነው» በማለት ሱፊዎች ወደአንድ ታሪክ መሸጋገሪያ የሚሆን ሃሣብ ይወረውሩልናል።

‹‹እንደእምነታችን በተደጋጋሚ የሚፈተን ነገር የለም። ሁሉን አዋቂ

የሆነው ፈጣሪ የእኛን የፈተና ውጤት አስቀድሞ ቢያውቀውም ራሳችንን በተሻለ እናውቀው ዘንድ ስለሚፈልግ ግን ለእምነት ፈተና አሳልፎ ይሰጠናል» ይላሉ:: በዚህ ሐሣብ ወደሚያነሱልን ታሪክ እንለፍ:-

አንድ ሰው ከገደል አፋፍ አዳልጦት ወደታች መንከባለል ይጀምራል:: በዚህ መሃል ከገደሉ አንድ ጥግ የበቀለች ቁጥቋጦ ላይ እጁ ያርፍና እሷን ይዞ እየጮኸ ድረሱልኝ ይላል:: ዓይኖቹን ወደታች ቢወረውር የገደሉ መጨረሻ አልታይ አለው:: የቁጥቋጦዋ ሥርም የዚህን ሰው ክብደት መሸከም የሚችል አልነበረምና ሥሯ ቀስ በቀስ መላቀቅ ይጀምራል:: በዚህን ጊዜ ይኸ ሰው ከዚህ አደጋ ከእግዚአብሔር በቀር ሊያድነው የሚችል ሌላ ኃይል እንደሌለ ይረዳል:: እግዚአብሔርንም አንጋጦ በጩኸት መጣራት ይጀምራል:: ለዚህ ድምፅ ምላሹ ሳይዘገይ ከእግዚአብሔር መጣ:- «በእጅህ የያዝከውን ቁጥቋጦ ልቀቀው!» ይኸ ሰው ለዚህ ምላሽ ጥቂት አሰበና አሁንም አንጋጦ ወደ ሰማይ እየተመለከተ:- «እባካችሁ! በሰማይ ላይ ሌላ ሊያነጋግረኝ የሚችል ካለ ያነጋግረኝ» በማለት የእምነቱን ልክ አሳየ ይላሉ:: የተነሳንበትን የእምነት ነገር ከሱፊዎች የተለያየ ገጠመኝና ተሞክሮ መመልከት ስንጀምር ጃሚ ይቀበሉናል:-

አንድ ሀብታም ሰው በአትክልተኛው ሚስት ቁንጅና ሁልጊዜ ይማረክ ኖሮ አንድ ቀን ወደሩቅ ቦታ እንዲሄድ ያዝዘዋል:: አትክልተኛ ውም ትዕዛዙን ተቀበሎ ሲሄድ ሴቲቱን ወደ መኝታ ቤቱ ይጠራና «በሩን ዝጊው!» ይላታል:: እሷም:- «ጌታዬ! ከአንድ በር በቀር ሁሉንም ዘግቻለሁ! እሱን በር ግን ለመዝጋት አይቻለኝም» ትለዋለች::

«የትኛው በር ይሆን ያልተዘጋ?» በማለት ቢጠይቃት «ለመዝጋት የማይቻለኝ በር በእኛና በእግዚአብሔር መካከል ያለውን ነው» በማለት መለሰችለት:: ሀብታሙ ሰውዬም በድርጊቱ ተፀፅቶ ይቅርታውን ለምኖ አሰናበታት ይሉናል::

እዚህ ላይ አል-ጋሀዛሊ ይመጣሉ:- «በእግዚአብሔር ላይ ፍፁም እምነትን መጣል ማለት እንደሕፃን መሆን ማለት ነው:: ሕፃኑ እናቱን አና፡ አውጥቶ ባይጠራትም ወይም በቃላት ፍላጎቱን ባይገልፅም የውስጡን ፍላጎት ግን በሚገባ እንደምትረዳለት ይገባዋል» ይሉናል::

አል-ጋህዛሊ እንደ ይጨምሩልናል፦ «በእግዚአብሔር ላይ እምነታችን ይፀና ዘንድ ሦስት መጋረጃዎችን ልንቀድ ተገቢ ነው፦ የመጀመሪያው በሁብታችን ደስታን ለማግኘት ማሰብ! ሁለተኛ ሀብት በማጣታችን ማዘንና ሦስተኛው በራስ ውዳሴ መደሰትን ነው» ይሉናል።

ቀጥሎ የምናገኛትን የሚነግሩን ደግሞ ሼኽ ሙዛፊር ናቸው፦ የሱፊው መምህር የአቡ አል-ቢስታሚ ደቀመዝሙር አንድ ቀን ወደእርሳቸው መጥቶ «የሁላችንንም እምነት ሰይጣን እየወሰደብን ተቸገርን» ቢላቸው አል-ቢስታሚም «ሰይጣንን ጥሩልኝ» በማለት ከፊታቸው እንዲቀርብ ያደርጉና ለምን የደቀ መዛሙርቶቻቸውን እምነት እንደሚሰርቅ ይጠይቁታል። ሰይጣንም፦ «ማንንም ሰው ቢሆን አንዳች ነገር እንዲያደርግ ማስገደድ አልችልም። ይኸንን ለማድረግ ለእግዚአብሔር ያለኝ ፍራቻና አክብሮት ያግደኛል። በእርግጥ አንዳንድ ሰዎች በየነገሩ እምነታቸውን እግራቸው ሥር ሲጥሉት አገኝና እኔ ደግሞ አንስቼ ከእነሱ እርቄ እጥለዋለሁ» በማለት መለሰላቸው።

ከሼኽ ሙዛፊር አንድ እንጨምር፦ ሀሰን አል-ባሳሪ በብዙ ሰዎች ታጅበው ወደመካ ሲሄዱ በመንገድ ላይ የውሃ ጥም ይበረታባቸዋል። ይሁንና በአካባቢው አንዳች የውሃ ዘር ማግኘት አልቻሉም። በድካም ውስጥ ሆነው ጥቂት እንደተጓዙ አንድ የውሃ ጉድጓድ ያገኙና ከተከታዮቻቸው ጋር ዙሪያውን ከበው ቢመለከቱት እጅግ ጥልቅ ይሆንባቸዋል። በዚህን ጊዜ አል-ባሳሪ «ሁላችንም በእምነት ብንፀልይ ውሃው ወደ ላይ ይመጣል» በማለት ተከታዮቻቸውን ይነግራሉ። ሁሉም በአንድ ልብ ሲፀልዩም ውሃው ወደላይ መምጣት ይጀምራል። አል-ባሳሪም እግዚአብሔርን አመስግነው ከተከታዮቻቸው ጋር ውሃውን ጠጥተው እንደረኩ አንዱ አንጠልጥሎት በነበረው ኮዳ ከውሃው መቅዳት ይጀምራል። ይኸን ጊዜ ውሃው በፍጥነት ወደነበረበት ይመለሳል። አል-ባሳሪም ለተከታያቸው ለምን ከውሃው መቅዳት እንደፈለገ ቢጠይቁት «ለወደፊቱ ውሃ ሲያስፈልገን እንዳንቸገር ብዬ ነበር» ይሉቸዋል። አል- ባሳሪም፦ «አየህ! እምነትህ ከእግዚአብሔር ወደ ቅልህ ሲዞር ውሃውም ወደነበረበት ተመለሰ» አሉት። አል-ጃሚ ከዚህች ታሪክ ጋር የምትጉዳኝ ምክር አለቻቸው፦ «በእምነት ጉዳና ላይ እየሄደ ለችግሩ

መፍትሔ የማያገኝ ማንም የለም»።

በሼኽ መሣፈር አንድ ታሪክ በመልካም ምግባር ሥር የጀመርነውን የእምነትን ጉዞ አብቅተን ወደ ትህትና እንዘልቃለን፦ ኻሊፍ ኦማር አንድ ቀን ሊወድቅ ካዘመመ የድንጋይ አጥር ሽሽቶ ሲሮጥ የተመለከቱት ወዳጆቹ፦ «ኻሊፍ! ከፍጻሜህ እየሸሸህ መሆኑ ነው?» በማለት ቢያላግጡበት ኻሊፍም መልሶ፦ «የለም! ከአንዱ ፍፃሜ ወደ ሌላ ፍፃሜ እየሮጥኩ ነው» አላቸው ይላሉ።

በመልካም ምግባር ሥር ከእምነት ቀጥሎ ሱፊዎች የሚያስቀምጡልን ትህትና (Humility) ነው። ትህትና የማንነት እውነታዊ መገለጫ ነው ይሉናል። ትህትና በልምምድ ሳይሆን በማሰብ እንደሚገኝ ሱፊዎች የሚያሳዩን የአሜሪካ ፕሬዚዳንት የነበረው ቤንጃሚን ፍራንክሊንን ተሞክሮን በመጥቀስ ነው። ፍራንክሊን በሳምንት አንድ ቀን ነገሩን ሁሉ በፍፁም ትህትና የሚያከናውንበት ቀን አድርጎት ነበር። በዚህ ልምምዱ እየገፋበት ሲሄድ ማምንቱን በሙሉ ትሁት መሆን ጀመረ። ነገር ግን ትህትናው ደግሞ በልምምድ ያገኘው ነበርና ቀስ በቀስ በራሱ እየኮራ እንዲሄድ አደረገው። በዚህ ኩራቱ ውስጥ ደግሞ ከሌሎች የተሻለ ትሁት አድርጐ ራሱን እንዲያስብ አደረገው። ዞሮ ዞሮ ይኸን ማሰቡ ደግሞ በውስጡ ትምክህትን ፈጠረ ይሉናል። ሱፊዎች ሲመክሩ «አንተ ከዚህ ዓለም ቀርቶ ከምትኖርበት አንባቢ ሕዝብ ጋር እንኳን ስትነፃፀር እጅግ ኢምንት ነህ። ስለአንተ ግድ የሚላቸው እጅግ ጥቂት ሰዎች መሆናቸውንም ተረዳ። ከእነሱም ውስጥ አብዛኞዎቹ በሚገባ አያውቁህም።» ለዚህ በቂ ግንዛቤ የምትሰጠንን የሱፊዎች ታሪክ ቀጥሎ እንቅመስ፦

አንድ የቢንቢ ኩሩ አባወራ ቤተሰቦቹን ይዞ በዝሆን ጆሮ ላይ ለጥቂት ጊዜ ኑሮውን ከመራ በኋላ በመጨረሻ መኖሪያውን ለመቀየር መወሰኑን ለዝሆኑ ሊነግረው በመፈለግ መጮኽ ይጀምራል። ነገር ግን አስቀድሞም የቢንቢውን መኖር የማያውቀው ዝሆን ለቢንቢው ጥያቄ መልስም ሳይሰጠው ዝም ይላል። ዝሆኑ ለቢንቢው መልስ ያልሰጠው የቢንቢውን ጩኸት ሳይሰማ ቀርቶ አልነበረም። ነገር ግን፦ «አስቀድሞም በላዬ መኖርህን አላውቅም ነበር» ቢለው የዚህን ቢንቢ ስሜት

መጉዳት አድርጎ ስለወሰደው ነበር፡፡ የሰውም ልጅ እንደዚያ ቢንቢ ነው፤ በታላቅ ውቅያኖስ ላይ የወደቀ ጠብታ፡፡

እዚህም ላይ ሼኽ ሙዛፊር ስለትህትና በሚነግሩን ታሪክ እንጀምራለን:- አንድ ቀን የሱፊው መምህር ቢያዚድ ቢስታሚን አንድ ሰው በዱላ ይመታቸውና ዱላው ይሰበራል፡፡ መምህሩ ግን ሌላ አዲስ ዱላ ያነሱና ማር ከሞላ ስልቻ ጋር ለሚመታቸው ሰው ይሰጡታል፡፡ መምህሩ ይኸን ሲያደርጉ ለሰውዬው እንዲህ በማለት ነበር፡ «በዱላ ጭንቅላቴን በመምታትህ ዱላው ተሰበረ፤ ስለዚህም በተሰበረብህ ዱላ ምትክ አዲስ ዱላ እነሆ፤ ለወደፊቱም ስትማታ ኃይል ይሰጥህ ዘንድ ደግሞ ማሩን አቀረብኩልህ» አሉት፡፡

የባባ ታሂርን ምክር እዚህ ላይ እናምጣት:- «ማንም በስጦታው ተደስቶ ነገር ግን ስጦታውን የሰጠውን ሰው የማይመለከትን እሱ ለስጦታ እንጂ ለሰጪው ግድ የሌለው ነው» ይሉናል፡፡

የሳሪን ገጠመኝ እናስከትል:- አንድ ቀን ባግዳድ የሚገኘው ታላቁ ባዛር በእሳት አደጋ መውደሙን አንድ ሰው ይነግራቸዋል፡፡ ሰውዬው አክሎም የእሳቸው ሱቅ ግን ከአደጋው መትረፉን ቢነግራቸው «እግዚአብሔር ይመስገን!» በማለት በደስታ ይጮኻሉ፡፡ ዛሬ ሱፊው ሳሪ ሲናገሩ «ከ30 ዓመታት በኋላ እግዚአብሔርን ያመሰገንኩበትን ጉዳይ እያሰብኩ ምን ያህል ራስ ወዳድ መሆኔ እየታሰበኝ ንስሀ እየገባሁ እገኛለሁ» ይላሉ፡፡

ወደ ሼኽ ሙዛፊር እንመለስ:- ሁለት ባልንጀሮች በመንገድ ሲሄዱ አንዱ «እግዚአብሔር በእኔ ባህርይና ድርጊት ሊደሰት ይገባል» ይላል፡፡ ሌላው ተቀብሎ «አንተ በእግዚአብሔር ላይ መደሰት አቅቶህ ስታንጉራጉር እየሰማህ እንዴት ሊደሰትብህ ይችላል?» በማለት ሲጠይቀው ባንልንጀራውም መልሱ:- «እሱማ ይቅር ማለት ይችላል እኮ!» አለው፡፡

ለዛሬ በሼኽ ሙዛፊር እንሰናበት:-

«አንድ ሰው እጅግ የተዋበና በዋጋው ውድ የሆነ ባርኔጣ ቢሰጥህ በስጦታው ደስ አይልህምን? ነገር ግን ከባርኔጣው ይልቅ እሱን የምታስቀምጥበትን ጭንቅላት በሰጠህ ደስ ይበልህ!» ◻

# «ልብ የሚያበቅለው በሕይወት ላይ ያብባል»

የሱፊዝም ዋነኛ አትኩሮት መንፈሣዊ የሚሉትን መንገድ በጥበብ መከተልና ከዚያ መንገድ የሚያወጣንን ነገርም ጠንቅቀን እንድናውቅ ማድረግ ነው። በውስጣችን ተቀብሮ የሚገኘና በአረብኛው «ነፍስ» የሚሉት ነገር አለ። (በእኛም ነፍስ የምንለው መሆኑ ነው።) ይኸ ቃል በሱፊዝም ጥበበኞች ሲተነተን «እኔነት» ይባላል። ለነፍስ ሌሎች ትንታኔዎች በየፈርጁ ቢሰጡትም የእኛ አትኩሮት እንግዲህ በእኔነት ላይ በመሆኑ ለጊዜው እነሱን እንዘነጋቸዋለን።

እንግዲህ በሱፊዝም ነፍስ ወይም እኔነት «ክፉውን ለመሥራት የሚያነሳሳ» ነው ይሉታል። ይኸ ደግሞ ራስ ወዳድነት፣ ስግብግብነት፣ ማቆሚያ የሌለው መሻትና ፍላጐት እንዲሁም ትዕቢትን ይጨምራል። ምናልባት አሁን ለምናነሳው ሐሣብ ተስማሚ የሚሆነው «ዝቅ ያለው ማንነት» የሚለው ይሆናል።

ዝቅ ያለው ማንነት በነፍስና ሥጋ ጥምረት ምክንያት የሚፈጠር ነገር አይደለም። ነፍስና ሥጋ ንፁህና በራሳቸው ነቀፋ የማይገኝባቸው ናቸው። ይሁንና ነፍስ በሥጋ በታቀፈ ጊዜ የነፍስን ተፈጥሮ ዘንግተን ከዓለም ጋር እንዘልቃለን፤ በዚህም ሂደት ስግብግብነት፣ ሥጋዊ ፍላጐትና ኩራት መገለጫችን ይሆናል።

በመንፈሣዊ ጐዳና ላይ ስንዘልቅ ግን ለእኛ የተሻለ የምንለውን ነገር በግልፅ ማወቅ እንጀምራለን። ስህተትና ጐጂ ናቸው ከምንላቸው ድርጊቶችም ለመራቅ ከራሳችን ጋር ትግል እንገጥማለን። ለምን መታገል አስፈለገን? ለዚህ መልሱ «አእምሮአችን አንድ ነገር ብቻ

ማሰብና ማድረግ ቢችል ኖሮ ይኸ ሁሉ ትግል ባላስፈለገ ነበር» የሚለው ይሆናል፡፡ አእምሮአችን የተበታተነ ሆኗል፡፡ ትክክል የሆነውን ነገር አእምሮአችን ተቀብሎት ቢያምነውም ዝቅ ያለው ማንነታችን ተቃራኒውን እናደርግ ዘንድ ይገፋፋናል፡፡ ትክክለኛው ነገር በግልፅ ቢታየን እንኳን ዝቅ ያለው ማንነታችን እንረግጠው ዘንድ ይጋርደናል፡፡

«ነፍሳችን እንደሚገባት ትሆን ዘንድ ዝቅ ያለው ማንነታችን እንዴት እንደሚሰራና እንደሚያስብ ከተረዳን ስለማንነታችን ከማወቅም ባሻገር ለምንነታችንም ክብር እንድንሰጠው ያደርጋል» የሚሉት ሱፊዎች ዝቅ ስላለው ማንነታችን ሊያካፍሉን ተነስተዋል፡፡

መነሻችን ሱፊ ሁጅዊሪ በሚነግሩን ቁም ነገር ይሆናል፡፡ ሁጅዊሪ «ዝቅ ያለው ማንነቴን እንደ አይጥ ሆኖ አየሁት» ይላሉ፡፡ «ማንነትህን ንገረኝ?» ብዬም አጥብቄ ያዝኩት፡፡ እሱም እንዲህ ሲል መለሰልኝ፡- «በመንገዳቸው ላይ ለሚያተኩሩት ጥፋት ነኝ፤ ክፋትን ይፈፅሙ ዘንድ አነሳሳቸዋለሁና፡፡ የእግዚአብሔር ወዳጅ ለሆኑት ደግሞ መዳኛቸው ነኝ፤ እኔ ባልኖር ኖሮ በንፅህናቸው ይኩራ፤ በድርጊታቸውም ይታበዩ ነበር፡፡ ነገር ግን እኔን በውስጣቸው ሲመለከቱኝ ኩራታቸው ሁሉ ለቅቋቸው ይሄዳል፡፡»

በካሻኒ ምሳሌያዊ አባባል ወደሌላው ታሪክ እናልፋለን፡፡ «በአብዛኛው ውጫዊ ማንነታችን ከውስጣዊውና ዝቅ ካለው ማንነታችን ይለያል፡፡ ሰዎች ባሉበት ቦታ ገፅታውን ቅንነት አላብሶ በምስጋና እያሞቀ ልባቸውን ይሞላና እነሱ በሌሉበት ግን በተቃራኒው ሲያዋርዳቸው ይታያል፡፡ ዝቅ ያለ ማንነት ልዩ ባህርይውም ይኸው ነው፡፡»

ወደ ሱፊው መምህር ሹህ ሙዛፊር ታሪክ ስንሻገር የሱፊውን መነኩሴ ገጠመኝ ያጫውቱናል፡፡

ሱፊው መነኩሴ አንድ ማለዳ ከደጅ ቆሞ እየሀለየ ባለበት ሰዓት አንድ ባለፀጋ በደጁ ሲያልፍ ይመለከተውና በመነኩሴው ቅንነትና በተለይም ለአምላኩ ባለው መሰጠት ተማርኮ አንድ ከረጢት ወርቅ ሊሰጠው ይወስንና ይጠጋዋል፡፡

መነኩሴውም «ጌታው! ይኸን ያህል ወርቅ መቀበሌን መጀመሪያ ትክክል መሆኑን ማረጋገጥ አለብኝ፡፡ እውነት ባለፀጋ ሰው ነህን? ከዚህ

በላይ ወርቅስ በቤትህ አለን?» ይለዋል።

«አ! ቢያንስ በቤቱ አንድ ሺህ ወርቅ መኖሩን ላረጋግጥልህ እወዳለሁ» በማለት ባለፀጋው መለሰ።

«አንድ ሺህ ተጨማሪ ወርቅስ ብታገኝ ትወዳለህን?» በማለት መነኩሴው መልሶ ጠየቀው።

«እሱማ እፈልጋለሁ! በየዕለቱ የምጥረውም ጥሪቴን ይበልጥ ለማብዛት እኮ ነው!» አለ።

«የምትመኘውን አንድ ሺህ ወርቅ ብታገኝም ሌላ አንድ ሺህ ወርቅ እንዲኖርህ ደግሞ መመኘትህን አታቆምም?» በማለት መነኩሴው እንደገና ጠየቀው።

«ትክክል ነው! በየቀኑ ጥሪቴ እንዲበዛ ከመጸለዬ በላይ እፀልያለሁ» አለው።

ይኸን ጊዜ መነኩሴው የወርቁን ከረጢት ወደባለፀጋው እየገፋው፦ «ወንድሜ! ራስህን እንደባለፀጋ እኔን ደግሞ እንደደሀ ቆጠረህ ይኸን ወርቅ ልትመፀውተኝ መነሳትህ አስገራሚ ነው። እኔ እግዚአብሔር የሰጠኝን በቂዬ ነው ብዬ የምኖር ባለፀጋ ነኝ። አንተ ግን የቱንም ያህል ሀብት ብትሰበስብ በቃኝን የማታውቅ፤ እርካታ የራቀህ ነህና ለአምላክህ የምታቀርበው ፀሎት ሁሉ 'ስጠኝ!' ብቻ ሆኖ ቀርቷል» በማለት አሰናበተው። ዝቅ ያለው ማንነት እንግዲህ በዚህ ባለፀጋ ነፍስ ውስጥ በሚገባ ተገልጦ አየነው በማለት ሼህ ሙዛፈር ወጋቸውን ይቋጫሉ።

«ዝቅ ያለው ማንነት እንደእሳት ነበልባል ነው» የሚሉን ደግሞ ባካራዚ ናቸው። «የእሳት ነበልባል ለዓይን ሲታይ ውበት ቢኖረውም የማጥፋት ብቃቱን በውስጡ ደብቋል፤ ቀለማቱ የቱንም ያህል ቢያምሩም ማቃጠሉን ግን አትዘንጋ» በማለት ዝቅ ያለውን ማንነት ተጠንቀቁት ይሉናል።

ሱፊው ሰማኒም ዝቅ ያለውን ማንነት በሌላ ምሣሌ ያሳዩናል፦

«የተዋበ ቤተመንግሥት ተገንብቶ አጠገቡ ቆሻሻ መጣያ ካልተሰራለት ጉደሉነቱን ማንም አይቶ ሊመሰክር ይቻላል። በአጠገቡ የቆሻሻ መጣያ ያልተሰራለት ቤተመንግሥት አሠራሩ የቱንም ያህል የተዋበ

ቢሆን የቆሸሸ መጣያ መስሎ መታየቱ ግን አይቀሬ ነው:: እንዲሁ ደግሞ እግዚአብሔር በንፅህና ብርሃን ተጠቅሞ የሰውን ልጅ ልብ ሲሰራ ንፅህና የጐደላትን ነፍስም (ዝቅ ያለውን ማንነት) ከአጠገቡ እንደቆሻሻ መጣያ ሰርቶለታል:: ይሁንና ባለማወቅ ጠባሳ ምክንያት ዝቅ ያለው ማንነት ብዙ ጊዜ ከንፁሁ ልብ ጋር አብሮ ከንፍ አውጥቶ ለመብረር ሲሞክር ይስተዋላል:: በጥቂቱ ልብ ሲያድግ፡ ንፅህና ቤቱን የሚገነባበት መሠረት ይሆነዋል:: ቀስቱ ቀጥ ያለ ቢሆንም ደጋኑ (ማስፈንጠሪያው) ጠማማ መሆኑን ልብ ይሏል:: ልብ ሆይ! እንደቀስት ቀጥ ያልህ ትሆን ዘንድ ይገባል:: ነፍስ ሆይ! አንቺ ደግሞ እንደማስፈንጠሪያው ጠማማ ትርዕ ያገር::

«እርግብ ክንፎቿን ስትዘረጋ በእያንዳንዷ የክንፏ ክፍል ደስተኛ ነች፤ ነገር ግን ወደእግሮቿ ደግሞ ስትመለከት ማፈሯ አይቀርም:: በእናንተ ውስጥ የሚገኘው የሀፍረት ጥቁር ነጥብ እንደርግቧ እግሮች አብሯችሁ መኖሩን ይቀጥላል::»

የሱፊውን አንድ ባህላዊ ምሣሌ እንሰንዝርና ወደሌላውና ዝቅ ያለ ማንነታችንን ወደምናይበት ታሪክ እንሻገር:- «ዝቅ ያለው ማንነትህን ጥላ በአንተ ላይ እንዳያርፍ ማድረግ ከቻልክ ሌሎች በአንተ ጥላ ሥር ለመኖር ደስተኞች ይሆናሉ::»

ቀጥሎ የምናየው ታሪክ ደግሞ የሱፊው መምህር የሩሚ ወግ ነው::

«የደራጐን አዳኝ ነኝ የሚል አንድ ሰው ከዕለታት አንድ ቀን ደራጐን ለማጥመድ ወደተራራ ጫፍ ላይ ይወጣል:: በተራራው ጫፍ ደርሶ ለሰዓታት ሲያስስ ከቆየ በኋላ ከአንድ ዋሻ ውስጥ የሞተ ደራጐን ያገኛል፡ አዳኙም የሞተውን ደራጐን በወጥመዱ ውስጥ ከከተተ በኋላ እየጐተተ ወደባግዳድ ከተማ ይዞት ይወጣል:: ብዙችም ባግዳድ ከተ ማ ወንዝ አጠገብ ተሰብስበው አዳኙ የፈፀመውን አስገራሚ ትዕይንት ማየት ጀመሩ:: አዳኙም ደራጐኑን ከተራራ ጫፍ ላይ አግኝቶ በሳንጃው ወግቶ ከገደለው በኋላ በወጥመዱ አስሮ ይዞት እንዳመጣው ለሕዝቡ መናገር ጀመረ:: ይሁንና ከጥቂት ሰዓታት በኋላ የደራጐኑን ገላ የባግዳድ ፀሐይ ሲያሞቀው በተራራው ቅዝቃዜ የተኮማተረው ደራጐን መፍታታትና ከክረምት እንቅልፉ መንቃት ጀመረ:: ይኸን

ትዕይንት ተሰብስቦ ይከታተል የነበረው ሕዝብ የደራጉኑን መንቃት ሲመለከት መሸሽ ጀመረ። በሽሽቱም አንዱ ሌላውን እየጨፈለቀ ብዙዎች ሞቱ። የደራጉኑ «አዳኝም» በድንጋጤ ቆሞ ሲንቀጠቀጥ በአንድ ጉርሻ ሰለቀጠው።

«እንግዲህ ዝቅ ያለው ማንነታችሁ እንደዚያ ደራጉን ጨካኝ አውሬ ነው። ቀዝቅዟል እንጂ አልሞተም። የሕይወታችሁን ደራጉን ራስን በመግራት በረዶ አቀዝቅዙት። ወደባግዳድ ፀሐይ አውጥታችሁም አታሙቁት። ደራጉናችሁ እንደቀዘቀዘ ይቀመጥ፤ አሻፈረኝ ብላችሁ ብትለቁት ግን ውጦ ያስቀራችኋል።»

ከዚህች ጣፋጭ የሩሚ ወግ ወደሌላ ታሪክ የምናልፈው በአንድ ባህላዊ ምሳሌ ይሆናል፡- «ዝቅ ሳለሙ ማንነታቸው የሞቱ እነሱ ለእግዚአብሔር ሕያው ናቸው።»

ከውጭ ሃገር የመጣ ሼክ አንዱን የሱፊ መምህር ሊጎበኟቸው ወደቤታቸው ይመጣና ስለእውነተኛው ሱፊዝም በሃገሩ የተማረውን እንዲነግራቸው ይጠይቁታል። ሼኩም «እግዚአብሔር አንዳች በረከት ሲልክልን በልተን እናመሰግነዋለን፤ ካላከልን ደግሞ እስኪሰጠን ድረስ በትዕግስት እንጠብቀዋለን» አለ። የሱፊው መምህር ይኸን ሲሰሙ፡- «ይኸማ በቤታችን የምናሳድገው ውሻም የሚያደርገው እንዲሁ ነው -- አጥንት ሲሰጠው በልቶ ይተኛል፤ ካልተሰጠው ደግሞ እስኪሰጠው ይጠብቃል» ይሉታል።

ይኸን ጊዜ ሼኩ፡- «እንግዲያውስ በእናንተ ዘንድ ያለውን ሱፊዝም ይንገሩኝ» ይላቸዋል። ሼኹም፡- «አንድ ነገር ስናገኝ ለሌሎች እንሰጣለን ወይም እናካፍላለን፤ ምንም ከሌለን ደግሞ ለሌሎች በረከት ይወርድ ዘንድ በምህረትና በይቅርታ እንዲጎበኟቸው እንፀልያለን» አሉት።

በሱፊዝም ዝቅ ያለው ማንነት መገለጫውም ይኸው ነው። ለዚህም ነው «ልብህ የሚያበቅለው በሕይወትህ ላይ ያብባል» የሚሉት። □

# «በራስ ላይ ለመቀለድ ጠቢብ መሆን ያሻል»

በዚህ ምዕራፍ የሱፊዝም ቀልዶችን የምናይ ሲሆን በእነሱ ቀልድ ውስጥ የምናልፍባቸውን መንታ መንገዶችም አብረን እንመለከታለን። እነዚህ መንታ መንገዶች የሕይወትን ሁለት ገፅታ የሚያሳዩን ሲሆን የመጀመሪያው የተለመደውና በየትኛውም ማኅበረሰብ ተቀባይነት ያለውን የአኗኗር ዘይቤ እያስቃኙ አብሮ ፈገግ የሚያስኙውን ነው፤ ሁለተኛው ደግሞ ከተለመደው ወጣ ያለውን የሕይወት መልክ በፈገግታ ሊያሳየን የሚሞክር ይሆናል።

ሱፊዎች ይኸ በቀልድ እያዋዙ ቁምነገርን የማቅረብ መንገድ ከየትኛውም የማስተማሪያና ዕውቀትን የማስተላለፊያ ዘዴ በእጅጉ የተሻለ እንደሆነ ይናገራሉ። ይኸው ዘዴም የሱፊዎች ባህል ሆኖ ለዘመናት ዘልቋል። ቀልዶች በተለይ የሰውን ልጅ ድክምና ስህተ ት በማሳየትና በማስተማር ረገድ ከፍተኛ መሣሪያ ሆነው ማገልገል እንደሚችሉ ሱፊዎች ይናገራሉ። የሱፊ ደቀመዛሙርት ሲናገሩ፦ «የሱፊዝም መምህራኖቻችን በቀልድ አዳብለው የሚነግሩን ቁምነገር ከጥፋታችን እንድንታረም፤ እውነተኛ ፍቅርና ወዳጅነታችን እየከሰመ መሆኑን እንድናይ፤ መምህር መንገዱን አሳይቶ የሚመለስ እንጂ ከእኛ ሳይለይ እጃችንን ይዞ ሲመራ የማይኖር መሆኑን እንድናውቅ፤ የወግና የባህላችን አንዳንድ አስተምህሮቶች እኛን ካለማወቅ የሚያነቁን ሳይሆኑ አትኩሮታችንን እና ትምህርታችንን ሰልበው በተሳሳተ መንገድ የሚወስዱ መሆኑን እንድናውቅ የሚያነቁን ኃያል መሣሪ ያዎች ናቸው» ይላሉ።

በአብዛኛዎቹ ሃይማኖታዊ ትምህርቶች ውስጥ አንድ ከስምምነት ላይ የተደረሰበት ጉዳይ ያለ የሚመስለው የሰው ልጅ ልብ መከፈት

የሚችለው በፀሎት፣ በስቃይ፣ በጥበብና በፍቅር ብቻ ነው። ይሁንና እነዚህ የተለመዱ መንገዶች ከዘህልና ወግ ጋር እየተገናኙ ሲጓዙም ይስተዋላል። በመሆኑም ቀልዶች የመንፈሳዊ ዕውቀት መሣሪያዎች መሆናቸው አሁንም እምብዛም ግንዛቤ አላገኘም። የሱፊ ምሁራን ግን ትምህርታቸውን በቀልድ የሚሞሉበትን ጥበብ ለዓመታት ይዘው በመዝለቃቸው ከፍተኛ ወጤት እንዳገኙበት ያምናሉ። የሱፊዎች ባህል እጅግ የበዛ ቀልድ (ቀልዶቹ በአብዛኛው በራሳቸው ሕይወት ዙሪያ የሚነገሩ ናቸው) የመፍጠር ብቃት እንዳለውም ለማስመስከር ችለዋል። ለብዙዎቻችን በራሳችን ጥፋት ላይ መቀለድና መሳቅ ስንችል ጥፋቱን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከውስጣችን አውጥቶ መጣያ የተሻለው መንገድ መሆኑንም ሱፊዎች ይመክራሉ። የሱፊው ወዳጃችን ሩሚ እንደሚነግሩን፡- «በራስ ላይ ለመቀለድ ጠቢብ መሆን ያሻል።»

በቀልድ እያዋዙ መማርን ሱፊዎች የሚመርጡት በትምህርት ውስጥ ያለውን ዕውቀት በቀላሉ ለማስተላለፍ ብቻ ሳይሆን ተማሪዎቹ የሚነገራቸውን ቁምነገር በቀላሉ እንዳይዘነጉትና ጥርጣሬ የሚፈጥርባቸውንም ጉዳይ ከውስጣቸው ለመፋቅ ነው። እንግዲህ ቀጥሎ የተቀመጡትን ቀልድ አዘል ወጐች አንባቢያንን ስጋብዝ ለመማርና ራስን ለመለወጥ የሚሻ ሁሉ ሊለወጥባቸው እንደሚችል ያለጥርጥር በማመን ነው። ነገር ግን እነዚህን ቀልዶች ተራ የቱርክ ባህላዊ ቀልዶች አድርጎ የሚመለከታቸው ደግሞ ከሳቅ ያለፈ አንዳች ነገር እንደማያገኝባቸው እርግጠኛ መሆን ይቻላል። እዚህ ላይ ለአንባቢቼ ልጨምሬ የማስተላልፈው መልዕክት በእያንዳንዱ ቀልድ ውስጥ የእናንተ የሕይወት እውነተኛ ሥፍራ የት ጋ እንደሚገኝ እንድትመረምሩት ነው። (የሱፊዎች የቀልድ ማዋዣ ሆጃ /ናስሩዲን/ ነው። እንደእኛው አለቃ ገብረሃና መሆኑ ነው።)

* * *

ሆጃ ከወዳጁ ጋር በአንድ መዝናኛ ሥፍራ ተቀምጦ ሻይ እየጠጣ ሲያወጋ አንድ የተማረ መነኩሴ ሁለቱ ወደተቀመጡበት ተጠጋና፡- «በዚህ ምድር ላይ ለሁሉ ነገር መልስ አለው!» አላቸው።

በዚህ ድንገተኛ ሰውና በንግግሩ ሳቁ የመጣበት ሆጃ «ነገር ግን እኔ

አንድ ባለጠጋና የተማረ ሰው ጥያቄ ጠይቶኝ ምላሽ አጥሮኝ ነበር» አለው::

መንከሲጡም በጉራና ትምክህት ተሞልቶ:- «እ! እኔ በዚያ ቦታ ብሆን ኖሮ ምላሹን እሰጠው ነበር! እባክህ ጥያቄው ምን እንደነበር እስቲ ንገረኝ?» አለ::

«በጣም ጥሩ» አለ ሆጃ:- «ጥያቄው ይኸ ነበር:- ትናንት ማታ በመስኮት ሾልከህ ቤቴ ውስጥ ገብተህ የነበረው ለምንድነው?»

* * *

አንድ ቀን ሆጃ ወደባለፀጋ ጓደኛው ይሄድና:- «እባክህ ጥቂት ገንዘብ አበድረኝ» ይለዋል::

ጓደኛውም:- «ለምን ገንዘብ ፈለግህ?» ይለዋል::

«ዝሆን ለመግዛት ፈልጌ» ይላል ሆጃ::

«ገንዘብ ከሌለህ ዝሆን ብትገዛ እንኳን ከየት አምጥተህ ትመግበዋለህ?» በማለት ጓደኛው ጠየቀው::

ይኸን ጊዜ ሆጃ:- «ወንድሜ! ገንዘብ እንጂ ምክር ልጠይቅህ አልመጣሁም» ብሎ ጥሎት ሄደ::

* * *

አንድ ዓርብ ሆጃ በአንድ መስጊድ መድረክ ላይ ለመስበክ ቆመ::

«እናንተ ምዕመናን! ዛሬ ስለምን እንደምናገር ታውቃላችሁ?» አለ ሆጃ::

«እንዴት ማወቅ እንችላለን?» በማለት ምዕመኑ ጥያቄውን በጥያቄ መለሱለት::

«ስለምን እንደምናገር ካላወቃችሁማ የእኔ መስበክ ምን ጥቅም አለው?» በማለት ከመድረኩ ላይ ወርዶ ወደ ቤቱ አመራ::

በቀጣዩ ዓርብም ሆጃ ወደመስጊዱ አመራና በመድረክ ላይ ቆሞ:- «እናንተ እውነተኛ ምዕመናን! ዛሬ ስለምን እንደምናገር ታውቃላችሁ?» አለ::

ይኸን ጊዜ ምዕመኑ በአንድ ድምፅ:- «አዎ! እናውቃለን!» አሉት::

«የምናገረውን ካወቃችሁማ የእኔ መናገር ከንቱ ድካም ነዋ!» በማለት ከመድረኩ ወርዶ ሄደ::

እንደገና በቀጣዩ ዓርብ ሆጃ ወደመስጊድ ያመራና በመድረኩ ላይ ቆሞ፡- «እናንት ምእመናን! ዛሬስ ስለምን እንደምናገር ታውቃላችሁ?» አለ፡፡

በዚህ ጊዜ ተዘጋጅቶ የነበረው ምእመን፡- «አንዳንዶቻችን እናውቃለን፤ አንዳንዶቻችን ደግሞ አናውቅም» አለ፡፡

«እንዲህ ከሆነማ» አለ ሆጃ «የምታውቁት ለማያውቁት ንገሯቸው!» በማለት ወደ ቤቱ አመራ፡፡

* * *

አንድ ቀን የሆጃ ጓደኛ ችግር ይገጥመውና በሳምንት ውስጥ እንደሚመልስለት ገልፆ ገንዘብ እንዲያበድረው ይጠይቀዋል፡፡ ምንም እንኳን ሆጃ ገንዘቡ እንደሚመለስለት እምነቱ ባይኖረውም ያበድርና ይሸኘዋል፡፡ ጓደኛው ግን ቃሉን በማክበር የተበደረውን በጊዜው ይመልስለትና ሆጃን ያስደንቀዋል፡፡ ይሁንና ከጥቂት ወራት በኋላ እንደገና የሆጃ ጓደኛ ሌላ ብድር ይፈልግና ተመልሶ በመምጣት ይጠይቀዋል፡፡

«ባለፈው ቃሌን አክብሬ ብድሬን እንደመለስኩ ታውቃለህ፡፡ አሁንም ተቸግሬአለሁና ሌላ ብድር አባክህ ስጠኝ» ይለዋል፡፡

ሆጃም፡- «ከእንግዲህማ ገንዘብ ለአንተ በድጋሚ አበድሬ መታለል አልሻም... ባለፈው ጊዜ ሳበድርህ ገንዘቡን እንደማትመልስልኝ እምነቴ ነበረኝ፤ ነገር ግን መለስክልኝ፡፡ አሁን ደግሞ እንደምትመልስልኝ አምኛለሁና መታለል አልፈልግም» አለው፡፡

* * *

ሆጃ የንጉሥ ወዳጅ ለመሆንም በቅቶ ነበር፡፡ በጥበብ የተሞላው አንደበቱና ቀልደኛነቱ ከንጉሡ ሞገስን አስቸረውና አብሮ ማዕድ ለመቋደስም በቃ፡፡ ንጉሡ በየዕለቱ ከማዕዱ ላይ ሆጃና የአትክልት ምግብ እንዳይጠፋ አዘዘ፡፡

«ይኸ የአትክልት ምግብ መልካም አይደለምን ሆጃ?» ንጉሡ አንድ ቀን ጠየቀ፡፡

«እጅግ ሸጋ ነው» ሆጃ መለሰ፡፡

ለአስራ አምስት ቀናት በተከታታይ የአትክልት ምግብ ብቻ ሲመገቡ ከሰነበቱ በኋላ ንጉሡ አገልጋዮቹን ጠርቶ፡- «ይኸ የአትክልት ምግብ

እጅግ ሰልችቶኛል! አስጠልቶኛልና ከእንግዲህ ከፊቴ እንዳይቀርብ» በማለት አዘዘ::

ይኸን የሰማውና መሰልቸቱን በልቡ ይዞ የቆየው ሆጃም:- «ንጉሥ ሆይ! ትክክል ብለዋል:: እንደዚህ ምግብ የሚያስጠላ የለም» አለ::

«ነገር ግን ሆጃ! ከጥቂት ቀናት በፊት ጣፋጭ ነው ስትል አልነበረምን?» አለ ንጉሡ በመገረም::

«እንዴ ንጉሥ ሆይ! እኔ እኮ የእርስ እንጂ የአትክልት ምግብ አገልጋይ አይደለሁም» በማለት መለሰለት::

* * *

በአንድ የበጋ ወቅት ሆጃ ለበቅሎው የሚያወጣው የቀለብ ወጪ ከፍተኛ እየሆነበት መጣና ዘዴ ቀየሰ:: የበቅሎዋን ቀለብ ቀስ በቀስ መቀነስ::

የመጀመሪያ ቀን ለበቅሎዋ የተለመደ ቀለቧን በግማሽ ቀንሶ ሰጣት:: በቅሎዋ ላይ ለውጥ አላየም:: እንዲህ እያለ በየቀኑ የሚሰጣትን በግማሽ እየቀነሰ ብዙም ለውጥ ባለማየቱ ሆጃ ያለፈው ዘመን አባካኝነቱ እየፀፀተውና በአሁኑ አስተዋይ ውሳኔው እየተደሰተ ማምንታት አለፉ::

ይሁንና አንድ ቀን ማለዳ ሆጃ እየቀነሰ እጅግ ጥቂት ያደረሰውን ቀለብ ይዞ ወደ በቅሎዋ ጋጣ ሲገባ ሞታ አገኛት:: በሁኔታው እጅግ እያዘነ ሳለ ወዳጁ በድንገት ይደርስና ሃዘኑን መጋራት ሲጀምር ሆጃ አቋርጦት:- «ወዳጄ! እኔ ያዘንኩት እኮ በቅሎዬ ያለምግብ ለመኖር ጥቂት ጊዜ ሲቀራት በመሞቷ ያሳለፈችው ድካሟ አሳዝኖኝ እንጂ ሌላ አይደለም...» በማለት ጓደኛውን ማፅናናት ያዘ::

* * *

አንድ ቀን ሆጃ በደረጃው ከፍተኛ የሚባል የእራት ግብዣ ላይ ይጠራና ወደዚያው ያመራል:: ይሁንና ወደግብዣው ያመራው በሥራ ልብሱ በመሆኑ ማንም ዞር ብሎ የሚያየው ከማጣቱም ባሻገር የሚቀመጥበት ወንበር እንኳን ማግኘት አልቻለም:: በዚህ ሁኔታ ጥቂት ደቂቃዎች በዚያ አዳራሽ ካሳለፈ በኋላ ማንም ሳያየው ሾልኮ በመውጣት ወደቤቱ ይሄዳል:: ቤቱ እንደደረሰም በፍጥነት የክት ልብሱን ቀይሮ ወደ ግብዣው አዳራሽ ይመለሳል::

በአዳራሹ ሲደርስ የሞቀ አቀባበልና ሰላምታ ይቀርብለታል። አስተናጋጆችም በፍጥነት ቦታ ሰጥተውት የሚጠጣውና የሚበላው ያቀርቡለታል። ሆጃም ምግቡን ከሰሀኑ ላይ አንስቶ ኮቱን መቀባት፣ መጠጡንም ሱሪው ላይ ማፍሰስ ይጀምራል። በዚህ ጊዜ ተጋባዥ ሁሉ ተደናግጦ የሆጃን ድርጊት ሲመለከት ጋባዦቹ ወደእሱ ያመራሉ።

«ሆጃ! ምን ማድረግህ ነው!» በማለት ከጋባዦቹ አንዱ ጮኸ።

«የጠራችሁትና የጋበዛችሁት ልብሴን መሆኑን ስላወቅሁ እሱን እየጋበዝኩላችሁ ነው» በማለት መለሰላቸው። □

pdf by @shuktus_books

# «ሊሳው ሲበላ በማየት የራስ ረሃብ አይታገስም»

«አንድን ነገር በሚገባ እናውቀው ዘንድ ልናፈቅረው ይገባል» የሚሉን ሱፊዎች አሁን ደግሞ በፍቅር ጉዳይ ላይ ይዘውን ይዘልቃሉ። በሱፊዝም አንድን ነገር እንጠበብበት ዘንድ ማፍቀሩ የሚቀድም ነው። ለምሣሌ ሙዚቃ፤ ስዕል፤ ወይም ማንኛውንም ዓይነት የዕውቀት ዘርፍ ሊሆን ይችላል... በዚያ ዕውቀት ታላቅ ደረጃ እንደርስ ዘንድ አስቀድመን እናፍቅረው ይላሉ። ፍቅር ሳይኖር የምናደርገው ጥናትም ሆነ ትምህርት መጨረሻቸው ጥራዝ ነጠቅ እውቀት ብቻ ሆኖ ይቀራልና። «እናም የታላቅ ዕውቀት ምንጩ፣ ፍቅር ነው ይሉናል» ሱፊዎች።

ለብዙዎቹ ሱፊዎች ሱፊዝም የፍቅር መንገድ ነው። ሌሎችን ማፍቀር የዚህን ዓለም ውበትና እንዲሁም አምላክን ማፍቀር ዋነኛ መርሆቻቸው ናቸው። ፍቅራችን ለሁሉ ነገር በጨመረ ቁጥር አምላካዊ ፍቅራችንም እንዲሁ ይጨምራል። አምላክን ባፈቀርን ቁጥር ደግሞ እያወቅነው እንመጣለን።

እንደሱፊዎች እምነት ብዙዎቻችን ፍቅርን እንፈራለን። ምናልባትም ከዚህ በፊት ከጓደኞችን ጋር በነበረን ፍቅር ሀዘንና ብስጭት አጋጥሞን ከሆነ ማፍቀርን እንደገና ለመለማመድ እንፈራው ይሆናል። ሱፊዎች ለዚህ ዓይነቱ ገጠመኝ የቱርኩን ተረት ዘወትር ያወሳሉ፦ «ሾርባ ያቃጠለው እሱ በእርጎ ይፎኻል»። እናም ያለፉት ጊዜያት የቱንም ያህል ጉዳትን በልባችን ለንትረው ይለፉ፤ ወይም ደግሞ የወደፊቱን ስቃይ የቱንም ያህል እንሽሸው ዳግመኛ ማፍቀርን እንማር ዘንድ ግን ይገባል ባይ ናቸው። በዚህ ሂደት ደግሞ የሱፊው መምህር ዋነኛ ተግባሩ ደቀመዝሙሩን ለፍቅር አስተማማኝ ወደሆነ ቦታ ማድረስ

ይሆናል፡፡

«ፍቅርን የምንፈራው በሌሎች በደረሰብን መከዳትና መገፍተር ብቻ አይደለም፤ ነገር ግን መሰወጥንም ስለምንፈራ ነው» የሚሉት ሱፊዎች ፤- «ከማንኛውም ነገር በላይ ፍቅር የሰውን ልጅ የመለወጥ ኃይል አለው» ይላሉ፡፡ ለእውነተኛ አፍቃሪ እኔነት ቦታ የለውም፤ እኔነት በፍቅር ውስጥ ይሟሟል፤ እናም አፍቃሪና ተፈቃሪ አንድ ይሆናሉ፡፡ ነገር ግን በአንዱ ውስጥ መሟሟትና መጥፋትን እኔነታችን ስለሚፈራው ዕለት ዕለት ከፍቅር ስንሸሽ ይስተዋላል፡፡ በዚህ ረገድ የሱፊ አፍቃሪዎች ታሪክ ፍራቻችንን ይቀርፍልን ዘንድ አስበናልና አንዳንዶቹን እንመልከት፡፡

በሱፊው ጃሚ ምክር እንጀምር፡- «ከራስህ ለመላቀቅ ብዙ ሺህ ነገሮችን ሞክረህ ይሆናል፤ ነገር ግን ብቸኛው ከራስ የመላቀቂያው መንገድ ማፍቀር ነው፡፡ ስለዚህም ከፍቅር አትሽሽ፤ ሰውን ማፍቀር ለመለኮታዊውና ዘላለማዊው ፍቅር መለማመጃ መሆኑንም አትርሳ፡፡ ቅዱስ መጽሐፍን አንብቦ ለመረዳት በቅድሚያ ፊደልን ማጥናትስ ተገቢ አይደለምን?» ይላሉ፡፡

ሌላውና የሱፊው መምህር ሼኽ ሙዛፊር ደግሞ ስለፍቅር እንዲህ ይሉናል፡- «ማፍቀር ማለት በምናፈቅረው ሰው ወይም ነገር ውስጥ ውበትን ብቻ ማየትና የአምላክን ስጦታና ደግነት እንዲሁም ርኅራኄ እየተመለከቱ ማድነቅ ነው፡፡ አምላክ ሁሉን ነገር አትረፍርፎ በማቅረቡም ማመስገን ነው፡፡ ወደአምላክ ፍቅር ስንገሰግስ የመጀመሪያው ደረጃ ይኸ ነው፡፡ ለአምላክ ምስጋና ማቅረብ በፍቅር ጉዳና የሚዘራ የመጀመሪያው ዘር ነው፡፡ እያደርም ዘሩ ያድግና ዛፍ ይሆናል፤ ዛፉም ፍሬን ያፈራል፡፡ ከዚያ በኋላ ከዛፉ ፍሬ የቀመሰ ሁሉ የእውነተኛ ፍቅርን ጣዕም የሚያውቅ ይሆናል፡፡ ችግሩ ግን ይኸን ፍሬ የቀመሰው ላልቀመሰው ሰው የሚናገርበት ቋንቋ አለመኖሩ ነው» ብለዋል፡፡

ከሼኽ ሙዛፊር አንድ እንጨምር፡- «ፍቅር ያናግረናል፤ ፍቅር ያስለቅሰናል፤ ፍቅር አስከሮ አውሬ ያደርገናል፤ አንዳንዴም ያነግሰናል፡፡ ፍቅርም ሆነ አፍቃሪ ቋሚ መመሪያ የሚሉት ነገር የላቸውም፡፡ አፍቃሪ በየትኛውም አቅጣጫ የሚወስደው ቢሆን እንኳን ከአፍቃሪው ጋር

ከተገናኘ ይነጉዳል:: አፍቃሪ በሚገኝበት ቦታ ሁሉ ተፈቃሪ ይገኛል:: አንዳች ነገር መስራትም ሆነ ለቅፅበት ከአፍቃሪ መለየት አያሆንለትም:: በእያንዳንዷ ደቂቃም ያፈቀረውን ሰው ያስባል:: አፍቃሪና ተፈቃሪ ሁልጊዜና ለዘላለም አንዱ በአንዱ ውስጥ ናቸው::»

ከሼኽ ሙዛፈር ወግ አሁንም አንድ እንመርቅ:- «ሼኽ ኡፋዶ ከአንድ ሰሞን ሕመማቸው አገግመው ከአልጋ ይነሣሉ:: ወቅቱ ክረምት ነበርና ሁሉ ነገር ቀዝቃዛ ስለሚሆን የኡፋዶ ደቀመዝሙር በማለዳ እየተነሣ ውሃ ያሞቅላቸው ነበር:: አንድ ቀን ግን ደቀመዝሙሩ እንቅልፍ ጥሎት ሼኽ ኡፋዶ ቀድመውት ይነሱና ሲንጉዳጉዱ ይሰማል:: ይኸን ጊዜ ደንግጦ በመነሣት ማንቆርቆሪያውን ውሃ ሞልቶ በልብሱ ውስጥ ከልቡ አስጠግቶ ይይዘዋል:: ሼኽ ኡፋዶም የሶላት ውሃ ፈልገው ደቀመዝሙራቸውን ቢጠይቁት በቅፅበት የሞቀውን ውሃ ከማንቆርቆሪያው ውስጥ ይቀዳላቸው ገባ:: በዚያ ፍጥነት ውሃ የማሞቂ ነገር የደነቃቸው ሼኽ ኡፋዶም ውሃውን እንዴት እንዳሞቀው ቢጠይቁት ደቀመዝሙሩ «መምህር ሆይ! በልቤ እሳት ላይ ጣድኩልዎ» አላቸው::»

ወደራቢያ እንሻገር:: አንድ ቀን ራቢያ እንዲህ ተጠየቀች:-

«ራቢያ ሆይ! አምላክሽን ታፈቅሪያለሽ?»

«በጣም አፈቅራለሁ!» ስትል መለሰች::

«ሰይጣንንስ ትጠያለሽ?» ትላለች::

«አልጠላም! ምክንያቱም ከአምላኬ ፍቅር የተረፈ ለጥላቻ የሚሆን ጊዜ የለኝምና» አለች::

በሌላ ጊዜ ደግሞ ለራቢያ ጥያቄ ቀረበላት:-

«ራቢያ ሆይ! የእግዚአብሔርን ነቢይ ታፈቅሪያለሽ?»

«አፈቅር ነበር:: ነገር ግን የፈጣሪ ፍቅር እሱ ከፈጠረው ነገር ሁሉ በልጦ ልቤን ወሰደው» አለች::

ወደሱፊው ኢታር እንለፍና ደግሞ የሚነግሩንን የፍቅር ታሪክ እንቃኝ::

አንድ ወጣት ከአንዲት የተዋበች ሴት ጋር በፍቅር ይወድቅና ቀንና ሌሊት እሷን መከተል ሥራዬ ብሎ ይይዘዋል:: በጉዳና ላይ እየጠበቀም ለእሷ ያለውን የማይሻር ፍቅር ዘወትር ይነግራት ጀመር::

«ይኸንኑ ደጋግሞ እየነገረ ማስፈያ ያሳጣት ቆንጆም አንድ ቀን እንደልማዱ ይኸንኑ ሲነግራት ቢጠጋት «አስከዛሬ እኔን ስለማፍቀርህ እስመልክቶ የምትነግረኝ ቃላት ሁሉ በጣም የተዋቡ ናቸው። ነገር ግን ከኋላዬ ታናሽ እህቴ እየመጣች ነው። የእሷን ውበት ደግሞ ብትመለከት ከእኔ በላይ እንደምታፈቅራት አልጠራጠርም» አለችው።

«መጣቱ ይኸን ሲሰማ ፊቱን በቅፅበት የሚያፈቅራት ሴት እህት ትመጣለች ወደተባለችበት አቅጣጫ አዞረ። ይኸን ጊዜ ቆንጆዋ። «እስከዛሬ ድረስ ፍቅርህ የማያረጅና የማይሞት መሆኑንም ስትነግረኝ አልነበረምን? እኔም አምኜ ተቀብዬህ ነበር። ይሁንና ከእኔ የበለጠች ቆንጆ ሴት የሚለውን ቃል ከአንደበቱ ስትሰማ ፊትህን በቅፅበት ከእኔ አዞርህ። አንተ ገና የፍቅር ትርጉሙ ምን እንደሆነ ያልገባህ ሰው ነህ» በማለት ጥለው ሄደች።

ከኢታር አንድ ወግ ስንጨምር ደግሞ የምናገኘው የባህሉልን ታሪክ ይሆናል። «ባህሉል በአምላኩ ፍቅር እጅግ የተቃጠለ ከመሆኑ በላይ ቀን ከሌሊት ወሬው ሁሉ ስለአምላክ ድንቃ ድንቅ ብቻ ሆነ። በመጨረሻም ራሱን በመጣል መውጣትና መግባቱ ሁሉ በአምላኩ ነገር ተሞላ። ሲበላም ሲጠጣም፤ ሲሄድም፤ ሲተኛም የሚያወራው ነገር ሁሉ ስለአምላኩ ብቻ በመሆኑ ብዙዎች መደነቅ ጀመሩ።

«ባህሉል ይኸንኑ ነገሩን ይበልጥ ቀጠለበትና በአምላኩ ፍቅር ራሱን መጣሉን አጥብቆ ያዘው። ስለኑሮው መጨነቅ አቁሞ የአምላኩን ነገር ብቻ በማሰብ ኑሮውን መግፋት ጀመረ። በዚህ የባህሉል ባህርይ የተደነቁ ሰዎች ራሱን ለመጠበቅ ትንሽ ጊዜ እንኳን እንዲሰጥ ቢጠይቁት «ለማፈቅረው ነገር ሁሉ የሚሰረቅ ጊዜ የባከነ ጊዜ ነው» በማለት ይመልስላቸው ነበር። አታር በዚህ ወጋቸው የፍቅር ኃያልነት ራስን እስከመርሳት እንደሚያደርስ ያሳዩናል።

ወደጃሚ አልፈን ስለፍቅር የሚነግሩንን ደግሞ እንቃርም፦

«ፍቅር ቤቱን የሠራበት ልብ እንዴት የታደለ ነው? ምክንያቱም ከዓለም ጭንቀት ሁሉ መዳኛው ፍቅር ነውና። ፍቅር ትዕግስትና ማመዛዘንን ወደምንዝምነት የሚቀይራቸው የነጉድጓድ ኃይል ነው። አፍቃሪ ስለራሱ ደህንነት ማሰብ አያውቅበትም፤ የትችት ተራራ ለእሱ

ከገለባ ከምር የቀለለ ነው:: እንዲያውም ትችት የፍቅሩን ኃያልነት የሚጨምርለት ጉልበቱ ነው» ይላሉ::

ከጃሚ አንድ እንጨምር:- «ፍቅር በውስጥህ ቦታን ሲያገኝ የውበት መገለጫው ትሆናለህ:: ፍቅር የያዘው ሰው ውበት የሚገነባረቅበት መስተዋት ነው:: ምክንያቱም ውበትም ሆነ ነብብራቱ መነሻቸው ፍቅር ነውና... የሁለቱም ምንጭ ፍቅር ነው::»

ወደሱፊው መምህር ሩሚ እንመለስ:- «በፍቅር መራራ ነገር ይጣፍጣል፤ መዳቡም ወደ ወርቅ ይለወጣል:: በፍቅር አቧራው ይጠራና ሁሉ ነገር በግልፅ የሚታይና የተዋበ ይሆናል:: በፍቅር የሞተው ነገር ሕይወትን ሲያገኝ ጌታ የነበረው ደግሞ ባርያ ይሆናል::»

«እንዲህ ዓይነቱ ፍቅር ከዕውቀት የሚገኝ ፍሬ መሆኑን አትርሳ:: የፍቅር እምነት ከሃይማኖቶች ሁሉ የተነጠለ ነው:: ለአፍቃሪ እምነቱም ሆነ ሃይማኖቱ እግዚአብሔር ብቻ ነውና:: አምላክህን ብቻ ዘወትር አስታውስ፤ ያን ጊዜ እኔነት ይረሳል:: በዚያም መንገድ ዘወትር የምትፀልይለት አምላክ አንተነትህን ይወርስና ለፀሎትም ጊዜ አይኖርህም::»

ወደሼኽ ሙዛፌር ተመልሰን መሰናበቻችን ይሁን:- «ፍቅር ልዩ የሆነ የስቃይ ደስታ ነው:: ማንም በልቡ ይኽን ያስቀመጠ ምስጢሩን የመረዳት ችሎታንም ያገኛል:: ሁሉ ነገር እውነት መሆኑንና ወደእውነትም እንደሚወስድ ይረዳል:: ከፍቅር በቀር ሌላ ነገር የለም:: በእውነት ባህር ውስጥ ለመስመጥ ፍቅር በልባችን ይንገሥ:: በፍቅር የተሸነፈ እሱ እውነትንም ያገኛታል» ይላሉ::

የፍቅር ነገር ሆነብንና አንድ እንመርቅ:- «ኻሊፍ ሀሩን ራሺድ ከብዙ የሴት ዕቁባቶቹ መካከል ለአንዷ የተለየ ፍቅርና ክብር ነበረው:: ለምን የሚል ጠያቂ ሲመጣበትም በተለያዩ ፈተናዎች ለእሱ የነበራትን ፍቅር ሲያሳያቸው በመቻሉ ነበር:: አንድ ቀን የረጅም ዘመን ወዳጁ ወደቤቱ ይመጣና ይኽንኑ ጥያቄ ቢያነሳበት የዚህችን ዕቁባቱን እውነተኛነት ሊያሳየው ፈተናውን ጀመረ::

«በቤቱ የነበሩትን ዕቁባቶች ሁሉ ሰበሰበና ወደግል ሀብቱ ማስቀመጫ ክፍል ይዟቸው በመግባት የወርቅና የአልማዝ እንዲሁም የዕንቁ

ሉ

ካዝናውን ከፈተላቸው:: ከዚያም በመካከላቸው ቆሞ የፈለጉትን ሁሉ
ይወስዱ ዘንድ አዘዘ:: ውሽሞቹ ሁሉ በካዝናው ውስጥ የነበረው ዕንቁና
ወርቅ ላይ ሲረባረቡ ያቺ ሴት ግን ወደእሱ ተጠግታ ቆመች::
«እሱም ፊቷን ወደእሷ በማዞር ለምን እንደሌሎቹ ሴቶች ከዕንቁና
ከወርቁ እንደማትወስድ ጠየቃት:-
«እሷም:- «እኔ የተፈጠርኩት አንተን በፍቅር ለማገልገል ነው::
ለእኔ ሽልማቴም የአንተ ፍቅር ብቻ ነው» በማለት አረጋገጠችለት::»
ለዚህም ይመስላል ሱፊዎች «ፍቅር እንደፀሐይ ነው! ለፍቅር
ያልታደለ ልብ ከሰባራ ሸክላ አይለይም» የሚሉት:: □

pdf by @shuktus_books

# ‹በፍቅር ውስጥ የሚመር ነገር የለም›

የመጀመሪያው የምድራችን ነቢይ አዳም ነው ይላሉ::
ሱፊዎች የመጀመሪያው የምድራችን ነቢይ አዳም ነው ይላሉ::
እግዚአብሔርም አዳምን ጠርቶ "ለፈጠርኳቸው እንስሳት በሙሉ
ስም አውጣላቸው" አለው:: አዳምም ያለአንድ ችግር ስም አወጣ::
የምድርን እንስሳ ሁሉ ስም ያወጣው አዳም ነው:: የእግዚአብሔር
የጥበብ ዘር በውስጡ ስለነበር አልተሳሳተም:: እኛም ስንፈጠር
እንዲሁ ተዘርቶብናል:: "የምንፈልገውንም ሆነ የምንመኘውን በዚያ
ዘር ውስጥ እናገኘዋለን" ይላሉ ሱፊዎች::
ለሱፊዎች ኢየሱስ እግዚአብሔር የላከው ታላቅ ነቢይ መሆኑን
ይቀበላሉ፤ ለዚህም ነው የእግዚአብሔር መንፈስ ብሎ የሚጠራው::
ይሁንና የእግዚአብሔር መለኮታዊ መንፈስ ደግሞ በፈጠረው ሰው
ሁሉ ላይ ይገኛል:: ያ መንፈስ ከአዳም ተጀምሮ እስከዛሬ ድረስ
አለ:: መንፈሱ በሙላት የሚገለጠው ግን በነቢያትና በመለኮታዊ
ሥልጣን ባላቸው ሰዎች ውስጥ ብቻ ነው... "ይኸንንም ማወቅ ተገቢ
ነው" ይላሉ ሱፊዎች::
ሱፊዎች ኢየሱስን የሚወዱትን ያህል ለሙሴም ታላቅ ፍቅርና
ክብር አላቸው:: እንዲያውም ከእግዚአብሔር ጋር የተነጋገረ ታላቅ
ነቢይ ነው ይሉታል:: አንድ የሱፊዎችን ጥንታዊ ታሪክ እንመልከት::
አንድ ቀን የእስራኤል ልጆች ወደ ሙሴ ተሰብስበው መጥተው
እግዚአብሔርን እራት ሊጋብዙት እንደሚፈልጉና ይኸንኑም
እንዲነግርላቸው ሙሴን ጠየቁት:: በዚህ የድፍረት ጥያቄ የሙሴ
ቁጣ ነደደ:: "እግዚአብሔር የሰውን ምግብ አይመገብም፤ ወደእናንተ
የራት ግብዣም አይመጣም" አላቸው:: የእስራኤል ልጆችም

እያዘኑ ተመለሱ:: በነጋታው ምሽት ላይ ሙሴ እንደለመደው ከእግዚአብሔር ጋር ሊነጋገር ወደተራራ ወጣ:: በተራራው ጫፍ ላይ ሲደርስ እግዚአብሔር ቆሟል::

እግዚአብሔርም "ባሪያዎቼ የእራት ግብዣ አድርገውልኝ ለምንድነው አሳፍረህ የመለስከብኝ..." በማለት በሀዘን ጠየቀው:: ሙሴም "ጌታ ሆይ! የሰው ምግብ አትበላም ብዬ ነበር:: እንዲህ ዓይነቱን የጥንቱ ግብዣም አትቀበልም የሚል እምነት አድሮብኝ ነው..." አለ:: እግዚአብሔርም አዘዘው፡- "ሂድና ለሕዝቤ ንገረው:: ነገ ማታ ለእራት እመጣለሁ፣ ግብዣቸውንም ተቀብያለሁ...::"

ሙሴም በሌሊት ወደሕዝቡ ተመልሶ እግዚአብሔር የእራት ግብዣቸውን እንደተቀበለ አበሰራቸው:: "ማታ እራት ከእናንተ ጋር ነኝ፣ ተዘጋጁ ብሏል" አላቸው:: ሕዝቡም ድግሱን ማዘጋጀት ጀመሩ:: በእስራኤል ምድር ታላቅ የተባለው ግብዣም ተዘጋጅቶ መሰናዶው ወደመጠናቀቁ በተቃረበበት ሰዓት አንድ በረሃብ የከሳና የጠወለገ ሽማግሌ ድንገት ወደድንኳኑ ደጃፍ ተጠግቶ "እባካችሁ ተርቤአለሁ... ከድግሱ የምበላው ትንሽ ስጡኝ..." በማለት ልመና አቀረበ:: ሕዝቡ ግን እያዳፉና እየሰደቡ አስወጡት... "እኛ የደገስነው ከእግዚአብሔር ጋር ለመብላት ነው..." በማለት አባረሩት::

የዚያን ቀን ማታ እግዚአብሔር ሳይመጣ ቀረ:: ሙሴም እጅግ አፈረ፣ ብዙዎቹም ከእግዚአብሔር ጋር ተነጋግሬ መጣሁ የሚለን ሐሰት ነው በማለት ጠረጠሩት:: በነጋታው ምሽት ላይ ሙሴ በሲናይ ተራራ ወጥቶ እግዚአብሔርን መጠበቅ ጀመረ:: እግዚአብሔርም በሰዓቱ መጣ:: ሙሴም በሐዘን "ጌታ ሆይ! የራት ግብዣቸውን እንደተቀበልህ ለሕዝብህ ነግሬ ነበር... አንተ ግን ቀርተህ አሳፈርኸኝ..." አለ::

እግዚአብሔርም "ሙሴ! በራት ግብዣችሁ ላይ ቀድሜ ነበር የተገኘሁት፣ ነገር ግን ገፍትራችሁ አባረራችሁኝ" አለ:: ሙሴም፡- "እኛ ያባረርነው ደሃ ሽማግሌ ነው፣ ሌላ ያባረርነው ሰው የለም" አለው... እግዚአብሔርም ጠየቀው፡- "ያን ደሃ ሽማግሌስ ማን ፈጠረው?" ሙሴም "አንተ ነህ ጌታ ሆይ!" በማለት መለሰ::

ይኸን ጊዜ እግዚአብሔር፡- "ታዲያ በፈጠርኩት ውስጥ መኖሬን ትጠራጠራለህ?" አለው:: ሙሴ አላስተባበለም:: ከታናናሾቼ ለአንዱ የአደረጋችሁት ለእኔ እንዳደረጋችሁት እቆጥረዋለሁ እንደማለት ነው::

እንግዲህ ሱፊዎች እዚህ ላይ ይመክራሉ፡- "አገልጋይህን ስትወድ የአንተ ጆሮ የእግዚአብሔር ይሆናል፣ ስለዚህም በአንተ ውስጥ እሱ መስማት ይጀምራል:: ዓይንህ የእግዚአብሔር ይሆናል፣ በአንተ ዓይን እሱ ማየት ይጀምራል:: አንደበትህ የእግዚአብሔር ይሆናል፣ በአንተም ምላስ እሱ ይናገራል" ይላሉ::

አንድ የተከበረ ሱፊ ከአንዲት ሴት ጋር በመንገድ ላይ ተገናኙና ይኸን ጠየቃት፡- "የፍቅር መጨረሻው ምንድነው?" እሷም መለሰች፡ - "...ፍቅር መጨረሻ የለውም::" ሱፊው ዳግመኛ ጠየቃት፡- "ለምን?" እሷም በመልሷ አስደነቀችው፡- "ምክንያቱም ፈጣሪ መጨረሻ የለውምና!!"

ሱልጣን መሐመድ እጅግ አድርገው የሚወዱትን አገልጋያቸውን አያዝን አንድ ቀን ወደገበታቸው በመጥራት ከፊታቸው ከተቀመጠው ፍሬ አንዱን አንስተው ሰጡት:: አያዝም ከሚወደው ጌታው እጅ የተቀበለውን ፍሬ በልቶ እንዳጋመሰ ሱልጣኑ ሌላ ፍሬ አንስተው አንዴ ገመጡና ትንሽ እኝከው ተፉት::

በመገረምም ወደ አያዝ እየተመለከቱ፡- "እንዲህ ዓይነት መራራ ፍሬ እንዴት ትበላለህ?" አሉት::

"የምወድህ ሱልጣን ሆይ" አለ አያዝ "የጣፈጠኝ ፍሬው ሳይሆን የሰጠኝ እጅህ ነው" በማለት መለሰ:: በፍቅር ውስጥ የሚመር ነገር የለም::

ማንሱር አል ሀላጅ በሕዝብ ፊት እንዲገደል ሲፈረድበት የሠራውም ወንጀል በአደባባይ ተነገረ:: ይኸውም "እኔ እውነት ነኝ" በማለት ሰብኳል የሚል ነበር:: እውነት ደግሞ ፈጣሪ ብቻ ነው፣ ስለዚህም ራሱን ከአምላክ ጋር አወዳድሯል ተባለና ተገደለ... የተቀደሱት ጁናይድ (ሱፊ ናቸው) ይኸን ሲሰሙ አዘኑ:: "ጁናይድ ሆይ! እኔ እውነት ነኝ ብሎ ከመስበክ ውጭ ምን ኃጢአት ይኖራል?"

ተብለው ተጠየቁ:: ጁናይድም መለሱ፡- "ከዚያ በላይ ኃጢአትማ 'እኔ ሐሰት ነኝ' ብሎ መስበክ ነው" አሉ::

ሱፊዎች ስለሙሴ ወደዛፉት ሌላ ታሪክ እንመለስ፡፡ አንድ ቀን ሙሴ ብቻውን በጫካ ውስጥ ሲሄድ አንድ ጎልማሳ ለእግዚአብሔር እየፀለየና እየሰገደ አገኘው:: ምን እያደረገም እንደሆነ ጠየቀው:: ጎልማሳውም፡- "የእግዚአብሔርን እጅ እየሳምሁ፣ መጎናፀፊያውንም እያጠብሁና ፀጉሩን እያበጠርሁ ነው" አለው:: ሙሴም በዚያ ጎልማሳ የድፍረት ንግግር ተናዶ ከቦታው አባረረው... በምሽት ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት ወደተራራው ወጣ:: እግዚአብሔርም በቁጣ ተቀበለውና "ሙሴ! በእውነት ከልቡ ያመልከኝ የነበረውን ጎልማሳ ዛሬ ከቦታው ስላባረርክብኝ ተቆጥቻለሁ... ከእነዚያ ስለ እኔ በአንደበት ጨዋታ ሲያወሩ ከሚውሉት ሊቃውንትና ጠበብቶች ይልቅ እሱ በጣም ለእኔ የከበረ እንደነበር አታውቅምን?" አለው:: ሙሴ በድርጊቱ አዘነ:: በነጋታው ያንን ጎልማሳ ፍለጋ ሙሴ ወደጫካው ወጥቶ ሊያገኘው ባለመቻሉ እያዘነ ወደከተማ ተመለሰ:: ሲመለስም ጎልማሳውን ከሊቃውንት ጋር በከተማ ቆሞ ሲነጋገር አገኘው::

በሱፊዎች የመጨረሻ ምክር ምዕራፉን እናብቃ:: ሱፊዎች ከማንም በላይ ኃጢአትን የፈፀመ ሰው ነው የሚሉት ጊዜውን በከንቱ የሚያባክነውን ነው:: ለዚህም ነው፡- "ከሚባክን ጊዜ በቀር ለኃጢአት ሁሉ ይቅርታ አለው" የሚሉት:: የሀበሻን ንስሐ ውሃ በላው ይሆን?

□

pdf by @shuktus_books

# "ከእብደት ምስጢር የእውነት ምንጭ ይገኛል"

የሱፊዝምን የእምነት ፍልስፍና ልናነሳ የሚገባን ምዕራፍ ላይ እንደምንገኝ እምናለሁ:: ስለሱፊዝም ምንነትና ትርጉም የማስረዳበት ቦታ አለኝ ብዬ አላስብም:: ባለፉት ምዕራፎች በተደጋጋሚ ይህንኑ የእምነት ፍልስፍና ለአንባቢዎቼ ሳስቃኝ በበቂ አንስቼዋለሁ የሚል እምነትም ስላለኝ በዚህ ምዕራፍ የሱፊዝምን የአስተማሪና የተማሪ ግንኙነት ጀምስ ፋዲማን እና ሮበርት ፍሬጀር በጋራ ከፃፉት "Essential Sufism" ውስጥ የቃረምኩትን እበትናለሁ::

በአረቦቹ ዘንድ ተወዳጅና ጣፋጭ ገፀ-ባህርይ ቢኖር ናስሩዲን ነው:: ናስሩዲን አድራጊና ፈጣሪ ያልሆነበት የዓረብ ታሪክ እምብዛም አይገኝም:: በተለይ በመካከለኛው ምሥራቅ ይኸው አካሄድ የተለመደ ነውና መንደርደሪያችንን በእሱው እናደርጋለን:: አንድ ቀን በቁጥር የበዙ ወጣቶች ወደናስሩዲን ቤት መጥተው አስተማሪያቸው እንዲሆን ይጠይቁታል:: እሱም በቀረበለት ጥያቄ ተስማምቶ የመጀመሪያውን ትምህርት ሊሰጣቸው ወደ ሱፊዎች ማረፊያ ይወስዳቸዋል:: መንገድ ሲጀምሩም ናስሩዲን እንዲት የአህያ ውርንጭላ ላይ ፊቱን ወደ ተከታዮቹ አዙሮ በመፈናጠጥ ወደኋላው ያስጋልባት ጀመር:: ይኸን ትዕይንት የተመለከቱ የከተማው ነዋሪዎች በናስሩዲን ድርጊት እየሳቁ በተከታዮቹ ሞኝነት ደግሞ ማላገጥን ያዙ::

ናስሩዲን በሱፊ ማረፊያ ደርሶ ሲመለከት ከተከታዮቹ ውስጥ አብዛኞቹ ከመሃል መንገድ ተመልሰው አንድ ብቻ ቀርቶ ነበር:: ይኸው እስከመጨረሻው ናስሩዲንን የተከተለው "ተማሪ" ወደ እሱ ተጠግቶ፡- "ናስሩዲን ሆይ! ለምን ይሆን ወደኋላ ትጋልብ የነበረው?" በማለት ጠየቀው:: ናስሩዲንም፡- "ተማሪዎች ከአስተማሪያቸው

ቀድመው መሄድ እንደሊሰባቸው ታውቃለህ ብዬ ስባለሁ:: አስተማሪ ደግሞ ለተማሪዎቹ ጀርባውን ሰጥቶ መሄድም የተገባ አይሆንም:: ስለዚህም የነበረኝ ምርጫ ከእናንተ ቀድሜና ራቴን ደግሞ ለእናንተ ትቼ መሄድ ነበር፡ ሳደርግ የነበረውም ይኸንኑ ነው" በማለት መለሰለት::

ሱፊዝም ይኸን ታሪክ የተለያዩ ደረጃዎች አሉት ይሉናል:: የመጀመሪያው ናስሩዲን የተማሪዎቹን ታዛዥነትና ትዕግስት ሊለካበት ችሏል:: ሁለተኛው ደግሞ የመልካም አስተማሪን ተሞክሮም አሳይቶበታል:: መልካም አስተማሪ መንገዱን የሚያውቅና አትኩሮቱ ግን በተማሪዎቹ ላይ የሆነ ነው:: በሦስተኛ ደረጃ ደግሞ የአስተማሪና የተማሪ ግንኙነት በመከባበር ላይ የተመሠረተ ሊሆን እንደሚገባም አሳይቶበታል ይላሉ::

በሱፊዝም እምነት አስተማሪ ማለት መንገዱን የሚያውቅ ማለት ነው:: ማንም ሰው ከራሱ በላይ ያደገ ዘንድ ከራሱ በላይ የሚያውቅ አስተማሪ ያስፈልገዋል:: ይኸ ሂደት በተሳሌ ሲቀመጥ፡- "ሰው የቱንም ያህል ጠቢብ ቢሆን ለራሱ የመጀመሪያ ዕርዳታ ከማድረግ ያለፈ ሕክምና ማድረግ አይችልም:: ራሱን ቀዶ የጠገን ስለማይገኝ ውስጣዊ ነገርህ ይሠራ ዘንድ ለሌላው እጥቂ ተውለት" እንደማለት ይሆናል::

ጠቢቡ ባሀሉልን እንመልከት፡- ባሀሉል የቱንም ያህል በጥበብ ቢበስል በዚህ ምክንያት የሚደርስበትን አደጋ ፍራቻ ጥበቡን በእብደት መጋረጃ ሸፍኖታል:: ስለዚህም ለማንም ሰው ያልተፈቀደውን "ጥበብን በአደባባይ የመናገር ዕድል" እሱ በዚያች መጋረጃ ተከልሎ ሲተነፍሳት ኖሯል:: አንድ ቀን ባሀሉል ወደቤተመንግሥቱ አዳራሽ ሳይታይ ገብቶ በንጉሡ ሀሩን ዙፋን ላይ ተቀምጦ ተያዘ:: በንጉሥ ዙፋን ከመቀመጥ በላይ ወንጀል በሌለበት በዚያ ምድር ባሀሉልና የያዙት ወታደሮች ቆዳው እስኪገለጥ ይተለትሉት ጀመር:: የባሀሉልን ጩኸትና ለቅሶ ከሌላው አዳራሽ ሆኖ የሰማው ንጉሥም ሲሮጥ ይጠማና ባሀሉልን አስጥሎ ጥፋቱን ይጠይቅ ጀመር::

"ንጉሥ ሆይ! በዙፋንህ ላይ ተቀምጦ አገኘነው" አሉ ወታደሮቹ፡ በዚህ ጊዜ ንጉሡ አዝኖ ባሀሉልን እያባበለ ወደወታደሮቹ ዞሮ፡

"እናንተ አብዶች! ባህሉል እብድ መሆኑን እንኳን አታውቁም:: ጤነኛ ሰው በእኔ ዙፋን ላይ ሲመጥ አይታችሁ ታውቃላችሁ?" በማለት አፈጠጠ:: ይኸን ጊዜ ባህሉል፡- "ንጉሥ ሆይ! ወታደሮችህን አትቆጣ:: እኔን ያስለቀሰኝ የእነሱ ግርፋት አይደለም:: ነገሩ ሌላ ነው..." አለው::

ንጉሡም ግራ ተጋብቶና ወደባህሉልም በአግራሞት እየተመለከተ "ያስለቀሰህ ሌላ ምክንያት ታዲያ ምን ይሆን?" አለው:: ባህሉልም፡ "ያስለቀሰህ ሌላ ምክንያት" - "ንጉሥ ሆይ! እኔ አንድ ቀን ለተቀመጥኩበት ዙፋን ይኸን ያህል ግርፋት ከደረሰብኝ አንተ ሃያ ዓመት ለተቀመጥክበት የሚደርስብህ መከራ ትዝ ብሎኝ ነው ያለቀስኩ..." አለው:: ንጉሡ ሁሩን ለዓመታት ያላየውን እውነት እብዱ ባህሉል አሳየው:: በቤተመንግሥቱም አስተማሪ አድርጎ ሾመው::

ንጉሡም አለ፡- "ከእብደት ምስጢር የእውነት ምንጭ ይገኛል"::

የሱፊዝም መምህር ተግባራት በዋነኛነት ስምንት ተደርገው ይወሰዳሉ፡- እነዚህም ተማሪዎችን እንደልጆቹ ማየትና ደህንነታቸውን መከታተል፣ ስለአገልግሎቱ ከተማሪዎቹ ምንም ዓይነት ክፍያም ይሁን ምስጋና አለመቀበል፣ የሚያውቀውን ነገር ሁሉ ከተማሪዎቹ አለመደበቅ፣ ተማሪዎቹን ከመጥፎ ምግባር ይመለሱ ዘንድ በሚያባብሉና ጥበብ በተሞሉ ቃላት መምከር እንጂ አለመስደብ፣ የሌላውን ተማሪ ሐሣብና እምነት አለማናናቅ፣ ተማሪዎቹ ሊሄዱ የሚችሉበትን የእውቀት ደረጃ ማወቅ፣ የቱንም ያህል የተወሳሰበ ትምህርቶች ቢሆኑ ተማሪዎቹ ሊረዱት እንደሚችሉ ማመንና ራሱ የሚያስተምረውን ነገር በተግባር ማሳየት መቻል ናቸው::

እንግዲህ በሱፊዝም አስተማሪና ተማሪ ሊኖራቸው የሚገባ ግንኙነት ይኸን ሲመስል ተማሪው ከትምህርቱ በተጨማሪ አስተማሪውንም ሊያጠና ይገባልም ይላሉ፣ አስተማሪው በራሱ ለተማሪው አንድ ትምህርት ቤት ነውና::

ከሞሐመድ ሻፌ ወጐች አንድ እንመልከት:: ወጣቱ ተማሪ የሱፊው መምህር ጋ ለዓመታት ከተማረ በኋላ ወደመመረቂያው ሲደርስ ሱፊው መምህር ለአንድ ወር ሽንት ቤት እንዲያፀዳ ይልኩታል:: በዚህ ተማሪ ምደባ እጅግ የተበሳጨው የተማሪው ወላጅ አባት ወደ

ሱፊው መምህር ሲሮጥ መጣ:: ይኸው አባት በሕክምና ሙያው በሃገሪቱ በጣም የታወቀና በሀብት ደረጃውም ቢሆን ካላቸው ወገኖች የሚመደብ ነበር:: የሱፊው መምህር የተማሪያቸውን አባት ጥያቄ በጥሞና አዳመጡ::

"እባክዎን ልጄን ከሽንት ቤት ዕዳት ያውጡልኝና ወደሌላ ትምህርት ያዛውሩት፣ በእሱ ምትክ ሽንት ቤቱን የሚያፀዱ አስራ ሁለት ባሮች እሰጥዎታለሁ" አለ::

የሱፊው መምህርም "አንተ ሐኪም ነህና አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ:: ልጅህ በአንድ ሕመም ተይዞ ወደአንተ ቢመጣ መድኃኒቱን ለአሥራ ሁለቱ ባሮች ትሰጣለህ?" የተማሪው አባት አፉን ይዞ እንደሄደ ሞሐመድ ሻፊ ነግረውናል::

ለዚህም ነው ሱፊዎች፡- "ያለአስተማሪ የሁለት ቀን መንገድ ሁለት መቶ ዓመት ይወስዳል" የሚሉት::

በዚህች ልሰናበት፡- የመጀመሪያውን የሱፊዎች ማረፊያ በሲራያ ራማላ ውስጥ ያስገነባው አንድ የክርስትያን ልዑል እንደነበር ይነገራል:: ይኸው ልዑል አንድ የመሰጠውን ትዕይንት በራማላ በኩል ሲያልፍ ተመለከተ:: ሁለት ሱፊዎች በመንገድ ላይ ሲሄዱ ይገናኙና በመተቃቀፍ ተሳስመው አንዱ የቋጠረውን ስንቅ በጋራ ሊመገቡ ተቀመጡ:: ይኸንን ትዕይንት ለአፍታ የተመለከተው ክርስትያኑ ልዑል ወደሁለቱ ሰዎች ተጠግቶ ስለትውውቃቸው ጠየቃቸው:: መመገባቸውን ሳያቋርጡ አንዱ ቀና ብሎ፡- "ከለዛሬ አይቼው አላውቅም..." አለው::

"ምናልባት የአንድ ሃገር ልጆች ትሆኑ?" አለ ልዑሉ::

"ሃገሩንም አላውቅም..." አለ ሰውዬው አሁንም መመገቡን ሳያቋርጥ::

"ታዲያ ለምንድነው እንዲህ ዓይነት ፍቅር ያሳየኸው...?" አለ ልዑሉ ተደንቆ፡-

"በእኔ መንገድ ላይ ሲጓዝ ስላገኘሁት ነው" አለው::

ልዑሉ መደነቁን ጨርሶ ዝም ብሎ አልሄደም:: በዚያ ቦታ ለሱፊዎች ማረፊያ የሚሆን ትልቅ ቤት ሠራ:: ዛሬ ቤቱ የሱፊዎች መፍለቂያ "ዩኒቨርስቲ" ሆኗል:: □

# "ከፍጥረ ሁሉ የሚበልጠው ምላሽ ሳያገኙ ማፍቀር መቻል ነው"

- ሰይጣን

ላለፉት አንድ ሺህ ዓመታት ሱፊዎች እምነታቸውን የማንነትና እግዚአብሔርን ወደማወቅ የመድረሻው "ታላቅ ፍፃሜ" አድርገው ሲወስዱት ኖረዋል:: ሱፊዝም የፍቅር፣ የመሰጠት፣ ብሎም የዕውቀት መንገድ ነው:: የሱፊዝም ትልቁ ተግባር በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያለውን መጋረጃ በመቅደድ የእውነትን ምስጢር ገልጦ ማሳየት ነው:: እውነት ደግሞ ለሱፊዝም እግዚአብሔር ነው:: ወደዚህ እውነት ወይም ወደ እግዚአብሔር መድረሻው መንገድን ዕውቀት ይሉታል:: ይኸንኑ እውቀት የሱፊው ፈላስፋ አል-ጋዛሊ ሲተነትኑልን፡- "እውነተኛ እውቀት በውስጡ የያዛቸው 'አንተ በራስህ ማን ነህ?' 'ከየትስ መጣህ?' 'የምትሄደው ወዴት ነው?' 'በዚህ ምድር የመምጣትህ ምክንያት ምንድነው?' 'የደስታና ሐዘንህ ምንጭስ እንዴት ያለ ነው?' የሚሉት ናቸው" ይሉናል:: ይሁንና እነዚህንና ሌሎች በርከት ያሉ ጥያቄዎችን ለመመለስ የሚያዳግተን በእውቀት መንገድ የምናገኛቸው መሰናክሎች ናቸው:: በተለያዩ አሳቢዎች የተመለከትነው ሰይጣን በዚህ ምዕራፍ በሱፊዝም መንገድ ልናየው እንሞክራለን:: በዚህም መንገድ ስለ እሱ ያለንን እውቀት እናበለፅጋለን::

ሰይጣን ከመላዕክት ሁሉ ተለይቶ ብቻውን የተገለለና በእግዚአብሔር የተጣለ መልአክ መሆኑን ሱፊዎች ይነግሩናል:: ፈጣሪ ከፍጥረት በአንዱ ቀን አዳምን ሰራውና ይሰግድለት ዘንድ ሰይጣንን ይጠራዋል:: በዚያን ጊዜ ሰይጣን መልአክ ነበርና ለሰው መስገዱን አሻፈረኝ አለ:: በዚህ መልሱ የፈጣሪ ቁጣ ነደደ:: ለሰይጣንም የመደራደሪያ እና ሃሳቡን የማቅረቢያ ጊዜ ሳይሰጠው

ወደምድር ይጥለዋል:: ፈጣሪ የተናደደው ለሰው ስላልሰገደ ሳይሆን የእሱን ትዕዛዝ ባለማክበሩ ነው:: ወደምድር ከተጣለም በኋላ ቢሆን ሰይጣን የመከራከሪያ ሐሣቡን ሰንዝሯል:: "እኔ መልአክ ሆኜ ተፈጥሬ ሳለ እስግድ ዘንድ የሚገባኝ መለኮታዊ ኃይል ላለው እንጂ ለሰው አልነበረም" አለ:: በጥፋቱ ተፀፅቶ ንሰሐ በመግባት ሁለተኛ የመመለስ ዕድሉን እንኳን እንዳይሞክር ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከገነት መባረሩን ቁርጥ አደረገው:: የገነት ደጃፎችም ተዘጉበት፣ የፈጣሪም ዓይን ከእሱ ላይ ዞረች::

ይሁንና ሰይጣን ከፈጣሪ ጋር ካጣላው ጉዳይ ውጪ ለእሱ የነበረው ፍቅር አልተዘተዘም ነበር:: ብቻውንም በተጣለ፣ ያለተስፋና ያለአንዳች እርዳታ በቀረ ጊዜ ብሎም ምላሽ ፍቅር እንደማያገኝ እርግጠኛ በሆነበት ሁኔታ ውስጥ እንኳን እሱን ከማፍቀር ወደኋላ አላለም:: ከፍቅር ሁሉ የሚበልጠው ምላሹን እንደማያገኙ እያወቁ ማፍቀር መቻል ነው:: ሰይጣን ደግሞ ምላሽና ዋጋ ባያገኝለትም እግዚአብሔርን ማፍቀሩን አላቋረጠም::

የዘላለምን መለየት የሚያህል ሽክም ተሸክሞ የሚጓዘው ሰይጣን አንዱ የፍቅሩ መግለጫ ደግሞ ለሰው ልጅ በየዕለቱ መሰናክልን ማስቀመጥ ነው:: በሱፊዝም እምነት የሰይጣንን መሰናክል ዕለት ዕለት እየዘለልን በማለፍ በእሱ ላይ አሸናፊነታችንን ባረጋገጥን ቁጥር የሚሰማን እርካታና ደስታ ከፍተኛ ነው:: በውስጣችን የተቀመጠውን ብቃት የማወቅ ምስጢርም ይኸው የሰይጣን መሰናክል ነው:: ቢያንስ ሰይጣን ሰውን በነገር ሁሉ ንቁ እንዲሆን በማድረግ ፍቅሩን ይገልፅለታል:: ይኸንኑ ሱፊዎች ሲገልፁት "የሰው ልጅ ሰይጣን ያስተማረውን ያህል የትኛውም መልአክ አላስተማረውም" ይላሉ::

እዚህ ላይ የምዕራባውያኑን ፍልስፍና ጣል አድርጎ ማለፍ ተገቢ ነው:: በምዕራባውያኑ ፍልስፍና መሠረት እግዚአብሔር ሰይጣንን የፈጠረው ለራሱ ሕልውና እንዲጠቅመው ሲል ነው:: ምክንያቱም የሰው ልጅ ሰይጣንን የሚያህል ባላጋራ የሚቋቋመው እግዚአብሔርን በመለመንና ወደ እሱ በመጠጋት ነውና ይኸው ሰይጣን ደግሞ የተፈጠረው በራስ በእግዚአብሔር ነው:: ምክንያቱም

ያለ እሱ የተፈጠረ አንዳች ነገር አለመኖሩን እናውቃለንና:: ስለዚህም ሰይጣን ያለመኖሩን በእርግጠኛነት የምናውቅበት መንገድ ቢኖረን ኖሮ የመጀመሪያውና በቅዕበት አላስፈላጊ የሚሆነው ነገር ራሱ እግዚአብሔር ይሆን ነበር:: ይኸው ፍልስፍናን በሃገራችን ተረት ስናጠጋጋው "አይጥ ከጠፋ ድመት አይፈለግም" እንደማለት ይሆናል::

ወደሱፊዝም ፍልስፍና ስንመለስ "ምንም እንኳን ፈተናዎቻችንና መከራዎቻችን ከሰይጣን የሚላኩብን ቢሆኑም ዞሮ ዞሮ ለእኛ እስከጠቀሙን ድረስ የፈጣሪ ስጦታዎች ናቸው" ይሉናል:: ወላጆቻችን በሕፃንነታችን ወቅት ብቻ ተንከባክበው አሳድገው ካደግን በኋላ ከዓለም ጋር እንድንጋፈጥ ትተውን እንደሚቀመጡ ሁሉ ፈጣሪም ለተወሰነ ጊዜ ተንከባክቦን ይቆይና ከሰይጣን ጋር እንድንታገል ትቶን ይቀመጣል:: (በትግሉ ያሸነፈ ወደ ፈጣሪ መንግሥት ሲገባ የተሸነፈው ደግሞ የሰይጣን መንግሥት አባል ይሆናል ማለት ነው):: ዞሮ ዞሮ ሰይጣን የጥንካሬአችን መፈተኛ እስከሆነ ድረስ ከእኛ ይልቅ የሚያሳዝነው ዘላለሙን ለትግል የተፈጠረው እሱ ነው::

ሰይጣን አንዳንድ ጊዜ የተፈረደበት ፍርድ ተገቢ አለመሆኑን ሲከራከርም እንሰማለን:: የሱፊው አናስ ይኸችን ወግ ይነግሩናል፡- አንድ ቀን ሰይጣን ‹‹ሁሉ ነገር የሚሆነው በፈጣሪ ሞገስና ፍላጐት መሆኑ እንጂ የእኔ ኃጢአት አሁን ከአዳም በልጦ ነው?" በማለት አንዱን መልአክ ይጠይቀዋል::

መልአኩም "ለአዳም ስገድለት ሲልህ አልሰግድም በማለትህ እኮ ነው የተባረርከው! ይኸ ደግሞ አለመታዘዝና ታላቅም ኃጢአት ነው" አለው::

ሰይጣንም መልሶ፡- "እኔ ለአዳም አልሰግድም በማለትና አዳም ደግሞ አትብላ የተባለውን ፍሬ በልቶ አለመታዘዙን በማሳየት መካከል ያለው ልዩነት ግን አይታየኝም" አለው::

መልአኩም "በእርግጥ እንዳልከው አዳም በፈጣሪ ፊት ሞገስ አግኝቷል" አለውና ነገር ግን የሰይጣንን ሐሣብ በመደገፉ ደግሞ መልሶ መደንገጥ ጀመረ::

ሰይጣንም፡- "ፈጣሪ አዳምን ይቅር ሲለው ሲፈልግ ከጥንቱ ከአዳም ጋር ቃልኪዳን አለኝ አለ:: ነገር ግን ከአዳም በፊት እኔ ነበርኩ:: የሚያሳዝነው ደግሞ የአዳም የአለመታዘዝ ምክንያትም እኔው መሆኔ ነው:: እነሆ ከአዳም ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ በራሱ ድክመት መሳሳቱን የሚያምን ሰው ለማየት አልቻልኩም:: ይልቁንስ ይኸ የከፋ ኃጢአት አይደለም?" በማለት መልአኩን ጠየቀው:: መልአኩ ግን መልስ ስለአጣ ፈጣሪን ሊጠይቅ ሲከንፍ ሄደ:: ይሁንና እስከዛሬ አልተመለሰም::

ሱፊው ሼክ ሙዛፊር ወዳሰፈሩት አንዲት የሰይጣን ታሪክ እንሻገር:: አንድ ዛፍ ቆራጭ በመንደሩ አጠገብ አረመኔዎች (ሃይማኖት የለሽ ሰዎች) እየተሰበሰቡ የሚሰግዱለት አንድ ዛፍ ይመለከትና ስለ እግዚአብሔር ቅናት ያድርበታል:: በቀጣዩ ቀንም መጥረቢያውን ስሎ ሲያበቃ ዛፉን ለመቁረጥ ወደዚያው ያመራል:: ነገር ግን ዛፉ ጋ ሳይደርስ ሰይጣን በመንገድ ላይ ይጠብቀዋል::

"ወንድሜ ወዴት ነው የምትሄደው" ይለዋል ሰይጣን::

የሰይጣንን ማንነት ያልተረዳው ዛፍ ቆራጭም "ከፊት ለፊቴ የማየውን ዛፍ ለመቁረጥ እየገሰገስኩ ነው" ይለዋል::

ሰይጣን በዚህ ጊዜ፡- "እባክህ ዛፉን እንዳትቆርጥ እለምንሃለሁ" በማለት በፍጥነት ከፊቱ ይቆማል::

"አንተ ለመሆኑ ማነህ ዛፉን አትቁረጥ ብለህ የምትናገር? ስለአምላኬ ስለፈጣሪ ስል ይኸን ዛፍ ዛሬ ሳልቆርጠው አልመለስም" በማለት ዛፍ ቆራጩ መልሶ ይፎክርበታል::

"እኔ ሰይጣን ነኝ:: ዛፉን እንድትቆርጠው አልፈቅድልህም" ይለዋል::

ዛፍ ቆራጩ፡- "አንተማ እኔን ለማቆም አትችልም" በማለት ትንቅንቅ ይገጥመዋል:: በሙሉ ኃይሉም ሰይጣንን ከመሬት ጥሎ ሲገድለው መጥረቢያውን አንገቱ ላይ ሊያስቀምጥ ሰይጣን፡- "ማመዛዘን በጣም ይጎድልሃል:: ያንን ዛፍ ለመቁረጥ ብትሞክር የሃገሩ ሕዝብ አያስነካህም፡ እንዲያውም ሊገድሉህ ይችላሉ:: ቤተሰብህን ደግሞ ያለረዳት በትነኸው ልትቀር ነው:: እባክህ

ጥቂት አስብ:: ይልቁንስ ይኸን ሐሣብህን ከተውከው ከአንተ ጋር ለመደራደር እፈልጋለሁ:: በዛፍ ቆራጭነትህ በቀን ሁለት ብር ብቻ እንደምታገኝ አውቃለሁ:: ይኸ ደግሞ ቤተሰብህን በሚገባ ለመርዳትና ለማኖር በቂ አይደለም:: ስለሆነም ከነገ ማለዳ ጀምሮ በትራስህ ሥር በየቀኑ ሁለት የወርቅ ማንቲሞች አስቀምጥልሃለሁ:: በዚያ ሽያጭ የተደላደለ ኑሮ መኖር ትጀምራለህ፣ ቤተሰብህንም በሚገባ ታኖራለህ..." አለው::

ዛፍ ቆራጩ በመጀመሪያ የሰይጣንን ሐሣብ በእጅጉ ተጠራጠረና ማረጋገጫውን ጠየቀው:: ሰይጣንም በነጋታው ሁለት የወርቅ ማንቲሙን ከአልጋው ትራስ ስር ባያገኝ መጥረቢያውን አንስቶ በመሄድ ዛፉን እንዲቆርጥ ፍቃድ ሰጠው::

በነጋታው የዛፍ ቆራጩ ትራስ ሥር ሁለት የወርቅ ማንቲም አገኘና ተደስቶ ዋለ:: በሁለተኛው ቀን ማለዳ ሲነሳ ግን የትራሱ ሥር ባዶ ሆኖ አገኘው:: በዚህም ዛፍ ቆራጩ በሰይጣን መታለሉን ተረድቶ መጥረቢያውን አንስቶ ዛፉን ለመቁረጥ መገስገስ ጀመረ:: ጥቂት ተጉዞ ከሩቅ ሲመለከት ግን ሰይጣን አሁንም በመንገዱ ላይ ቆሞ እንደሚጠብቀው ተረዳና ፍጥነቱን ጨምሮ በመሮጥ አጠገቡ ሲደርስ ትንቅንቅ ጀመረ:: ለሰይጣን ግን ዛፍ ቆራጩ ከአንድ ቀን በፊት እንደጠነከረበት አልነበረም:: በቀላሉ ከመሬት ጥሎ ሊገድለው ሲዘጋጅ ዛፍ ቆራጩ "እባክህን ሳትገድለኝ አንድ ነገር ብቻ ትነግረኝ ዘንድ እለምንሃለሁ?" አለው:: ሰይጣንም እጁን ሰብስቦ የሚጠይቀውን መጠበቅ ጀመረ:: ዛፍ ቆራጩም "በቀደም ከመሬት ጥዬ ልገድልህ ስታገልህ የዛሬን ያህል ኃይል አልነበረህም:: ለመሆኑ የዛሬው ኃይልህ ምስጢሩ ምን ይሆን?" አለው::

ሰይጣንም፡- "በቀደም የነበረኝ ኃይልም ሆነ የዛሬው ልዩነት የለውም:: ልዩነቱ ያለው ከአንተ አቋም ላይ ነው:: በቀደም ስትታገለኝ የነበረው ስለአምላክህ እግዚአብሔር ቀንተህ ነበር፣ ዛሬ ደግሞ የታገልከኝ ስለሁለት የወርቅ ሳንቲሞች ስትል ነው" አለው:: ...ዛፍ ቆራጩ ንስሐ እስኪገባ እንኳን ሰይጣን የጠበቀው አይመስለኝም::

ሱፊዎች በስተመጨረሻ የሚያስምሩበት ሐሣብ ቢኖር

ስለሰይጣን እናስብ ዘንድ የተገባ አለመሆኑን ነው:: ለምን? ቢሉ ስለሰይጣን ብናስብ ሆኖ ሆኖ "እግዚአብሔር ከሰጠን ጊዜ ሰርቀን ስለሰይጣን ብናስብ ሆኖ ሆኖ ኃጢአተኞች መሆናችንም አይደል?" ይሆናል መልሳቸው:: እንዲህ ከሆነ ደግሞ የእግዚአብሔር ድካም ከንቱ ሊቀር ነው:: እሱ ለእኛ መፈተኛ ብሎ ያዘጋጀልንን ሰይጣን እስከመፈጠሩም ብንረሳው እግዚአብሔር ደግሞ የፈጠርኩትን ረሳችሁብኝ በማለት ሊያዝንብን ነው:: በሱፊዝም ፍልስፍና ለዚህ ዓይነቱ ጥያቄ የሚሰጠው መልስ ቢኖር፦ "ጥሩ ጥያቄ የመልስ ያህል ይቆጠራል" የሚል ይሆናል:: □

pdf by @shuktus_books

# “ማንነትን ከማወቅ በላይ እውቀት የለም”

የሰው ልጅ ባወጣው የራሱ የጊዜ ቀመር አዲስ ዓመትና አዲስ ዘመን ውስጥ እንደገባ አድርጎ ራሱን እያደሰ መኖር ከጀመረ አሁንም "በራሱ አቆጣጠር" ዘመናት ተቆጠሩ:: ይኽ ግን "ራስን እንደማታለል" አሊያም "ራስን አለማወቅ" መሆኑን ሱፊዎች ይናገራሉ፡፡ ራስን ማታለልን አስመልክቶ ከሱፊዝም እምነትና ፍልስፍና በመቃረም ለመበተን ወደድሁ::

የሱፊዝም ራስን የማታለል ፍልስፍና የሚጀምረው በምክር ነው፡- "የቱንም ያህል ቢፍጨረጨር የሁንቅላቱን ኋላ (ጀርባ) ማየት የቻለ ሰው የለም:: የሚገርመው ግን የእኛው አካል የሆነው ዓይናችን ሊያየው ያልቻለውን ነገር ሌሎች አይተው ይነግሩናል" ይሉናል:: አንዳንዴ ስለራሳችን ከራሳችን ይልቅ ሌሎች የሚያዩት ይበልጣልን? እንደማለት ነው::

ሱፊዎች ራስን ማወቅ ከሰይፍ ስለት የሰላ ኃይል አለው ይላሉ:: ምክንያቱም እንዲህ ዓይነቱ ዕውቀት ውስጥ ድረስ ዘልቆ የመግባት ብቃት ያለው በመሆኑ ነው:: ራስን በመውደድ እሳት የሚቃጠል ሰው በእሳቱ ብርሃን ውስጥ ራሱን ሲያታልል ይመለከታል የሚባለው ለዚህ ነው:: “ራስን ማታለል የሚጀምረው ራስን አጥብቆ ከመውደድ የተነሳ ከሆነ ራስን መጥላት ባይቻል እንኳን አለመውደድ እንደሚቻል ደግሞ ከጥንቶቹ አስተምህሮት ልንቃርም ይገባል" ይሉናል ሱፊዎች::

“ከእኛ በፊት ኖረው ያለፉት በትምህርታቸውና በምክራቸው ጽፈውልን ያለፉትን ስናገላብጥ የማሰብ ንቃት ጨምረውልንና እንደሚገባንም እንድንመላለስ ቀርፀውን አልፈዋል:: እግርህ ሥር

የሚያደናቅፍህ ድንጋይ ተተምጦ ዓይንህን ከድንጋዩ ለማሸሽ ብትሞክር ራስህን ማታለልህ በትዕበት ይገባሃል:: ድንጋዩ የሚመታው ዓይንህን ሳይሆን እግርህን ነዋ! ብዙዎች ራሰን በማታለልና በመሸንገል መንገድ ሲሄዱ "እውነት" እያሰናከለች ስትጥላቸው የምንመለከተውም ለዚህ ነው:: የጠቢብ እጅ የያዘ ተማሪ አስተድጥ እንዳይሰናከል ጠቢቡ ያስተምረዋል፣ አላዋቂነቱ አይሎበት ቢሰናከል ደግሞ እንዴት እንደሚነሳ አሁንም ያስተምረዋል" ይላሉ::

እውነተኛ አስተማሪ በምትሄድበት መንገድ መምራት ብቻ ሳይሆን ከእሱ የተሻለ ርቀት እንደት መጓዝ እንደምትችልም ያሳይሃል:: ይኸ ደግሞ ማንነትን ገልፆ የማሳየት ጥበብ መሆኑን ሱፊዎች ይናገራሉ:: "ማንነትን ከማወቅ በላይ እውቀት የለም" የሚሉት ሱፊዎች "አውቃለሁ በማለት ከሚመፃደቀው ይልቅ አለማወቁን የተረዳው እሱ ታላቅ ጠቢብ ነው" ይላሉ:: ምክንያቱም አህያ የቱንም ያህል መጽሐፍ ቢጭኗት አህያነቷ አይቀርምና:: ቁምነገሩ መጽሐፍን ማንበቡ ሳይሆን ባነበቡት ላይ ተመስርቶ የባህርይ ለውጥ የማምጣቱ ጉዳይ ነው:: በዚህ ረገድ ከሱፊዝም ወጎች አንዳንዶቹን እንቀንጭብ፡-

አንድ ቀን ናስሩዲን እግሩ ላይ መጽሐፍ አስሮ በመንገድ ሲሄድ የተመለከተው ጓደኛው ወደ እሱ ጠጋ ብሎ "እግርህ ላይ መጽሐፍ አስረህ የምትሄድ ምን ሆነህ ነው?" በማለት ቢጠይቀው 'እንዳይጠፋብኝ!" ሲል ይመልስለታል::

ከድርጊቱ ይልቅ በመልሱ የተገረመው ጓደኛው "ነገር ግን በእግርህ ላይ ካሰርከው ልታነበው አትችልም እኮ?" በማለት መልሶ ቢጠይቀው ናስሩዲንም "ከጠፋብኝም እንዲሁ ላነበው እንደማልችል አታውቅም?" በማለት መለሰለት:: የናስሩዲን መንገድ ከአህያዋ መንገድ ጋር ተመሣሣይ ሆነብኝ:: ልዩነታቸው ናስሩዲን የተሸከመውን ማወቁ ሲሆን አህያዋ ደግሞ አለማወቋ ይሆናል::

የሰው ልጅ ባህርይ አራት መገለጫዎች እንዳሉት ሱፊዎች ይነግሩናል:: የመጀመሪያው ከፈጣሪ ጋር፣ ሁለተኛው ከራሱ ጋር፣ ሦስተኛው ከሰዎች ጋር ሲሆን የመጨረሻውና አራተኛው ደግሞ

ከዓለም ጋር ነው። ከፈጣሪ ጋር የሚኖረን የባህርይ መገለጫ በሰባት መርሆዎች ላይ መመስረቱን የሚነግሩን ሱፊዎች እነሱም፡- የሚገባውን መስጠት፣ ልኩን ማወቅ፣ ስለስጦታው ማመስገን፣ ሕጉን መቀበል፣ በፈተናዎቹ መታገስ፣ ታላቅነቱን ማሰብ እና እሱን መሻት ናቸው። ከራስ ጋር የሚኖረን መገለጫም እንዲሁ ሰባት መርሆዎች አሉት ይሉናል - ፍርሃትን ማስወገድ፣ ለበጎ ነገር መጣር፣ ክፉን መቋቋም፣ ለመንፈሳዊ ሕግጋት መገዛት፣ ሐቅና ቅንነትን መከተል፣ ራስ ወዳድነትን ማራቅና በድህነትም ውስጥ ቢሆን እነዚህን ጠብቆ መኖር ናቸው።

የሰው ልጅ ባህርይ ሦስተኛው መገለጫ በሆነውና ከሰዎች ጋር ሊኖረን በሚገባው ባህርይ የሚገኙት ሰባት መርሆዎች ደግሞ ቻይነት፣ ይቅር ባይነት፣ ትህትና፣ ለጋስነት ርህራሄ፣ መልካም ምክር፣ ፍትሕና ሚዛናዊነት ናቸው።

አራተኛው ከዓለም ጋር የሚኖረን ባህርይ ሰባቱ መርሆዎች ደግሞ ኑሮዬ ይበቃኛል ማለት፣ ከማናገኘው ይልቅ የምናገኘውን መምረጥ፣ አስቀያሚ የሆነውን ነገር መጣል፣ የተትረፈረፈውን ነገር መጥላት፣ መታቀብን መምረጥ፣ በዓለም ክፉ የሆነውን ነገር ማወቅና መሻቱንም ማስወገድ እንዲሁም ክፉው ነገር እንዳይሰለጥንብን መቃወም ናቸው። በእነዚህ ዙሪያ ለዘመኑ የሰው ልጅ ባህርይ ይጠቅማሉ የምላቸውን በሱፊስቶች ወግ ላይ ተመስርቼ ልገፋባቸው ወደድሁ።

አንድ ቀን ሱፊው ጁናይድ በመንገድ ሲሄዱ አንድ ሰው አስቁሞ "አምላካዊ ትዕዛዝን የሚያውቅ እውነተኛ ጓደኛ ከየት ማግኘት እችላለሁ?" በማለት ጠየቃቸው። ጁናይድም ጥቂት አሰቡና "መከራህን የሚሸከምና ፍላጎትህን የሚያሟላ ጓደኛ የምትሻ ከሆነ አታገኝምና ባትለፋ ይሻላል። መከራውን ተሸክመህ ፍላጎቱን ለማሟላት የምትሻው ጓደኛ ፈልገህ ከሆነ ግን ብዙ ሺህዎችን ላስተዋውቅህ እችላለሁ" አሉት። ይኸች ጨዋታ የሱፊው መምህር የአል-ጋዛሊ ነበረች። ከአል-ጋዛሊ ጨዋታ እንደጋግም፡-

አንድ ቀን የእምነት አባት አብርሃም በመንገድ ላይ ያገኘውን አንድ

ጎረቤቱን ቤቱ፡ መጥቶ እራት እንዲጋብዝ ይነግረውና ያልፋል:: ታዲያ የዚያን ቀን አብርሃም በሄደበት ቦታ የጋበዘው ሰው አመንዝራና ጠጪ መሆኑን ከሌሎች ይሰማል:: እንዲህ ዓይነቱን ሰው በቤቱ መጋበዙ የቆጨው አብርሃም የራት ሰዓት ሲደርስ በሩን ከውስጥ ጠርቅሞ ይቀመጣል:: ጎረቤቱም የአብርሃም ቤት በር መዘጋቱን ተመልክቶ እያዘነ ተመልሶ ይሄዳል:: በዚህ ቅጽበት ግን የእግዚአብሔር ድምጽ ወደ አብርሃም ይመጣል፡- "ወደ አንተ ለእራት መጥቶ የነበረው ሰው ሰባ ዓመቱ መሆኑን ታውቃለህ?" በማለት እግዚአብሔር አብርሃምን ጠየቀው:: አብርሃምም በመንቀጥቀጥ እንደማያውቅ መለሰለት:: እግዚአብሔርም "አንተ ለአንድ ቀን ልትመግበው የተፀየፍከውን ሰው እኔ ግን ለሰባ ዓመታት ሳይሰለቸኝ መግቤዋለሁ:: የእሱ ኃጢአት ከእኔ ይልቅ ለአንተ በልጦ የተሰማህ በምን ምክንያት ይሆን?" በማት ጠየቀው:: አብርሃም በሥራው ተፀፀተ:: (ይኸም ጽድቅ ሆኖ እንደተቆጠረለት ግን የማውቀው ነገር የለም)::

"ክፋትና ትዕቢት በሰው ልጅ ላይ በሦስት ምልክቶች ይገለፃሉ" ይሉናል ሱፊዎች:: እነሱም፡- ብቻውን ሲሆን በሚያዝንና ከሰዎች ጋር ደግሞ ሲሆን በሚደሰት፣ ሰዎች ሲያመሰግኑት አምላኩን በሚያመሰግን፣ እንዲሁም ሌሎች ሰዎች ስለ እሱ ክፉ ሲናገሩ አምላኩን በሚረሳ ሰው ባህርይ ውስጥ ነው ይላሉ:: ይኸ ሃሳብ ወደ አል-ጋዛሊ ይመልሰናል::

"እንዳንዶች" ይላሉ አል-ጋህዛሊ "በሕግ ከቁጣ፣ ስስትና፣ ግብዝነት እንድንታቀብ ታዟል ይላሉ:: ከእነዚህ ለመታቀብ ግን ፈጽሞ አንችልም:: ምክንያቱም አብረው በውስጣችን የተፈጠሩ ነገሮች በመሆናቸው ነው:: ጥቂቱን ነቅ አድርጉ የሚል ትዕዛዝ የለምና:: ብዙዎች እነዚህ ተግባራት በሕግ ነቅለን እንድንጥላቸው የታዘዙ ይመስላቸዋል:: ነገር ግን ሕግ የሚያዘን ልጓም በማበጀት እንድንቆጣጠራቸው ነው:: ታላላቁን ኃጢአት ብቻ ታስወግድ፣ ለትንንሾቹ ደግሞ ይቅርታን ታገኛለህ" ይሉናል::

ሌላ የሱፊ ጨዋታ እናምጣ፡- አንድ በሃይማኖቱ ጠንካራ የተባለ ሰው ኢየሱስን ተከትሎ በጎዳና ላይ ይጓዛል:: ይኸን የተመለከተና

በሌብነቱ ሃገር ያወቀው ሰው "ምናልባት ከዚህ ሃይማኖተኛ አጠገብ ሂጀ ብቆም እግዚአብሔር ለእሱ ሲል አብሮ ይቅር ይለኛል" በማለት አሰበና ተጠግቶ መንገዝ ጀመረ:: ጥቂት እንደተጓዙም ሊባው ያሳለፈውን ቆሻሻ ሕይወት እያሰበ መፀፀትና ራሱን መውቀስ ይጀምራል:: በዚህ ወቅት ሃይማኖተኛው በአጠገቡ የቆመውን ሊባ ይመለከትና ምናልባት ጥላዬ ሲያርፍበት እኔም አብሬ እረክሳለሁ የሚል ስሜት ያድርበታል:: ወዲያውም ሊባው ከአጠገቡ እንዲርቅ ይጮኸበታል:: ይኸን የተመለከተው ኢየሱስ "እነሆ የሃይማኖተኛው መልካም ምግባርና የሊባው ኃጢአት በዚህ ቅጽበት እኩል ታጠበ:: የሃይማኖተኛው መልካም ምግባር የታጠበው በትዕቢቱ ሲሆን የሊባው ኃጢአት ደግሞ በትህትናው ምክንያት ነው:: ሁለቱም ከዛሬ ጀምሮ አዲስ ጉዞ ይጀምራሉ" አለ::

ሱፊዎች ራስን ስለማታለል ወይም ራስን ስለማወቅ ሲነሳ የሚሰነዝሯት አንዲት ምክር አለች፡- "ፈረሱ ከተሰረቀ በኋላ የጋጣውን በር መዝጋት ጥቅም የለውም:: እንዲሁም የሰው ልጅ እኪያረጅ ጠብቆ ንስሐ ለመግባት መሞከሩ በከንቱ ያባከነውን ጊዜ በእርጅናው ለመመለስ የመፀፀት ያህል ነው:: በስተርጅናህ "ዓለም ከንቱ ናት፣ አሁን እግዚአብሔርን አገኘሁ" ብትለው ምን ጥቅም አለው? በምድር ላይ የሰው ልጅ ለሚሰራቸው ኃጢአቶች በሙሉ ምህረት ቢኖረው እንኳን ጊዜውን በከንቱ ላባከነ ኃጢአተኛ ግን ፍፁም ምህረት የለውም" ይላሉ::

በሱፊው መምህር በአቡሻንጃ ምክር እንለያይ፡- "አንድ ኃጢአት ፈፅመህ የኃጢአቱ ደስታ ተከትሎህ ካልሄደ ያ ንስሐ ማለት ነው:: ኃጢአትን ከመሥራትህ በላይ የሚጎዳህ የኃጢአቱን ደስታ እያሰብክ መኖር የጀመርክ ቀን ነው:: ግላህ የፈፀመው የጥቂት ሰዓታት ኃጢአት ደስታው ሲያልፍ የሚቀር ሆኖ ሳለ ልብህና አእምሮህ እሱን እያኘክ ከኖረ በእርግጠኛነት ፍፃሜህ ገሃነም ነው" ብለዋል:: ‹‹የሰሩትን ኃጢአት እንደማሰብ ትልቅ ኃጢአት የለም›› ማለታቸው መሰለኝ:: □

# "ገነት - በተሰጠኝ ሕይወት የምትኖርበት እንጂ ስትሞት የምትሄድበት አይደለም"

በዓለማችን ላይ ሁለት ዓይነት አመለካከቶች መስፈናቸውን ስንረዳ እነዚህ አመለካከቶችም በሰው ልጅ ዕድገት ሰፊውንና ትልቁን ቦታ ይዘው እናገኛቸዋለን:: የመጀመሪያው አስተሳሰብ "ገነት ከዚህ ዓለም የተለየና ከሞት በኋላ የምንሄድበት ቦታ ነው" ሲሉ ሌላው አስተሳሰብ ደግሞ "የለም! ገነት ማለት ይሄ ምድርና በተሰጠኝ ሕይወት የምትኖርበት ቦታ እንጂ ስትሞት የምትሄድበት አይደለም" ይላሉ::

እንደሱፊዎች ደግሞ "ይኸ ዓለም ገነት ሊሆን ይችላል" ይላሉ:: "ስናፈቅርበት፣ ስንባርክበት፣ ስናገለግልበት፣ እንዳችን የሌላችን ዕድገት መሰላል ስንሆንበትና ሌሎችንም ስናድንበት... ያን ጊዜ ምድር ገነት ትሆናለች::... በእርግጥ ይኸ ዓለም ገሃነም ልናደርገው እንደምንችል ደግሞ መዘንጋት የለብንም:: መከራ፣ ክፋት፣ ጥላቻና ጥፋት ሲሞላብን... ዓለም ገሃነም ትሆናለች" ይላሉ:: ለዚህም ነው ምድር የገነት አበባ መትከያና የገሃነም እሳት መሞቂያ ነች የምትባለው:: በሱፊዎች ጉዞ ቀጥለን ዓለምን በመለኮታዊ መስታወት ደግሞ እንመልከታት::

ለሱፊዎች የእግዚአብሔር መገኛ ይኸ ዓለም ነው:: ብዙዎች ይኸን ዓለም በሰውና በእግዚአብሔር መካከል እንደመጋረጃ ያስተምሩታል:: ሱፊዎች ደግሞ "ዓለምን በእኛና በእግዚአብሔር መካከል እንደመጋረጃ ያስተምሩነው እኛው ነን" ይሉናል:: በዓለም ውበት መደነቅ ስትጀምር በተዘዋዋሪ የምታደንቀው ፈጣሪውን ነው:: ለዚህ እንደማብራሪያ የምታግዘን እንዲት የሱፊዎች ተረት አለች::

አንድ ጠያቂ የሱፊውን መምህር ሙባፊርን በዓይናቸው

የማያዩትን ነገር "አምላኬ ነው" በማለት እንዴት ሊያመልኩት እንደቻሉ ጠየቃቸውና እንዲህ ሲሉ መለሱለት፡- "በበረሃ ስትሄድ የግመል ዱካ በረዥሙ ተዘርግቶ ብታይ በዚያ ቦታ ግመል ማለፉን ትጠራጠራለህን!" አሉ:: ጠያቂውም "ዱካውን ካየሁማ እንዴት እጠራጠራለሁ!" አለ:: መምህሩም "እንግዲያውስ የአምላካችን ዱካዎች ደግሞ እኛ ብሎም ይኸ ዓለም ነውና ለእምነቴ የግድ እሱን ማየት የለብኝም" አሉት::

እንደሱፊዎች እምነት ይኸ ዓለም ለእኛ እንደመስታወት ነው:: ውድቀታችንንም ይሁን ዕድገታችንን በመለኮታዊ መስታወት ግልፅ ብሎ ይታየናል:: ለዚህም ነው ሱፊዎች፡- "የእኛ ሥራ ይኸን መለኮታዊ መስታወት ዕለት ዕለት መወልወል ነው:: በዚያ መስታወት እያንዳንዱ ሥራውን በግልፅ እንዲያየው እናደርጋለን" ይላሉ::

ሌላው የሱፊ መምህር ጃሚ ሲናገሩ "በዓለም ላይ ውብና ፍፁም የሆነን ነገር ስትመለከት በእርግጥ የአምላክን ምልክት ማየትህን አትጠራጠር" ይላሉ:: "አንድ የተዋበ ፍጡር በምድር ላይ ስታይ ከሰፊው የእግዚአብሔር የአትክልት ቦታ አንዲት ፅጌሬዳ ፈንድታለች ማለት ነው" በማለት እናስታውሰው ዘንድ የተገባ ነገር አክለው ይነግሩናል፡- "አስታውስ! አንድ የተዋበ ምስል ሲወይብ ወይም አንድ አበባ ሲረግፍ ብትመለከት ያን ጊዜ በመለኮታዊው መስታወት ላይ ወጥቶ የነበረው ብርሃን በጨለማ ተጋርዷል ማለት ነው" ብለዋል:: ለዚህም ነው የብርሃኑ አመንጪ ብቻ ዘላለማዊ ነው የምንለው:: ጃሚ ይመክራሉ፡- "ታዲያ ዛሬ ታይቶ ነገ በሚጠፋ ነገር ላይ ለምን ታተኩራለህ? ይልቁንስ ወደምንጩ ተጠጋና ዘላለማዊውን ብርሃን ለማግኘት ሞክር::"

በዚህ ምድር የምታየው ነገር ሁሉ እውነተኛ መገኛ መለኮታዊው ዓለም መሆኑን ሱፊዎች ያምናሉ:: እኛ እንዲሁም በዚህ ዓለም ያለው ነገር ሁሉ የመለኮታዊው ዓለም ነፀብራቅ መሆኑ ነው:: ለዚህም ሳይሆን ይቀራል በዓለም ላይ የምናየው፣ የምንሰማው፣ የምናደንቀው፣ የምንወደው... ነገር ሁሉ ሲያልፍ የምናየው? እንዳችም ነገር ፀንቶ

ባለማየታችን እውነታው በሌላ ዓለም መገኘቱን እንድናስብ ዘንድ የግድ ይለናል:: "የሚያልፈው እውነት በሌላ ዓለም ከተገኘ እሱ በእርግጥ ዘላለማዊ ነው" የሚሉን ሱፊዎች በሩሚ ተረት ይኸንኑ ያጠናክሩልናል::

አንድ ቀን ታላቁ የቻይና ንጉሥ በፊቱ ጠቢባን ነን የሚሉ ወደ እሱ እንዲመጡ ባዘዘ ጊዜ የቻይና ጠቢባንና የግሪክ አዋቂዎች በፊቱ ቀረቡ:: ቻይናውያኑ ጠቢባን፡- "ታላቅ የሆነ ውበትን መፍጠር እንችላለን" ሲሉ ግሪካውያኑ አዋቂዎች ደግሞ፡- "እኛ ግን ታላቅ የሆነ ውበትን ማሳየት እንችላለን" አሉት:: ንጉሡም የሁለቱም ሃገር ጠቢባን ትይዩ የሆነ ክፍል ውስጥ ተቀምጠው ሥራቸውን እንዲሠሩና ይኸንኑም ውበት ፈጥረው እንዲያሳዩት አዘዛቸው:: ቻይናውያኑ ጠቢባን ለሥራቸው የተለያዩ ቀለማትና ብሩሾች እንዲሰጣቸው በጠየቁት መሠረት ንጉሡ ፈቀደላቸው:: ግሪካውያኑ የጠየቁት ቢኖር መስታወትና የመስታወት መወልወያ ጨርቆችን ብቻ ነበር:: እነሱም የተፈቀደላቸውን ይዘው ወደክፍላቸው ገቡ:: ከጥቂት ቀናት በኋላ ንጉሡ በቅድሚያ ወደ ቻይናውያኑ ክፍል ሲገባ በተመለከተው ድንቅ የአሳሳል ችሎታና ውበት እጅግ ተመሰጠና አድናቆቱን ገለፀላቸው:: ወደግሪካውያኑ ክፍል ሲገባ የተመለከተው ግን ይበልጥ ለመናገር እስኪቸግረው ድረስ የሚደንቅ ሆነበት:: ይኸውም ግሪካውያኑ መስታወቱን መልውለውና በግድግዳ ላይ በቅርፅ በቅርፁ አስቀምጠው ከፊት ለፊታቸው በሚገኘው ክፍል በቻይናውያኑ የተሠራውን ስዕል መልሶ እንዲያንፀባርቅ አድርገውት ነበር::

ንፁህ ልብም እንዲሁ ውበትን ከሚታየው በላይ አስውቦ የማሳየት ብቃት አለው:: ምነው ቢሉ የፍጡራን ሁሉ መለኮታዊ መስታወት ልባቸው ነውና:: ስለዚህም የተዋበውን የፈጣሪን ሥራ ታንፀባርቅ ዘንድ የልብህን መስታወት ከፊት ለፊት አስቀምጠው::

በመለኮታዊ መስታወት ማየት ስትጀምር ምልከታህ ሁሉ የተለየ ይሆናል:: ሱፊው ኢብን አል-ኢማድ አንድ ቀን በእጃቸው አንዲት እንስሳ እንጠለጠለው ሲሄዱ የተመለከተ ወዳጃቸው፡- "ኢብን ሆይ!

በእጅህ ያንጠለጠልከው እንስሳ የረከሰና አንተንም የሚያረክስ መሆኑን አታውቅምን?" ይላቸዋል::

ኢብንም፡- "ወዳጄ ሆይ! ለመሆኑ ይኸን እንስሳ ማን ፈጠረው?" ይሉታል::

እሱም፡- "የፈጠረውማ እግዚአብሔር ነው" በማለት ይመልሳል::

ኢብን ይኸን ሲሰሙ፡- "እንግዲያስ እግዚአብሔር ርኩስ ነገር ይፈጥራል እያልከኝ ነው?" በማለት መንገዳቸውን ቀጠሉ:: በመለኮታዊ መስታወት ስትመለከት የረከሰ ምንም ነገር አይገኝም::

አብዛኛው የሱፊ ተረት ወዳገኘንባቸው ወደሼኽ ሙዛፈር እንለፍ:: ሼኽ ሙዛፈር በአብዛኛው ተረታቸው ዋነኛው ገፀ-ባህርይ (ጠቢቡ) ሞኙ ባህሉል ነው:: ባህሉል አንድ ቀን ንጉሡን ሀሩን አል-ራሺድን ለማግኘት ችቦ ለኩሶ ወደ ቤተመንግሥታቸው ይሄዳል:: ለረዥምም ቀናት ጠፍቶና ሳያዩት የከረመው አሽሟጮቻቸው ባህሉል ሲመጣ ተመልክተው ንጉሡ ሲደሰቱም በእጁ በእሳት የተቀጣጠለ ችቦ ይዘው ቢመለከቱ ደግሞ መልሰው ደነገጡ:: "ባህሉል! የት ጠፍተህ ከረምህ?" የሉታል::

ባህሉልም፡- "ንጉሥ ሆይ! ገሃነም ሄጄ ነበር" ይላቸዋል::

በባህሉል መልስ ፈገግ ያሉት ንጉሥ፡- "ታዲያ በእጅህ የያዝከው እሳት ከዚያ የመጣ መሆኑ ነው?" ይሉታል::

"የለም ንጉሥ ሆይ! በገሃነም እሳት ስለሌለ እንድለኩስ መልሰው ወደምድር ልከውኝ ነው" ይላል::

ንጉሡም፡- "በገሃነም እሳት የለም እንዴ?" በማለት ተደንቀው ቢጠይቁት ባህሉልም፡- "ንጉሥ ሆይ! እያንዳንዱ ሰው የራሱን እሳት እየለኮሰ በመያዝ ወደ ገሃነም ይገባል እንጂ በዚያ የተዘጋጀ እሳት የለም" በማለት መለሰላቸው:: በመለኮታዊ መስታወት የገሃነም እሳትም እንዲህ የተለየ ነው... ያቃጥላል እንጂ አይለኮስም::

ወደ አል-አጃሚ ተረት ደግሞ እንንገርና በመለኮታዊ መስታወት መታመን (እምነት) የቱን ያህል እንደሚሄድ እንመልከት፡፡

ሀቢብ ከላያቸው ላይ ወልቆ የማያውቅ አንድ ካባ ነበራቸው:: በዚህ ካባቸውም ሃገሬው ሁሉ ስለሚለያቸው እንደመታወቂያ ሆኖላቸው

ነበር:: አንድ ቀን ሀቢብ ይኸን ከባ መንገድ ላይ ጥለው ወደ መስጊድ ይገባሉ:: ካባው በወደቀበት መንገድ ያልፍ የነበረው ታላቁ የሃይማኖት መሪ ሀሰን አል-ባስሪ የወደቀውን ካባ ሲመለከት የማን መሆኑን ለመለየት አፍታም አልፈጀበትም:: ስለዚህም ከካባው ጋር ቆሞ በሌባ እንዳይወሰድ በመጠበቅ የሀቢብን መመለስ መጠባበቅ ጀመረ:: ሀቢብ ከመስጊድ ወጥተው ሲመለሱ ሀሰን ከካባቸው አጠገብ ቆሞ ሲጠብቅ አገኙት:: ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ "ሀሰን ሆይ! መንገድ ዳር ቆመህ ምን ታደርጋለ?" ይሉታል::

ሀሰንም "ካባዎ ከመንገድ ዳር ወድቆ በመመልከቴ ሌላ ሰው እንዳያነሳው እየጠበቅሁልዎት ነው:: ለመሆኑ ካባዎን መንገድ ዳር ጥለው የሄዱት ማን እንዲጠብቅልዎ ታምነው ነው?" በማለት ጠየቃቸው::

ሀቢብም፡- "ካባዬን እንድትጠብቅ አንተን የላከህን ነዋ! ሌላ ማንን እታመናለሁ?" አሉትና ካባቸውን ደርበው ወደቤታቸው አቀኑ::

በሱፊዝም እምነት መለኮታዊ መስታወት የማያሳየው ነገር የለም:: ስለሰንፍና ኢብን አራቢ የተረቱትን ደግሞ እንመልከት:: አንድ ቀን ካሊፍ አማር በእግር ሲጓዙ በአንድ ቦታ ጉረምሶች ሥራ በመፍታት ተሰብስበው ሲያወሩ ተመለከቱና፡- "ለመሆኑ እናንተ ማን ናችሁ?" ይሏቸዋል:: ጉረምሶቹም፡- "እኛማ ጉዳያችንን ሁሉ በፈጣሪ እጅ አስተምጠንና እሱን አምነን ተዓምራቱን የምንጠብቅ ነን..." ይሏቸዋል:: ይኸን የሰሙት አማር፡- "በእርግጥ እናንተ እንደዚያ አይደላችሁም:: ነገር ግን የምድር ትሎችና ሸክሞች ናችሁ... በአምላኩ በእውነት የታመነ ሰው በተፈጠረበት ምድር ዘርን ዘርቶ የማብቀሉን ድርሻ ደግሞ ለፈጣሪው የሚተው ነው" በማለት ገሰፆቸው ሄዱ::

በሱፊዎች እምነት ለመልካም ሥራህ ከሰው ልጅ ምስጋና አትሻም:: "የመልካም ሥራህ ደመወዝ ሁሉ በአምላክ ይከፈልሀ ዘንድ ለእሱ ተውለት እንጂ መልካም ያደረግኸለት ሰው ለሥራህ አንተን ማመስገንና ማወደስ ከጀመረ እምላክህ ሊከፍልህ ያዘጋጀውን ደመወዝ ግማሹን አስቀድሞ ከፈለህ ማለት ነው" ይላሉ:: □

# “የምታውቀውን ሳትፈፅም የማታውቀውን ለምን ትሻለህ?”

የሱፊዝም እምነትና ፍልስፍናን በቃኘንባቸው ቀደምት ምዕራፎች ሱፊዝም የእስልምና መንፈሳዊ ኃይል መሆኑን ቃኝተን ነበር:: ሱፊዎች እያንዳንዱ ግድት የእስልምና እምነት ተከታይ የፈጣሪን ዓይን ማየት እንደሚችል አምነው "እኛ ግን እስከዚያው ትዕግስቱ የለንም፣ ፈጣሪን ዛሬና በየዕለቱ ማየት አለብን" የሚሉ ናቸው:: ይኸም በሕይወታቸው ይፈፀም ዘንድ የሚጠበቅባቸውን ሁሉ ለመክፈል የተዘጋጁ ሆነው እናገኛቸዋለን::

በሱፊዝም እምነትና ፍልስፍና ‹‹ጥበብ›› እንዴት እንደምትቃኝ ለማየት ጉዞአችንን ስንጀምር ደግሞ አዘውትረው የሚናገሯትን ጥበባዊ ንግግር መነሻችን በማድረግ ይሆናል:: "ሁላችንም ራሳችንን ጥበበኛ አድርገን ከማሰብ የበለጠ የሚያስደስተን ነገር አይኖር ይሆናል:: ለዚህም ነው ሕይወታችን ከስህተቱ ለመላቀቅ ሲሳነው የሚስተዋለው:: ስህተቶቻችንን አጥርተን ማየት ሳንጀምር ጥበብን እንዴት እናስተውላት ዘንድ ይቻለናል? ለዚህም ነው ትህትናና ራስን ማወቅ የጥበብ መጀመሪያ ናቸው የምንለው" ይሉናል::

ሱፊዎች ትህትናና ራስን ማወቅ ግን የጥበብ መጀመሪያ እንጂ መጨረሻ ናቸው አይሉንም:: ነገር ግን ጥበብ በተግባር እስካልተገለጠ ድረስ ተከማችቶ የተቀመጠ እውቀት ነው ይሉታል:: ለዚህም ነው "እህያ የቱንም ያህል መጽሐፍ ብታሸክማት አህያነቷ አይቀርም " የሚሉት:: ነገር ግን እውቀታችንን በተግባር ስንገልጠው ያን ጊዜ ለጥበብ በራችንን ከፍተናል ማለት ይሆናል:: ከሱፊዝም መሪዎች አንዱ ሼክ ሳፊር ሲናገሩ፡- "ስለሱፊዝም ብዙ አውቃለሁ ማለት አልችልም፣ የማውቃትን ያህል ግን በፍቅር ተማርኳት፣ እነሆ ላለፉት

አርባ ዓመታትም በተግባር እየተረጎምኳት አገኛለሁ" ብለውናል:: የጠቢባንን ቃል ሰምተን በእነሱ የጥበብ መንገድ መጓዝ ብንጀምር እኛስ ጥበበኛ መሆናችንም አይደል?

አንድ ታላቅ ንጉሥ በሃገሩ የሚገኙ ጠቢባንን ሁሉ በዙሪያው እንዲሰበሰቡለት አዘዘ:: ጠቢባኑ በዙሪያው ተሰባስበው ሲያበቁም፣ - "በውስጤ መረጋጋትን የሚሰጠኝን ቃል ከእናንተ እሰማ ዘንድ እሻለሁ:: ይኸ ቃል ሳዝን ደስታን የሚፈጥርልኝ፣ ስደሰት ደግሞ ሐዘኔን የሚያስታውስ ይሁን:: ይኸን ቃል ፈጥናችሁ ትነግሩኝ ዘንድ አዝዣለሁ፤ ከእኔም ጋ ለዘላለም ኗሪ ይሆናል" አላቸው::

ብዙዎቹ ጠቢባን ያመጡት ምክር በንጉሡ ዘንድ አልተወደደምና ንጉሡ መከፋት ጀመረ:: ይኸን ያስተዋለ አንደ ጠቢብ ሱፊ ግን ወደንጉሡ ተጠጋና፡- "ንጉሥ ሆይ! ለዘላለም የሚጠቅምህን ምክር አገኝሁልህ" አለው::

ንጉሡም ለመስማት በመጓጓት "እስቲ ንገረኝ" ይለዋል::

ጠቢቡም "ንጉሥ ሆይ! ስታዝን 'ይኸም ያልፋል' ትላለህ" አለው::

ንጉሡም "ስደሰትስ?" አለው::

"ስትደሰትም 'ይኸም ያልፋል' ትላለህ:: ያን ጊዜ ዘላለማዊ የሆነው ነገር ብቻ ያስጨንቅህ ይጀምራል" ብሎት ሄደ::

በጥበብ መንገድ ላይ መሆናችንን ሳንዘነጋ ወደ አሊ ራሚኒ ደግሞ እንለፍ:: አሊ ራሚኒ ጥበብ የሚሻ ሰው በመንገድ ላይ ያገኙና አድራሻዋን ነገሩት፡- "ጥበብ በባህር ውስጥ የምትገኝ ዕንቁ ናት:: እሷን ማግኘት ብትሻ አስቀድመህ ያለህበትን በረሃ ጥለህ ወደባህሩ ተጓዝ:: ባህሩን አግኝተህ ዕንቁዋን (ጥበብን) ማግኘት ቢያቅትህ እንኳን መገኛዋን ባህሩን አግኝተሃልና በዚያ ደስ ይልሃል" አሉት::

በጥበብ ጉዳይ ‹‹ሞኙ›› ናስሩዲንም ይነሳል:: አንድ ቀን በአደባባይ ተሰብስበው በሞኝነቱ ለሚስቁበት ሰዎች እንዲህ የሚል ጥያቄ ሰነዘረ፡- "ወዳጆቼ! እውቀትን ያለችግር፣ እውነትን ያለሐሰት፣ ስኬትን ያለጥረት፣ እድገትን ያለመስዋዕትነት... ትፈልጋላችሁን?"

ሕዝቡም በአንድ ቃል፡- "እንፈልጋለን!" በማለት ጮኹ::

"እንግዲያውስ ጥሩ ነው! እኔም ይኸንኑ ስለምፈልግ ያገኘሁት

ቀን እንገራችኋለሁ…" በማለት ተሰናብቷቸው ሄደ።

ወደ ራቢዓ ደግሞ እንሻገር። ራቢዓ አንድ ቀን በመንገድ ላይ ሲጓዙ በላዩ ላይ ጽሑፍ የተቀረፀበት ድንጋይ ይመለከቱና ተጠግተው ሲመለከቱት "ከጀርባ የተፃፈውን ተመልከት!" የሚል አነበቡ። ከድንጋዩ ጀርባ የተፃፈውን ለማንበብ ተጣድፈው ሲዞሩ "የምታውቀውን ሳትፈፅም የማታውቀውን ለምን ትሻለህ?" የሚል ተፅፎ አገኙበት።

ራቢዓ ሌላም ታሪክ አላቸው። አንድ ኸሊማሳ ወደ እሳቸው ዘንድ ይመጣና ስለመቀደስ ይጠይቃቸዋል።

ራቢዓም፡- "ቅድስናን ከፈለግኸት ልብህን ወደ ሕፃናት ልብ ቀይረው" ይሉታል።

ኸሊማሳውም "ለምን?" በማለት ይጠይቃል።

"ሕፃናት አምስት መልካም ነገሮች በልባቸው እንዳሉ አታውቅምን?" አሉና ራቢዓ ዘረዘሩለት፡- "ሕፃናት ስለዕለት እንጀራቸው አይጨነቁም፤ ሕመም ሲሰማቸውም ቀንና ሌሊት ስለመጥፎ ዕድላቸው አያንጐራጉሩም፤ በእጃቸው የያዙትን ምግብ ሁልጊዜ ያካፍላሉ፤ ሲጣሉ ቂም በልባቸው አያሳድሩም (ይረሱታል)፤ እንዲሁም ጥቃቅኑ አደጋና ማስፈራራት ሁሉ ያስፈራቸዋል፤ ዕንባ በዓይናቸው እንዲሞላም ያደርጋል" በማለት መለሱለት።

የሱፊዎችን ተደጋግሞ ቢነገርና ቢሰማ የማይሰለቸውን ወጋቸውን መቅዳትስንቀጥል ሼህ ሙዛፈር ወዳሜዉቱን ቁምነገር ደግሞ በመዘር ነው። ዝናቸውና ችሎታቸው በምድሪቱ ላይ የናኘ የአንድ ታላቅ ሼኽን ዝና የሰማ በሀብት የናጠጠ ሱልጣን አንድ ቀን ሼኹ ወደሚያስተምሩበት ቤት ይመጣና የፈጣሪን ስም ጠርቶ እንዲያስተምሩት ይማፀናቸዋል። ሼኹም ይፈቅዱና ሱልጣኑ እየተመላለሰ ሲማር ቆይቶ አንድ ቀን፡- "አባክዎን! ትምህርትዎንም ሆነ ምግባርዎን ከልቤ ወድጃለሁና በሥልጣኔና በሀብቴ ላደርግልዎት የምችለው ነገር ካለ ይንገሩኝ" ይላቸዋል።

ሼኹም ጥቂት አሰቡና፡- "ሱልጣን ሆይ! ሊታደርግልኝ የምትችለው አንድ ነገር ብቻ ነው" ይሉታል። □

ሱልጣኑም በጉጉት የሼኹን ጥያቄ መጠበቅ ቀጠለ፡፡
"እባክህ ከዛሬ ጀምር ወደዚህ አትምጣ" አሉት::
የሱልጣኑ ድንጋጤ አይነገርም፡- "ምን አጠፋሁ?" ይላቸዋል::
ሼኹም፡- "አንተስ የአጠፋኸው ነገር የለም:: ነገር ግን ተማሪዎቼ አንተ ወደዚህ ቤት መምጣት ከጀመርክበት ቀን አንስቶ አስተድዋ ዓይናቸውን ከማሰብት ከፈጣሪ ላይ አንስተው ወደአንተ ሲመልሱ በማየቴ አዝኜ ነው:: ለማንኛውም በመካከላችን የአንተን ሕልውና ለመሸከም ብርቱ ያለው ለጊዜው ባለመኖሩ ባትመጣ እመርጣለሁ" አሉት::

ለዚህም ነው በሱፊዎች እምነት "ከዓለም ሀብት ጋር ራሱን ያጣመረ እውቀቱን ያጠፋል፤ ከብዙ ሰዎች ጋር የተወዳጀ እሱ ብቸኛ ነው፤ በሥራ ብቻ የተጠመደ ሰው እሱ ሌላ ነገር ለማሰብ ጊዜም አይኖረውም፤ ከፈጣሪው ጋር የተወዳጀ ግን እሱ ታላቅ ሀብረትን የፈጠረ ነው" በማለት ሲመከሩ የምንሰማቸው::

ኢሻይር የሱፊዝም መምህር ናቸው:: የእሳቸውንም ምክር ለጠቢባን ጆሮ ማድረስ የተገባ ነውና እንዲህ እናቅርበው፡- "ብዙ ሰዎች ስለሀብትና ድህነት አበክረው ሲናገሩ እሰማለሁ:: ከሁለት አንዱንም እንደምርጫቸው ይዘውታል፡ እኔ ግን ከሁለት አንዱ መርጠ ፈጣሪ የሰጠኝን ተቀብዬ ለመኖር ተስማምቻለሁ:: ፈጣሪዬ በሀብት ካፀናኝ አልረሳውም፤ በድህነትም ውስጥ ካስተመጠኝ ስግብግብና አመፀኛ አልሆንም:: ሀብትም ይሁን ድህነት መለኮታዊ ስጦታዎች ናቸው:: ሀብት ፈጣሪን በመርሳት፤ ድህነት ደግሞ በስግብግብነት ባይበላሹ እንኖርባቸው ዘንድ የተሰጡን አይደሉምን?" ይሉናል::

ኢሻይር እንዲት ወግ ይጨምሩልናል፡- አሊ የተባለ ተማሪያቸው ነቢዩን እንዲህ ሲል ጠየቃቸው፡-

"ፍፁም የማይጠፋና ዋጋ ቢስ ያልሆነ ሥራ ወኔወን እፈልጋለሁና ምን ላድርግ?"

ነቢዩም መለሱለት፡- "እውነትን ፈልጋት:: እውነት ደግሞ ያለችው በውስጥህ ነው:: በውስጡ ያለችውን እውነት ያገኘ እሱ ራሱን አገኘ ማለት ነው:: ከአዋቂዎችና ጠቢባን ጋር ወዳጅ

ሁን:: እነሱ በሚናገሩትም ተስማማ:: በምትናገረውም ነገር ትንንት አይትደልሀ:: እንዴት ምላስ ሁለት ነገር ልትናገር አይገባትምና:: ማንንም እናንተሀና አሳንሰህ ለማሳየት አትሞክር፣ ምክንያቱም በአንተ ውስጥ ያለ ፍላጐት በእያንዳንዱ ሰው ውስጥ ሁሉ የሚገኝ ነውና... የአንተ ያልሆነውን ነገር ሁሉ አትንካ:: ሰው ከምላበት በታ ርቀህ ብቸኝነትን ፈልጋት:: ከሰዎች መራቅ ባትችል እንኳን በሰዎች መካከል ከራስህ ጋር ብቸኛ ለመሆን ሞክር:: የእውነት መገለጫ በታ ብቸኝነት ናትና" በማለት ጥለውት ሄዱ::

ወደሩሚ እንመለስ፡- "አንድ ቀን ሙሴ በመንገድ ላይ ሲጓዝ ሳለ አንድ እረኛ ተንበርክኮ ለፈጣሪው ፀሎት ሲያቀርብ ሰማው:: እረኛው በፀሎቱ የፈጣሪውን ፀጉር ለማበጠር፣ ልብሱንም ለማጠብ፣ እንዲሁም እጆቹን ለመሳም ሲማፀነው ሙሴ በመስማቱ በእረኛው ድፍረት በቁጣ ነደደ:: "የፈጣሪን ፀጉር ለማበጠር፣ ልብሱንም ለማጠብ እንዴት ይቻላል? እግዚአብሔር መንፈስ መሆኑን አታውቅምን?" በማለት ሠኘበትና እረኛውን ከበታው በማባረር መንገዱን ቀጠለ::

ነገር ግን ጥቂት እንደተጓዘ እግዚአብሔር በትሪው በቁጣ እንደነደደ በሙሴ ፊት ተገለጠ፡- "ሙሴ! በጥበባቸውና በእውቀታቸው የእኔን ልብ ለማግኘት ከሚሞክሩ የአንተ ጠቢባን ይልቅ በእረኛው የዋህነት እንደምደሰትና ለምላሹም እንደምፈቅን አታውቅምን?"

ሙሴም በድርጊቱ ተፀፅቶ ወደ እረኛው ተመልሶ ሄደ:: እረኛው ግን ከጠቢባንና ሊቃውንት እግር ሥር ተቀምጦ እንዴት ለፈጣሪው መፀለይ እንዳለበት መማር ጀምሮ ነበር::

በሱፊዎች ምክር እንሰናበታለን፡-

"የማያውቅና አለማወቁንም የማያውቅ ሰው ሞኝ ነውና እርሱን አርቀው፣

"የማያውቅና አለማወቁን ግን የሚያውቅ እሱ ሕፃን ነውና አስተምረው፣

"የሚያውቅና ማወቁን ግን የማያውቅ ተኝቷልና አንቃው፣

"ነገር ግን የሚያውቅና ማወቁንም የሚያውቅ እሱ ጠቢብ ነውና ተከተለው::" □

# "ከከፉ ሰው ይልቅ እውቀት የሌለው ታላቅ ጥፋት ያደርሳል"

ስለሱፊዝም እምነት በተደጋጋሚ የሄድንበት ስለሆነ ስለእምነቱ ምንነት ወይም ስለተከታዮቹ ማንነት በመዘርዘር ጊዜና ቦታ አላባክንም:: በተጥታ ወደሱፊስቶች የእውቀት አገመራ ገብተን ማጨድ እንደላለን::

በሱፊዝም እውቀት (Knowledge) እና በጥልቅ ማሰላሰል (Contemplation) የማይለያዩ፣ አንዱ የአንዱ መገለጫ ናቸው:: ምድራዊ እውቀት ሁሉ በጥልቅ ማሰብ (ማሰላሰል) የሚገኝ ሲሆን ሳታስበው አገኘሁት የምትለው እውቀት ግን እንደገለባ በቀላሉ በንፋስ ሊበተን እንደሚችል ይናገራሉ:: እናም የሱፊዝም የእውቀት ጉዞ መሠረቱ ማሰብ (ማሰላሰል) ይሆናል:: ከማሰብ የሚገኝ እውቀት ለምድራቱ የፀሐይን ምስጢር እንደሚፈታ፣ የታወረንም ዓይን እንደሚያበራና መማር የሚሻንም ልብ የሚከፍት ነው:: እነሆ በማሰብ የሚገኝ እውቀት ጥልቀቱን በሱፊዝም ጥበብ ስንቃኝ በታላቁ የሱፊዝም መምህር እንሳሪ ምክር በመጀመር ይሆናል::

እንሳሪ ሲናገሩ፡- "ሦስት ነገሮችን የሚያውቅ እሱ ከሦስት ነገሮች ራሱን ያድናል፡-

- እምላክ ፍጥረትን ሁሉ ሲፈጥር አንዳች ስህተት እንዳልፈፀመ የተረዳ እሱ በከንቱ ከመድከም የዳነ ነው::

- ያለውን ነገር ያለእድልዎ የሰጠ እሱም ከተናነተኛ መንፈስ የነፃ ነው::

- ከየት እንደተፈጠረና ለምን እንደተፈጠረ የሚያውቅ እሱም ከትዕቢት የዳነ ነው::"

እናም እንሳሪ "እውቀት ከከንቱ ድካም፣ ከተናነተኛነትና ከትዕቢት

መዳኛ መድኃኒት ነች" ይሉናል።

ሱፊው ሞሐመድም ሌላ ሦስት ነገሮችን ያነሱልንና እነሱንም የሃይማኖት መጥፊያዎች ናቸው ይላሉ። እነሱም "መጥፎና ቂሙ መምህር፣ ጨቋኝ መሪና እውቀት የሌለው ሰባኪ ናቸው" ይላሉ። የሞሐመድን ሌላ የእውቀት ምክር ስንጨምር እውቀትና ትዕቢት (ሁንጋ) ርቀታቸውን እንድናይበት ትረዳናለች። ሞሐመድ ሲመክሩ፡- "የሰው ልጅ ጥንካሬ በጉልበቱ ብርታትና በሚሸከመው ሸክም ብዛት አይደለም፣ እንዲያማ ቢሆን ለጉልበቱ ፈረስ፣ ለሸክሙም አህያ ተወዳዳሪ አይኖራቸውም ነበር። ነገር ግን የጥንካሬ ቁም ነገር የሚገኘው ቁጣንና ተናዳጅነትን በመግታት ላይ ነው" ይላሉ። በተቆጣህ ቁጥር ከእውቀት ጋር ርቀትህን እያሰፋህ መምጣትህን ማወቅ እንደማለት ነው።

ከሱፊው ሞሐመድ አሁንም ሌላ ወግ እንጨምር፡-

"አንድ ቀን የሱፊው መምህር በሚያልፉበት መንገድ ላይ ሰዎች ተሰብስበው አንድ ነቢይ ሲያደንቁ ይሰማና ተጠግቶ ለጥቂት ጊዜ ሲያስተውል ከቆየ በኋላ፡- "ለመሆኑ የዚህ ነቢይ እውቀት ምን ያህል ነው?" በማለት ይጠይቃቸዋል።

እነሱም፡- "እኛ በፀሎቱ ምን ያህል ትጉህ መሆኑንና የሚሰራቸውን መልካም ሥራዎች እያየን እንደነቃለን፣ አንተ ስለ እውቀቱ ትጠይቀናለህ? በማለት ይመልሱለታል።

ሱፊው መምህርም፡- "ክፉ ሰው በክፋቱ ከሚያደርሰው ጥፋት ይልቅ አላዋቂ ሰው ከእውቀት ማጣት የሚያደርሰው ጥፋት እጅግ የከፋ ነው" ብሏቸው መንገዱን ቀጠለ።

ሱፊዎችን "ጥበብን ከዐይኑ ሰውር ተማሩ" ይላሉ። እውር በፊቱ ያለውን መንገድ ሳይፈትሽ እንደማይረግጥ ስትመለከቱ የእውቀት ጉዞም እንዲሁ መሆኑ ይገባችኋል እያሉን ነው።

የሞሐመድን አንድ ወግ እንጨምርና ወደሌሎቹ እንሻገራለን፡-

"አንድ ቀን አሊና ሀሰን የተባሉ ጓደኛሞች ለአደን ይወጣሉ። ነገር ግን ለአራት ቀናት ያህል በዱር ቢያሳልፉም አንዳች ዝር የሚል ነገር ማየት አልቻሉም። የእያንዳንዱ ቀን ውሎአቸውን በዚህ

ዓይነት ሁኔታ ያሳለፉና ሲመሽ በአትራቢያቸው ወደሚገኝ መንደር በመሄድ የድብ ቆዳ በጥቂት ቀናት ውስጥ አድነው ይዘውላቸው እንደሚመጡ ለነዋሪዎቹ በመንገር የቆዳውን ዋጋ ሲደራደሩ ያመሹ ነበር:: (አዳኞች የሚያድኑትን አውሬ ቆዳ መሸጥ በዘመኑ የተወደደና የተለመደም ነበር::)

አሊና ሀሰን ለአራት ቀናት የአውሬ ድምፅ እንኳን ሳይሰሙ ቆይተው በአምስተኛው ቀን በማለዳ ተነስተው በወጡበት ዱር ግዙፍነቱ ከሚያስፈራና ቆዳውም እጅግ ከሚፈለገው ድብ ጋር ተፋጠጡ:: በዚህ ጊዜ አሊ በፍርሃት፡- "ከዚህ ድብ ጋር ለመጋፈጥ መፍራቴን ልደብቅህ አልሻም" አለው::

ሀሰን በጓደኛው አሊ ንግግር ተገርሞ እየሳቀ፡- "አንተ ከፈራህ ለእኔ ተውልኝ" ይለዋል:: በዚህ ጊዜ አሊ ከአጠገቡ ያለ ዛፍ ላይ በፍጥነት ወጥቶ ከላይ ይቀመጥና ጓደኛውንና ድቡን ቁልቁል መመልከት ይጀምራል:: ሀሰንም ጠመንጃውን ደግኖ በተጠንቀቅ የድቡን እንቅስቃሴ ሲከታተል ቆየ:: ነገር ግን ድቡ በሚያስፈራ አካሄድ እየተረበው ሲመጣ ሀሰንም ፍርሃት ይጀምረዋል:: ይሁንና እንደምንም ተረጋግቶ የተኮሰው ጥይት ድቡ አጠገብ ሳይደርስ ይቀራል:: በዚህ ቅፅበት ግን ድቡ በሚያስፈራ ቁጣ ተሞልቶ እየገሰገሰ ሀሰን ጋ ሊደርስ ሆነ:: ይኸን የተመለከተው ሀሰን ድብ የሞተ ሰው እንደማይነካ በልጅነቱ የሰማው ታሪክ ትዝ አለውና ጠመንጃውን ጥሎ እንደሞተ ሰው ይዘረራል:: ድቡም ሀሰን አጠገብ ይደርስና ዙሪያውን እየዞረ ካሸተተው በኋላ የሞተ መስሎት ጥሎት ይሄዳል:: ይኸን የተመለከተው አሊ ከዛፉ ላይ በፍጥነት ወርዶ ሀሰንን "ነፍስህን በማዳንህ እንኳን ደስ ያለህ" በማለት አቅፎ ከሳመው በኋላ "ለመሆኑ ወደጆሮህ ተጠግቶ ሲያሸትህ የነገረህ ነገር ነበር?" ይለዋል::

ሀሰንም "ድብን ሳትይዝ ቆዳውን ለመሸጥ አትደራደር በማለት ነው የመከረኝ" አለው:: ጠቢብ ሰው በእጁ ላይ ባለው እንጂ በተስፋ እምነት አያታይም እንደማለት ነው::

ወደሱፊው ኢታር ደግሞ እንለፍ፡- ሳሊህ የሱፊዝም መምህር ናቸው:: ታዲያ አንድ ቀን ደቀመዝሙሮቻቸውን "ሁልጊዜ

በሩን አጥብቆ የሚያንኳኳ አንድ ቀን ይከፈትለታል" በማለት ሲያስተምሩ ሌላዋ የሱፊ መምህር ራቢያ ይሰሙና "ሳሊህ ሆይ! እስከመቼ ነው 'ይከፈትለታል' እያልክ ተማሪዎችህን ስለወደፊቱ የምታስተምራቸው፤ ለመሆኑ በሩ ተዘግቶስ ያውቃል?" በማለት አፋጠጧቸው አሉ:: የእምላክ ደጆች የሚዘጉት ለሰነፎች እንጂ ጠቢባንማ ሁልጊዜ ተከፍቶ ይጠብቃቸዋል እንደማለት ተርጉመን የኢታርን ወግ ማለፍ እንችላለን::

ሌላ የኢታርን ወግ ደግሞ እንጨምር፤-

"ሀሰን አል-ባስሪ አንድ ቀን ሐቢብ አል-አጃሚ ቤት በምሽት የፀሎት ሰዓት ይደርሱና ስፀሎት አብረው ይቆማሉ:: ነገር ግን ፀሎት እንደጀመሩ አል-አጃሚ አንድ ቃል አበላሽተው ሲናገሩ ይሰማሉ:: አል-ባስሪ በተበላሸ ቃል ከሚፀልይ ሰው ጋር መተላተል ስላልፈለጉ ለብቻቸው መፀለይ ይጀምሩና ጨርሰው ይተኛሉ:: በእንቅልፍ ሰዓት በሕልማቸው ፈጣሪ ይመጣና፡- "ሀሰን! በተበላሸ ቃላት ከፀለየው ከአል-አጃሚ ኋላ ቆመህ ወደ እኔ ፀልየህ ቢሆን ኖሮ በዕድሜ ዘመንህ ከፀለይኳቸው ሁሉ ይኸን እሰማልህ ነበር:: አንተ የቃላት እንጂ የልብን መበላሸት አላስተዋልክም:: እኔ ግን በፀሎቱ ቋንቋ ከሚማርከኝ ይልቅ በልቡ ንፅህና የሚቀርበኝ በእኔ ፊት የተወደደ ነው" በማለት ገስጿቸው ሄደ:: የልብ ንፅህና ከእውቀት ሁሉ የላቀ ነው እንደማለት ወስደን የኢታርን ታሪክ አሁንም ከግምት ውስጥ እናስገባዋለን::

የሱፊዝምን እውቀት ስናነሳ የማይዘነጉትን ባያዚድ ቢስጣሚን ማንሳት ተገቢ ነው:: ከምክራቸው ስንነሳ፡- "በሰውና በፈጣሪ መካከል ያለው ትልቅ መጋረጃ የሰው ጥበብ ነው፡ ምዕመናን ብዙ ጊዜ ከእምላካቸው ይልቅ የጠቢብን ሰው ጥበብ ማምለክ ይቀናቸዋል" ይላሉ:: የቢስጣሚን ሌላ ወርቅ የሆነች ጥበብ እዚህ ላይ እናምጣት፡- "መንፈስ በውስጣቸው የሚገኝ ፍጡራን ብቻ ሳይሆኑ ነገር ግን ተግባር፡ ቃላት፡ ሐሣብ እንዲሁም ስሜቶች ውስጥ መንፈስ አለ:: ለዚህም ነው አንዳንዴ የንፍስ የተጣበ ሥራ እንደመልዕክ ሲገለጥ የምናየው" ይላሉ::

በሼክ ባድሩዲን የእውቀት ጉዞ እናጠቃል:: ሼክ ባድሩዲን የእውቀት ጉዞአቸውን አስመልክተው ሲናገሩ፡-

"በመጀመሪያው የእውቀት ጉዞዬ በገዢዎችም ሆነ በተራው ሕዝብ ዘንድ የተወደደች እውቀት አገኘሁ፤ በሁለተኛው ጉዞዬ ደግሞ በገዢዎች ዘንድ የምትወደድ ተራው ሕዝብ ግን የማይቀበላትን እውቀት አገኘሁ፤ በሦስተኛው ጉዞዬ ደግሞ ገዢውም ሆነ ተራው ሕዝብ የማይቀበሏት እውቀት ላይ ደረስሁ::

"እንግዲህ የመጀመሪያዋ እውቀት ንስሐ ትባላለች፤ ገዢዎችም ሆኑ ተራው ሕዝብ የሚቀበሏት እውቀት ናት:: ሁለተኛዋ ደግሞ በፈጣሪ መታመን ስትሆን ይኸችን እውቀት ገዢዎች እንጂ ተራው ሕዝብ አያውቃትም፤ ሦስተኛ የደረስኩባት እውቀት እውነት ስትባል ይኸች እውቀት ከሰው ልጅ የመማር ኃይልም ሆነ አስቦ ከመድረስ ችሎታው በላይ ሆና አገኘኋት፤ ስለዚህም የሰው ልጅ ሊቀበላት አይፈልግም..." ይሉናል::

ለሱፊዎች የእውቀት ረሃብ አለ:: ይኸ ረሃብ ዳቦ እንደሚጠግበውና በእፍታ እንደሚሻረው የሆድ ረሃብ ዓይነት አይደለም:: ሱፊዎች እንደሚነግሩን የእውቀት ረሃብ የሚሻረው በማሰብ ብቻ ነው:: ለዚህም ነው ሩሚ ሲናገሩ፡- ማሰብ የማይችል ሰው በገሃነም ተጥሎ ሳለ ነገር ግን ስለዘላለማዊነት አሁንም የሚጨነቅ ሰውን ይመስላል የሚሉን:: □

# “በፍቅር የተሠራ ኃጢአት ፍቅር ከሌለበት አምልኮ ይበልጣል”

በዚህ ምዕራፍ ከሱፊ ባህር ልንቀዳ የወደድንነው የየዕለት ኑሮአችንን አስመልክቶ ከሱፊዝም እምነትና ፍልስፍና ያሰፈሩልንን ይሆናል:: ለሱፊዎች ይኸች ዓለም እንደመድረክ የተብረቀረቀችና በተለያዩ ብርሃናት የደመቀች ናት:: ተመልካቹ በመድረክ ላይ ትዕይንት ተመልክቶ እንደሚወሰድ ሁሉ ዓለምም የሚመለከቷት የሚወሰዱባት መድረክ ትሆናለች:: ዓለምን በሚገባ የሚመለከቱ ግን "የእውነት ዓይን" ያላቸው ብቻ ናቸው:: "ወደመድረኩ የሚያተኩረው ዓይንህ እውነትን ማየት ሲችል ያን ጊዜ በመድረኩ ፈጣሪ ዓይን መመልከት ትጀምራለህ" ይላሉ::

በሱፊዎች እምነት በእኛና በፈጣሪ መካከል ሰባ ሺህ መጋረጃ ተጋርደዋል:: እነዚህ መጋረጃዎች ደግሞ በአብዛኛው ልማዶቻችንና ሃሣቦቻችን ናቸው:: ከመለኮታዊ ፈጣሪ ጋር መገናኘት ያገዱንን እነዚህን መጋረጃዎች ዕለት ዕለት በቀደድን ቁጥር ደግሞ ወደመንፈሳዊ ማንነት እየቀረብን ነው ማለት ይሆናል:: እውነትን ለማድረግ ከመሞከር በፊት እውነትን ማወቅ እንደሚገባ የሚመክሩን ሱፊዎች ‹‹እውነትን በራሱ ማወቅም እንደማድረግ ይቆጠራል›› ይላሉ:: ‹‹እንዴት ሆኖ?›› ቢሏቸው እውነትን አውቆ ሳያደርጋት የሚኖር የለምና ነው መልሳቸው:: ዕለታዊው የሰው ልጅ ሕይወት የብዙ ነገር ማለፊያ ነውና ሕይወቱን ዕለት ዕለት በሚያባክነውና በአንፃሩ ደግሞ በቅጡ ሕይወቱን በሚጠቀምባት መካከል ያለውን ልዩነት በምሣሌ እየመዘዙ አሳይተውናል::

ሱፊው እንሳፈን መግቢያችን ስናደርግ ንግግራቸውን በመጥቀስ ይሆናል:: "የምትሰራውን ሥራ ልብ በል፣ የአንተም ዋጋ ዕለት

ዕለት በምትሰራው ሥራ የሚተመን መሆኑን ታውቃለህ? እውነተኛ ሥራ ፆምና ፀሎት ሳይሆን የተፈጠርክበትን ዓላማ በሥራ መግለጥ ነው::"

በሱፊዝም ጉዞ የማይለዩን ሼኽ ሙዛፈር "በዕለታዊ ሕይወት" ጉዞአችን ላይ የሚነግሩን ደግሞ አለ፡- አንድ ቀን በአብዶች ሆስፒታል በራፍ ላይ ያልፍ የነበረ ወጣት በድንገት ቀና ብሎ ወደሕንፃው ሲመለከት አንድ እብድ በመስኮት ጭንቅላቱን አውጥቶ ወደደጅ ሲያማትር ይመለከታል፡- "ለመሆኑ በዚያ ሆስፒታል ውስጥ ያላችሁት እብዶች ስንት ትሆናላችሁ?" በማለት ሎ'ኸ ይጠይቀዋል::

እብዱም ለጠያቂው ሰው ፈገግታን ለግሶ፡- "ለመሆኑ እዚያ ደጅስ ስንት ጤነኞች አላችሁ?" በማለት ጥያቄውን በጥያቄ መልሶለታል::

ብዙዎቻችን የሰዎች ድክመት፣ እብደት፣ ስንፍናና ጭካኔ ይታየናል እንጂ የየዕለት ሕይወታችን ብንመረምር እጅግ ብዙ ጉዶሎ እንዳለብን ማስተዋል በቻልን ነበር:: ለዚህ ነው ሱፊዎች "የላቀ እውቀት ራስን ማወቅ ነው" የሚሉት::

ከሼክ ሙዛፈር አንድ እንጨምር፡- አንድ ውሸት የመናገር ችግር ያለበት ሰው ወደሱፊው መምህር ይመጣና ይኸንኑ ችግሩን ይነግራቸዋል:: ሱፊውም እንዲህ ሲሉ መከሩት፡- "እሳት እግኝቶት የማይተጣጠል እንጨት እንደሌለ ሁሉ እንዲሁ ሐሰት መልካሙን ነገር ሁሉ ታጠፋዋለች:: እውነት ለጊዜው የምትጎዳህ ይምሰል እንጂ እያደር ማዳኗን ግን አትዘንጋ:: በውሸት ለመዳን መሞከር ከንቱ ድካም ነው:: በእውነት ሕይወትን ለመኖር ከፈለግህ እውነት ብቻ ተናገር" በማለት ሸኙትውታል::

የሼክ ሙዛፈር የዕለታዊ ሕይወት አስተምህሮት ብዙ ነውና አንድ እንመርቅ::

አል-ጋዛሊ ተማሪዎቻቸው አንድ ቀን እንዲህ በማለት ጠየቋቸው፡- "መምህር ሆይ ገንዘብ የሰውን ልብ ያስንፋል የሚባለው እውነት ነውን?" አል-ጋዛሊም፡- "ልጄ ሆይ በገንዘብ ልባቸው የሚሰንፍና የሚለዋወጥ ሰዎች እነሱ ገና ብዙ ትምህርት ይጐድላቸዋል..." አሉት::

ወደ አሉ-ጃሚ ደግሞ እንለፍ፡- አንድ ሰው ሊሞት በሚያጣጥርበት ሰዓት የመጨረሻ ኑዛዜ እንዳለው ተጠይቆ ወንድ ልጁን እንዲጠሩለት ያዛል:: ወንድ ልጁም ወደ እሱ በቀረበ ጊዜ እንዲህ አለው፡- "ልጄ ሆይ! ከፊት ለፊትህ ያስቀመጥኩት መቶ መሐለቅ ወርቅ ነው:: ይኸን ወርቅ ትወስድና በዚህ ምድር ላይ እጅግ ሞኝ ሰው ያጋጠመህ ዕለት ለእሱ ስጠው:: ይኸ አደራዬ ነው" በማለት ይሞታል::

ልጁም በአባቱ ኑዛዜ መሠረት ይኸን ወርቅ ተሸክሞ የምድራቱን ሞኝ ፍለጋ ሲዞር ይከርምና አንድ ቀን አንዲት ከተማ ይደርሳል:: በዚያች ከተማም ሕዝብ የተሰበሰበበት አደባባይ ይመለከትና ተጠግቶ የሚሆነውን ሲጠይቅ የሃገሪቱን ሚኒስትር ንጉሠ ነገሥቱ ስላዘነበት አንገቱን ተቆርጦ እንዲሞትና በእሱም ሬሣ ላይ አዲሱ ሚኒስትር እንዲራመድ ስላዘዘው ይኸው ሥርዓት የሚፈፀምበት ዕለት ነው ይሉታል:: ወጣቱም ከሕዝቡ ጋር ተቀላቅሎ የሚሆነውን ሲጠብቅ ንጉሡን ያሳዘነው ሚኒስትር በወታደሮች ተከቦ በሕዝቡ ፊት ይቆምና አንገቱን አስጎንብሰው በሰይፍ ሲቆርጡት ይመለከታል:: ይኸም ብቻ አልነበረም:: አዲሱ ሚኒስትር ደግሞ በፈገግታ ተሞልቶ አንገቱ ተቆርጦ የወደቀውን ሚኒስትር ሬሣ ተራምዶ ሲያልፍ ሕዝቡ በዕልልታና በጭብጨባ ያጅበዋል:: ይኸን ጊዜ ወጣቱ ወደአዲሱ ሚኒስትር ሲገሰግስ ሄዶ የተሸከመውን መቶ መሐለቅ ወርቅ ተረከበኝ ይለዋል::

አዲሱ ሚኒስትር በነገሩ ግራ ተጋብቶ፡- "በእርግጥ በእኔ ሹመት ተደስተህ ነው ይኸን ሁሉ ወርቅ የምትሰጠኝ?"አለው::

"የለም! አባቴ በኑዛዜው ሰዓት በዓለም ላይ እጅግ ሞኝ ሰው ፈልገህ ይኸን ወርቅ ስጥልኝ ባለኝ መሠረት ነው የምሰጥህ..." ይለዋል:: ሚኒስትሩ ግራ ተጋብቶ "እንዴት እንዲህ ትለኛለህ?" ቢለው "ይቅርታ አድርጉልኝና ዛሬ ተራምደውት የተሾሙትን ሚኒስትር ሬሳ ነገ የእርስዎን ሌላ እንደሚራመደውና እንደሚሾምበት ሳያውቁ የቀኑ በመሆንዎ ለእኔ ከዚህ በላይ ሞኝ ሰው ላገኝ አልችልም..." በማለት ወርቁን ጥሎለት ሄደ::

ለሱፊዎች በዚህ ዓለም ላይ ያለው የሰው ልጅ ኑሮ መድረሻና ግብ አለው:: መድረሻው የአእምሮ ብስለት ሲሆን ግቡ ደግሞ ነፃነት ነው:: ለምሣሌ የዛፍ ፍሬ እስኪበስል ከዛፉ ላይ ተጣብቆ ይቆይና ከዚያ በኋላ ወደመሬት ይወድቃል:: ገበሬም እንዲሁ ዘርን ይዘራና ይጠብቀዋል:: ዘሩም ይበትላል፣ ለአጨዳም የደረሰ እህል ይሆናል:: እህሉ ደግሞ ዘር ነው:: ቀድሞ ወደነበረበት ይመለሳል ማለት ነው:: ዑደቱም ሙሉ ክብ ይሆናል፣ የሕይወትን ሙሉ ክብ መዞር ደግሞ ነፃነት ይባላል::

ወደሼክ ሀምዱን እንለፍ:: የሼክ ሀምዱን የቅርብ ወዳጅ በአልጋው ላይ ተኝቶ ለመሞት ያጣጥራል:: ሼኹም ሻማ አብርተው ከዘመዶቹ ጋር በፀጥታ ሲያስተውሉት ከቆየ በኋላ የመጨረሻ ሕቅታውን ይውጣታል:: ሼኽ ሀምዱንም የወዳጃቸውን ሞት እንደተመለከቱ ቶሎ ብለው ሻማውን ያጠፋሉ:: ይኸን ጊዜ የሟቹ ዘመዶች ሻማውን ለምን እንደሚያጠፉና ብርሃን ይበልጥ በሚያስፈልግበት ሰዓት በጨለማ እንደሚያስቀምጧቸው በቁጣ ሲጠይቋቸው፡- "ወዳጆቼ! የዚህ ሻማ ባለቤት አሁን ሞቷል:: ስለዚህ ወራሾቹ እውቀው እነሱ እስኪፈቅዱ ድረስ ድጋሚ ማብራት አልችልም" ብለዋቸዋል::

እውነትን የሚከተሉ ሰዎች "በፍቅር የተሠራ ኃጢአት ፍቅር ከሌለበት አምልኮ ይበልጣል" ይላሉ:: ፍቅር የሌለበት አምልኮ ዋጋው ከከንቱ ድካም ጋር የሚስተካከል ነውና:: እናም ሼክ ሀምዱን ሲናገሩ፡- "በፍቅር የተሠራ ኃጢአት ቢያስቀጣም ያስደስታል:: ስለዚህም የምታደርገውን ነገር ሁሉ (ኃጢአትም ቢሆን) በፍቅር አድርገው" ይላሉ::

ሱፊዎች በአንድ ነገር ተመስጦ መኖርን የተለማመዱ ናቸው:: መልካምም ይሁን መጥፎ ነገር በዚያ ነገር ተመስጠው መከተልና በዚያም መኖር ይችላሉ:: አማራጭ ሲጠፋ መንገድ ዳር መተኛትንም የግድ ልንቀበለው ይገባል ባይ ናቸው:: የሰው ልጅ ከአፈር የተሠራ ነውና መሬቱ ላይ መተኛቱ የራሱን አንድ ክፍል ይዞ እንደተኛ ሊያስቆጥረው ይገባል ይላሉ::

እንዲት የሱፊ ወግ ልጨምር፡- አንድ ወቅት አንድ የዓረብ

ተጓዥ በበረሃ መንገዱ ይጠፋበትና ሲንከራተት ቀናትን ያሳልፋል:: በዚህም ሁኔታ ምግብና ውሃውን ጨርሶ በረሃብና ጥም ሲሰቃይ ሳለ በከረጢት የሞላ ነገር በመንገዱ ላይ ወድቆ ያገኛል:: በልቡም ምናልባት በከረጢቱ የሞላው የእህል ዘር ሆኖ ረሃቡን ማስታገስ ይችል ዘንድ በጉጉት ቢከፍተው ከረጢቱን የሞላው እንደጠበቀው የእህል ዘር ሳይሆን ዕንቁ ሆኖ ያገኘዋል:: ዐረቡ ከብዙ ድካም በኋላ የበረሃ ተጓዦች ሕይወቱን እድነውት ሲናገር፡- "ያንን ከረጢት ስከፍት የእህል ዘር ሳይሆን ዕንቁ ሆኖ በማግኘቴ እጅግ ያዝንኩበትና የተከፋሁበት ቀን እንደነበር አስታውሳለሁ" ብሏል:: ሱፊዎች ይመክራሉ፡- ያለጊዜው ከሚመጣ ሀብት በጊዜው የሆነ ድህነት ይሻላል::

በሼኽ መሀፈር ንግግር ልሰናበት፡- "ሰዎች ከግመል እበት ገንፎ መሥራትን ቢከለክሉ ብዙዎች እስከዛሬ የግመል እበት እያቦኩ በበሉ ነበር:: ምነው ቢሉ የሰውን ልጅ አንድ ነገር ሲከለከሉት ለእሱ ጥቅም ሳይሆን 'አንድ ጥሩ ነገር ቢኖረው ከለከሉኝ' የማለት ጥርጣሬን በውስጡ ያነገሰ ነውና" ብለዋል:: ለዚህም ነው ሱፊዎች "ቅንነት የታላቅነት መሠረት መሰላል ናት" የሚሉት:: □

# “ኃጢአትን ከማድረግ በላይ ካደረጉት በኋላ ማሰቡ የከፋ ነው”

በዚህ ምዕራፍ ስለሱፊዝም የምናነሳው "ራስን ማታለልና ራስን ማወቅ" ነው:: የቱንም ያህል በመስተዋት ላይ ብታፈጥ፣ አልያም ወደኋላህ ለመዞር ብትሞክር የጭንቅላትህን ጀርባ ለማየት አይቻልህም የሚሉት የሱፊው መምህር አል-ጋዛሊ፦ "በግልፅ እናየዋለን ብለን በምናስበው ነገር ላይ እንኳን የማናየው ነገር መኖሩን የማናውቅ ብዙዎች ነን:: እነሆ የማናየው ነገር ደግሞ ለብዙዎች መሳሰቂያ ያደርገናል" ይላሉ::

እናም ራስን የማወቅ ሰይፍ፣ ራስን በግልፅ የማየት ችሎታ፣ ያለማወቃችንን መከራ ሲያሳጥረው ይገኛል:: ራስን በማወቅ እሳት ስንለበለብ ራስን ማታለልና ግራ መጋባት ደግሞ ከየአቅጣጫው የሚያቃጥሉን ፍሞች ይሆናሉ:: ራስን በማወቅ አደጋ ውስጥ ስናልፍ የከፋ ነገር እንዳይገጥመን ሰፊዎች "እኛ ጋ ምክሩ አለ" ይላሉ::

ከእኛ በፊት ቀድመው ያለፉ አባቶችና ጠቢባን ትተውልን ያለፉት ትምህርትና ምክር የዛሬው መንገዳችን ጠቋሚ ሆኖ ቆሞልናል:: ካለማወቃችን በላይ የሚያፀናን፣ የሚያቆመንና እንዲሁም በጨለማው መንገዳችን ላይ ብርሃን እንደሚሆንልን የሚነግሩንን ምክርና ታሪክ እንቃኛለን:: መምህር የተማሪዎቹን እጅ ይዞ እግራቸው እየመራ በመንገዳቸው ሁሉ የሚከተል ሳይሆን ውስጣቸውን ለማግኘት በሚያደርጉት ጥረት አጋዥ ሆኖ ይቆምላቸዋል:: በውስጣችን ከተቀበረው ጥበብ ጋር የሚያገናኙን የሱፊዎችን ጥበብ የምንጀምረው በአል-ጋዛሊ ነው::

አል-ጋዛሊ ሲናገሩ፦ “አንዳንዶች ‘ከቁጣ፣ ከስግብግብነትና ከግብዝነት እንድንታቀብ ሕግ አዞናል ይላሉ:: ነገር ግን ይኽ በፍፁም የሚቻል አይደለም፣ ምክንያቱም እነዚህ ባሀርያት ሁሉ

አብረውን የተወለዱ ናቸውና:: ጥቂቱን ነው እናደርገው ዘንድ እንደማዘዝ ነው' ይላሉ:: እነዚህ ሰዎች የዘነጉት ነገር ቢኖር እነ ሕግ እነዚህን ባህርያት ንቀላችሁ ማለ አይልም፡ ነገር ግን በልክ ግቧቸው፡ ቆጣጧቸው ነው የሚለን:: ታላቅ ኃጢአትን በማስወገድ አግረመንገዳችንን ታናሽ ለሆነው ኃጢአት ይቅርታና ምህረትን እናገኝ ይሆናል:: የእግዚአብሔር መልዕክ እንዲህ ሳይቀር፡- 'እኔም እንደናንተ ፍጡር ነኝ፣ እንደብዙዎችም እቆጣለሁ' ይላል:: በቁራን ደግሞ 'እግዚአብሔር ቁጣቸውን ወደውስጣቸው የሚውጡትን እነሱን ያፈቅራል' ተብሎ ተጽፏል" ይሉናል:: እንደእሊ-ጋዛሊ እምነት ውስጥን የማወቂያው አንዱ መንገድ ሕግን በአግባቡ መረዳት ነው:: አልያማ (እንደሱፊዎቹ አባባል) "አህያ የቱንም ያህል ቅዱስ መጽሐፍን ብትሸከም ያው አህያ ነች" የሚለውን በድጋሚ ልናነሳ እንገደዳለን::

ሱፊዎች አንድም ወደ ውስጣችን የመመልከቻው መንገድ ጊዜን በአግባቡ መጠቀም መሆኑን ያበክራሉ:: በጊዜው ያላደረግከው ነገር ካለፈ በኋላ ማድረግ ከንቱ መባዘን መሆኑን የሚነግሩንም በምሳሌ አስደግፈው ነው፡- "ፈረሶችህ ከተሰረቁ በኋላ የጋጣውን በር የምትዘጋው ለምን ይሆን? በእንዲህ ዓይነቱ የእርጅናህ ሰዓትም 'ዓለም ከንቱ ነች፡ አሁን አምላኬን አገኘሁት' ትላለህ:: ነገር ግን ጥቅም የለውም:: ከኃጢአቶች ሁሉ ምህረት የሌለው ጊዜን በከንቱ ማጥፋት ነው" ይላሉ::

ወደ ቡሻንጂ እንለፍ፡- ኃጢአትን ከማድረግ በላይ ካደረጉት በኋላ ማሰቡ የከፋ መሆኑን እዩት ይሉናል፡- "ኃጢአትን ፈፅመህ ደስታው ተከትሎህ ካልሄደ ንስሐ ገብተሃል ማለት ነው:: ምክንያቱም ኃጢአትን እንደመሻትና እንደማሰብ ማድረጉ አይጎዳም:: ድርጊቱ ጊዜያዊና ኃላፊ ሲሆን መሻትና ፍላጎቱ ግን ቀጣይና የማያቋርጥ ነው:: አንድን ኃጢአት በገላችን ማድረግ በአእምሮና በልብ ሲያኝኩት ከመኖር ጋር ሲነፃፀር ፍፁም የማይወዳደር ነው?" ይሉናል::

ብዙዎች በፀሎታቸው የአምላካቸውን ስም ምን ያህል ደጋግመው እንደጠሩት ሲያስቡ፣ ከአንደበታቸው ግን በየሰለቱ የሚወጣውን ከንቱ ቃል አስበውት አያውቁም፡ እዚህ ላይ ካሲፍ አማር እንዲህ

ይላሉ፡፡- "በመጨረሻው የፍርድ ቀን ሳያስመዝኑህ አስቀድመህ ከእንደበትህ የሚወጡትን ቃላት መዝናቸው::"

"የባህርይ ሥራ አራት መገለጫዎች አሉት፡- ከፈጣሪ ጋር የሚኖረን ባህርይ፣ ከራስ ጋር የሚኖረን ባህርይ፣ ከሰዎች ጋር የሚኖረን ባህርይ እንዲሁም ከዓለም ጋር የሚኖረን ባህርይ ነው:: እነዚህ ባህርያት ደግሞ በሰባት መመሪያዎች ላይ የተመሠረቱ ናቸው:: ከፈጣሪ ጋር ለሚኖረን ባህርይ ሰባቱ መመሪያ፡- ለእሱ የሚገባውን መስጠት፣ ማንነቱን ማወቅ፣ ስለስጦታው ማመስገን፣ በቃሉ በቃኝ ማለት፣ በፈተናዎቹ መታገስ፣ ቅድስናውን ማክበርና ለእሱ መገዛት ናቸው::

"ከራስ ጋር ለሚኖር ባህርይ ሰባቱ መመሪያ ደግሞ ፍርሃትን መቀነስ፣ መጣር፣ ችግርን መቋቋም፣ መንፈሳዊ መርሆን አጥብቆ መያዝ፣ እውነትንና ቅንነትን መከተል፣ ከሥጋ ፍላጐት ራስን ማላቀቅና በልክ መኖርን ማወቅ ናቸው::

"ከሰዎች ጋር በመኖር ለሚኖረን ባህርይ ሰባቱ መመሪያዎች ደግሞ፡- ትዕግስት፣ ይቅር ባይነት፣ ትህትና፣ ቸርነት፣ ርህራኄ፣ መልካም ምክር፣ ፍትሕና ሚዛናዊነት ናቸው::

"ከዓለም ጋር ለሚኖረን ባህርይ ሰባቱ መመሪያዎች ደግሞ፡- በእጅ ባለን ነገር በቃኝ ማለት፣ ከሌለን ይልቅ ያለንን ነገር መምረጥ፣ እምቢተኛነትን ማስወገድ፣ ውትረፍረፍን መጥላት፣ ከሁሉ ነገር መታቀብን መምረጥ፣ የዚህን ዓለም ክፉ ነገር ማወቅና የእነሱን ፍላጐትም ማስወገድ እንዲሁም በክፉ ላለመሸነፍ በፅናት መቆም ናቸው" ይለናል::

ራስን በማወቅና ራስን በማታለል የጀመርነውን ጉዞ ስንቀጥል የሱፊው አል-ዋሪ ምክር መሸጋገሪያችን ትሁን፡-

"አንድ ሰው 'እንዴት ጥሩ ሰው ነህ' ቢልህ ይኸ አስተያየቱ 'እንዴት መጥፎ ሰው ነህ' ከሚለው ይልቅ ካስደሰተህ አንተ በእርግጥ መጥፎ ሰው ነህ" ይላሉ:: ‹‹ውስጥህን በሚገባ ትመረምር ዘንድ የሚገፋህ አስተያየት እሱ የተሻለ ነው›› እንደማለት ይሆናል::

ወደ ሼህ ሙዛፈር እንሂድና ውስጥን ስለማወቅ ያሰፈሩልንን ደግሞ እንመልከት፡-

"አንድ ሰው ለሱፊው መምህር ገንዘብ ለመለገስ ይፈልግና ወዳሉበት በመሄድ ገንዘቡን ይዘረጋላቸዋል:: ሱፊውም:- "ሀብታም ከሆንክ ገንዘቡን አቀበልሃለሁ፤ አለበለዚያ አላደርገውም" ይሉታል:: ሰውዬውም "በጣም ሀብታም ነኝ" በማለት ማረጋገጫውን ይሰጣል::

"ሀብታም ከሆንክ የገንዘብህን መጠን ንገረኝ" ይላሉ መምህሩ::

"ሁለት ሺህ ወርቅ አለኝ" በማለት ሰውዬው መለሰ::

"አራት ሺህ ወርቅ ቢኖርህ ትመኛለህ?" አሉት መምህሩ::

"በእርግጥ እመኛለሁ" አለ::

"ስምንት ሺህ ወርቅ ቢኖርህስ?" በማለት በድጋሚ ጠየቁት::

"እሱንም እመኛለሁ" አለ::

"እንግዲያውስ ሀብታም ስትሆን ስጦታህን ትሰጠኛለህና ያን ጊዜ ተመልሰህ እንድትመጣ" በማለት አሰናበቱት:: ‹‹ሀብታም ማለት በውስጡ በቃኝን የሚያውቅ ብቻ ነው›› ማለታቸው መሰለን::

ታላቁ የሱፊ መምህር ቢያዚድ ቢስጣሚ እንደነበሩ ይነገራል:: ቢስጣሚ ታዲያ በትምህርታቸው ብዙ ነገር ፈልገው ሲያገኙ ማግኘት ያልቻሉት አንድ ነገር ብቻ ነበር:: ይኸንንም በዚህ ምልልሳቸው እንመልከት፤-

አንድ ቀን የቢስጣሚን ትምህርት የተጠማ ሰው ወደቢታቸው በማለዳ ይመጣና በር ያንኳኳል:: በሩን የከፈቱት ደግሞ ከጠዋት ፀሎታቸው የተነሱት ቢስጣሚ ነበሩ፡-

"ማንን ትሻለህ?" ይሉታል::

"ቢያዚድ ቢስጣሚንን" ይላል ሰውዬው ቢስጣሚንን በጉጉት ዓይን እየተመለከተ::

"እዬ! ከንቱ ለፋህ:: ቢስጣሚንን ለማግኘት እነሆ እስከዛሬ እኔም ደከማኋለሁ:: እሁንም የተነሳሁት ከዚያው ፍለጋ ነው..." በማለት አሰናበቱት:: ይኸንንም "ራስን ፈልጎ እንደማግኘት የሚያደክም ነገር የለም" አድርገን ወሰድነው::

ለሱፊዎች ራስን የማወቅ አንዱ ምልክት ትዕግስት ነው ብለናል:: ሼኽ ሙዛፈር የሚያሜውቱን አለ፡-

"አንድ ቀን የሱፊው መምህር ኢብን አራቢ በተማሪያቸው

ስለትዕግስት ተጠይቀው በጥበብ የተሞላ አጠቃቀሞችን ሲያካፍሉ አባብ እየተሳበ ወጥቶ እግራቸውን ይነድፈዋል፤ ይሁንና ኢብን አራቢ ንግግራቸውን ሳያቋርጡ ማስተማራቸውን ይቀጥላሉ:: "በመካከል ግን ሁኔታውን የተረዱ ተከታዮቻቸው እግራቸው ሲነደፍ ለምን ከተቀመጡበት እንዳልተነሱ አልያም ደግሞ እንዳልጮኹ አቋርጠው ይጠይቋቸዋል::

ኢብን ራቢም፡- "እያስተማርኩ ያለሁት ስለትዕግስት መሰለኝ:: የራሴን ትዕግስት በተግባር ሳላሳይ እንዴት እናንተን በጉዳዩ ላይ ማስተማርና መምከር ይቻለኛል? በውስጤ የሌለውን እንደሆነ አድርጎ እንደመናገር የሚያሳፍረኝ ነገር የለም::" በማለት መለሱላቸው::

ድርጊቶቻችን ሁሉ በዕውቀት ካልታገዙ ዞሮ ዞሮ ጥፋት ማድረሳቸው አይቀሬ ነው:: የሱፊው መምህር አንሳሪ ደግሞ እንዲህ ይሉናል፡- "አንድ ቀን ብዙ ሰዎች ተሰብስበው ከመካከላቸው በፀሎተኛነቱና በለጋስነቱ የታወቀን አንድ ሰው ሲያመሰግኑና ሲያደንቁ የሱፊው መምህር በቦታው ይደርሳሉ:: መምህሩም የሆነውን ሁሉ በርጋታና በጥሞና ካስተዋሉ በኋላ፡- 'ለመሆኑ ይኸ የምታደንቁት ሰው እውቀቱ ምን ያህል ነው?' በማለት ይጠይቃሉ."

"ሕዝቡም፡- 'በፀሎቱ ምን ያህል ትጉህና በለጋስነቱም ታላቅ እንደሆነ እየነገርንዎ ስለእውቀቱ ይጠይቁናል?' በማለት ያፈጡባቸዋል.. "የሱፊው መምህርም 'ክፉ በክፋቱ ከሚያደርሰው ጥፋት ይልቅ አላዋቂ ሰው ባለማወቁ የሚያደርሰው የከፋ ነው' በማለት ጥለዋቸው ሄዱ." ይሉናል::

ማቆሚያችን የሱፊው መምህር የካቢር ምክር ይሆናል፡- "የእግዚአብሔርን ስም በመጥራት እርካታ ማግኘት ከተቻለ፡ የከረሚላን ስም በመጥራት አፍን ማጣፈጥ ከተቻለ፡ እሳትን በመጥራት እግር ቢቃጠል ኖሮ፡ ውሃን በመጥራት ጥምን ማርካት ቢቻል፡ ምግብን በመጥራት ረሃብን የሚታገስ ቢሆን... ይኸች ዓለም ነፃ በሆነች ነበር..." ይሉናል::

ይኸንንም "እውነትን በሕይወታችን ስንኖ መናገር ሳይሆን ማድረግ ተገቢ ነው" በሚለው እንወስደዋለን:: □

# "እውነተኛ ሀብት ማለት የሌለህን አለመመኘት ማለት ነው"

ከሱፊስቶች የመልካም ምግባር አስተምህሮት ዙሪያ ‹ድህነትን› እንዲሁም ‹ትዕግስት› እና ‹ለጋስነትን› እንቀነጭባለን::

ሱፊዎች ታላቁ ገጣሚ የጊሪ ስናይደርን አባባል እዚህ ላይ በመጥቀስ ያስቀድሙታል፡- "እውነተኛ ባለፀጎች ፍላጎታቸውን ሁሉ መግደል የቻሉ ብቻ ናቸው":: የስናይደር አባባል ቁሳዊ ሀብትን የሚመለከት አለመሆኑን የሚያስምሩበት ሱፊዎች ነገር ግን የልባችንን ሁኔታም በሚገባ የሚያሳይ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል ባይ ናቸው::

ምንም እንኳን አብዛኞዎቹ ሱፊዎች ጥቂት ወይም ምንም ዓይነት ንብረት የሌላቸው ቢሆኑም ይኸ ግን የምርጫ ጉዳይ እንጂ ሀብት የማያስፈልግ ሆኖ አይደለም:: እውነተኛ ሀብት ማለት የሌለህን አለመመኘት ማለት ነው:: ለሱፊዎች "ድህነት" ማለት የምትተነፍሰው አየር፣ የምትበላው ምግብ እንዲሁም እንቅልፍህን ስታጣ ብቻ ነው:: በዚህ ዓለም ነገር የተሞላ ልብ ለፈጣሪው ቦታ አይኖረውም:: በአንፃሩ ባዶ ልብ ደግሞ ፈጣሪው የእሱ የሆነውን እስኪሞላለት ድረስ አጥብቆ ይሻል::

እዚህ ላይ ስለደሀው ሱፊ ዓሣ አጥማጅ ታሪክ እናንሳ:: ይኸ ድሃ ዓሣ አጥማጅ አዘውትሮ ዓሣውን ለማጥመድ ወደ ወንዝ ይወርድና የያዘውን ይዞ ወደመንደሩ ይመለሳል:: ነገር ግን ከጠመደው ዓሣ ለራሱ አንድ ወይም ቢበዛ ሁለት አስቀርቶ የተቀረውን ለመንደሩ ሲያድል ይውል ነበር:: የእሱ ደቀመዛሙርትም በዓሣ አጥማጅ መምህራቸው ባህርይና ቸርነት ይደሰቱ ነበር::

ከዚህ የሱፊ መምህር ደቀመዛሙርት መካከል አንዱ ነጋዴ ነበር:: ይኸ ነጋዴ አንድ ቀን ከርዶባ ወደምትሰኘው ከተማ

ለንግድ ሥራው ሊሄድ መሆኑን ለሱፊው መምህር ቢነግረው በዚህ ከተማ እጅግ የሚወዳቸውና የሚያደንቃቸው መምህሩ ኢብን አራቢ መኖራቸውንና ሰላምታውንም እንዲያደርስለት ነግሮት እግረመንገዱንም በመንፈሣዊ ሕይወቱ የጠበቀውን ያህል ማደግ አለመቻሉን አድርሶለት ምክራቸውን ይዞ እንዲመጣ ነገረው::

ይኽ ነጋዴ ኮርዶባ ሲደርስ በቀጥታ ያመራው ወደ ኢብን አራቢ ቤት ነበር:: ነገር ግን የኢብን አራቢ ቤት እንደመምህሩ የደሀ ጎጆ ሳይሆን ከአንድ ቤተመንግሥት የማይተናነስና በብዙ ጠባቂዎችም የተከበበ መሆኑን ባስተዋለ ጊዜ መደነቅ ጀመረ:: ወደውስጥም ሲዘልቅ ብዙ አገልጋዮች ሲወጡና ሲገቡ ተመለከተ:: ወደገበታም ወስደው ምግቡን ከወርቅ በተሰራ ትሪ ላይ አድርገው እጅግ በሚያማምሩ ልጃገረዶች አቅራቢነት ሲስተናገድ ቆየ:: በዚህ የኢብን አራቢ ኑሮ መደነቁ ቃላት ሊገልፀው ከሚችለው በላይ ሆነበት:: በመጨረሻም አንድ ሱልጣን የሚለብሰውን ዓይነት እጅግ ውድ የሆነ ልብስ ወደለበሱት ኢብን አራቢ ዘንድ በአገልጋዮች አማካይነት ቀረበ:: እሱም የመምህሩን ሰላምታ በማስቀደም የእሳቸውን መንፈሣዊ ምክር መምህሩ በእጅጉ እንደሚፈልግ ገለፀላቸው::

ኢብን አራቢም ነገሩን አቅልለው "ለተማሪዬ እንዲህ ብለህ ንገረው፤ አንተ በጣም ዓለማዊ ሰው ነህ!"

ይኽን የሰማው ነጋዴው ደቀመዝሙር እጅግ ደነገጠ፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ እጅግ ዓለማዊ በሆነ ሁኔታ እየኖረ የሚገኝ ሰው የእሱን ደቀመዝሙር ሲኮንንበት መስማት አናደደው::

ሃገሩ እንደደረሰም መምህሩ ተቀብሎት ከኢብን አራቢ ጋር ስለነበረው ግንኙነትና ምን እንዳሉት ጠየቀው:: ነጋዴውም የኢብን አራቢን ቃል በመድገም ከነገረው በኋላ ነገር ግን ከእንዲህ ዓይነት ሀብታምና ዓለማዊ ሰው ይኽን ዓይነቱን ቃል መስማቱ እንዳበሳጨው አክሎ ነገረው::

መምህሩም መልሶ፡- "ሁላችንም ነፍሳችን እግዚአብሔርን ልትረሳ በማትችልበት መጠን ሀብት እናገኝ ዘንድ የተገባ ነው:: በአራቢ ውስጥ ያየኸው ቁሳዊ ሀብት ሳይሆን የደረሱበትን መንፈሣዊ ደረጃ

ነው" ካለው በኋላ ዕንባ በተሞሉ ዓይኖቹ ይኸን አክሎ ነገረው፡
- "ኢብን አራቢ ትክክል ናቸው:: ብዙ ጊዜ ማታ ማታ በውስጡ
በጣም ጥቂት ብቻ የዓሣ ሥጋ ያለውን ሾርባዬን ከምድጃ በማውጣት
ወደመመገቢያ ዕቃዬ ስገለብጥ 'ምናለበት የዓሣው ሥጋ ብዙ በሆነልኝ'
የማለት ምኞቱን አቋርጬ አላውቅም::"

ኢብን አራቢ ሲመክሩ "ከዚህ ዓለም የሚያስፈልግህ ነገር ቢኖር
ረሃብን ለማስታገስ የሚበቃ ዳቦ፤ እርቃንህን መሸፈኛ ጨርቅና
ለሥጋህ ማደሪያ የሚሆን ቤት ነው:: ከዚህ ዓለም የምትጠይቀውም
ነገር ከዚህ ያለፈ አይሁን" ይላሉ::

አል-ጋዛሊ ሌላ ምሳሌ ይነግሩናል፡- "ከማንኛውም ሰው በላይ
ቀላል ሕይወትን በዚህ ምድር ላይ ያሳየን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው::
ድንጋይ ተንተርሶ መተኛቱን የተመለከተው ሰይጣን ዓለምን
በእውነት ንቆ እንደሆነ ለምን ድንጋይን ትራስ አድርጎ እንደተኛ
ቢጠይቀው ኢየሱስም የተንተራሰውን ድንጋይ ወርውሮ መልስ
ሳይሰጠው ተኛ" ይሉናል:: በፈጣሪ ዘንድ ቅዱስ እንባል ዘንድ በዚህ
ዓለም ነገር መስገብገብ አይገባንም:: ዓለምን ተመኝቶ ፊትን ከፈጣሪ
ማዞር በጊዜያዊና የሚያልፍ ነገር መጠመድ ሲሆን ሌላኛውን ዓለም
ተመኝቶ ፊትን ወደ ፈጣሪ ቢያዞሩ ግን በዘላለማዊ ነገር መጠመድ
ነው::

ወደኢብራሂም አዳም አትንተን ደግሞ አንድ የእሳቸውን ወግ
እንቅመስ፡- አንድ ሰውዬ ሁልጊዜ ድህነቱን በሰዎች ፊት ሳይተር
ሲረግም ይውል ነበር:: ይኸን እርግማኑን የሰሙት ኢብራሂም
"ምናልባት ለዚህ ድህነትህ ጥቂት ሳትከፍልበት አልቀረህምና
አትርገመው" ቢሉት "የምታወራው ነገር የማይረባ ነው፤ እንዴት
ሰው በገንዘቡ ድህነትን ይገዛል?" በማለት ይጠይቃቸዋል::

ኢብራሂምም መለሰው፡- "እኔን አስመልክቶ ከሆነ የምትጠይቀኝ
በፍቃዴ የመረጥኩት ነገር ውስጥ እየኖርኩ ነው፤ ከዚያም በላይ
የዚህን ዓለም ሀብትና ታላቅነት ከፍዬበት አሁን ያለሁበትን ድህነት
ገዝቼዋለሁ:: እንዲህ ዓይነቱን ሌላ ድህነት ባገኝ ቢቻለኝ በመቶ
ዓለማት ከመለወጥ ወደኋላ አልልም:: ያለምንም ጥርጣሬ የድህነትን

ዋጋ በሚገባ አውቄዋለሁ፤ አንተ ባለማወቅ በድህነት ውስጥ ስትኖር እኔ ደግሞ ከምስጋና ጋር የኖርኩበት ነው" አሉት::

ከዚህ በኋላ ሁለተኛው ርዕስ ጉዳያችን ወደሆነው «ትእግስት» እንሸጋገርና ከዚያም በመጠኑ የሱፊዎችን አመለካከት እንቃኝ::

ለሱፊዎች የእምነት ግማሹ መንገድ «ትዕግስት» ነው:: እንዲያውም የመንፈሣዊ ብቃት ደረጃ ማወቂያው አንዱ መንገድ እሱ መሆኑን አበክረው ይናገራሉ:: ትዕግስት የሌለው ሰው በዛሬ ውስጥ ሳይሆን በነገ ውስጥ የሚኖር ነው:: ነገ ደግሞ ሕልም እንጂ እውን ያልሆነ ነገር ነው:: እናም ትዕግስት አልባ ሰው በሕልም ዓለም እንደሚኖር ሰው ተደርጐ ሊቆጠር ይገባል ባይ ናቸው::

ታላቁ የሱፊ መምህርና ፈላስፋ ኢብን አረቢ ትዕግስትን የወረሱት ከመምህራቸው መሆኑን ይናገራሉ:: አንድ ቀን መምህራቸው ከቁራን ላይ አንድ ጥቅስ ያነቡላቸዋል፡- "ከእነሱ ዘንድ አንዳች አትራቡት አላሻኝም፤ ይመግቡኝም ዘንድ አላስፈለገኝም":: መምህሩ ይኸን ጥቅስ እንዲያብራሩላቸው በወቅቱ ተማሪያቸው የነበሩትን ኢብን አረቢን ይጠይቃሉ:: ኢብን አረቢም ጥቂት አስበው ምላሽ ሳይሰጡ ወጥተው ይሄዳሉ:: ከአራት ዓመታት በኋላ ኢብን አረቢ ተመልሰው ወደመምህራቸው ሲመጡ መምህራቸው በፈገግታ ተቀብለው፡- "አረቢ ሆይ! ለጥያቄዬ አራት ዓመት በቂ ጊዜ ነውና ምላሽ ይዘህ እንደሆነ እንድትሰጠኝ አሁንም እጠይቅሃለሁ" አሏቸው:: የመምህራቸው ትዕግስት በኢብን አረቢም ልብ ውስጥ ነፍስ ዘርቶ መንቀሳቀስ የጀመረው ከዚያ ወዲህ መሆኑን አረቢ ይመሰክራሉ::

ከሼኽ ሙዛፈር የትዕግስት ወግ አንድ እንመልከት፡-

ካሊፍ የተባለ የሱፊ ተማሪ ለምናኔ ጉዞ ይነሳና ምናልባት በበረሃ ውሃ ቢጠማው ከጉድጓድ ቀድቶ የሚጠጣበት ቅልና ገመድ ከያዘ በኋላ የቀረውን ሁሉ በአምላኩ ታምኖ ከቤቱ ይወጣል:: በበረሃ ማቋረጥ እንደጀመረም የውሃ ጥም ያበረታበታል:: ጥቂት ርቀት እንደተጓዘ ግን በአንድ የጉድጓድ ውሃ አጠገብ አውሬዎች ዙሪያውን ከበው ውሃውን ሲጠጡ ይመለከትና መጠጋት ይጀምራል:: አውሬዎቹም የካሊፍን ወደጉድጓዱ መጠጋት ሲያዩ ይበታተናሉ:: ነገር ግን ካሊፍ

በጉድጓዱ አጠገብ ሲደርስ ውሃው ጥልቅ ወደሆነ ርቀት መውረድ ይጀምራል:: ካሊፍም ጉድጓዱን ተጠግቶ በገመዱ ያሰረውን ቅል ቢልክ ይደርስበት ዘንድ አልተቻለውም:: በዚህም ሁኔታ የተበሳጨው ካሊፍ አምላኩን፡- "ለምን እንዲህ አደረግከኝ?" በማለት ቢጮኽ አምላካዊ መልስ በትዕቢት መጣለት፡- "በሁሉ ነገርህ እኔን አምነህ ስትወጣ ለውሃ ግን የታመንከው ገመድና ቅልህን ነበር:: ስለዚህ የታመንክባቸውን ያህል ብቻ ልረዳህ እኔም ወስኜ ወጣሁ" አለው::

አምላኩን በትዕግስት ለጠበቀ አንዳች የሚያስፈልገው ነገር እንዳይጐድልበት ሱፊዎች ይናገራሉ::

በመጨረሻም በሱፊዎች መልካም ምግባር ርዕስ ሥር የምንቃኘው ‹‹ሊጋስነትን›› ነው:: "ሁሉ ነገር ከእግዚአብሔር ከመጣና ተመልሶም ወደ እሱ ከሄደ የእኔ የምንለው አንዳች ነገር አለን?" በማለት ይጠይቃሉ::

የሊጋስነት መልኩ ብዙ ዓይነት ነው:: ብዙዎቻችን አንዳች ነገር (ገንዘብ፣ ጊዜ፣ ምክር) ለሰው ስንሰጥ ሊጋስ የሆንን ይመስለናል:: እንዲሁም ሊጋስነታችን የተሳካ የሚመስለን ድርጊታችንን ሰዎች ሲመለከቱት፣ እውቅና ሲሰጡት፣ ሲያመሰግኑን እንዲሁም ሲያወድሱን ነው:: "ይኽ የሊጋስነት የሚታወቀው ደረጃ ነው" ይላሉ ሱፊዎች:: እውነታውም በሊጋስነታችን ብድራትን መቀበል መቻላችን ነው:: ሊጋስነት ምላሽ ሲሰጠው ግን ንግድ ይሆናል:: ታላቁ የሊጋስነት ደረጃ መለገሳችንን እንጂ ምንና ለማን እንደለገስን አለመጨነቃችን ላይ ነው:: እንዲህ ዓይነቱ ሊጋስ ሰው ዋጋውን የሚቀበለው እንደላይኞቹ በቀጥታ ወይም በሌላ ሰው ሳይሆን ከራስ ነው:: "በመለገስ ደስታን ማግኘት በራሱ ታላቅ ዋጋው ነው" ይላሉ ሱፊዎች::

የሊጋስነትን ወግ በሩሚ እንጀምራለን፡- አንድ ቀን ሙላ ናስሩዲን በአንድ ሐይቅ አካባቢ ሰዎች ተሰብስበው ሲፏፏፉ ይሰማና ወደዚያው እየሮጠ ይሄዳል:: በቦታው ደርሶ ሲመለከትም በስግብግብ ባህርያው በአካባቢው ዘንድ የሚታወቀው ጃሉል በሐይቁ ውስጥ ገብቶ "አድኑኝ" በማለት እየጮኸ ሲንፈራገጥ በሐይቁ ዙሪያ የቆሙት ደግሞ "እጅህን ስጠን!" በማለት ሲጮሁ ይመለከታል::

ይኸን ጊዜ ሙሉ ናስሩዲን ሰዎቹን በፊቴ'ኸት፡ እስቲሞ በሐይቁ ውስጥ ሊሰምጥ ወደሚንፈራገጠው ጃሉል ተጠግቶ፡- "እጄን ውሰድ!" በማለት ይጮኻል:: ይኸን ጊዜ ጃሉል በቅፅበት የሙላን እጅ ጨምድዶ ይይዝና ከውሃ ውስጥ ተጎትቶ ይወጣል::

በሙላ ናስሩዲን ፈጣን ድርጊት የተገረሙት ሰዎች ተጠግተው እንዴት ጃሉልን በዚህ ፍጥነት ለማዳን እንደቻለ ሲጠይቁት፡- "እናንተ ስትጮኹ የነበረው እጅህን ስጠን እያላችሁ ነበር:: እኔ ደግሞ የጃሉልን ስግብግብ ባህርይ በሚገባ አውቃለሁ:: ስጠኝ የሚባለው ነገር በእሱ ሕይወት ውስጥ ቦታ የለውም:: ለዚህም ነው እጄን ውሰድ ያልኩት" በማለት ሚስጥሩን ነገራቸው::

በሼኽ ሙዛፈር ወግ እናብቃ፡- አንድ ሰው ወደ ታላቁ የሱፊ መምህር ኢብራሂም አዳም ይሄድና የገንዘብ ስጦታ ሊያበረክትላቸው እንደሚወድ ይነግራቸዋል:: እኚህ የሱፊ መምህርም የሰውዬውን ጥያቄ ከሰሙ በኋላ፡- "በእርግጥ ሀብታም ከሆንክ የገንዘብ ስጦታህን ለመቀበል እወዳለሁ፣ ደሀ ከሆንክ ደግሞ አልቀበልም" ይሉታል::

ሰውዬውም "በእርግጥ ሀብታም መሆኔን አይጠራጠሩ" ይላቸዋል::

"ሀብታም ከሆንክ እንግዲያውስ ምን ያህል ገንዘብ አለህ?" ይሉታል::

"ሁለት ሺህ ወርቅ አለኝ" በማለት ይመልሳል::

"አራት ሺህ ቢሆንልህ ትመኛለህ" ይሉታል::

"በእርግጥ እመኛለሁ" ይላል::

"ስምንት ሺህ ወርቅስ ቢሆንልህ ትመኛለህ?" ይሉታል::

"መመኘቴማ አይቀርም" ይላቸዋል::

"አሥር ሺህ ቢሆንልህስ...?" ይላሉ ሼኽ ሙዛፈር በድጋሚ::

"በእርግጥ እመኛለሁ" ይላቸዋል...

"ስትመጣ ሀብታም ነኝ ብለኸኝ አልነበረምን? ነገር ግን አንዳች የሃብት ምልክት አላየሁብህም:: እንዳንተ ዓይነት ደሀና ብዙ የሚመኝ ሰው አይቼ ስለማላውቅ ከአንተ ገንዘብ መቀበሉ አግባብ መስሎ አይታየኝም:: ለእኔ ልትሰጠኝ ያመጣኸውን ገንዘብ በጉድለትህ ላይ ጨምርበትና ደስታን ለማግኘት ሞክር" በማለት አሰናበቱት:: □

# "አንድ ዓመት ከምትፀልይ አንድ ሰዓት አስብ"

የሱፊዎችን ምክርና የጥበብ ቃላት ስንጨልፍ ምንጮቻችን ሩሚ፣ ጃሚ፣ አል-ጋኸዛሊ እና ሌሎች ታላላቅ የሱፊዝም መምህሮቻችን ናቸው፡ አብዛኛዎቹን የጥበብ ቃላትና ምክሮች በምሣሌ አስደግፈው ሲነግሩን መነሻቸው "ሀዲስ" ወይም የነቢያት ወግ የሚሉት መሆኑንም አስረድተውን ነው:: እነዚህ የጥበብ ቃላትና ምክሮች ጊዜ የማይሽራቸው ጥበቦች እንዲሁም ለብዙዎች እውነተኛ የሕይወት መመሪያ ሆነው አገልግለዋል:: የዚህ ምዕራፍ መነሻችን አል-ጋኸዛሊ ቢሆንስ፡-

አንድ በፆምና በፀሎት የበረታ ሱፊ ወደ አል-ጋኸዛሊ ይመጣና፡ - "መምህር ሆይ! በፆም በፀሎት ዓመታትን አሳልፌ እነሆ ዛሬ መጣሁ..." ይላቸዋል:: የሱፊው መምህር አል-ጋኸዛሊም፡- "ወንድሜ ሆይ ይልቅ ባሳለፍካቸው ዓመታት አንድ መልካም ነገር ፈፅመህ እንደሆን እሱን ወዲህ በል!" አሉት::

ሩሚ ስለእምነት ሲያስተምሩ ያልገባው ተማሪ፡- "መምህር ሆይ! ስለእምነት የሚነግሩን እውን እንዳች እምነት በእኛ ዘንድ የለችምን?" በማለት ቢጠይቅ ሱፊው ሩሚ መለሰው፡- "እምነትኮ የልብ ዕውቀት፣ የምላስ ቃል፣ የሰውነት ተግባር ተደምረው የሚገልጡት ነው:: በአንተ ምላስ ቃል የሆነው እምነት በልብህ እውቀት እስኪሆን ድረስ አስተምርሃለሁ..." አሉት::

የሱፊዎች ጥበብ አይጠገብምና ከሩሚ አንድ እንጨምር፡- የሩሚ ደቀመዝሙር "ስለድሆች ማዘን አይገባንም?" በማለት ቢጠይቃቸው

"ድሆችን መርዳት እንጂ ለእነሱ ማዘን አያስፈልግም:: ይልቁንስ በምድር ላይ የሚታዘንላቸው ሦስት ዓይነት ሰዎች መኖራቸውን ልብ በል:: የሚወዳትን ሴት በሞት የተነጠቀ፣ ሀብቱ ከስሮ ለድህነት የተዳረገና በመጨረሻም በአላዋቂዎች መካከል የሚኖር ጠቢብ ሰው:: ለእነዚህ ሰዎች በእርግጥም እዘንላቸው..." አለት::

ወደሱፊው መምህር ጃሚ ደግሞ እንለፍ፡- አንዱ ደቀመዝሙራቸው ዘወትር ሲፈኑት ያዩት ጃሚ ምክንያቱን ቢጠይቁት፡- "መምህር ሆይ! ብዙ ነገር አለማወቄ ነው የሚያስፈነቅኝ" ቢላቸው ጃሚም መልሰው፡- "እኔ ደግሞ የሚያስፈንቀኝ የአንተ ብዙ አለማወቅ ሳይሆን አውቅሁ የምትለውን ጥቂቱንም ስትሰራበት አለማየቴ ነው" በማለት ቁርጡን ነገሩት::

በሱፊዎች እምነት በፈጣሪ ዓይን የተናቁ ሦስት ዓይነት ሰዎች አሉ:: እነሱም፡- "በሀብት የናጠጠ ነገር ግን ክፉ ሰው፣ በዕድሜው የሸመገለ ነገር ግን አላዋቂ፣ በመጨረሻም ራሱን ብቻ የሚወድ ደሀ ሰው ናቸው" ይላሉ::

ሱፊዎች በወቅቱ ተፀፅቶ ንስሐ የሚገባን ያደንቃሉ:: እንዲያውም ስለእንዲህ ዓይነቱ ሰው ሲናገሩ፡- "በኃጢአቱ ተፀፅቶ ንስሐ የሚገባ ሰው ኃጢአት አድርጎ ከማያውቀው ጋር እኩል ነው" ይላሉ::

አል-ጋዛሊ ገንዘቡን እያስቀመጠ በሀብቱ ብዛት ታላቅ ሆኗል ስለሚባል ሰው በደቀመዛሙርታቸው ሲነገር ሰምተው፡-"ወዳጄ! ሀብታም ማለት ገንዘቡን የከመረ ሳይሆን ፍላጎቱን የገዛ ነው" ብለውታል:: ከዚሁ ጋር የአል-ጋዛሊን ምክር አብረን እናንሳት ዘንድ የተገባ ትሆናለች::

"ለጠቢብ ሰው እውነተኛ ገንዘቡና ሀብቱ አራት ነገሮች ናቸው፡-" ከአንደበቱ የሚወጣው ቃል እውነት ብቻ ሲሆን፣ ንዴትና ቁጣውን መግዛት ሲችል፣ ስለሚመገበው ምግብ እምብዛም ግድ ከሌለው፣ በሁሉ ነገር የሚታመን ሲሆን... በእርግጥም ሀብታም ነው" ይላሉ::

አል-ጋዛሊ አንድ ቀን በጎዳና ላይ እየሄዱ ሳለ ሁለት ወጣቶች በሃይማኖት ክርክር ተጠምደው ያገኟቸዋል:: በወጣቶቹ ሁኔታ የተበሳጩት አል-ጋዛሊም፡- "በሃይማኖት ጉዳይ በመከራከር

ለምን ጊዜያችሁን እንደምታጠፉ አልገባኝም፣ ስለሃይማኖት በተከራከራችሁ ቁጥር ሃይማኖት ውስብስብና ግራ አጋቢ ነገር እየሆነ እንደሚመጣ አታውቁምን… ፈጣሪ ሃይማኖትን ሲፈጥረው እኮ ቀላልና ግልፅ አድርጎ ነው" በማለት በከንቱ ጊዜያቸውን ከማባከን ይልቅ እንዲሰሩበት መክረዋቸው አለፉ::

አል-ጋዛሊ በሌላ ቀን ለወዳጃቸው፡- "ወንድሞቼ ሁሉ ከእኔ የተሻሉ መሆናቸውን እመሰክራለሁ" ይሏቸዋል::

ወዳጃቸውም፡- "ከአንተ መሻላቸውን በምን አወቅህ!" በማለት ቢጠይቋቸው "ሁሉም እኔ ከእነርሱ የተሻልኩ እንደሆንኩ አድርገው ያስባሉ፣ ማንም እኔን ከእሱ የተሻለ አድርጎ የሚያስበኝ ደግሞ እሱ ከእኔ የተሻለ መሆኑን አረጋገጠ ማለትም አይደል?" በማለት አስደምመዋቸዋል::

እንዲሁ በሌላ ጊዜ አል-ጋዛሊ ከወዳጃቸው ጋር ሲጫወቱ ወዳጃቸው፡- "ለመሆኑ በእውነት ለፈጣሪ የተሰጠ ሰው በአምላኩ የሚረካው መቼ ነው?" በማለት ቢጠይቋቸው፡- "በበረከቱ ጊዜ የሚያገኘውን ደስታ በመከራውም ጊዜ መግለጥ ከቻለ በአምላኩ ረክቷል ማለት ነው" አሏቸው::

ይኸችን ፈገግ የምታደርግ ወግ ደግሞ እንደመሸጋገሪያ እንቅመሳት፡-

አንድ ቀን ንጉሥ ግብር ያገባና ታላላቅ ባለሟሎቹና ባለሥልጣናት ቦታ ቦታቸውን በመያዝ ላይ ሳሉ አንድ ከነመኖሩም የማይታወቅ ሰው ወደአዳራሹ በመግባት በቀጥታ ከንጉሡ ዙፋን ከፍ ብሎ የሚገኝ ወንበር ላይ ሄዶ ይቀመጣል:: ታዳሚው በነገሩ ተደናግጦ ሲመለከት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ይነሳና ሰውዬውን መጠየቅ ይጀምራል፡-

"አንተ የታላቁ ንጉሥ አማካሪ ነህን?"

"አይደለሁም! ከአማካሪው በላይ ነኝ" ይላል ሰውዬው::

"ጠቅላይ ሚኒስትሩ አንተ ነህን?"

"አይደለሁም! ከጠቅላይ ሚኒስትሩ በላይ ነኝ" አሁንም ሰውዬው መለሰ::

"እንግዲያው ንጉሡ ነህን!" በማለት ይቀልድበታል::

"ከንጉሡም በላይ ነኝ" አለ ሰውዬው::

"በዚህ ዓይነት አንተ ፈጣሪ መሆንህ ነዋ!?" ይለዋል ጠ/ሚኒስትሩ::

"አይደለሁም! ከእሱም በላይ ነኝ" አለ ሰውዬው::

"ከፈጣሪ በላይማ ምንም ሊኖር አይችልም" ይላል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወደ እሱ እየቀረበ::

"አሁን አወቅኸኝ፣ ያ ምንም እኮ እኔ ነኝ" በማለት ወንበሩን ለቅቆ ከአዳራሹ መውጣት ጀመረ:: ይኸ ሰውዬ የሼኽ ሙዛፈር ደቀመዝሙር ሳይሆን አይቀርምና ወደእሳቸው እንለፍ::

አንድ ሰውዬ ከታላቁ ጠቢብ ሰሎሞን አጠገብ ተቀምጦ ሳለ የሞት መልዐክ በድንገት በመካከላቸው ይከሰትና በመደነቅ ሰውዬውን ማየት ይጀምራል:: ሰሎሞንም ለሰውዬው በመደነቅ አፍጥጦ የሚመለከተው የሞት መልዐክ መሆኑን ሲነግረው ይበልጥ ተሸብሮ፡- "ሰሎሞን ሆይ! እባክህ አርቀህ በመንፈስህ ላከኝና ከዚህ የሞት መልዐክ ላምልጥ" ይለዋል:: ሰሎሞንም ጥበቡን ተጠቅሞ ነፋሳትን በማዘዝ ሰውዬውን ወደቻይና በቅፅበት ይልከዋል:: የሞት መልዐክም አብሮ ይሰወራል::

ከጥቂት ጊዜ በኋላ የሞት መልዐክ ተመልሶ ይመጣል፣ ሰሎሞንም"- "ያንን ሰውዬ እንደዚያ በመደነቅ ትመለከተው የነበር ለምንድነው?" በማለት ይጠይቀዋል::

የሞት መልዐክም፡- "የዚህን ሰውዬ ነፍስ ከቻይና እንዳመጣት በፈጣሪ ተልኬ ከመጣሁ ጥቂት ቀን ሆኖኛል:: ሆኖም የደነቀኝ እሱን ከአንተ ጋ እዚህ ኢየሩሳሊም ውስጥ ተቀምጦ ማግኘቴ ነበር:: የላከኝ እንደማይሳሳት ግን ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት አረጋግጬ መምጣቴ ነው" በማለት መለሰለት::

ከሼኽ ሙዛፈር አንድ እንጨምር፡- የሞት መልዐክ የአብርሃምን ቤት አንኳኩቶ ነፍሱን ሊወስዳት እንደመጣ ይነግረዋል:: አብርሃምም በቅድሚያ ከእግዚአብሔር ጋር እንዲነጋገር ዕድሉን እንዲሰጠው ጠይቆት ወደቤቱ ተመልሶ ገባ፡፡ እግዚአብሔርንም በፀሎቱ ይጠራውና ይጠይቀዋል፡- "ለመሆኑ ጌታ ሆይ! የወዳጁን ነፍስ የሚወስድ ጓደኛ አይተህ ታውቃለህን?"

እግዚአብሔርም መለሰለት፡- "አንተስ ወዳጁን ለመገናኘት የማይጓጓ ጓደኛ አይተህ ታውቃለህን?"

አብርሃም መልስ አጠረው:: በሩን ከፍቶ ሲወጣም የሞት መልዐክ ቆሞ ሲጠብቀው ተመለከተ::

ሼኽ ሙዛፊር አሁንም አለቀቁንም፤ ይኸች ወጋቸው ጣፋጭ በመሆኗ እኛም ልናሰፍራት ተገቢ ሆነች፡- አንድ ቀን ከኢየሱስ ደቀመዛሙርት አንዱ በአንዲት ትንሽ ከተማ ቆሞ ሲሰብክ ሳለ ሕዝቡ ሁሉ ከሙታን መካከል ሰው በማስነሳት ተአምራት እንዲያሳያቸው ይጠይቁታል::

ይኸው ደቀመዝሙር የሕዝቡን ጥያቄ ተቀብሎ ወደመቃብር ቦታ ይዟቸው ይሄድና በአንድ መቃብር ላይ ቆሞ መፀለይ ይጀምራል:: በቅፅበትም መቃብሩን ፈንቅሎ አንዱ ይነሳና፡- "አህያዬን! አህያዬ የት ሄደ?" በማለት መጮኸ ይጀምራል:: ለዚህ ሰው በሕይወት ዘመኑ ትልቁ ዋጋ የሚሰጠውና አለኝ የሚለው ሀብቱ አህያው ብቻ ነበር::

"ይኸ ነገር እንግዲህ ለእናንተም እውነት መሆኑን እውቁ" ይሉናል ሙዛፊር:: "በዳግም ትንሳኤ ጊዜ በሕይወት ዘመናችሁ እጅግ የወደዳችሁት ነገር ጋር አብራችሁ መኖራችሁ አይቀሬ ነውና"::

አል-ጋዛሊ አንድ ቀን ደቀመዛሙርቶቻቸውን ሲያስተምሩ ሳለ አንድ ተማሪ "መምህር ሆይ! ከአንድ ዓመት በፊት የነገሩኝ ምስጢር ለመፍታት እነሆ አንድ ዓመት ፀለይሁ:: ነገር ግን ምስጢሩን መፍታት አልተቻለኝም:: ይሄ ነገር ያቃተኝ ከእኔ ፀሎት ይሆን? ወይስ ፈጣሪ የፀሎትን ምስጢር ለመግለጥ ስለማይቻለው?" በማለት ቢጠይቃቸው:: አል-ጋዛሊ መልሰው፡- "ልጄ ሆይ! ችግሩ ከሁለቱም አይደለም፤ አንድ ዓመት ከምትፀልይ አንድ ሰዓት አስበህ ቢሆን ኖሮ የነገሩክህን ቁም ነገር ምስጢሩን ለማወቅ በተቻለህ ነበር" አሉት:: □

# "በፍቅር የተጠመደ ሰው ነፍሱ ከእሱ ዘንድ የለችም"

ከሱፊዝም የእምነትና የሕይወት ፍልስፍና አያሌ ቁም ነገሮችን እየቀዳን "ልብን ስለመክፈት" እና ስለ "ፍቅር" ከማነግሩን ላይ ደረስን::

"የልብ ዓይን ሲከፈት የዚህን ዓለም ውስጣዊ ገፅ በሚገባ እናየው ዘንድ እንችላለን:: የልብ ጆሮዎች ሲከፈቱ ደግሞ ከቃላት ጀርባ የተሸሸገውን ነገር መስማት እንችላለን... እሱም እውነት ይባላል" የሚሉን ሱፊዎች "ልብን መክፈት ማለት በአጭሩ ወደአምላክ መጠጋት ነው" በማለት ፈጣሪ በነቢዩ ሙሐመድ ውስጥ ሲናገር እንዲህ ማለቱን ይገልፃሉ:- "ዓለማት በእኔ ልክ ሊሆኑ የማይችሉ (የማይበቁኝ) አምላክ ነኝ፣ በእውነት የሚያመልከኝ ሰው ልብ ግን ለእኔ የሚበቃኝ ነው" ይላል:: ለዚህም ነው ሱፊዎች የሰው ልጅ ልብ የፈጣሪ ቤተመቅደስ ነው የሚሉን:: ምንም እንኳን የሰው ልጅ ልብ ሁሉ የፈጣሪ መቅደስ ነው ቢባልም በሩ የሚከፈተው ግን በመንፈስ ቅዱስ ሕልውና መሆኑ ሊዘነጋ አይገባውም:: ሱፊዎች በሰው ልጅ አፈጣጠር መጀመሪያ ፈጣሪ አዳምን ሲፈጥረው:- "የሕይወትን (የመንፈስን) እስትንፋስ እፍ አለበት" መባሉን አትዘንጉ ይላሉ:: በዚህ መንፈስ የፈጣሪ ጥበብ፣ ፍቅር፣ እውቀት ወደውስጣችን እንዲዘልቅ አምነን ከሱፊዎች "የልብ መከፈት" ወግና ምክር አንዳንድ እንቆንጥር::

የሱፊው ደቀመዝሙር አማር መምህሩን በዚህ ምድር ላይ አጥብቀን እንፈልገው ዘንድ የሚገባን ቁምነገር ምን እንደሆን ጠየቃቸው:: መምህሩም:- "ፈጣሪዋን በማስታወስ የተጠመደች

ምላስ፣ አመስጋኝ ልብና እሱን የምታምን ሚስት ካገኘህ ቁም ነገርን ጨብጠሃታል" ማለታቸውን አል-ጋዝዛሊ ይነግሩናል::

ከአል-ጋዝዛሊ አንድ እንመርቅ፡- "እውነት የተተከለችው በልብህ መካከል ነው" ይላሉ፡- "ይኸችን እውነት ትጠብቃት ዘንድ ደግሞ በፈጣሪህ እምነት ተጥሎብሃል:: የዚህ መገለጫው ደግሞ እውነተኛ ንስሐና እውነተኛ ሥራ ብቻ ነው:: ያን ጊዜ የእውነት ውበት በፊትህ ላይ ያንፀባርቃል:: ከአምላክህ ጋር መገናኘት ስትጀምር ቅድሚያ የምታደርገው ነገር በምላስህ ማመስገን ይሆናል:: ልብህ በመንፈስ ሲነቃ ደግሞ ምስጋናህን የምታቀርበው በልብህ ቋንቋ ይሆናል" ይላሉ::

"የፍቅር መኖሪያው ልባችን ነው" የሚሉት የሱፊው መምህር አል-ጋዝዛሊ "ፍቅር ልዩና የሚያስደስት ስቃይ የተሞላ የፈጣሪ ስጦታ ነው" ይሉናል:: "ፍቅርን በልቡ ተሸክሞ የሚዞር እሱ ምስጢሩን ለማወቅም የሚቸግረው አይሆንም:: ፍቅርን ስትሸከም ነገር ሁሉ ለአንተ እውነትና ወደእውነት ብቻ የሚወስድ ይሆናል:: በፍቅር ውስጥ ከእውነት በቀር ሌላ ነገር የለም:: ለዚህም ነው አፍቃሪዎች በእውነት ባህር እየተሸነፉ ሲሰምጡ የምናየው" ይላሉ አል-ጋዝዛሊ::

በጃሚ ምክር ወደፍቅር ወግ እንሸጋገራለን፡- "ፍቅር ቤቱን የሰራበት ልብ እንዴት የታደለ ነው፤ ፍቅር የዓለምን ቍንቀት ሁሉ የሚያስረሳ ነው:: ፍቅር እንደመብረቅ ኃያልና ትዕግስትንና ማሰብንም ወደምንም እና ከንቱ ነገር የሚቀይር ጥበብ ነው:: አፍቃሪ ስለራሱ ደህንነት አንዳች የሚያስበው ነገር የለውም:: ትችትና ነቀፋ እንደተራራ በዙሪያው ቢቆም ለፍቅር ግን ገለባና ምናምንቴ ነው:: እንዲያውም ለአፍቃሪ ልብ ስድብና ትችት ፍቅሩን የሚጨምርለት ኃይል ይሆነዋል::

"ፍቅር ተራሮችን በመቅደድ ወደመድረሻችን የሚወስደን ተዐምር ነው:: በፍቅር የተጠመደ ሰው ነፍሱ በእሱ ዘንድ የለችም:: አፍቃሪ ሰው ያፈቀራትን ከሚያጣ አካሉን ቢያጣ ይመርጣል:: በፍቅር ውበት ተጠምዶ ልና ለእሱ ስቃይና መከራ የማይነገር ደስታና ሐሴት ይፈጥርለታል::"

ወደሼኽ ሙዛፈር ወግ ስናልፍ የምናገኛት የምትቀጥለዋን ታሪክ ይሆናል፡- አንድ ቀን አል-ጃሚ ከደቀመዛሙርቶቻቸው ጋር ስለፍቅር ሲያወጉ አንዱ ደቀመዝሙር ወደአል-ጃሚ ተጠግቶ፡- "መምህር ሆይ! ለመሆኑ ፍቅርን እንዴት ይገልፁታል?" አላቸው::

አል-ጃሚም ከምላሹ አስቀድመው ጥያቄውን በጥያቄ ወረወሩለት፡ - "ፍቅር ይዞህ ያውቃል?"

ደቀመዝሙሩም፡- "በሚገባ እንጂ!" ሲል መለሰ::

አል-ጃሚም፡- "እንግዲያውስ በፍቅርና በምታፈቅራት ሴት መካከል ልዩነት የለም:: ፍቅር ማለት የሚያፈቅሩት ሰው በሥጋ ሲገለጥ ማለት ነው" አሉት::

ለዚህም ይመስላል ሱፊዎች ‹‹በምድር ላይ ለምናፈቅረው ነገር በምርጫችን ካልተጠነቀቅን በትንሣኤ እስከዘላለም ከእኛው ጋር ይኖራል›› የሚሉን::

በሱፊዎች ልብ መከፈት አንዱ መገለጫ ልግስና ነው ብለናልና ወደ አል-ጋዛሊ ዞረን ይኸችን ወግ እንመልከት፡-

አቡ ሱሌይማን ደቀመዛሙርታቸው የልግስናን ልኩን እንዲነግሩት ቢጠይቃቸው፡- "ይኸችን ዓለም ጠቅለዬ በወንድሜ አፍ ውስጥ የመክተት ችሎታው ቢኖረኝና እሱም በዚያ እርካታን የሚያገኝ መሆኑን ባውቀው አደርገው ነበር" አሉት::

ይኸን ጊዜ ደቀመዝሙሩ፡- "ለመሆኑ በዚህ ድርጊትዎ እርካታን የሚያገኙ ይመስልዎታል?" በማለት ጠየቃቸው::

አቡ ሱሌይማንም፡- "ወንድሜ! በወንድምህ አፍ ውስጥ የከተትከውን ጉርሻ በጉሮሮህ ማጣጣም ስታውቅ ያን ጊዜ አንተ ለልግስና ልቡ የተከፈተ ሰው ትባላለህ" በማለት መለሱለት::

ፍቅር ሲኖርህ ልግስናህ በተከፈተ ልብ መሆኑ አይቀሬ ነው:: ለዚህ ደግሞ ሱፊው ሼኽ ሙዛፈር በሚነግሩን ወግ እናብቃ፡-

አንድ ቀን ኢየሱስ ክርስቶስ በአይሁድ የገበያ ቦታዎች ሲዘዋወር አንዳንድ እስራኤላውያን ይዘባበቱበትና ይሰድቡት ጀመር::

ኢየሱስ ግን ለሕዝቡ ስድብና መዘባበት ምላሹን በስማቸው እየፀለየ ለኃጢአታቸው ይቅርታ መጠየቅና ትህትና ነበር::

በሁኔታው ከተገረሙትና ዳር ቆመው ከሚመለከቱት አንዱ ወደኢየሱስ ተጠግቶ፡- "ይኸን ያኸል እየሰደቡህና እያዋረዱህ ለእነሱ ትፀልያለህን? ጥቂት እንኳን ንዴትና ሐዘን በፊት ላይ እንዴት አላይም?" በማለት ይጠይቀዋል::

ኢየሱስም፡- "ሁሉ በከረጢቱ ከተሸከመው ይዘረግፋል፤ እኔም በከረጢቴ ከተሸከምኩት ውጭ ሌላ የማወጣው ነገር የለኝም!" በማለት አልፎት ሄደ::

የሰው ልጅ በከረጢቱ ከተሸከመው መዘርገፉ የማንነቱ መገለጫ ነውና ኢየሱስ ለዚህ መፀለዩ ተገቢ ነው:: ቁጣና ንዴት በኢየሱስ ከረጢት አልነበረም ለማለት ባንችልም የትና በማን ላይ መክፈት እንዳለበት አውቋልና እናደንቀዋለን፤ እናከብረዋለን:: □

# "ክፉን ሰው በትህትና ማስተናገድ በሕመሙ ላይ መርዝ እንደመርጨት ይቆጠራል"

የሱፊዝምን ጉዞ ከምንጠቀልልበት የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ ደረስን:: መሰነባበቻ ይሆነን ዘንድ የመረጥኩት ደግሞ ‹‹እምነትን›› ነው::

ሱፊው መምህር ሩሚ ራስን የመለወጥና ፈጣሪንም የማምለኪያው ጥበብ "እምነትን በተግባር መተርጎም" እንደሆነ ይነግሩናል:: የሰው ልጅ አብዛኛው ድርጊቱ የተቆራኘው ዋጋን ከማግኘት ጋር ነው:: ይኸ ዋጋ ገንዘብ፣ ክብር፣ ምስጋና... ወዘተ ሊሆን ይችላል:: ነገር ግን በሱፊዎች ዘንድ አገልግሎት ማለት አንዳች ዋጋን ሳያስቡ "ለፈጣሪ ሲባል" ብቻ የሚከናወን ድርጊት ነው:: እንዲህ ዓይነቱን ተግባር ለመፈፀም አስቀድሞ የፈጠረንን ማመንና ማክበር የሚገባ ሲሆን ይኸም ሰማያዊ ክብርና ፀጋን ለማግኘት ከማለም ሳይሆን እሱን ከማፍቀርና ከመከተል ብቻ የመነጨ መሆኑን ማሳየት እንደሚገባ ይናገራሉ:: እዚህ ላይ አንድ ልንዘነጋው የማይገባን ቁምነገር ‹‹ፍቅር የሌለው አገልግሎት የተዋበ አስከሬን ከመሆን አይለይም›› የሚሉን ሱፊዎች ‹‹ከላይ ሲታይ ቢያምርም ውስጡ ግን ሕይወት አልባ መሆኑን አትዘንጉ›› ይላሉ::

"አገልግሎት ታላቅ የሚያደርግና በሰዎች ዘንድ መደነቅን የሚፈጥር አድርጎ ማሰብ የዋህነት ነው" በማለት ሱፊው ሩሚ በተጣይዋ ወግ ያንደረድሩናል::

ከብዙ ዓመታት በፊት ከኦቶማን ሱልጣኖች የአንዱ እናት የሆነች ሴት ራሷን በበጎ አድራጎት ሥራ በእጅጉ የተጠመደች አድርጋ ትኖር ነበር:: በቱርክ ግዛት ውስጥ ታላላቅ መስጊዶችና ሆስፒታሎች እንዲሁም የውሃ ጉድጓዶችን በማስቆፈር ሕዝቡ

የተሻለ ሕይወት በሁሉም አቅጣጫ እንዲኖር ትጥራለች:: አንድ ቀን በከተማ ውስጥ በማስራት ላይ የምትገኘውን ሆስፒታል ለመጐብኘት ወደዚያ አምርታ እየተዘዋወረች ስትመለከት መሠረቱ ገና ባልደረቀ የሲሚንቶ ልስን ላይ አንዲት ጉንዳን ስትወድቅ ተመለከተች:: በፍጥነትም እጇን ሰንዝራ ጉንዳኗን ከወደቀችበት ሲሚንቶ ላይ በማንሳት በምድር ላይ አስቀመጠቻት::

"ይኸች ሴት ከጥቂት ዓመታት በኋላ ከዚህ ዓለም በሞት ትለይና በዚያው ቀን ለብዙ ጓደኞቿ በሕልማቸው ትታያለች:: በመልኳ እጅግ ተውባና በውስጧም በደስታ የተሞላች ሆና የተመለከቷት ጓደኞቿ ያለጥርጥር በሰራቻቸው በጐ ምግባሮችና ቸርነቶች ገነት ገብታለች ማለት ይጀምራሉ:: ይኸን ጊዜ ይኸች ሴት ለሁሉም ሴቶች በሕልማቸው የነገረቻቸው ነገር ቢኖር፡- "እኔም እንደእናንተው በበጐ ሥራዬ ገነት እንደምገባ ስመካና ስታበይ ኖሬ ነበር:: ነገር ግን በፈጣሪ ዘንድ ታላቅ ሥራ ተደርጐ የተቆጠረልኝ በእኔ ልብ ውስጥ ቦታ ያልነበረውና አንዲት ጉንዳንን ከሲሚንቶ ላይ አንስቼ ሕይወቷን ማትረፌ ነበር" አለች:: እነሆ ሱፊዎች ሲመክሩ "በሰው ልጅ ዓይን ትንሽ መስሎ የሚታየው ድርጊት በፈጣሪ ዓይን ታላቅ ይሆናል:: ሰው የሚመካበት ሁሉ በፈጣሪው ዘንድ ከንቱና የከንቱም ከንቱ ነው" ይላሉ::

ወደሼኽ ሙዛፈር ወግ ደግሞ እንለፍ፡-

አንድ ምሽት የሱፊው መምህር ስለትህትናና አገልግሎት ደቀመዛሙርቶቻቸውን ሲያስተምሩ ነበር:: በተለይም የራስን ፍላጐትና ስሜት ከሌሎች አለማስቀደምና ለበጐነት ሁሉ በጐነትን ምላሽ ማድረግ እንደሚገባ በተዋበ አገላለፅ ሲያስተምሩ በድንገት ከደቀመዛሙርቶቹ አንዱ ተነስቶ፡- "መምህር ሆይ! ለክፉ ሰው ግን እንዴት መመለስ እንዳለብን አልነገሩንም" አላቸው::

መምህሩም፡- "ለክፉማ ክፋትን ትመልሳላችሁ" በማለት ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ተናገሩ:: በዚህ ንግግራቸው ደቀመዛሙርቱ ሁሉ ደነገጡ:: መምህሩም የደቀመዛሙርቶቻቸውን ድንጋጤ ተመልክተው፡- "ክፉን ሰው በትህትና ማስተናገድ በሕመሙ ላይ

መርገዝ እንደመርጨት ይቆጠራል:: ትህትና ለክፉ ሰው መድኃኒት ሳይሆን መርዝ ነውና አትስጡት" አለ::

ከሼኽ ሙዛፈር አንድ እንመርቅ፡-

የሱፊውን መምህር አንድ ወዳጃቸው እንዲህ ሲል ጠየቀ፡- "ለመሆኑ በልጅ ላይ ከአባቱና ከእናቱ የበለጠ ሥልጣን ያለው ማነው?"

መምህሩም ጥቂት አሰቡና፡- "እናት በልጁ ላይ ያላት መብት ከአባት የላቀ ነው" አሉት:: ሰውዬው መምህሩን ይኸንኑ ጥያቄ ደጋግሞ ቢጠይቃቸውም በእርግጠኝነት የእናት መብት በልጁ ላይ ከፍተኛ እንደሆነ አረጋግጠው ነገሩት::

"ይኸን ያህል የላቀ መብት ለእናት የተሰጣት ለምንድነው?" በማለት መምህሩን ጠየቃቸው::

"እናትህ በማህፀኗ ዘጠኝ ወር ተሸክማሃለች፣ ከዚያም በምጥ ተጨንቃ ወልዳሃለች:: ከወለደችህ በኋላ እንቅልፍ ሳያምራት በሌሊት ስታጠባህ፣ በእጆቿ ተሸክማ ስታስተኛህ፣ ስታጥብህና ስታፀዳህ ኖራለች:: ለዓመታት ምግብህን ስታበስል፣ ስትመግብህ፣ ልብስህን ስታጥብ ሕይወቷን ለአንተ ሰጥታለች:: በሰላሳና አርባ ዓመትህ እንኳን ሕይወትህን እየተከታተለች ዕድገትህን በጉጉትና በናፍቆት ትጠብቃለች:: አባትህ በእናትህ ማህፀን ውስጥ ከዘራህ በኋላ ምግብህንና የምትለብሰውን ያቀርባል:: ታዲያ ይኼ ከእናት ጋር የሚስተካከል ይመስልሃል?" በማለት መምህሩ አስረዱት::

ወዳጃቸው አሁንም ጥያቄውን ቀጠለ፡- "መልካም! ነገር ግን ለእናቴ ለዚህ ሁሉ ሥራዋ ውለታዋን እንዴት ከፍዬ እንደምወጣው እርግጠኛ አይደለሁም" አለ::

መምህሩም፡- "የእናትህን ውለታ በቀላሉ ትከፍለው ዘንድ አይቻልህም" አሉት::

"ነገር ግን እናቴን በዕድሜ ዘመኗ ሁሉ በጀርባዬ ተሸክሜአት ብዞር፣ የምትመገበውን እያቀረብኩ ባኖርኳት፣ የሚያስፈልጋትን ሁሉ በእጆቼ ብፈፅም ውለታዋን የከፈልኩ አይመስልዎትም?" በማለት አሁንም ጠየቀ::

መምህሩም፡- "አየህ! አሁንም በአንተና በእናትህ መካከል ትልቅ ልዩነት አለ:: እናትህ የምታደርገውን ሁሉ እያደረገች እድገትህንና መኖርህን ስትጠብቅ አንተ ደግሞ የምታደርገውን ሁሉ እያደረግህ የምትጠብቀው ሞቷን ነው" አሉት::

ስለአገልግሎትና ፍቅር ካነሳን ዘንድ የአል-ጋዝዛሊን ወግ ከዚህ ላይ እናምጣ፡-

አንድ ሰው በእድሜ እጅግ የሸመገለ አባቱን ይዞ ይኖር ነበር:: ይሁንና የዚህ ሰው ሚስት አማቷ በጣም በማርጀታቸው ከእንግዲህ የመጠር ግዴታ እንደሌለባቸው ዘውትር ባሏን ትጨቀጭቀው ነበር:: ይብሱንም አንድ ቀን ከቤት አውጥቶ እንዲጥላቸው አለበለዚያ ጥላው እንደምትሄድ አስጠነቀቀችው::

ሰውዬው የተቻለውን ያህል ሊያሳምናት ቢሞክርም ሚስቱ ከሃሳቧ ፍንክች የምትል ሆና አላገኛትምና ተጨነቀ:: በመጨረሻም ትዳሩን ከማፍረስ አባቱን አውጥቶ መጣል እንደሚሻል አመነና፡- "አባቴ ሆይ! ወደተራራው ጫፍ ለሽርሽር እንውጣ በማለት ወንድ ልጁን አስከትሎ በጋሪ ይዟቸው ወጣ::"

ሽማግሌው ከልጃቸው ልጅ ጋር እየተጫወቱ በአቅራቢያቸው ወደሚገኝ የተራራው ጫፍ ከደረሱ በኋላ ሰውዬው ለአባቱ አንዲት አልጋ ዘረጋና በዚያ ላይ አስተኝቶ ሲያበቃ ከአጠገባቸው ጥቂት ምግብና ውሃ አስቀምጦ፡- "ጥቂት ከልጄ ጋር ተንሸራሽረን እንመጣለን" በማለት ልጁን ይዞ ተመለሰ::

ይሁንና ወደቤታቸው እየተመለሱ መሆኑን ከመንገድ ላይ የተረዳው የሰውዬው ልጅ፡- "አባባ! አያቴን ከተራራው ጫፍ ትተነው የመጣነው ለምንድነው? ተመልሰን እናምጣው" በማለት አባቱን መወትወት ያዘ:: አባትዬውም፡- "ከእንግዲህ አባቴ አርጅቷልና ልንጦረው ስለማንችል እዚያው ይቀመጥ ዘንድ የተገባ መሆኑን ትምኝበታለህ" አለው::

ልጁ ግን አያቱን እጅግ አድርጎ ይወድ ነበርና እያለቀሰ ተመልሰው አያቱን እንዲያመጡ ቢመፀንም አባትዬው ሊሰማው ፍቃደኛ አልሆነም::

ይኸን ጊዜ ልጁ፡- "አባባ! እኔም ሳድግ አንተ ማርጀትህና አቅሙ ደካማ መሆንህ አይቀርም... ያ ጊዜ ሲደርስ ከተራራው ጫፍ ወስጄ እንደማስቀምጥህ ግን አትዘንጋ" አለው።

ሰውዬው የሰራው ስህተት በልጁ ንግግር ግባውና ተፀፀተ። ከልጁም ጋር አባቱን ወዳስቀመጠበት ቦታ ተመልሶ በመሄድ እግሩ ላይ ወድቆ ይቅርታ መለመን ጀመረ። አባቱም የልጁን ጭንቅላት እያሸ፡- "ልጄ! አባቱን በስተርጅና ዘመኑ ከተራራ ጫፍ ላይ ወስጄ አልጣልኩትም፤ ታዲያ እኔንስ ፈጣሪ እዚህ እንድትጥለኝ ይፈቅድ ይመስልሃል?" አሉት። የሰውን ልጅ ማገልገል ፈጣሪን እንደማገልገል መሆኑን ሱፊዎች አጥብቀው ይመክራሉ። ቀጣይዋን ኢታር ወግ ደግሞ ተምሳሌትነቷ አገልግሎትን ከሕይወትነት ጋር በእጅጉ አቆራኝታ የምታሳይ ትመስላለች፡-

ሃልቬቲ በተባለች ከተማ የሚኖር ሼኽ የእሱን ተተኪ ለመሾም ደቀመዛሙርቱን ፈተና ሰጣቸው። ፈተናውም መኖሪያውን በልዩ መዓዛ ሊያውድ የሚችል አበባ እንዲያመጡ ሲሆን ይኸን ያደረገ የእሱን ወንበር እንደሚሰጠው ተናገረ። ደቀመዛሙርቱም፣ ወደሜዳ በመውጣት የሼኹን ልብ በመዓዛው ሊያሸንፍ የሚችል አበባ ሲሰበስቡ ለቀናት ቆይተው በመመለስ በፊቱ አቀረቡ። ነገር ግን ከደቀመዛሙርቱ አንዱ ለሼኹ ያከረበው አንዲት ጠውልጋ የደረቀች አበባ ነበር። ሼኹ በዚህ ደቀመዝሙር ድርጊት ተደንቆ የማይረባና የደረቀ ቅጠል ለምን እንዳመጣለት ጠየቀው።

ደቀመዝሙሩም፡- "ደቀመዛሙርቱ እየቀጠፉ ሲሰበስቧቸው የነበሩ አበቦችን በሙሉ ስመለከታቸው የአምላክን ድንቅ ሥራ በውበታቸው እየገለጡ የሚያመሰግኑ መሰለኝ። ነገር ግን ከመካከላቸው ይኽች አበባ ደርቃና ጠውልጋ አንዳች ውበት የማይታይባትና የፈጣሪንም ድንቅ ሥራ መግለፅ ያበቃች መስላ ብትታየኝ አዉን አመጣሁልዎ" አለው።

ሼኹም፡- "በእርግጥ እኔን መተካት የምትችል አንተ ነህና ወንበሬን ከዛሬ ጀምሮ ተረከበኝ" በማለት ከተቀመጠበት ተነሳለት።

□

እንድ ቀን ኢየሱስ ክርስቶስ በአይሁድ የገበያ ቦታዎች ሲዘዋወር አንዳንድ እስራኤላውያን ይዘባበቱበትና ይሰድቡት ጀመር::



ኢየሱስ ግን ለሕዝቡ ስድብና መዘባበት ምላሹ በስማቸው እየፀለየ ለኃጢአታቸው ይቅርታ መጠየቅና ትህትና ነበር:: በሁኔታው ከተገረሙትና ዳር ቆመው ከሚመለከቱት አንዱ ወደኢየሱስ ተጠግቶ፡- "ይኸን ያኽል እየሰደቡህና እያዋረዱህ ለእነሱ ትፀልያለህን? ጥቂት እንኳን ንዴትና ሐዘን በፊትህ ላይ እንዴት አላይም?" በማለት ይጠይቀዋል::

ኢየሱስም፡- "ሁሉ በከረጢቱ ከተሸከመው ይዘረግፋል፤ እኔም በከረጢቴ ከተሸከምኩት ውጭ ሌላ የማወጣው ነገር የለኝም!" በማለት እልፎት ሄደ::

* * *

አንድ ፈላስፋ ወደ ናስሩዲን ዘንድ በመምጣት፡-
‹‹ለበርካታ ዓመታት የዓለም መጨረሻ መቼ እንደሚሆን በመራመር፣ ሳሰላስልና ስፈተሽ ኖሬያለሁ:: ነገር ግን ልደርስበት አልቻልኩም:: ለመሆኑ በአንተ ዘንድ ይኽ ምስጢር ይገኝ ይሆን›› በማለት ጠየቀው::
ናስሩዲንም፡- ‹‹ይኽንማ ካወቅሁት በርካታ ዓመታት አልፈዋል›› ሲል መለሰለት::
ፈላስፋውም፡- ‹‹እባክህን ይኽን እውቀትህንማ ልታካፍለን ይገባል:: ለመሆኑ የዓለም መጨረሻ መቼ ይሆን?›› በማለት በድጋሚ ጠየቀው::
ናስሩዲንም ‹‹የዓለም መጨረሻ የሚሆነው እኔ ስሞት ነው›› በማለት መለሰለት::
‹‹እርግጠኛ ነህ? እንዴት አንተ ስትሞት ለእኛ የዓለም መጨረሻ ይሆናል?›› አለ ፈላስፋው በጥርጣሬ::
ናስሩዲንም ፈገግ ብሎ፡- ‹‹ቢያንስ ለእኔ ይሆናል›› ሲል አረጋገጠለት::